# ሰበር ጋህዲ2

ከአስገደ ገ/ስላሰ ወ/ሚካኤል የህ.ወ.ሓ.ት መስራች ከመቀሌ

## መግቢያ

## መለስ በ17 ዓመት የትጥቅ ትግልና በ21 ዓመት የመንግስታዊ ስልጣን ዘመናቸውና ጉዞዋቸው ሲተረክ

በዓለማችን ታሪክ ሲፃፍ ብዙዉን ጊዜ ያየነውና የሰማነው በዛ ትክክለኛ ታሪክ የተሰራበት (የሰሩ) ሳይሆን የሚፃፍ ጊዜ ሰጥቶዋቸው ወደ ስልጣን ለወጡት በታሪክ ሥራ ላልነበሩት በግለሰዎች ፍላጎትና ስሜት ከአለቆቻቸው ክብርና ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ታሪክ የሰሩት በመቅበር በስልጣን ኮረቻ ለወጡ ብቻ ይፅፋሉ: አንደዳንድ ባለስልጣኖች የድሮ ነገስታት ደግሞ በፀሐፊ ትእዛዛቸው አድርገው በወቅቱ ለነበረው ንጉስ ስመ ገናናነት በሚሰጥ መልኩ ይፅፉትነበር: ሲፃፍም ለንጉሱ ደካማ ነገር የማይገልፅ ለንጉሱ ብቻ ያልሰራው ሁሉ ሰርቷል ብለው በመደርደር በማሞገስናማሽሞንሞን ወርቃማ ታሪክ ይለጥፉለታል: የነዚህ ባልሰሩት ታሪክ እንደሰሩት ቆጥረው የሚኮፈሱ: በሬድዮ በተለቪዥ'ን በጋዜጣ በፅሂት በመፅሐፍ በፎቶግራፍና ፖስተር በፊልም በትያትር ተቀናብሮ በመድረክ በትምህርት ቤቶች በምርጥ አዳራሾች በአድርባይ ፓናሊስቶች ይተረክላቸው ነበር: ጊዜው የታሪክ ሂደቱ የማይረዳ ወጣት ሕብረተሰብ ተደናግሮ ሊያመልክላቸው ይጀምራል: እነዛ ንጉሶችም ባልሰሩት ታሪክ በሕብረተሰቡ ተቀባይነት ሳላገኝ ዉሸት መሆኑ እያወቁ በመድረክ እየወጡ ጉራቸዉን ሲያሰራጩ ይታያሉ::

አሁን ባለነበት የዚህ ተመሳሳይ በሃገራችን ከኛ ዕድሜ በፊት የተፃፉ መፃሕፍት ስለሃፀይ ምንሊክ ሃፀይ ቴድሮስ ሃፀይ ዮሃንስ ራስ አሉላ አባነጋ የነ ንጉስ አባጅፋር የነ በላይ ዘለቀስለኦሮሞ የገዳ ስርዓት ወዘተ ብዙ መፃሕፍቶች ተፅፈዋል ፊልምና ትያትር ተሰርቶላቸዋል:እስከ አሁንም እየተፃላቸው ይገኛል::

እነዚህ ታሪካዊ ፅሑፎች አብዛኛቹ በዋናው የታሪክ ሥራ የተሳተፉ በሺ የሚቆጠሩ ታሪክ ሰሪ የጦር አበጋዞች መሪዎች አርቲስቶች የሳይንስ ተመራማሪዎች የታሪክ ተመራማሪዎች ወዘተ ታሪካቸው ደብዛው ጠፍቶ ብዙዉን ጊዜ በወቅቱ ቁንጮ ለነበሩ ብቻ ነው የሚፃፈው: ያ የሚፃፈዉም በጥናት ያልተመሰረተ አንድ አንድ ዘረኝነት የሚቀሰቅስ ሌላዉም የተሰራ ታሪክ አድበስብሰው ግልፅ ያልሆነ ወይም ያልተሟላ ታሪክ ነው ተዘግቦ የሚገኘው: እነዚህ የታሪክ ዉጤቶች የገዥዎች ተፅእኖ እንደ ነበራቸው ግልፅ ነው: የድሮ ነገስታትና ጀግኖች ታሪክ አፃፃፍ ካየን በአሁኑ ጊዜስ ምን ዐይነት የታሪክ አፃፃፍ ይታያል::

በአሁኑ ጊዜም ከ1960 ዓ.ም ወዲህ የ40 ዓመት ታሪክ ስመለከት የደርግ ስርዓት የኃይለስላሴና ተቃዋሚ የነበሩ ፖለቲካ ፓርቲዎች በሚመለከት የተለያዩ ፀሐፊዎች ስለኢ.ህ.አ.ፓ ስለግንባር ገድሊ ሓርነት ትግራይ: ስለተጋድሎ ሓርነት ትግራይ ጠረናፊት ኮሚቴ ስለኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሕብረት ኢ.ድ.ዩ ስለኦነግ ስለአብነግ ስለየዓፋር ፓርቲዎች ስለየጋንቤላ ፓርቲዎች ስለኢፐዴኤ ስለህ.ወ.ሓ.ት ስለቅንጅት ወዘተ ብዙየታሪክ መፃሕፍት ተፅፈዋል: ሌላ ቀርቶ ኮነሬል መንግስቱ ኃይለማርያም ፅፈዋል: በጋዜጣ በፊልም በኢኔት መልክ ተሰንደዋል: ከላይ የተዘረዘሩ ነገስታትና ፖለቲካ ፓርቲዎች ግለሰቦች መሪዎች ታሪክ ተፅፎላቸዋል ተገጥሞላቸዋል ለሁሉ ሲነገርላቸው እስከ አሁን ያየናቸው ፀሓፊዎች ገለልተኛ ሁነው በስልጣን ያለው ፓርቲና ከስልጣን ዉጭ ያለው አካል ደካማና ጠንካራ ጎናቸውን በትክክል ግልፅ በሆነ ሚዛናዊነት ያለው የሚፅፍ አልታየም: የሚፃፉ መፅሐፎች አንዳንዳቸው ፍፁም አድርባይነትና ለጥቅም የህዝብ ታሪክ የሚያስቀድሙ ሳይሆን ለጥቅም ለሽመት ለሽልማት ብለው ባለው መንግስት ሊወደዱ የሚጥሩ ናቸው::

ሌሎች ደግሞ በህዝቦች ስምምነት ፍቅር አንድነት የማይፈጥሩ ዘረኝነት የሚቀሰቅሱ የህዝቦች አንድነት የሚያላሉ አሉ: ቀጥለዉም በዘመኑ ተሰሚነትን ያላቸው ባለስልጣናት አጀቤ ሊባልላቸው በስልጣን ላሉት

ቁንጮዎች ለይተው በመምዘዝ ያልሰሩት ያልነበሩበት ያላዩት ያልሰሙት ጀግንነት ችሎታ ታታሪነት ለመስዋእት ቅሩቡነት የልማት አርበኛ የጦር መሃንዲስ የዲፕሎማሲ ፈር ቀያሽ የሰላም ሉኡክ ወዘተ በማለት የዉሸት ታሪክ የሚፅፉ አሉ::

እነዚህ የፅሕፈት ዉጤቶች በዘመኑ ባለስልጣኖች በትላልቅ ሆቴሎች እየተመረቁ የመንግስትና የፓርቲዎች ብዙሃን መገናኛዎች ሰፊ ሽፋን ይሰጣቸዋል::

ጥቂት ፀሐፊዎች የሚፅፉዋቸው የታሪክ መፃሕፍታች ተጠንቅቀው ትክክለኛ ባለታሪኮች ማሽል አድርገው የፃፉዋቸው አሉ: እነዚህ መፃሕፍቶች በገዢዎችና ደጋፊዎቻቸው በጭፍን በማጥላላት መሪዎች በምረቃው አይገኙም: ሌላ ቀርቶ በመንግስትና ፓርቲዎች ሬድዮ ጣብያዎች በተለይ ደግሞ በየጎጡ የሚገኙ ኤፍ ኤሞች ህዝብ እንዳያነባቸው ያጥላሉዋቸዋል: ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ በሃገራችን ያሉ ፀሐፊዎች ከነ መፃሕፍታቸው የቤትና የዳር ልጆች ሁነዋል: ሐቅ የፃፉ ፀሐፊዎች ጋዜጠኞች ታስረዋል ተከሰው በየ ፍርድ ቤቶች እየተንገላቱ ይገኛሉ::

ከላይ ያስቀመጥኩት መግቢያ ሃሳብ ያለ አንዳች ምክኒያት አይደለም: በሃገራችን ስለህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ታሪክ በተለይ ደግሞ ስለህ.ወ.ሓ.ት የ17 ዓመት የትጥቅ ትግል ስለየህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች የሚተርኩ ብዙ መፃሕፍት ተፅፈዋል: ከነዛ መፃሕፍት ዉስጥ የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች ሆን ብለው ተወዳጅነት ለማግኘትና በዛው ሰበብ ኢኮኖሚያዊ ችግራቸውን ለማረድ ሲሉ የትግራይ ህዝብና የታጋዮቹ ታሪክ በማበላሸት በትግሉ ወቅት ያልነበሩ (ቢኖሩም ያልሰሩት) ታሪክ በመለጠፍ ታሪክ እያበላሹ ይገኛሉ: እነዚህ የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎችና ካድሬዎች ያልሰሩትን ታሪክ የሚያበላሹ መፀሐፍቶች ተራራዎች ያንቀጠቀጠ ትውልድ በተለይ ገብረአብ ፅናት የሚል መፅሐፍ በሃይላይ ሐድጉ መርትዖ ፍኖተ ገድሊ በብስራት አማረ ባድመ እንደምክኒያት ወዘተ የሚባሉ መፃሕፍቶች የትግራይ ህዝብ የ17 ዓመት የትግል ዉጤት ያበላሹና በትግሉ ጊዜ

ያልሰሩትን ታሪክ ለግለ ሰቦች የሸለሙ: ያልተሰራ ያልተነገረ ታሪክ በመፃፍ የዉሸት ታሪክ የተፃፈባቸው ናቸው: እነዚህ መፃሕፍት የህ.ወ.ሓ.ት ጉዞ የሚያውቅ ህዝብና ታጋይ እጅጉን የተጠሉ ናቸው: ስለዚህ እነዚህ መፃሕፍቶች በፃሐፊ ትእዛዞች የተፃፉና የህዝብ ታሪክ የማያንፀባርቁ ናቸው::

ላይ የተዘረዘሩ መፅሐፎች የተበላሹና ተቀባይነት የሌላቸው ቢሆኑም የአሁኑ የባሰ ግን ከጠ/ሚኒስተር መለስ ሞት ተያይዞ የሚፃፉ ያሉ መፅሂቶች፣ መፃሕፍቶች፣ ጋዜጦች፣ ፖስተሮች፣ ፎቶግራፎች፣ ፊልሞች፣ ትያትሮች እየሰሩና እየፃፉ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የ17 ዓመት ትግልና የ21 ዓመት የስልጣን ዘመኑ የተሰሩ ሁሉ በሚልዮን የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች የትግል ዉጤት እያለ በተጨማሪ የብዙ ሙሁራንና ተመራማሪዎች ፈላስፋዎች የሥራ ዉጤት ለጠ/ሚኒስተር መለስ ጠቅልለው ሲሰጡ ታዩ: ይህ ደግሞ የቀዳሞቹ የመሳፍንት ፀሐፊ ትእዛዞች አፃፃፍ መፃሕፍት በአሁኑ 21ኛው ክፍለ ዘመን በተጠናከረ እየደገሙት ይገኛሉ: ይህ ደግሞ አስፈሪና ታሪክን ወሮ ባለታሪክ ላልሆነ አካል መስጠት ነው::

ለዚሁ እንደማስረጃ አዲስ ራዕይ 8ኛ ዓመት ቅፅ 4 ልዩ እትም የኢትዮጵያ ህዝቦች አቢዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ) የንድፍ ሃሳብ መፅሂት: መለስ ለሰው ልጆች ምቾት የተፋለመ የዘመን ስብእና የሚል:በተጨማሪ መለስ ብዙሃንነት ከአግባቡ ያስተናገደ የእኩልነት አራማጅ በመፅሂቱ ጀርባ የተፃፈ: በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ህዝብ ግንኙነት ክፍል የተዘጋጀ መፅሂት 80ገፅ ዋጋው 100 ብር: ካነበብኩ በኋላ በመፅሂቱ የተሰነደ ታሪክ የ38 ዓመት የኢትዮጵያ ህዝቦች ታሪክ በሙሉ ለመለስ ጠቅለል አድርጎ ከመስጠት አልፎ እጅግ ብዙ መሰረታዊ የሆኑ ታሪኮች በማዝበት መለስ ይቅር ሊሰሩት የማያውቁት በህ.ወ.ሓ.ት ዉስጥ ያልተሰሩት በፀሐፊ ትእዛዞች ተሰንደው ሲቀርቡ ይህ ታሪክ ለመለስ መሰጠቱ ፍትሃዊ ስለአልሆነ ሐቁን መገለፅ አለበት ብየ ስለአመንኩ በመፅሐፍ (መፅሂት) ተሰንደው ያሉ ዉሸቶች 3 ወይም ከዛ

በላይ መፃሕፍት ሊፃፍበት የሚችል ቢሆንም እስቲ ቀንጨብ ቀንጨብ አድርጌ ሐቁን ለማስቀመጥ ልሞክር በማለት እነሆ ገፀ በረከት ለአንባብያን::

ይህ መፅሂት ባለፉት 8 ዓመታት በየ ሁለት ወር የሚታተም ሆኖ መፅሂቱ ከተመሰረተ ጀምሮ መለስ ከአዘጋጆች አንዱ ነበሩ: ያልተሳተፉበት መለስ ከሞቱ በኋላ የታተመች እቺ ብቻ ናት: የዚህ መፅሐፍ ይዘት ቀጥሎ በሰፊው ይቀርባል::

## ክፍል1

ህ.ወ.ሓ.ት የሚባል ፓርቲ ከ1967 ዓ.ም በፊት የነበሩ ጨቋኝ ገዢዎች በፈጠሩት አስከፊ ብዝበዛና ሰቆቃ ኢፍትሃዊ የተበላሸ አስተዳደር በመኖሩ ብሶት የወለደው ነበር: ህ.ወ.ሓ.ት ከመጀመርያ ትጥቅ ትግል ለመጀመር በረሃ ከመዝመቱ በፊት እንቅስቃሴው በሃገር ደረጃ ከነበረው ቀደም ሲል የዘውዳዊ ጭቆና አገዛዝ ኋላም የደርግ ፋሽሽታዊ ስርዓት ይቃወሙ ከነበሩ ኃይሎች አብሮ በመሰለፍ ሚናዉን ተጫውተዋል: ቆየት ብሎ በሃገር ደረጃ ከነበረዉ አሰላለፍ ራሱን አግልሎ የራሱን የትግል ንድፈ ሃሳብ ይዞ ነፍጥ አንስቶ ፀረ ገዢዎች ለመታገል በረሃ ወጣ: ህ.ወ.ሓ.ት ወደ ትጥቅ ትግል ሲዘምት በአጠቃላይ ለዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት መጠበቅ በሃገራችን ህዝባዊ መንግስት ይመስረት እጅጉን አጥብቆ ያነሳው እስከ ዛሬም ያልተለየዉ ሃገራዊ ኃላፊነት የጐደለዉ የኢርትራ መገንጠል የሚል አቋም አጥብቆ ይዞት የነበረ ነው: ህ.ወ.ሓ.ት ከጅምሩ ለኢትዮጵያ ህዝብ ፍትህ ነፃነት ዴሞክራሲ እታገላለሁ የሚል ሃሳብ ይኑረው እንጂ በተግባር ግን ለሻዕብያ አጠናክሮ ኢርትራ ለመገንጠል የተሰራ ፓርቲ ነበር::

ህ.ወ.ሓ.ት ከ1967 እስከ 1983 ዓ.ም ደርግ እስከ ተወገደበት ዕለት ድረስ አንድ ታሪክ ሰርተዋል: ከዚያ በኋላም ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በሚል ስም መንግስት መሰረተ እነሆ እስከ የጠ/ሚኒስተር መለስ ሞት ድረስ ሁለት ምዕራፎች አልፈዋል: ሶስተኛው ምዕራፍ የመለስን ለጋሲ legacy

(ውርስ) እንከተላለን አንጓዛለን ይሉናል: ከዛ አልፎ መለስ አልሞተም አሁንም በሙውት መንፈስ ይመራናል የሚሉ መሪዎች አይተናል::

በነዚህ ሶስት ምዕራፎች የነበረዉና ያለዉ አመራር: አንደኛና ሁለተኛ ምዕራፍ የጦርነትና የሰላም አመራር በሙሉ ጠ/ሚኒስተር መለስ ብቻቸውና ለብቻቸው እየመሩን እንደመጡ ታሪክ ሲነግሩን አሁን ላለዉ የመጨረሻ ምዕራፍ ደግሞ እነ ጠ/ሚኒስተር ኃይለማርያም ደሳለኝ ጠ/ሚኒስተር መለስ በሞት ቢለዩም ከ40 ዓመት እስከ 50 ዓመት የሚያሰራ መመርያ አስቀምጠዉልናል አሁንም አልሞቱም በመንፈስ እየመሩን ነው ያሉ ብለዉናል: ይህ አባባል ጌታ እየሱስ ክርስቶስ ሞተ ተሰቀለ ወረደ ዓይነት አዎ የመለስ አምልኮት እየነገሩን ይገኛሉ::

የህ.ወ.ሓ.ት የ17 ዓመት የትጥቅ ትግል በመቶ ሺ የሚቆጠሩ የትግራይ ወጣት ህዝብ ሃብትና ንብረት ያለቀበት: ከመለስ ዜናዊ የበለጡ ለሳቸው ይመሩ የነበሩ ጀግኖች የተሰዉበት አካላቸው የጐደለበት በአጠቃላይ ብዙ ታሪክ ሰሪዎች ያለፉበት የጀግኖች የድል ዉጤት እያለ ጠ/ሚኒስተር መለስ ዜናዊ ራሳቸው የሰሩት ታሪክ ከኖረ እንደመተረክ ፈንታ የጀግኖች ሥራ ምርምር ፍልስፍና ዉጤት መስጠት በትግሉ ጊዜ የነበሩ ታጋዮች የህዝብ ምልሻዎች የሲቪል ካድሬዎች አይቀበሉቱም: የመለስ ታሪክ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ::

ሌላ የደርግ ከስልጣን መውረድ ዉጤት ምንም እንኳ በደርግና ህ.ወ.ሓ.ት ወታደራዊ ጥቃት በዉስጣቸው የነበረ ችግር ቢከስምም እነዛ ፓርቲዎች እስከሚጠፉ ደርግን ለመጣል ባደረጉት ትንቅንቅ ብዙ መስዋእት ከፍለዋል: እነዚህ ድርጅቶች ለደርግ መታገል ብቻ ሳይሆን እስከ አሁንም በትግል ላይ ይገኛሉ ለዚሁ ማረጋገጫ ኦነግና ሌሎችም አሉ: ከ1983 ዓ.ም እስከ የመለስ ህልፈተ ሞት ያለ የልማት ሰራዊት ጭምር ምርጥ ፍልስፍና ዕድገት ዉጤቶች በሃገራችን ያሉ ባለሙያዎች ተመራማሪና ፈላስፎች የሥራ ዉጤቶች እያለ ሁሉም ነገር 21 ዓመት ሙሉ የተሰራ አድካሚ ሥራዎች ዉጤት መለስ ዜናዊ ብቻቸው ለብቻቸ ው ታሪክ እንደሰሩ በዚህች ሃገራችን ያሉ ሙሁራን 21 ዓመታት ሙሉ

*ምንም ነገር እንዳልሰሩ አድረጎ የሚያስቀምጥ ሌላ ቀርቶ ለመለስ ዜናዊ የሚመሩ ካቢናቸው ጭምር ምንም የማይሰሩ እንደነበሩ የአምልኮት ታሪክን እየነገሩን ይገኛሉ: ላይ ከተቀመጡ የሶስት ምዕራፎች የ38 ዓመታት አመራር ፍልስፍና ምርምር ባለራዕይ ብቻቸው ነበሩ የሚለው የታሪክን ሞኖፖሊ ለሁሉም ህዝብ አግራሞት ፈጥሮለት ያለዉ: ለኔ ያስጨነቀኝና ያሳሰበኝ በነዚህ 38 ዓመታት የትግልና የልማት ዘመናት የተሰሩ የተባሉ ሁሉ አብዛኛቹ ስራዎች ማን ፈለሰፋቸው ምርምሮችስ የማን ናቸው ማን ነበር ጀግና የሚሉ ሁሉ የማወቃቸው በአካል የነበርኩበ ት ያየሁዋቸው በመሆናቸው ማን ነበረ ጀግና የሚሉ ሁሉ የማወቃቸው ብዙ ነገሮች ለማሰብ ተገደድኩ: በተለይ ያሳሰበኝ ጊዜው እየረዘመ በሄደ ቁጥር የኢትዮጵያ ታሪክ እየተቀየረ ያልነበሩ ያልሰሩ ታሪክ እንደ ሽልማት የሚቸርላቸው ታሪክ በተደጋጋሚ የዉሸት ዘመቻ እንደሚገነባ አረጋገጥኩ::*

*ወገኖቼ ላይ ያስቀመጥኩት መንደርደርያ ሃሳብ ዝም ብየ አይደለሁም: ጠ/ሚኒስተር መለስ ህመምና ከህልፈተ ሞታቸዉም በኋላ ያለዉ ብዙ ተነግረዋል ቆየት ብሎም ደግሞ ሰው ሁሉ ያስገረመ ነገር ስለአዲስ ራዕይ የሚል መፅሄት የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ካድሬዎች ልሳን በሆነዉ 80 ገፅ ያለዉ መፅሄት ነው: መለስ ለሰው ልጆች ምቹ እንዲሆን የታለመ የዘመን ስብእና በአንድ ገፅ በሌላ ገፅ ሽፋኑ ደግሞ መለስ ብዙሃኑን ከአግባቡ የአስተናግዶ የእኩልነትን አራማጅ የሚል ሆኖ በሽፋኑ ጊርጌ ዋጋዉ 100 ብር ይላል: መፅሐፉ አግኝቸ በዝርዝር አነበብኩት ደግሜ አነበብኩት አንድ ጥያቄ ግን መጣልኝ 17 ዓመታት የተከፈለ መስዋእት እንዴት ለመለስ አምልኮ ብቻ ነበር ብየ ጠየቅኩ አሰብኩ አሰብኩ በዚህ ጊዜ እኔም የህ.ወ.ሓ.ት ታሪክ ሓቅን በመፅሐፍ መልስ መስጠት አለብኝ የሚል ሃሳብ መጣልኝ: ያቺ ገደብ ደግሞ አለች ግን አልቻልኩም ደጊሜ አሰብኩና እነዚህ ሰዎች እነ ማን ናቸው: መለስ ባልሰራዉ ታሪክ አምልኮት የሚያሰርፁ የሚፃፍ ከአሁን በፊት የትግራይ ህዝብ የ17 ዓመት መራራ ትግልና ከባድ መስዋእት የተከፈለበት ሃይላይ ሓድጉ የሚባል ለስዩም መስፍን አምልኮ*

*የሚያሳድር የዉሸት መፅሐፍ ፅፈዋል: ስንት ጊዜ ታሪካችን ይበረዝና ይነጠቅ? እንቢ ለዉሸት ታሪክ አላመልክም ብየ መለስን እንደጌታችን እየሱስ ክርስቶስ የሚያመልክ መፅሐፍ ሓቁና ዉሸቱ ይገለጥ በማለት መልስ ለመስጠት ወሰንኩ::*

*የተከበራቹሁ ወገኖቹ ይህ መፅሐፍ ለመፀፃፍ የተገደድኩት ታሪኩ ከህ.ወ.ሓ.ት ታሪክ ጋር ስለሚያያዝ ህ.ወ.ሓ.ት ከተመሰረተበት እስከ የመለስ ህልፈተ ሞት ድረስ እኔ የማውቀው ያየሁት በአካል የነበርኩበት ብቻ እፅፋለሁ: ሌላ የጐደለ የሚያውቁት ዜጎች ራሳቸው ይፃፉ ወደ ዋና ታሪክ ከመግባቴ በፊት ግን መጀመርያ ስለመለስ ህመምና ህልፈቱ ቀጥሎ ስለመለስ አምልኮት የሚተነትን መፅሐፍ በዝርዝር ገፅ በገፅ በአንቀፅና በመስመር መልስ ለመስጠት እሞክራለሁ::*

## ***<u>የመለስ ህመም ለምን ግልፅ አልሆነም?</u>***

*በማንም ሃገር የመንግስት ባለስልጣን ርእሰ ቢሄሮች ሲታመሙ አደጋ ሲያጋጥማቸው ሲሞቱ ይቅርና የሃገራቸው ህዝብ ለዓለም አይደበቅም:: እንደአብነት በቅርብ ጊዜ የጋና መሪ ታመሙ ወድያዉ ለህዝብና ለዓለም ህዝቦች ተሰራጭተዋል የአመሪካ ዉጭ ጉዳይ ሚኒስተር ሄራሊ ኪሊንቶን ጭንቅላታቸው ህመም አጋጥሞዋቸው ሰዓታት በማይሞላ ጊዜ የአመሪካ ህዝብ አውቀዋል: የደቡብ አፍሪካ ለዴሞክራሲና ፀረ አፓርታይድ ዘረኝንነት ታግለዉ ነፃ ያወጡ ማንዴላ በ94 ዓመት ዕድሜያቸው ታመዉ ተብለው ለደቡብ አፍሪካ ህዝብ ይፋ ሆኖ ህዝባቸዉም ያከበራቸ ው ስለሆነ ጤናቸዉን በመመኘት በየ ሃይማኖቱ የፀሎት ማእከል ፀሎት ተደረገላቸው::*

*የሃገራችን መሪ መለስ ዜናዊ ህመም ግን የኢትዮጵያ ህዝብ በተለያየ መንገድ የታመሙ መሆናቸው እያወቀ ህወሓቶች ግን የማይደበቅ ነገር ደበቁት: የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ታመዉ ዉጭ ሃገር ሄደው የአልጋ ኀደኛ*

ከመሆናቸው በፊት ወደ ዉጭ ለሥራ ምክኒያት ደርሰው ሲመለሱ ለመጨረሻ ጊዜ ታመው በድብቅ ሄደዉ የተኙባት ዋዜማ ሰዉነታቸው ቀንሶ ፊታቸው ገርጥጦ አይቶ እነኚህ ሰዉየ ታመዋል ብሎ ትእዝብቱን ገለፀ: ምክኒያቱም ከዚያ በፊት መለስ ዉጭ ሃገር ደርሰዉ ሲመለሱ ቀልተዉና ወፍረዉ ነበር የሚመለሱ: መለስ አመሪካና መክሲኮ ደርሰዉ ከተመለሱ ግን ድምፃቸው ጠፍቶ ከተለቪዥን መስኮት ተሰወሩ::

የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች ከበረሃ ይዘዉት የመጡ ሚስጢር የመደበቅ ልምድ: በመለስ ህመም የማይደበቅ ጊዜው የተክኖሎጂ ዘመን መሆኑ ዘንግተው ደበቁት: እሳቸው የሚያስታምሙ ሚስታቸው አዜብ መስፍን ብርሃነና ገ/ክርስቶስ ካልሆነ ሌሎች የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎች ግን ጆሮ ከባለቤቱ ባዐድ ነው እንደሚባለው የሚያውቁት ነገር አልነበረም: ሌላ ቀርቶ ታመዉ ወደ በልጆም ሃገር ሲሄዱ እስኪመለሱ ድረስ ሃገሪቱ የሚመራት ወክለዉ አልሄዱም እንዴት ነው ሕገ መንግስቱ ሲፀድቅ የምክትል ጠ/ሚኒስተር ስልጣን በግልፅ ባለመቀመጡ ያለፈው ኃይለማርያም ደሳለኝም ስልጣናቸው ስለአልተቀመጠላቸው ደንበር በር ተፈጠረ: አንድ አንድ ምልክት ግን ይታይ ነበር እነሱም እንደነ በረከት ስምኦን ያሉ በተለቪዥን ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ::

በማኸሉ ግን በሓምሌ 2004 ዓ.ም ጠ/ሚኒስተር መለስ በበልጆም ብራሰልስ ከተማ በአንድ የካንሰር ህክምና ሆስፒታል ሞቱ ተብሎ ሚስጢሩ በኢሳት ተለቪዥንና ሬድዮ ጣብያ አፈትልኮ ወጣና ለዓለም ተሰራጨ በእንተርኔትም ህዝቡ አወቀዉ: የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች ግን የመለስን ህመም ደብቀው ቆይተው በሃገር ዉስጥና በዉጭ ብዙሃን መገናኛ ብቅ እያሉ መለስ ታመው ነበር ከህመማቸው አገግመው ከጥቂት ቀን በኋላ ተመልሰው ምድብ ሥራቸዉን ሊጀምሩ ነው ይላሉ: ሌላ ደግሞ መለስ ታመዉ ከነበሩበት ሆስፒታል ወጥተው ካረፉበት ሆቴል ከሁለቱ ሱዳን አስታራቂዎች ስለእርቁ በስልክ ተናጋግረዋል: በእርቁ እንደሚገኙ ተነጋግረዋል ስለሶማል ምርጫም እጅጉን ስለሚያሳስባቸው ኬንያና ኡጋንዳ መሪዎች ተነጋግረዋል የሚል ወሬ ይነዛል::

ቆየት ብሎ መለስ መሞታቸው ተጧጧፈ ወሬው ሃገር ተናጠች ሪፖርተር ጋዜጣ ምንም መረጃ የሌለው ዓላማው ምን እንደሆነ የማይታወቅ ባሳተመው ጋዜጣ መለስ ከነበራቸው ህመም ድነው ከባለቤታቸውና ልጆቻቸው ጋር አመሪካ ሂደው እርፍታቸው እየወሰዱ ነው አለ:: ህዝቡ ግራ ተጋባ::

መለስ ሙተዋል ተብሎ መርዶ ሊነገር ሳምንታት ሲቀሩት አቶ ስብሃት ነጋ በድምፅ ሬድዮ አመሪካ ተጠየቀው ሲመልሱ ምንም መንደርደርያ ሃሳብ የሌላቸው መለስ ቢሞት ፈይሳ ይተከዋል ፈይሳ ቢሞት በቀለ ይተከዋል በቀለ ቢሞት ፈጡማ ብትሞት ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የሚባል ፓርቲና መንግስት እስካለ ምንም ችግር አይፈጥርም አሉ: የአቦይ ስብሃት የአሽሙር አነጋገር የሚያውቅ ሁሉ መለስ እንደሞተ አረጋገጠ: አቦይ ስብሃት ቀጥሎ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስተር ቃለ አቀበይ ዲናሞ በረከት ሶምኦን ደግመዉ መለስ የዓመት የፓርላማ መዝጊያ ተገኝተው ባጀት ያፀድቃሉ አሉ: ለኢትዮጵያ ሁሉም ዐይነት መረጃ ተዘጋው::

የህ.ወ.ሓ.ት ከፍተኛ ካድሬዎች ደግሞ በበረከት ሶምኦን በደመቀ መኮነን በአባዱላ ገመዳ በአዲሱ ለገሰ በብርሃነ ፍትህ ሚኒስተር በስብሃት ነጋ በዉጭ ጉዳይ ሚኒስተር ቃል አቀባይ መግለጫዎች እጅጉን ይሰራጩ አሉ: አንድ ቀን ወደ አንድ የትግራይ ክልል ትልቅ ቢሮ ለሥራ ሄድኩ የፈለግኩት የቢሮው ኃላፊ ነው: ሄድኩና ፀሐፊዋ ስልክ ይዘዋል ቁጭ ብለህ ጠብቅ አለችኝ እኔም ቁጭ አልኩኝ: ኃላፊው ቢሮዋቸው ገጥሞው ሳይዘጉት ጮህ ብለው በስልክ ይነጋገሩሉ ከሳቸው የሚነጋገር ሰው ለማወቅ አይቻልም: ግን ከኔ ጋር የነበሩ የቢሮ ኃላፊ እነኚ ምን ስሩልኝ የሚሉ ምንድነው የሚሉ ያሉ ሃዘናችን በሰላም እንዳናካሂድ እየረበሹን ናቸው በተለይ ደግሞ በረከት ስምኦንና እቲ አረጊት ሰብኣይ (ያረጀ ሰዉዬ) ትእግስት እንዲያደርጉ ለምን አንድ አታደርጉም ሲሉ ሰማሁ: ከዚያ በኋላ ያናጋገው ያለው ሰው ጠርቶት ነው መሰለኝ ተጨንቀ ው ሆኖ እኔን የፈለኩት ጉዳይ ሳያናጋግረኝ ሄደ: ይህ የሚያመለክተዉ

መለስ ዜናዊ የኢሳት ተለቪዥ'ን ያፈተለከው ሚስጢር መሞታቸው ሃቂ መሆኑ የሚያረጋግጥ ነገር ነው አልኩኝ ከዚያ እኔ ወደ ሥራዬ ሂድኩኝ::

የፍትህ ጋዜጣ ትንበያም በተደጋጋሚ ይወጣል: ይወጡ የነበሩ ትንበያዎች ለህ.ወ.ሓ.ት ኢሃዲጎች ካድሬዎች ይመሩዋቸው የነበሩ መጨረሻዉም ፍትህ ጋዜጣ አዘጋጆች 40ሺ እንዳሳተሙ በኢትዮጵያ ፍትህ ሚኒስተር ታያዘ ፍትህ ጋዜጣም ታገደች: ቆየት ብሎም ፍነተ ነፃነት ተዘጋጀች ህዝብ ያስተነፍስባቸው የነበረ ጋዜጦች ተዘጉ: በአጠቃላይ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎች የሚይዙት የሚጨብጡት አጡ: ሁሉም እርሱ በእርሱ የሚጣረስ መግለጫ ይሰጣሉ እርስ ብእርሳቸው ይጋጫሉ ጭራሽም ወደ ጭልምልም ገቡ::

# ለሃዘን ዝግጅት

የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎች ከብዙ ጭንቅንቅ በኋላ አማካሪ አግኝተው ነው መሰል ቀድሞ ካለዉ ጠ/ሚኒስተር በሃገር ደረጃ ታዋቂና ከፍተኛ የሚኒስተርነት ስልጣናቸው ቀምተው ታች አውርደው በአንባሳደርነት ጥሎዋቸው የነበሩ አንጋፋ መሪዎች: እነ ግርማ ብሩ ስዩም መስፍን ተሾመ ቶጋ ተቀዳ ዓለሙ ሙሉጌታ ዓለምሰገድ ተገልለዉ የነበሩ አቶ አባይ ፀሃዬ ሌሎችም ታማኝ ሚኒስቴሮች: የክልል መሪዎች በተለይ የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ በአዲስ አበባ ቤተመንግስት ተሰባሰቡ: የአንባሳደሮች ዓመታዊ ስብሰባ በሚል ሽፋን ድብቅ ስብሰባ ያደርጉ ነበር::

ከሚኒስቴሮችና አንባሳደሮች ስብሰባ ጎን ለጎን የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ታማኝ ጋዜጠኞች በድብቅ ለስልጠና ተብለው በባህርዳር ተሰባሰቡ: በበረከት ስምኦንና ሌሎች የህ.ወ.ሓ.ት ባለስልጣኖች በስብሰባው ተገኙ: ስለጠናዉ በግልፅ የሚታወቅ አልነበረም: ከስብሰባዉ ዉስጥ ግን ሽልኮው የወጡ ሚስጢሮች ነበሩ: የሸሎኩ ሚስጢሮቹም መለስ ስለትርፈ የማረፋቸው ጉዳይ ለሁሉ ሰው እንደሚደርስ ሞት ቢሆንም አሁን የመለስ ሞት ለሃገራችን የወደፊት እጣ የተቃና እንዲሆን በኢትዮጵያ ህዝብ ተቀባይነ

ት አጊኝቶ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ እንዴት ታማኝነት እንደሚያገኝ በማትኮር በመለስ አገዛዝ የተገኙ ሁለገብ እድገትና ለዉጥ ህዝቡ አውቆ በምሬት እንድያዝን አድረገን የኢ.ህ.አ.ዴ.ግና ለቀረዉ አመራር ታማኝነት ለማግኘት ያተኮረ የፖለቲካ ቅስቀሳ አቅጣጫ እንዲቀይሱ ለተመለመሉ የመንግስትና የፓርቲዎች ብዙሃን መገናኛ በአንድ ወጥ የፕሮባጋንዳ ሥራ እንዲሰሩ ጥብቅ መመርያና እቅድ ተሰጣቸው: ከዚያ በኋላ በሁሉም የክልል ከተሞችና አዲስ አበባ በየ ክፍለ ከተሞች ሚስጢር ይጠበቃሉ ተብሎ: የታመነባቸው ምርጥ ካድሬዎችና ከፍተኛ የመሰረታዊ ድርጅት ኃላፊዎች በሚስጢር በህቡእ ቦታዎች ለመለስ ሞት መርዶ ተነገራቸው ስለአስከሬኑ አቀባበልና የቀብር ስነ ስርዓት አፈፃፀም በሚመለከት ሰፊ ማብራርያ ከተሰጠ በኋላ የመለስ ፎቶግራፎች ለሁሉ አዲስ አበባና ክልሎች ወረዳዎች እሰከ ቀበሌዎች ጭምር ተሰራጭተው እንዲቆዩ: ጥቁር ካናቴራዎች ጥቁር ሸሚዞችና ሱሬዎች ቆቦች ተዘጋጅተው ለህዝብ ሲሸጡ ፋብሪካዎች በፍጥነት ሰርተው እንዲያዘጋጁ በሁሉም የልብስ ሰፌዎች ሱቆች የሚገኙ ጥቁር ልብሶች ያላቸው ባለሱቆች እንዲጠሩና መርዶ እንዲነገራቸው ህዝብ እንዲገዛ ግፊት እንዲደረግ ታዘዘ ለዚህ ሁሉ ጥብቅ መመርያ እንዲሰጥ ተነገረ::

የመለስ ሞት (መርዶ) ከተነገረ በኋላ ተደራጅተዉ የቆዩ ካድሬዎች በፍጥነት በከተማም በገጠር ተሰራጭተዉ እስከ ቀበሌ በመውረድ ከቀበሌ ም አልፈዉ እስከ ጎጥና ቤት ቁጥር በመቀስቀስ ህፃናት ሳይቀሩ የሃዘኑ ተካፋይ እንዲሆኑ ጠንክረዉ እንዲሰሩ ተደረገ::

የመለስ ሞት በማያያዝ ብዙሃን መገናኛ የመንግስትና የፓርቲ ሚድያዎች ባለፉት የትጥቅ ትግልና 21 ዓመት የሰላም አገዛዝ የሚባሉ የተሰሩ ሥራዎች ምርምሮች ፍልስፍናዎች ፖሊሲዎች የዲፕሎማሲ ሥራዎች በሙሉ የመለስ ዉጤቶች ናቸው በሚል አቅጣጫ እንዲ ንቀሳቀሱ መመርያ ተሰጣቸው::

አስከሬኑ ሃገር ዉስጥ ገብቶ የቀብር ስነ ስርዓት እሰኪጠናቀቅ በማኻሉ ያለዉ ጊዜ እንደሚኖርም ተነገራቸው: መለስ መሞታቸው ከመነገሩ

በፊት ብዙ ጋዜጤኞች በመላዉ ሃገራችን እስከ ቀበሌ ካሜራቸዉ ይዘዉ ተሰማሩ: ብዙ የመንግስትና በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስር የሚገኙ የእርዳታ ድርጅቶች፣ የትእምት፣ ጥረት፣ አልማ፣ ድንሾ፣ ወ.ዘ.ተ: የመንግስት ማኪናዎች በተጨማሪ ተሰማሩ::

የዚህ ስምሪት የሚያስተባብሩ ከህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አመራር ተመደቡ: እነሱም በረከት ስምኦን፣ ስዩም መስፍን፣ አባይ ፀሃዬ፣ ካሳ ተክለብርሃን: ከፀጥታ ኃይሎች ጀነራል ሳሞራ የኑስ ከነ መዋቅራቸው፣ ከደህንነት ጌታቸው አሰፋ ብርሃነ ገክርስቶስ ተደራጅተዉ እንደሚመሩት ተነገረ: በክልሎችም በክልል አስተዳደር ፕረዘደንቶች የሚመሩት እስከ ቀበሌ ኮሚቴዎች ተዋቀሩ: የመጀመርያ ሃዘኑ እንዴት ይፈፀም የሚል ምእራፍ ተጠናቀቀ::

## መርዶ

የመለስ ህመም ተደብቆ ከቆየ በኋላ በነሐሴ 15/2005 ዓ.ም 12 ሰዓት በኢትዮጵያ ተለቪዥን ተነገረን: ህዝቡ አብዛኛው በዝምታ የሚገለፅ ካልሆነ በስተቀር ከጥቂት ዜጎች በስተቀር መጀመርያ ቀን ሃዘኑ ብዙም አልነበረም: ይሁን እንጂ በ15/12/2005 ዓ.ም ሙሉ ቀን ከሃገር እስከ ቀበሌ የመንግስት ሰራተኞች፣ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ካድሬዎች በህዝቡ በማሕበራት፣ በዕድሜ ባለፀጋዎች ቤት ለቤት እየሄዱ በሃዘን ሜዳዎች እንዲወጡ ማስገደድ አይባል በፍላጎት አይባል እንዲወጣ ተደረገ: በተለይ በከተማ ማን ወደ ሃዘን ወጣ ማን አልወጣም የሚል የሚከታተሉ ማንነታቸው የማይታወቅ (ጀሮደግፍ) የሚል ስም የተሰጣቸ ው በየ ቀበሌ፣ የንግድ ማእከሎች፣ በሻሂ ቤቶች፣ ቡና ቤቶች፣ በካፌዎች ብዙ ሰው የሚሰበሰብባቸው ስፍራዎች፣ በመጠጥ ቤቶች እየ ዞሩ ፎቶግራፍ የሚስሉ ነበሩ: በመንግስትና በግል መስርያ ቤቶች የሥራ ቦታዎች የሚገኙ ሰራተኞችም መነጋገር የሚባል ነገር አይታይም ሰው ሁሉ ዐይን ለዐይን ይተያያል እንጂ አይናገርም::

ከ17/12/2005 ዓ.ም ጀምሮ መለስ ግብአተ መሬት እስከ ገቡ ድረስ በሁሉም የወረዳ ከተማዎች፣ በቀበሌዎች፣ ቤተክርስቲያኖች ሃዘኑ ተጧጧፈ: በቀን ሰልፍ ፖስተር ፎቶግራፎች ተዘረጉ በንዴራም በቁጥር ይለያሉ እንጂ ባንዴራ በማውጣት የተለመደ ነው: በቀብር አለቃቀስ በክልሎች ሕግ ይከለከላል በመለስ ግን ሕግ ሁሉ ተጣሰና አስለቃሾች የት አሉ እየተባሉ ተጠሩ ጥቁር ቆብ ተደረገላቸው በሚልዮን የሚቆጠር ካናቴራ ተገዛ የተገዙ ጥቁር ካናቴራዎች፣ ሸሚዞች፣ ሱሪ ተለበሰ፣ ጥቁር ቆብም ተደረገ: ሃዘኑ በቀን ብቻ ያበቃ አልነበረም ማታም ጥዋፍና ሻማ በማብራት ሰልፍ ወጣ: ለጥዋፍ መግዣም ልክ እንደጥቁር ልብስና ፖስተር በብዙ ሚልዮን የሃገር ሃብት እንደጠፋ ለጥዋፍም ብዙ ሚልዮን ወጪ ሆኖዋል: የ80 ሚልዮን ህዝብ የ14 ቀን ሃዘን ሥራን ትቶ ሰልፍ ውጥቶዋል ብዙ ነዳጅ ባክነዋል እረ ስንቱ በገንዘብ ቢታሰብ እጅጉን ብዙ ነው: በኢትዮጵያ ያሉ መኪኖች ባጃጅ ጋሪ ወ.ዘ.ተ ለሃዘን በሰልፍ ወጥተዋል ብዙ ነዳጅ ባክነዋል የሃገር አቋራጭ አዉቶቡሶች የከተማ ታክሲዎች የቅርብ ርቀት አዉቶቡሶች ሰልፍ በመውጣት ብዙ ከስረዋል::

የመንግስትና የፖለቲካ ፓርቲ መገናኛ ብዙሃን በተሰጣቸው የፕሮፓጋንዳ አቅጣጫ መሰረት ቅስቀሳቸው አጧጧፉት: በቅስቀሳቸው ያስተጋቡት የነበሩ መለስ በ17 ዓመት የትጥቅ ትግል ወታደራዊ ፖለቲካዊ መሃንድስ ነበር መለስ ህ.ወ.ሓ.ትን ፈጥረው አሳድገው ኢ.ህ.አ.ዴ.ግን መርተው ደርግን ያስወገዱ ፖለቲከኛ ናቸው: ከደርግ ማስወገድ በኋላም ብቻቸውና ለብቻቸው ለዚህች ሃገር መርተው በሃገራችን መብራት አልፎም የአፍሪካ ፈላስፋና አባት በማለት የመለስ አምልኮትን አሰረፁ::

የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎች እነ አባይ ፀሃዬ፣ ስዩም መስፍን፣ በረከት ስምኦን፣ አዲሱ ለገሰ፣ ካሳ ተክለብርሃን፣ ጀነራል ሳሞራ የኑስ፣ ጀነራል ሰዓረ መኮነን፣ በ10ሺ የሚቆጠሩ የህ.ወ.ሓ.ት ታጋዮችና ጀግና የሰራዉ ታሪክ ጠቅለል አድርገው ለመለስ ሲሰጡ በመድረክ ታየ: የህ.ወ.ሓ.ት ጉዞ የሚያውቁ ዜጎቹም ምንም እንኳን ሃቁን

ለመናገር ሞራል ባይኖራቸው ሃቁን ባለመናገራቸው ትልቅ የታሪክ ስህተት ፈፀሙ::

የመለስ አስከሬን ለመቀበልም ያለ ብዙ ቀናት ተደራጅቶ በከፍተኛ መሪዎች በድብቅ ቅስቀሳ ሲሰጡ የሰነበተ ወጣት የአካባቢያቸው ቀበሌ ወጣቶች በተለያዩ መንገዶች በመሰባሰብ ታማኝ የመንግስት ሰራተኞች፣ የፖለስ፣ የሃገር መከላከያ ሚኒስተር፣ ወታደሮች የሲቪል ልብስ በማልበስ፣ የሃገራችን የደህንነት አባላት፣ ከክልሎች ሳይቀር በማስመጣት የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ወጣት ሊግ ፆታ በማይለይ፣ የቀበሌ ታማኝ ሴቶች፣ እንዲሁም የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ታማኝ ማህበራት፣ ከቤተ መንግስት እስከ ቦሌ አዉሮፕላን ማረፍያ ዘርግተቶ በመቆየት የአቀበቀበል ስነ ስርዓት ተደረገ: ተዘጋጅቶ የሰነበተ ፖስተር ፎቶግራፍ ሞፈክር በሌሊቱ መውጣት ተጀመረ: የአቀባበሉ ዝግጅት ለረጂም ሳምንታት ጊዜ ተወስዶ የተዘጋጀ እንደሆነ ግልፅ ነበር: በተቀባይ ህዝብ የነበረ መፈክር መለስ አልሞተም አሁንም መሪያችን ነው ለወደፊትም መሪያችን ነው: መለስ አሁንም ለ50 ዓመት ሊመራን ነው: መለስ አባይ የደፈረ ጀግና አይሞትም ጀግና አይኖርም የተምታታ ዓለም የመሰከረለት ጀግና መለስ ያፈራች መሬት ክርንትት (አቃቂማ) አይበቅላትም: መለስ ለኢትዮጵያ ለአፍሪካ ረእይ ያለመሪ ነበር: መለስ የሰላም አባት መለስ የአፍሪካ ሞዴል መሪ ወ.ዘ.ተ የሚሉ ሞፎክሮች ነበሩ::

አስከሬኑ አዲስ አበባ ቤተ መንግስት እንዳረፈ በነጋታዉ በሃገር ደረጃ ተዘጋጅቶ የቆየ የመለስ ፎቶግራፍ የተለጠፈበት ጥቁር ካናቴራና ሸሚዝ ሁሉም የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አካላት ሁሉ ለበሱ የማይናቅ ቁጥር ያለው ተራ ህዝብም አዝኖ ካናቴራው ለበሰው: አብዛኛው ወጣትም እንደፋሽን አድረጎው ለብሰው ወጡ: ተሰራጭቶ የቆየ ትላልቅ ፖስቶሮች በመላው የሃገራችን ከተሞች በየ ጎዳናው ተዘረጉ::

በብዙ ሚልዮን የሚቆጠር መለስ 38 ዓመታት የተሳሉትን ፎቶግራፎች በሙሉ የህ.ወ.ሓ.ት ንብረት መሆኑ የሚታወቅ ሜጋ ህትመት በመቀሌና አዲስ አበባ እየታተመ በአየርና ማኪናዎች መጓጓዣ ተጉዞ ህዝቡ

እንዲገዛው እየ ተሸጠ ነበር: በከተማም በቤት ቁጥር እየዞሩ ይሸጡት ነበሩ: ሌሎች የግል ህትመት ቤቶች ፎቶ ቤቶች የመለስ ፎቶግራፍ በማተም ተጠመዱ: በሰበቡ ደህና ገቢ አገኙ::

ህወሓቶች ለገነዘብ ማግኘት የነቁ ፓርቲ ሃዘኑ የመለስ ፎቶግራፍና ፖስተር በመቸብቸብ ብዙ ገቢ አገኙ: የሚገርመዉ የመለስ ሃዘን ተቀይሮ የገቢ ማግኛ ዜዴ ተጠቀሙበት: የሴቶ ጉዳይ በየ ክልሉ የሚገኙ የሴቶች ጉዳይ በማስተባበር ሴቶች ሁሉ ጥቁር ልብስ እንዲለብሱ የኩታቸው ጥለት ደፍተዉ እንዲለብሱ ተደረጉ: በአጠቃላይ መለስ አስከሬናቸው አዲስ አበባ ገብቶ ካረፈ እስከ ግብአተ መሬት ሊገቡ ዋዜማ የነበረ የሃዘን ሂደት ከላይ የተጠቀሱ ሁኔታዎች ነበሩ:በሌላበኩል በ17 ዓመት ከአንድ ቤት ከአንድ እስከ 4ና ከዛ በላይ ልጆቻቸው በትግሉ የሞቱባቸው ልጆቻቸ ውን የመለስ ታሪክሊገነቡ ነው ያለፈ በማለት ሃዘናቸው ተቀሰቀሰ::

## ለቀብር ዝግጅት

መለስ ዜናዊ አስከሬናቸው ወደ ሃገር ዉስጥ ከገባ ጀምሮ እስከ ግብአተ መሬት የሚገቡበት ዋዜማ የነበረዉ እንቅስቃሴ: ሃዘኑ እንደሽፋን ሆኖ ዋና ዓላማው ግን አሁን ያሉ መሪዎች መለስ ባለፉት 17 ዓመታት በትጥቅ ትግልና የ21 ዓመታት የልማት ዘመን የተሰሩ ሥራዎች እንደጥሩና ህዝብ ለሁሉም ነገር እንደተቀየረ እንደለማ የወደፊት ዕድሉ ብሩህ ተስፋ እንደሆነ በማመን ለወደፊት የሚኖሩ የሀ.ወ.ሓ.ት ኢ.ሀ.አ.ዴ.ግ መሪዎች በመለስ ስም ተቀባይነት እንዲኖራቸው ግምት ላይ ያስገባ የፖለቲካ ሥራ መስራት ዓላማ ያደረገ ነበር: በተለይ ደግሞ በተደረገዉ ፖለቲካዊ ዘመቻ ህዝቡ ሀ.ወ.ሓ.ት ኢ.ሀ.አ.ዴ.ግ ጥሩ ሰርተዋል ብሎ በጭፍን በዉሸት ህዝቡ በማደንቆር ሀ.ወ.ሓ.ት ኢ.ሀ.አ.ዴ.ግ በህዝብ እያደረሰ የመጣ ችግር አፈና ማሰር ማንገላታት መሰወር ነፃነት መንጠቅ ህዝቦች በሃገራቸው 2ኛ ዜጋ ሆኖው እንዲኖሩ እያደረገው የመጣ ረስቶ እንደመልካም ሥራ ሰርቶ ሊቀበለው እንደመጣ ለወደፊትም በተደረገ ፖለቲካዊ ዘመቻ ጥሩ ነበርን እንዴት ብሎ አሜን

ብሎ እንዲገዛና ከህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ዉጭ ሌላ እንዳያመልክ ታስቦ የተሰራ ነበር: በተለይ ደግሞ የመለስ የሥራ ዉጤቶች በፖስተር በነፎቶ በፊሊም ላለፉት 21 ዓመት ሙሉ በየ ኮንፍረንሱ፣ ጉባኤዎች፣ ሰሚናሮች፣ ስብሰባዎች፣ በሙሊንዮም አዳራሽ የደሰኮሩዋቸው የዓለም አቀፍ ስብሰባዎች፣ ንግግሮች ጥሩ ጥሩዎቹን በመምረጥ ለ24 ሰዓት በሙሉ በመለስ ንግግር በመሸኘት በተለቪዥን፣ በሬድዮ፣ በጋኤጦች፣ መፅሄቶች ህዝቡ አደነቆሩት::

በተጨማሪም የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አመራር የመለስ ሞት ምክኒያት በማድረግ የተሰሩ ሥራዎች ሲገለፁ መለስ ብቻቸውና ለብቻቸው ዝናና ስም ይሰሩ እንደነበሩ በትእዝብት ላይ ወደቁ: ይህ መጀመርያሳገባቸው ነበር የተናገሩ: የሚናገሩት የነበረ ተመልሰው መቆርቆር ጀመሩ ህዝቡም ለመሪዎች ሁሉ ይንቃቸው ጀመር ንቀቱ ለወደፊትም መቋጫ የሚኖረው አይመስልም::

እዚህ ላይ ያሉ በኔ እምነት በአዲስ ራዕይ 80 ገፅ ፅሑፍ የሚታይ ሆኖ መለስ ግን ባለፉት 38 ዓመታት በፍትህ በመልካም አስተዳደር በዴሞክራሲና ሰብኣዊ መብት አጠባበቅ በሃገር ሉእላዊነት መጠበቅ፣ በመማጎት በምንም ዐይነት የሚመሰገኑ አይደሉም ብቻ ሳይሆን ሃገር አልሚ ሳይሆኑ አጥፊ ድህነት ያጠፉ ሳይሆኑ ድህነት እንዲመጣ ያባባሱና ስደት ሥራ አጥነት  በዝቶ ሃገራችን በዉሸት ልማት ሃብታም ያደረጉ መሪ ነበሩ ነው እምለው::

ለመለስ ቀብር 80 ሚልዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ምልመላ ተደረገ: በሃገር ዉስጥ ከሁሉም ክልሎች ገጠርና ከተማዎች በሚገኙ ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ ቀበሌዎች፣ የመንግስት ሰራተኞች፣ ታማኝ ሰዎች ተመልምለ ው በመንግስት ገንዘብ የዉሎ አበል፣ የመጓጓዣ ገንዘብ፣ ተከፍሎዋቸው ወደ ቀብር እንዲሄዱ ተደረገ: የመንግስት ማኪናዎች ከኮፕራ እሰከ አዉቶቡስ፣ የዩነቨርሲቲዎች ሰርቪስ አውቶቢሶች የትእምት፣ የጥረት፣ የደንሾ ማኪናዎች፣ ሁሉም በመንግስት ነዳጅ

ተንቀሳቅሰው: አዲስ አበባ እንዲገቡ ተደረጉ በዚህ ጊዜ ገንዘብ ይባክናል የሚል አስተሳሰብ አልነበረም::

በሌላ በኩል ቀባሪዎች ከመሰብሰብ ጎን ለጎን የአዲስ አበባና አካባቢዋ ከ24/12/2004 ዓ.ም እስከ ዓርብ 25/12/2004 ዓ.ም በመስቀል አደባባይና ቤተ መንግስት ህዝቡ እየ ሄደ አስከሬኑን እንዲሰናበት ተደረገ: የሚሰናበት ሕብረተሰብ የሃገር ደረጃ በዕድሜ ባለፀጋዎች፣ ነዋሪ ህዝብ፣ ማሕበራት፣ የመንግስተና መንግስት ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የንግድ ሕብረተሰብ፣ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ሴቶች፣ የወጣት ሊጎች፣ አስተማሪዎች፣ የፋብሪካ ወዛደሮች፣ ፌደራል ፖሊስ፣ የሃገር መከላከያ ሰራዊት፣ የብራንዳ አዳሪዎች፣ የገጠር ገበሬ ማሕበራት፣ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባሎች ወ.ዘ.ተ፣ በሚልዮን የሚቆጠር ህዝብ በየ አደባባይ በነቂስ ወጣ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ካድሬዎች፣ የወረዳ የቀበሌ አስተዳዳሪዎች የመንደሩ የሴት ተላላኪዎች ማን ወጣ ማን አልወጣም በሚል በማስገደድ የሚሰልሉ በየ ቦታው እየዞሩ ያዩ ነበረሩ: እንዲሁም የሁሉም ዐይነት ሃይማኖት መሪዎች በሰልፍ አስከሬኑ እንዲሰናበቱ ተደረገ::

በነዚህ ቀናቶች በመላዉ ሃገራችን ትናንሽ መንደሮች ሳይቀሩ በሁሉም የሃይማኖት ማእከላት የሙስሊም መስጊዶች፣ ቤተክርስቲያኖች፣ የካቶሊክ ፣ የሙሉወንጀል፣ ዴንጦ ቆስጦ እነዚህ ሁሉ የፍትሃት ፀሎት እንዲያደርጉ ታዘዙና ሲፈፅሙ ሰነበቱ: የመጨረሻዋ የሽኝት ቀን ቅዳሜ እስከ 5ሰዓት ነበረች፣ በዚህች ቀን የክልል ተወካዮች፣ የሃገርና የዉጭ አንባሳደሮች፣ የአዲስ አበባና አካባቢዋ የሚገኙ አድባራት የሃይማኖት መሪዎች፣ በነዚህ መንደሮች ዉስጥ የሚኖሩ ወደ ፀሎት ያልወጡ ከተገኙ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ካድሬዎች ጥርጣሬ ዉስጥ ይገባሉ፣ ሌላ ቀርቶ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የስለላ መዋቅሮችና ካድሬዎች በየ ቦታው እየዞሩ እገሌ አላዘነም መለስ በመሞቱ ተደስተዋል እያሉ ያዋክቡታል::

የተከበራቹሁ ወገኖች የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ የሁንኩ ለመለስ ዜናዊ ወደ ትጥቅ ትግል የወጣሁ ከሱ በፊት በሶስት ወር ቀደም ብዬ ነው፣ ከታችኛዉ ተከዘ ወንዝ ወደ ወልቃይት መሸጋገርያ ሂደን ተቀበልነውና

ወደ ደደቢት የነበሩ ጓዶች ወስደን ቀላቀልናቸው: በዚያን ጊዜ እኔና ሌሎች ጓዶች ነበርን፣ አቶ ገሰሰዉ አየለም አብረዉን ይመሩን ነበሩ፣ ለመለስ ወታደራዊ ስልጠና ያሰለጠንኩዋቸው እኔ ነኝ፣ 17 ዓመት ሙሉ አብረን ታግለናል፣ ብዙ ጥሩና መጥፎ የሂወት ንሮ አብረን ገፍተናል፣ ደርግ ከተወገደም ሶስት ጊዜ ተገናኝተን ነበር፣ በትግል ወቅት የነበራቸው ባህሪና ተግባር በዋና ፅሑፍ እገልፃለሁ፣ ሆኖም ግን እኔ የአቶ መለስ ፖለቲካዊ አቋም ፖሊሲ እጅጉን እጠላለሁ ብቻ ሳይሆን ፉፁም እቃወማቸዋለሁ፣ እንደሰው እንደአብረን የታገልነው እንደዜጋ በመሞታቸው እጅጉን አዝኛለሁ::

በሃገራችን ካሉ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎች ካድሬዎች በበጎም በመጥፎም ሥራቸው እሳቸው ይሻላሉ፣ ዝርዝሩ በዋናው መፅሐፍ ይተረካል: የሆነ ሆኖ መለስ ለመቅበር ለዚያች ያለችኝ ድህነት ሳልንበረከክ 3500 ብር ወጪ በማድረግ ከመቀሌ ወደ አዲስ አበባ ቤተ መንግስት ድረስ በመሄድ ሃዘኔን በማልቀስ ገልፃለሁ: ሆኖም ግን ወደ ሽኝቱ ለመግባት ትልቅ ፈተና አጋጥሞኛልና ከመስቀል አደባባይ እስከ አራት ኪሎ በፀጥታ ኃይሎች ብዙ ችግር አጋጥሞኛል: ነገር ግን መተዋወቅ ጥሩ ነው በፍተሻዉ አካባቢ እንግዳ ተቀባዮች በትጥቅ ትግል ጊዜ ወታደራዊ ስልጠና የሰጠሁዋቸውና እማቸው የነበርኩ አገኘሁና ከነሱም ተሳሳምነና ናፍቆታችኝበመግለፅ ፍተሻው ያሳልፉኝ ነበር: በመጨረሻ አራት ኪሎ ወደ አቶ መለስ አስከሬን ለመግባት ሲጠጋ የደህንነት ምንጋ አጋጠመኝ ሰው ሁሉ በደርዘን ነው እየተፈተሸ በማሕበር ወይም የፓርቲ አባል መሆኑ የይለፍ ወረቀት መያዝ የግድ ነበር እኔ ግን የዓረና መድረክ የሥራ አስፈፃሚ አባልነት መታወቅያ ነበረኝ: ከኔ ጋር የነበረ የወንድሜ ልጅ አዲስ አበባ ነው ተወልዶ ያደገውና ያን ሁሉ እንግልት ሲያይ ይጨነቅ ነበር: ከትግራይ የመጡ ማሕበራት ይገቡ ስለነበሩ እያለፉ ለምን ትከለክሉት አላቹሁ በማለት ተቃዉሞቸው ይገልፁ ነበር: ሃዘን ለመድረስም ወዳጅና ጠላት ነበረበት: ከዚያ በኋላ በአካባቢው ያገኘናቸው ባለስልጣናት ለኡሁድ የቀብር ስነ ስርዓት

መግቢያ ወረቀት ሊሰጡኝ ጠየቅኩዋቸውና አንድ ባለስልጣን ያለኝ ለቀብር መግቢያ ካርድ ልንሰጥህ ይቅርና ወደዚህ መግባትህ እንኳ እድለኛ ነህ አለኝ ይገርማል::

## ለኡሁድ 24/12/2004 ዓ.ም ግበአተ መሬት ዝግጅት

የቀብሩ ስነ ስርዓት ሲፈፀም የሚገቡ ሰዎች ሁሉ በይለፍ ወረቀት እንዲገቡ ተደረገ: ወረቀቱ የሚወጣው የደህንነት ባለስልጣን ጌታቸው አሰፋና ጀነራል ሳሞራ የኑስ እየተፈረመ ነው: ሲሰጥ ደግሞ ለየክልሉ ፕረዘደንቶች በኃላፊነት ወስደው እነሱ ደግሞ ለመዋቅራቸው ይሰጣሉ: ለአብነት ከትግራይ ከሂዱትና አዲስ አበባ ነዋሪዎች የሆኑ ወረቀት ያገኙ በማሕበር ተደራጅተው ለመጡ ማሕበራት ወ/ሮ ሮማን ገ/ስላሴ ነበሩ: ከወልቃይት የመጡ በአዲስ አበባ የነበሩ የአዜብ መስፍን ዘመዶች በልዩ መልክ የሚጠራ የትግራይ ክልል ወህን ቤቶች ኃላፊ አቶ ፈረደ ሺወንድም የአዜብ መስፍን የቅርብ ዘመድ ነበሩ: በየ ክልሉ አከፋፋዮች ነበሩ: የቀብር የይለፍ ወረቀት የተሰጣቸው አብዛኛቹ ሴቶች ሆኖው ወደ ቀብሩ ይገባል ተብሎ የተገመተው 60ሺ ሲሆን በዘመድ አዝማድ ሰበብ የገባው ከ 100ሺ በላይ ነበር: የኢአዴግ የቅርብ የሆኑ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የአየለ ጩሚሶ፣ የቅንጅት፣ የኢደፓ ወ.ዘ.ተ መሪዎችና የክብር ጥሪ ተሰጥቶዋቸው ነበር: በሃገራችን ያሉ ትክክለኛ ተቃዋሚዎች እንደመድረክ ያሉ ፓርቲዎች ይቅርና ወደ ቀብር ሊገቡስ ስለመለስ ሞት የሃዘን መግለጫ ሰጥተው ሲያበቁ በሁሉም የመንግስት ፕሬስ ኮንፍረንስ ጠርተው መገናኛ ብዙሃን ሲገልፁ የመንግስት ሚድያዎች ግን ዝምታን መረጡ: በህ.ወ.ሓ.ት ባለቤትነት የሚታወቅ ሬድዮ ፋና ለተሰጠ መግለጫ ትርጉሙ በመለወጥ የመድረክን መልካም ስም ለማጥፋት ባለው ፍላጎት አበላሽቶ አስተላለፈው እጅጉን አስቀያሚ: በሃገራችን ባህል ሰዎች በነብስ ግድያ ይጣሉና በሃዘንና በደስታ የግድያ የፈፀመ ግለሰብ አይደበለቅም እንጂ ሌላው የሁለቱ ወገን ዘመድ አዝማድ አብረው

የሃዘኑም የደስታም ተካፋይ ይሆናሉ: የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎች ግን ከገበሬው ህዝብ ንቃተ ህልና ወርደው የወደቁ ሆኖው አገኘሁዋቸው::

በዚህ በቀብር ዋዜማ የነበረው አሳዛኝ ነገር ከሁሉም ክልሎች ከሞያሌ እስከ ባድመ ከሶማል እስከ ጋንቤላና ጉሙዝ ከአፋር እስከ መተማ ጫፎች በግድ ለቀብር ወደ አዲስ አበባ የገቡ የተሰጣቸው የአዲስ አበባ ትምህርት ቤት ነበር: ለመሪዎች ለካድሬዎች ለከተማ ቀመስና ለወዳጃቸው ሴቶች ምርጥ ሆቴሎች ተሰጣቸው: ድሃውና ተገዶ የመጣ ገበሬ ግን በትምህርት ቤት ብራንዳ ተጣለ::

አንድ አስገራሚ ግን ከወረዳ እስከ ክልል ተመልምለው ለቀብር የመጡ አዲስ አበባ የቆዩ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎች በሃዘኑ ምክኒያት በመገናኘት እንደመልካም አጋጣሚ ሆኖላቸው በቦሌ፣ በካዛንቺስ፣ በወሎ ሰፈር፣ በ22 ማዞርያ፣ በፒያሳና ሌሎች ክፍለ ከተማዎች ሰግሬቶ፣ ጌሰት ሃዉስ፣ ቡና ቤቶች ከየአካባቢው ከመጡት ሴት ወዳጆቻቸው በዉስኪ ቁርጥና ጥሬ ስጋ ክትፎ በቀዝቃዛ ቢራና ዉስኪ እያወራረዱ ያመሹ ነበር: ለነገሩ የመለስ አስከሬን አዲስ አበባ ከገባ ቀን ጀምሮ አብዛኞቹ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎች ካድሬዎች ጓደኞቻቸው ሃብታሞች ጋር በመሆን ለሊት ለሊት የሃዘን ደበስ ዉስኪና ቁርጥ ጥብስ እያሉ ቤት ዘግተው ሲዝናኑ ነበሩ: የመለስ ቀብር በአንዱ ገፅ ለጓደኞቻቸው መዝናኛ ነበር ማለት ይቻላል::

በቀብሩ ጊዜ የሃገር ዉስጥ ደህንነት የፌደራል ፖሊስ የመከላከያ ሰራዊት ወታደሮች ሲቪል የለበሱ በ10ሺ የሚቆጠሩ ሆኖው አመራራቸው በጌታቸው አሰፋና ጀነራል ሳሞራ የኑስ በጀነራል ሰዓረ መኮነን ኮማንድ ፖስት (ወታደራዊ ማዘዣ) ጣብያ ይመራ ነበር: የዉጭ መንግስታት መሪዎች አንባሳደሮች ሉኡካንም የሚቀበሉ በዉጭ ጉዳይ ሚኒስተር ኮማንድ ፖስት የሚመራ ሆኖ ንኡስ ኮማንድ ፖስት በጊዮን ሆቴል ሆኖ የእንግዳ አቀባበል ይደረግ ነበር: በዚያን ዕለት የመንግስት ሰራተኛ ሁሉ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎችና ካድሬዎች የስነ አእሙሮ ጭንቀት ነበራቸው: አዲስ አበባም ከመላው ሃገራችን ቀባሪዎች ጭነው የመጡ

ትላልቅ ማኪናዎች መካከለኛና ዝቅተኛ አውቶቡሶች ኮብራዎች ተጥለቀለቁና መንቀሳቀሻ አላገኙም: በየ ክልለሉ ለቀብር የመጡ ገበሬዎች ሌላ ዜጎችም ቦታ ስለማያውቁ ብዙ መደናገር ነበር: መለስ ታመው ዉጭ ሃገር በነበሩበት ጀምሮ የነበረ ወሬ አሁንም ተጧጧፈ ወሬዉም በሽታቸው ምን ነበር? ለምን የአስከሬኑ ፊት እንደ አዉነ ጳውሎስ አይታይም የሚሉ ጥያቄያቸው የብዙዉን ቀባሪ ጥያቄ ነበር::

በሌላ በኩል መለስ የሚለዉም የመለስ ህመም የጭንቅላት ካንሰር፣ ያንጀት ካንሰር፣ የጉበት ካንሰር ነበር እያሉ የተለያዩ ሰዎች ይናገሩ ነበሩ: ሌሎችም የመለስ ህመም አመሪካ ሄደው በነበሩበት ሲአይኤ በጨረር መታቸው የጋና መሪ አብረው የነበሩ ሞቱ፣ የታንዛንያ መሪም ታመዋል ተባለ ግን ደግሞ የታንዛንያ መሪ ግን ለቀብር መጥተው አዲስ አበባ ይገኛሉ: የዉስጥ አዋቂዎች የሚሉት ደግሞ መለስ በህመሙና በተደረገላቸው ህክምና ጭንቅላታቸው ስለፈረሰ ክብደታቸው ስለቀነሰ ለማሳየት አስቀያሚ ስለሆነ ነው ይላሉ: አንደ አንድ ደግሞ ሬሳቸው የለም የቻይና መንግስት የመለስ መሞትና አፍሪካ ሃገሮች መለስ ስለጠፉበት ተናዶ አስከሬኑ ለመመርመር እወስዳለሁ ብሎ ስለወሰደው በሳጥኑ አስከሬኑ አልነበረም ይላሉ: ወሬው በደርዘኖች እየተባዛ ተለቀቀ::

ሌላ አነጋጋሪ የነበረ ያሁኑ ጠቅላይ ሚኒስተር ኃይለማርያም ደሳለኝ ከቀብሩ በፊት ተጠባባቂ ጠ/ሚኒስተር የሚል በህ.ወ.ሓ.ት ተችሮላቸው ቆይቶ በዋዜማው ተነጠቁ ምክትል ጠ/ሚኒስተርና ዉጭ ጉዳይ ሚኒስተር መጠራት ስለጀመሩ ብዙ ሰዎች ከፍተኛ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎች ሳይቀሩ ማን ይሁን ጠ/ሚኒስተር ማለት ጀመሩ: የዉጭ ሃገር ልኡካን ፈረንጆችም በቤተ መንግስትና በዉጭ ጉዳይ ሚኒስተር በብዙ ባለስልጣን እየቀረቡ ወሬን ያነፈንፉና ያድኑ ነበሩ: ሆኖም የቀብሩ ሰዓቱ ደረሰ አስከሬኑ ቅድስት ስላሴ ቤተ ክርስቲያን የተዘጋጀላቸው መቃብር አመሩ የቄሶች ብዛት መንጋ ነው: በዚህ ጊዜም አዲስ ወሬ ተጧጧፈ እሱም መለስ ሃይማኖት ነበራቸው እንዴ በበረሃ

እያሉ ራሳቸው ይቅርና ለይምሰል የሆነ ሃይማኖት መሪዎች በጣም ይጠሉ ነበሩ ብቻ ሳይሆን የሃይማኖት መሪዎች የሚናገሩት ሰበካ ይጠሉ ነበር ይላሉ: አንዳንዱ ደግሞ አጼነ ጳውሎስ መሞታቸው ታይቶዋቸው ስለነበር አስቀድሜ ልጄን አስቀርቤው እመጣለሁ ብለው በልጃም ሄደው ቁርባንን ሰጡዋቸው: በሌላ በኩል አይደለም ከአራት ዓመት በፊት ሚስታቸው አዜብ መስፍን ይዘው ቤተ ክርስቲያን ገበተዋል ነገር ግን ቁርባኑ በመቃወም አልቀረቡም ይላሉ: ሃምየቱ እየ ተጧጧፈ እያለ የኦርቶዶክስ ዘማሪያን በነጋሪት ፀናፅል መሬቱን እያስጨነቁ ስርዓተ ፍትሃት የሚፈፅሙ ካህናትም ለሙታን የምትሰጥ ፍትሃት እንዳትቀር በጥንቃቄ እየፈቱ በመጨረሻ የመለስን አስከሬን በተዘጋጀ በእምነበረድ የተሰራ ጉድጓድ በወርቃማ ሳጥን ገብታ አረፈች::

በዚህ ቀን መለስ የሃገራችን ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ ቀበሌዎች፣ ቤተ ክርስቲያኖች፣ መስጊዶች፣ ሰው ሁሉ ላይ እንደገለፅኩት በፀጥታ ኃይሎች፣ ፖሊስ፣ ምሊሽያ እየተገደደ በሚልዮኖች የሞቆጠር ህዝብ በልቅሶ ዋለ በቃ የመለስ አስከሬን በቤተ መንግስት በር በህ.ወ.ሓ.ት ሱካር ጨው በርበሬ የሚቋጠርበት የነበረ አልፎም እንደልብስ ምንጣፍ ይጠቀሙባት የነበሩ እሳቸዉም ጨርቅ ያሉዋት ባንዴራ ሬሳቸው ሽፍና 13 ቀን በሚልዮን የሚቆጠር የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲሰናበት ሰንብቶ በዕለተ 27/12/2004 ዓ.ም በቅድስት ሲላሴ ቤተ ክርስቲያን አረፈች አበቃ አቶ መለስ ሃገር ቀይረዉ አረፍ ብለው ነብሳቸው ይማራቸው: ለዚህች ሃገር በጎዉም ኩፉም ሥራ ሰርተዋል ምንም ይሁን ምን የሚሰራ ሥራ ሁሉ ቅድሚያ ለራሳቸውና ለብቻቸው ታዋቂነት፣ የበላይነት የሚሉ ቢሆኑም ከነዛ ተኝተው ዉለው ማታ ማታ በጨለማ በዉስኪና ሌሎች መጥፎ ሥራ እየሰሩ በሙሱና የተጨኛለቁና ያለ አግባብ ሃብት እያካበቱ ከሚኖሩ አቶ መለስ ይሻላሉ: ይሻላሉ ስል ግን ከግላቸው በእጃቸው ሙሱና አይፈፅሙት እንጂ ከቤታቸው ወለል ዉስጥ ጀምረው እስከ ሚኒስቴሮች አንባሳደሮች ከፍተኛ የፖሊስና የጦር መኮነኖች ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣኖች እስከ ወረዳ ቀበሌዎች ያለው የሙሱና የእሳት

ሰደድ በደንብ ያውቃሉ: ዋና ስህተታቸው ደግሞ ለዚች የያዙዋት ወንበር እስካል ተጫረታቸው አይነኩትም: ለመወዳደር ከሞከረ ግን እንደታምራ ት ላይነ ወደ ወህን ቤት መወረወር ማግለል ነው ተግባራቸው የነበረው::

## ቀብሩ ተጠናቀቀ እንግዶች ወደ የመጡበት ተሸኙ

የጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ህመምና ሞት ተከትሎ የሃዘን ጊዜ ሲደረግና ለቀብርና ለሃን ሽኝት አዲስ አበባ የገባው ህዝብ ድብልቅልቅ ያለ ነበር የፀጥታ ህውከት መጠናቀቁ ምን ይሁን ምን ብዙ ሰው የተንግላታና መብቱ የተጣሰ ቢሆንም የፀጥታ አከባበር በሚመለከት ለኢትዮጵያ ፀጥታ ኃይሎች ጥንካሬ እጅጉን ያስመሰግናቸዋል: ይህ የፀጥታ ጥበቃ ግን በሰላም ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች እንደዚሁ ፀጥታቸው ቢጠብቁዋቸው ለሁሉም ነገር ጠቃሚ ነበር::

## መለስ ግብአተ መሬት ከገቡ በኋላ የታዩ ክስተቶች

መለስ ከተቀበሩ በኋላ መለስ ታመው ተብለው ግን ደግሞ ሙተዋል አልሞቱም እየተባለ ኢትዮጵያ በወሬ ስትናጥና መሞታቸው ታውቆ አስከሬናቸው አዲስ አበባ እስከ መቀበራቸው የነበረው የስልጣን ሽኩቻ ከቀብር በኋላም ተጠናክሮ ቀጠለ: መንግስት እንዴት ይዋቀር የሚል የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባል ፓርቲዎች የአንድነት በፓርቲ በተናጠል ዉይይት ተጧጧፈ: የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች በዉስጣቸው የመለስ ጉሩፕ በአንድ ገፅ በተፃራሪ ይታዩ የነበሩ ጉሩፕ በሌላ ገፅ: በሌላ በኩል ስብሃት ነጋ የሚሰብኩት በአንድ ገፅ ዉይይቱ ተጧጧፈ: በህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ የነበረ በሙተካካት የወጡ እነ ስብሃት ነጋና ስዩም መስፍን አባይ ፀሃዬ ሌሎቹም ወደ ነበሩበት ስልጣን ይመለሱ ህ.ወ.ሓ.ት ይጠናከር የሚል ሃሳብ: በሌላ በኩልም በ1993 ዓ.ም ከህ.ወ.ሓ.ት ተገንጥለው ለወጡ በተለይ ደግሞ በመወላወለ ላይ ያሉ ማ/ኮሚቴ ህ.ወ.ሓ.ት ነበር ይመለሱ እንታረቅ አሉ: በተባለው ሁሉ የመለስን

*ራዕይና ለጋሲ ተከታዮች (አከራሪዎች) አበድን አይሆንም አሉ በህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ ትልቅ መጨናነቅና ህውከት ማኩረፍ ሰፈነ: ስብሃት ነጋ ምንም የሌለው የስልጣን ፕሮቶኮል የማይፈቅድለት ወደ የግል ጋዜጣ ድምፅ ሬድዮ አመሪካ ብቅ እያለ ህውከት የሚፈጥሩ ነገሮች ጣል ያደርግ ነበር::*

*በህ.ወ.ሓ.ት የነበረ እንደተጠቀሰ ሆኖ በባአዴንም ከፍተኛ የስልጣን ቦታ ማን ይያዝ በስብሰባ ተጠመዱ የሚያደርጉት የነበረ ዉይይት በግልፅ አይታወቅም አንድ ምልክት ግን በዘመነ ጠ/ሚኒስተር ደብዛቸው ጠፍቶ የነበረ እነ ተፈራ ዋልዋ፣ አዲሱ ለገሰ፣ ብርሃነ ፍትህ ሚኒስተር ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ በረከት ስምኦን የሃገር ዉስጥና የዉጭ የብዙሃን መገናኛዎ ች ጭራሹን ተቆጣጠሩዋቸው: ኃይለማርያም ደሳለኝ ለስሙ ጥብቅ ጠሚኒስተር ይባሉ እንጂ በማኻሉ ተቅበዘበዙ::*

*ኦሆዴድ የሚባል ፓርቲም አሁን በሚፈጠረው የመንግስት አወቃቀር የኛ ቦታና ድርሻ ምን ይሆናል በሚል ስብሰባ ተናጡ: በተጨማሪም በዉስጣቸው ማጥራት የሚባል ሥራ በመስራት እነ ጁነዲን ሳዶ አስቴር ማሞና ሌሎቹም የክልልና የዞን አመራሮች በማሽቀንጠር ስለስልጣን ይውጣ ዉይይት ጀመሩ: ሁሉም ፓርቲዎች ግን የጠቅላይ ሚኒስተር ቦታ ይፈልጋሉ ቢያንስ የምክትል ጠ/ሚኒስተር ለመያዝ ይፈልጋሉ: በዉጭ ጉዳይ ሚኒስተርም ተፈላጊ ነበር በደቡብ ህዝቦችም ኃይለማርያ ም ደሳለኝ በሕገ መንግስቱ መሰረት ጠሚኒስተር በሌለበት ተክቶ ይሰራል የሚል መከበር አለበት የሚል አስተሳሰብ ያዙ: በሌላ በኩል አመሪካና የአስያ ሃገሮች ማን ወደ ስልጣን ይመጣል የሚል ይጨነቁበት ነበር: ፕረዘደንት ኦባማ ለኃይለማርያም ደሳለኝ በተደጋጋሚ ስልክ እየደወሉ አይዞህ እያሉ ያበረታቱዋቸው እንደነበሩ የዓለምና የሃገር ዉስጥ ብዙሃን መገናኛዎች ይናገሩ ነበር: የቸይና መንግስት ለኢትዮጵያ መንግስት ብዙ እርዳታ አደረገ የምዕረራብ መንግስተታት ለጠ/ ሚኒስተቴር መለስ በማሞገስ በከፍተኛ ደረጃ ተንቀሳቀሱ እርዳታም መስጠት ጀመሩ::*

*በወሬ ደረጃም ቴድሮስ አድሃኖም (ሶፍያን አህመድ) ምክትል ጠ/ሚኒስቴሮች ከሁለቱ አንዱ ሊሆኑ ይችላሉ በሚል ወሬ በሰፊው ይወራል: በተለይ ቴድሮስ አድሃኖም አመሪካና እንግሊዝ ስለመለመሉት እሱን ሊያመጡ ናቸው የሚሉ ነበሩ: በዚያን ጊዜ እነ አባዱላ ገመዳ ግርማ ብሩም ወጣ ወጣ አሉ አባዱላ ገመዳ አፈጉባኤ ከሆኑ ጀምሮ ደረጃቸው ጥለው ዝምታ ይመርጡ እንደነበሩ ሁሉ ሰው የሚያውቀው ነው::*

*በህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባል ድርጅቶች ዉጥረት ነገሰ: አጋር ፓርቲዎቹም እኛም ተወዳድረን ቦታ የማግኘት መብት አለን ማለት በማጉረምረም የሚገለፅ ሁኔታ ነበር: በተለይ በህ.ወ.ሓ.ት ፓርቲ ትልቅ ዉጥረት ነበር: የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ አዲስ አበባ ተሰበሰበ: ስምምነት አልነበራቸዉም: ከብዙ ክርክር በኋላ ለጊዜው ታርቀው የህ.ወ.ሓ.ት ሊቀመንበር ክፍተት በሞምላት ሃላ በሃገር ደረጃ ሶስት ምክትል ጠ/ሚኒስተር የተሸሙት መፈተኛ ሁለት የህ.ወ.ሓ.ት ምክትል ፕረዘደንት ሽመው ወደ መቀሌ ተመለሱ::*

*የህ.ወ.ሓ.ት መዋቅር ከተስተካከለ በኋላ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ምክር ቤትና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ኃይለማርያም ደሳለኝ ጠ/ሚኒስተር አድርጎ በፓርላማ ካፀደቀ በኋላ ትልቅ ፍጥጫ የነበረ የምክትል ጠ/ሚኒስተርና የዉጭ ጉዳይ ሚኒስተር ማን ይያዘው የሚለው ነበር: የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ፓርቲዎች ሁሉም ተፋጠጡና ማግባባት አልተቻለም: የኋላ ኋላ ግን ደመቀ ሞኮነን ምክትል ጠሚኒስተር ሆነና በአዴን ትንሽ ተነፈሱ: በህ.ወ.ሓ.ት ግን ከተራ አባሉ እስከ ማ/ኮሚቴ ያለው ካድሬ ያቺ የጠባብነትና የትምክህት ስሜትና እምነት ተዳምራ የስልጣን መያዝ ስለጠፋ ከእንግዲህ  ትግራይ ያሁሉ መስዋእት ከፍላ ልጆቻና ንብረቷ አጥፈታ በቃ ተገለለች ከእንግዲህ ወድያ ስልጣን ወደ ትግራይ አትመጣም አሉ: አኮረፉ ሞራላቸው ተነካ ይህ ሃቅ ነው: በነ አቶ ስብሃት ነጋም መጥፎ ስሜት ተፈጥሮ መለስ ብቻውና ለብቻው ሲታይና ዝናው ለማሳደግ ሲል ትግራይ ተመልሳ ወደ ስልጣን እንደማትመጣ አድርጓታ*

ል ብለው ነበር: መለስ አልሞተም አሁንም በመንፈስ ለ40 (50) በዓመት ይመራናል እያለ የመፎክር ሞገድ እንዲሰራጭ ያደርግ የነበረ ካድሬና የህ.ወ.ሓ.ት አባል ረጂም ሳይጓዝ የአቶ ስብሃት ነጋ ኮቴ ተከትሎ ማማት ጀመረ::

የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባል ፓርቲዎች ኃይለማርያም ደሳለኝ ስልጣን እንደማቆያ ነው እንጂ ለመጪው ጊዜ በስልጣን እንዲቆዩ እንደ ማይፈልጉ ከኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መንደር ሾልከው ይወጡ ነበሩ: ነገር ግን በህ.ወ.ሓ.ትና በአዴን በስልጣን ስስት ምክኒያት ጨለምተኛነት ይተይ ነበር: በመሆኑ የሁለቱ ድርጅቶች መሪዎች በየ ክልላቸው በመውረድ ለካድሬዎቻቸውና ለአባሎቻቸው ሲቀሰቅሱ ባጁ ሆኖም ግን ዉጤቱ አነስተኛ ነበር: አሁን የቀረቹው ስልጣን የዉጭ ጉዳይ ሚኒስተር ነበረች: እሱዋም ህ.ወ.ሓ.ት ይፈልጋታል ኦሮሞም ይፈልጉዋተል አማራም አልጠገቡም: የባሰው ግን አራት ሚልዮን ህዝብ የያዘው ህ.ወ.ሓ.ት ነው::

የመድረክ ፓርቲ ግን ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህአዴጎች 3/4 ምክትል ጠ/ሚኒስተር ሊሾሙ እንደሚፈልጉ ሚስጢር አፈተለኮ አጊኝቶ በመግለጫ ደረጃ ሕገ መንግስት ለመናድ ዕቅድ እንደነበራቸው ያውቁ ነበር: የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ሚስጢር በየት አፈተለከች ብለው እርስ በራሳቸው ተጠራጠሩ: ከብዙ ዉጣ ዉረድ በኋላ ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አስበዉት የነበረ የሁለት ምክትል ጠ/ሚኒስተር ሹመት የዉጭ ጉዳይ በቴድሮስ አድሃኖም ተያዘ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ምክትል ጠሚኒስተር በደብረፅዮን ገመድህን ተያዘ: ይህ ስልጣን ለኦሆዴድ ለባአዴን አዲስ መርዶ ሆነ: እነ አባዱላ ገመዳም አኮረፉ: በረከት ስምኦንም ድምፁ ጠፋ: የህ.ወ.ሓ.ት ካድሬዎች ተኮፈሱ: እዚህ ላይ የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎችና ካድሬዎቻቸው ድሮ የነበረ የጠባብነት ማንነታቸው አገርሽቶበት ተጋለጠ::

የስልጣን የበላይነት ህ.ወ.ሓ.ት መያዙ የህ.ወ.ሓ.ት አጋር የሆኑ ጥገኛ የትግራይ ተወላጆችም ከጠባብነት አምልኮታቸው ተነስተው በዊስኪ እየተራጨ ወድያው መለስ እንደሞተም ተሰብስበው በመነጋገርና

በመምከር ለአንድ አንድ የህ.ወ.ሓ.ት ባለስልጣናት ያላቸው ቢኖር የጠሚኒስተር ስልጣን እንዳትለቁዋት በገንዘብ የሚሆንና የሚያስፈልግ ከሆነ ሀብታችን ሁሉ አሟጠን እንሰጣለን አሉዋቸው::

የተከበራቹ ወገኖች ይህ አባባል የ3 ወይም 4 ሚልዮን የትግራይ ህዝብ ስሜትና ፍላጎት አልነበረም: የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ባለስልጣኖችና ከሌቦች የመንግስት ሰራተኖች በክራይ ሰብሳቢነት የተቆራኙና ተጠቃሚ የቦኑ ጥቂት ሰዎች ናቸው: የዚህ ታሪክ በሚቀጥለው የአዲስ ራዕይ የመለስ ታሪክ የሚገልፅ ግብረመልስ በጥልቀትና በስፋት ልገልፀው እሞክራለሁ::

ላይ የተዘረዘረው ተግባር የሚያስረዳን የመለስ የብዙሃን መብት አጠባበቅ በቋንቋ በባህል የተመሰረተ ፌደራሊዝምና የክልል አከላለል መሰረት እንደሌላው ኢትዮጵያ ሃገራችን የሚበታትንና ከህዝቦች ፍላጎት ዉጭ የሚደረግ የመንግስት አወቃቀር መሆኑ ያሳያል::

## <u>ከመለስ ግብአተ መሬት በኋላ ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ሲከተለው የባጀ የፖለቲካ ቅስቀሳ</u>

የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎች መለስ ታመው (ሙተው) በልጀም ብራስልስ ከተማ ሆስፒታል እያሉ የመለስ ሞት ከሰሙ እንዴት ለወደፊ ት ፖለቲካ ጉዞዋችን ንጠቀምበት ብለው አስበውበት ተወያይተው አንድ በአንድ ዓላማ አስቀምጠው ናቸው እየተንቀሳቀሱ የከረሙ: ካስቀመጡዋ ቸው ዓላማዎች፦

1. የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አቢዮታዊ ዴሞክራሲ ዓላማዎችና የመለስ ፍልስፍና ፖሊሲዎች በማጉላት የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ታክቲክና እስትራተጂ ዉጤታማ መሆኑ የተሰሩ ኣበይት ስራዎች : እንደአባይ ግድብ፣ የባቡር ሐዲድ፣ የሱካር እንዳስትሪ፣ የኮንዶሚንዮም ቤቶች ወደፊት በማምጣት ህዝቡ እንዲያምንበት ማድረግ

2. በዚህ ቅስቀሳ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች በማግለልና በማጋለጥ ለወደፊት ለሚደረጉ ምርጫዎች ቦታ እንዳያገኙ ማድረግ: በ21 ዓመታት የተሰሩ የልማት ስራዎች በፎቶግራፍ፣ በፖስተር፣ በፊልም፣ በሁሉም ዐይነቶች የብዙሃን መገናኛዎች በሃገር ዉስጥና በዉጭ እንዲስተዋወቁ ማድረግ
3. የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የልማት ዉጤት በማጉላት ህዝቡ የመለስ ራዕይና ጀማሪዎች እምነትና አምልኮት በማሳደር ያለ መለስ ሌላ አታምልክ ብሎ ከአምላክ በላይ እምነት አሳድሮ ከአርባና አምሳ ዓመት በላይ ሌላ ስርዓት እንዳይመጣ እየተከላከለ እንዲኅዝ በማድረግ
4. የመለስ ሃዘን 80 ሚልዮን የኢትዮጵያ ህዝብ አደባባይ ወጥቶ እንዲያጅብ ማድረግ አስቀድሞ ታች ወረዶ በመደራጀት ሚስጢራዊ በሆነ መንገድ የሃዘን ልቅሶው ወደ ፖለቲካዊ ማዕበል ተቀይሮ ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሰረት እንዲኖረው ማድረግ
5. የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባላት በዚህ የሃዘን ሂደት እያንዳንዱ አባል ማጥናትና ወዳጅና ጠላት መለየት
6. ከመለስ ቀብር በኋላ የመለስ ራዕይ ለማስፈፀም ዕድሜው የደረሰ ሁሉ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባል እንዲሆን ማድረግ በዛው አድርጎ የተቀዋሚ ፓርቲዎች ድጋፍ እንዲደርቅ ማድረግ የሚቀሩ ጥቂት አባለቶቻቸው ከሁሉም ነገር በመነጠል ከገፅ መሬት እንዲጠፉ ማድረግ

በነዚህ የተጠቀሱትን አቅጣጫዎች ህዝቡ አንዳ አንድ ሰው ለማሰለፍ ከህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ጀርባ እንዲቀም ማድረግ ወ.ዘ.ተ የሚሉ ነበሩ: እነዚህ ዕቅዶች ከወጡ በኋላ መለስ ሞቱና ተቀበሩ በልቅሶና በቀብር መደረግ የሚገባው ዘመቻ የተፈፀሙ ከቀብር በኋላ ላይ የተዘረዘሩ ዕቅድ መሰረት፦

1. መጀመርያ የከፍተኛና መካከለኛ አመራር ገምገማዊ ስልጠና በሚል ሽፋን የህ.ወ.ሓ.ት ካድሬዎች ሁሉ በመንግስት

የሥራ ጊዜ በመንግስት ገንዘብ ዉሎ አበል እየተከፈላቸው ለአንድ ወር ሰለጠኑ

2. በሁሉም በሃገራችን ዞኖች ወረዳዎች ያሉ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባላት የመንግስት ሰራተኛ በሁሉ ዓይነት የመንግስት ሥራ ዉሎ አበል እየተከፈላቸው 10 ቀናት ስልጠና ተሰጠ በነዛ ስልጠናዎች የተካፈሉ የፓርቲ አባላት ያል ነበሩ ግዴታ አባላት እንደሆኑ ፎርም ሙሉ ተባሉ ፎርም ለሞምላት ፍቃደኞች ያልሆኑ ሰርተው የመብላት ዕድላቸው ጥያቄ ዉስጥ ገባ: ዜገነች በዜግነታቸውና በሙያቸው ሰርተው የመኖር መብታቸው ተነጠቁ::
3. የመቀሌ አስተዳዳሪዎች የቀበሌ ካድሬዎች ምልሻዎች ለብቻቸው ለ7 ቀን ሰለጠኑ: እነዚም በመንግስት አበል ነው
4. ዕድሜ ደረስ የሆነው ሁሉ የኢትዮጵያ ነዋሪ በከተማ በገጠር ሴቶችና ወንዶች ለየብቻቸው ለ5 ቀን በመሰብሰብ ለሴቶች 30 ብር ለወንዶች 35 ብር አበል በመመደብ አሰልጥነው የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ሁሉ አባልፓርቲ እንዲሆን አስገደዱት
5. ፖሊሶች የሃገር መከላከያ ሚኒስተር ወታደሮች እንደዚሁም ዳኞች አቃቢ ሕግ ሕገመንግስት ሽፋን በማድረግ ለ5 ቀን ያህል ሰለጠኑ

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ሃገራችን ህዝብ በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባል ያልሆኑ የመይኖሩበት ሃገር ሆነች የተደረጉ ስልጠናዎች አንዱ አጀጀንዳ እቺ ሃገር ያለ ተቃዉሞ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ብቻ እየተመራች የመለስ ራዕይና ከአቢዮታዊ ዴሞክራሲ እምነት ዉጭ ሌላ እንዳያምን ተቃዋሚዎች ለማግለል የተሰጣቸው ስልጠና ነበር: ለአብነት በትግራይ የነበረ ዓረና ትግርይ (ኮረኮንች) አቋቁሞ የጥፋት መልእክተኛ ፀረ ህዝብ ትግራይ የሆኑ የትምክህት ኃይሎችና እንደነ መራራ ጉዲና የጠባብ ኃይሎች

ከኢሰፓ አብሮዋል በመስዋእት የመጣ ስርዓት ሊቀሙን በማለት ስም በማጥፋት ተንቀሳቀሱ::

ህዝብ ባለፉ 21 ዓመታት የተመዘገቡ ልማት መለስ ብቻው እንዳ መጣቸው መለስ ለዚች ሃገር ሲል ለሊት ከቀን በሥራ ተጠምዶ ሳይታክት ሲሰራ ደክሞ አረፈ (ሞተ) በማለት በሃገራችን ያሉ ባለስልጣኖች ሥራቸው ምን ይሰሩ ነበሩ እንዳይባሉ እንኳን አላፈሩም: ብቻው ነበር ሁሉም ነገር ሰሪ የአባይ ግድብ ፈለሰፈ የእርሻ ሳይንስ የመዓድን የወታደራዊ ሳይንስ አጠቃላይ የልማት ፈላስፋ ብቻው ነበር አሉ: ዉጭ ህዝብ ግንኙነት በኩልም ዉጭ ጉዳይ ሚኒስተር እንዳለ ተቆጥሮ ነበር በመለስ የዉጭ ግንኙነት መሃንዲስ ተባለ: መለስ የአፍሪካ ፈላስፋ በዓለም መንግስታት ታዋቂነት ያተረፈ ነበረ ተባለለት: መለስ ይቅርና ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሉእላዊነት የቆመ ነበር አሉ: መለስ ግን ኢትዮጵያ ሃገራችን በዘመነ መለስ ሉኡላዊነቷ ተደፍሮ በኢርትራ በሱዳን የተወሰደ መሬታችን ኢትዮጵያ የባህር በር እንዳይኖራት ያደረገ ነበር::

በስልጠናው በመለስ ፖሊሲ ጥራት ህዝባችን ሶስት ጊዜ በልቶ ጠግቦ እየኖረ ነው ተባለ: ህዝባችን ግን ይቅርና ሶስት ጊዜ ሊበላ አንድ ጊዜ ለመብላትም በመከራ ያገኛታል አብዛኛው ህዝባችን ቁምራ (ቁርስ ምሳ ራት) በአንድ ጊዜ ይበላና ይተኛል: ሁኔታው ይህ እያለ የመለስ አምላኪዎች ህዝብ ጠግቦ ዋለ አሉን መቸ ይጉዳይ ብቻዉን: ህዝባችን እየፈለሰ በባዕድ ሃገር አይደለ የሚሰቃይ ያለው በሚቆጣ ሰው አጀንዳ ተከታተሉ::

የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎችና ካድሬዎች ለመለስ በዚህ ሃገር እንደልዩ ፍጥረት ተቆጥሮ ህዝብ ላይ አምልኮ አሳድሮ በባዶ ሆዱ አሁንም ለላሸቀው ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ተሸክሞት ለጓዝ በሰበቡ አሁን ያሉ መሪዎች እየተኮፈሱ ተንደላቅቀው ሊኖሩ የሚያደርግ ሌት ተቀን እንቅልፍ አጥተው ሰበኩ::

# በመለስ ሞት ምክኒያት ብዙ ገንዘብና ንብረት ባከነ

በሃገራችን ሰው ሲሞት ተስካር አታድርጉ በትንሽ ወጪ ፈፅሙት: ወደ ድህነት ትገባላቹሁ እየተባለ በመንግስት ደረጃ በብዙሃን መገናኛ፣ በኮንፍረንስ፣ በጉባኤ ብዙ ተነግረዋል በቀብር ጊዜም ብዙ ህዝብ መውጣት የለበትም ሰው ከሥራ መተጓጐል የለበትም፣ አስለቃሾች እንዳይኖሩ፣ ቀባሪ ህዝብ ሥራው እንዳይጎዳ: ቀብር በጧቱ ይጨረስ ተብሎ በየ ወረዳው በየ ቀበሌው ሕግ ወጥቶበት ከሕግ ዉጭ የሰሩ ገበሬዎች ብዙ ተቀጥተዋል: ሰርግ ክርስትና የልጅ የልደት በዓልም አባካኝ ስለሆነ እንዳይደረግ ተወስናል ሕግም ወጥቶዋል: በተጨማሪም የሃዘን ቀን ከሶስት ቀን በላይ እንዳይሆን ይነገርና ሕግ ይወጣ ነበር::

በመለስ ሞት ግን የወጣ ሕግ ሁሉ ተናደ: መለስ ከሞተ ጀምሮ ለፎቶግራፍ፣ ለፖስተር፣ ለካሜራ፣ ወደ ሃዘን የወጣ ህዝብም በሃገር ደረጃ 13 ቀን ሙሉ ሰልፍ የወጣው በ9 ክልሎችና አዲስ አበባ ደሪዳዋ እስከ ቀበሌዎች ድረስ ድንኳን ተተክሎ ሰው ሁሉ 3ቀን ሙሉ ሃዘን ተቀመጠ: ሃዘንተኛ ተቀባዮች የቀበሌ ሴቶች ነበሩ: የቀበሌ ሴቶች በተራ እየወጡ ህዝቡ የዕለት ጉርሱ እየቀነሱ እንጀራ ወጥ ዉሃ ለስላሳ አልፎ ቢራ ከዛም በላይ በጀት አውጥተዋል: ህዝቡ ሰላማዊ ሰልፍ ዉጣ ጥዋፍ ሻማ ግዛ እየተባለ ለብዙ ገንዘብ ከስረዋል: ይህ በመንግስት ከተገዛ ሻማና ጥዋፍ አይጨምርም: ጥቁር ካናቴራ ጥቁር ልብስም እንዲ ገዛ ተብለዋል ተገድደዋል: ከክልሎች ሁሉ ቀባሪ ህዝቦች ሥራቸው ጥለው ተጉዘዋል ለመጓጓዣ ለአበል በመቶ ሚልዮን የሚቆጠር ገንዘብ ወጥተዋል: ለሆቴል ሌላ ወጪ ተደርገዋል የመንግስት ማኪናዎች፣ አየር፣ ባቡር ያወጡት ለነዳጅ ገንዘብ እጅጉን ብዙ ነው::

ከቀብር በኋላ ከህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ቁንጮዎች እስካለ ስብሰባ ቀበሌ የወጣ ዉሎ አበል፣ መጓጓዣ፣ የመንግስትና የህዝብ የሥራ ሰዓት መባከን በገንዘብ ሲተመን በመቶ ሚልዮን የሚቆጠር ገንዘብ

ነው: በአጠቃላይ የመለስ ቀብርና ከዚያ በኋላ ለመለስ አምልኮን ለማስረፅ የአባይን ግድ ለማስገደብ የሚችል ገንዘብ ባክነዋል ባንልም በቢልዮን የሚቆጠር የሃገራችን ሃብት ግን ባክነዋል::

የተከበራቹ ወገኖቼ ለመለስ ሞት ለምን ታዘነ ከሚል መንፈስ በመነሳት አይደለም ይህ ታሪክ የተፃፈው: እንደ ዜጋም እንደመሪም መታዘን አለበት ግን ይህ ቀብርና ሃዘን የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎች በሃዘኑ አሳብበው በመለስ አምልኮ የራሳቸው አምልኮ ተብሎ ለርካሽ ፖለቲካ ተሰሚ ተብሎ የሃገር አንጡራ ሃብት ማባከን ወንጀል ከመሆኑም በላይ ለትውልድም መጥፎ ልምድ የሚያስተላልፍ የሚያሳፍር ነው: እንግዲህ እስከ አሁን የመለስ ህመም፣ ሞት፣ ቀብር፣ ከቀብር በኋላ የነበረ ሁኔታ: መላው የኢትዮጵያ ህዝቦች በተለያዩ መንገድ የሚያውቁት ነው: ግን ይህን ለመፃፍ የተፈለገበት ምክኒያት የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎችና ካድሬዎች የዉስጣቸው ችግር ለመሸፈን መለስ ሙቶ ተብሎ አስከሬኑ ሃገር ዉስጥ ገብቶ ግብአተ መሬት ገብቶ እስከ አሁን ለመለስ የተሰጠ የራሱ ያልሆነ ታሪክ የኢትዮጵያ ህዝብና ታጋዮች ያለፉትና ያሉት ሥራ በሙሉ ለመለስ ሲሰጡት አይተናል ሰምተናል: እስከዚህ ድረስ ድንገተኛ ሞት ስለሆነ በመደናገጥ ሊፈፀም የሚችል ነው ይቻል ነበር: የተደረገው ሁሉ ሆን ተብሎ ለፖለቲካ ትርፍ የተሰራ መሆኑ መረጋገጫ ደግሞ በታህሳስ መጀመርያ ወር ታትሞ የወጣ አዲስ ራዕይ የሚል ስለመለስ አምልኮ ብቻ ያስቀመጠው ሃሳብ በትክክልም ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ሆን ብሎ የሰራውና የሚሰራው ያለው መሆኑ በመረጋገጫ ይህ ጉዳይ ግብረ መልስ መስጠት አለበት ከሚል እምነት ነው:: ስለዚህ ፅሑፉ ሃቅን በመመስከር ለመደገፍ ለመቃወም በማመን ተፅፈዋል: ከላይ የተዘረዘረው ሃሳብ እንደ መንደረደሪያ ነው የተቀመጠው::

## ክፍል 2

## "መለስ ዕድሜ ልኩ ለብቻው እውቅና ብቻ የተገለ መሪ"

አዲስ ራዕይ ጥቅምት 2005 ዓ.ም ልዩ እትም: ላይ እንደተገለፀው የዚህ ፅሑፍ ዓላማ የመለስን የትግልና የ 21 ዓመት የግዛት ታሪክ አስመልክቶ አዲስ ራዕይ መለስ ለሰው ልጆች ምቾት የተፋለመ የዘመን ስብእና የሚል 80 ገፅ መፅሓፍ በሚልዮን የሚቆጠር መፃሕፍት ታትሞ በመላው ሃገራችን ተሰራጭተዋል እኔም መፅሐፉ ደጋግሜ አነበብኩት: የመፅሐፉ ይዘት ህ.ወ.ሓ.ት 17 ዓመት የትጥቅ ትግል ታግሎ ብዙ ጀግኖችና ፈላስፋቆች የተሰዉበት በ21 ዓመት የመለስ አገዛዝ ተብሎ የሚነገርለትም ብዙ የኢትዮጵያ ሙሁራን ተመራማሪዎች ባለሙያዎች እንዲሁም ከሞት የተረፉ ብዙ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ታጋይ የነበሩ የሰሩት ሥራ ሁሉ የአዲስ ራዕይ ፀሐፊዎች ጠቅለል አድርገው ለጓድ መለስ እንደሰጡዋቸው ተመለከትኩ::

እኔም ይህ መፅሐፍ ታሪክን ለባለታሪክ እንደመስጠት ጠሚኒስተር መለስ የሰሩትና ያልሰሩት ሁሉ መስጠት ፍትሃዊ ሆኖ ስላልታየኝ የአቅሜን የማውቀውና ያየሁት በአካል የነበርኩበት አስተካክየ ለህዝብ ሃቁን እንዲያውቅ አደርጋለሁ በማለት: መስተካከሉ የሚጀምረው ከመጀመር ያው የማውጫ ገፅ ይጀምራል: 8ኛ ዓመት ቅ4: 2005 ዓ.ም ልዩእትም በዚህ ገፅ ሁለት የመለስን ህልፈተ ሂወት አስመልክቶ ከተነገሩት፦

- በዚህ ገፅ የሩዋንዳ፣ የኡጋንዴን፣ ደቡብ አፍሪካ፣ የደቡብ ሱዳን፣ የቀድሞ የደቡብ አፍሪካ ፕረዘደንት ነበር የአመሪካ በአፍሪካ ጉዳይ አስፈፃሚ ሱዛን ራይዝ፣ ወ.ዘ.ተ መለስ ዜናዊ ሙተው በስርዓተ ቀብር ተገኝተው ስለመለስ አድናቆት ንመልከት
- "መለስ ይላሉ የአፍሪካ የኔፓድ ተዋናኝ ትልው ራዕይ የነበራቸው በተለይ ደግሞ ለአፍሪካ ወክለው በቡድን 8፣ በቡድን 20፣ በአየር ንብረት መከላከል በመሳተፍ የአፍሪካ ባንዴራ እንዲውለበለብ፣ የኔፓድ ሊቀመንበር በመሆን፣

ለአፍሪካ ብሎም ለመላው ዓለም ወሳኝ ሚና እንደነበራቸው፣ በፍትህ፣ ነፃነት፣ በልማት በሚመለከት ለሚነሱ ጥያቄዎች ተጋፍጦ የሚታገል ትልቅ መሪ ብለው ያመጉሱዋቸው አይቻለሁ::"

- በነዚህ ታላላቅ መሪዎች የሞጎሳ ሃሳብ እጅግ ጥሩና ለመለስ የሚገልፁዋቸው ናቸው እኔ መለስ ስለአፍሪካ አመልክተው ለአፍሪካ ነፃነት አፍሪካውያን በዓለም መድረክ እኩል እንድንታይ ማድረጋቸው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያውቀዋል የአፍሪካ ነፃነት በሚመለከት ጃንሆይ ለህዝባቸው በዝበዥ ዘረኛ ሁሉም ዐይነት ሰብኣዊና ዴሞክራሲያዊ መብት የማያከብሩ ቢኖሩም ስለአፍሪካ ነፃነት አንድነት ግን ፊር ቀዳጅ ነበሩ በርቀዳም የተጋፈጡ ስለሃገራችን ሉኡላዊነት ስለ 3ሺ ዓመት ታሪካችን ስለየነፃነት ባንዴራችን ፍፁም የማይንበረከኩ ነበሩ::
- ኮነሬል መንግስቱም በሃገራችንና በህዝባችን የፈፀሙት ፋሺሽታዊ ግፍና ጭፍጨፋ እንዲሁም የዘር አድልዎ የሃይማኖት ነፃነት መንጠቅ ቢኖሮዉም ስለአፍሪካ ነፃነትና አንድነት ጠንካራ ነበር: በደቡብ አፍሪካበዝንባብዌ ትልቅ ሥራ ዘርግተዋል
- ስለዚህ መለስ ከላይ የጠቀስኩዋቸው ስርዓቶች የሚያመሳስላ ቸው መለስም ለአፍሪካ ነፃነት የነበራቸው ኣቋም አንድ ናቸው::
- በሃገር ዉስጥ ከህዝባቸው የነበራቸው መልኩ ይለያያል እንጂ በሰብአዊ መብት አጠባበቅ፣ በፍትህና መልካም አስትዳደር፣ በሕግ የበላይነት፣ ነፃ ምርጫ አለመኖር፣ በግለሰብ መብት አጠባበቅ፣ በብዙሃን ፓርቲ መኖርና በዉድድር በህዝብ ዳኝነት በሰላም ስልጣን መሽጋገር በሌለወንም ሶስቱ መንግስታት አንድ ናቸው::

- በመለስ ስርዓት ለዩስሙላ ተቃዋሚ ፓርቲ ቢኖሩም ለዩስሙላ የፕሬስ ነፃነት ቢኖርም በአጠቃላይ በሕገመንግስቱ የሰፈሩ ሃቅ ነገሮች ቢኖሩ መለስ በረቀቀ ዘዴና መንገድ ስለዓፈኑዋቸው አልሰሩም፣ መንግስቱ ሰው ይገድል ነበር ጠረኛ ነበር በመለስ ጊዜም ሰው በጅምላ ሙተዋል፣ 1997 ዓ.ም ምርጫ በጋምቤላ በሌሎችም ብዙ ዜጎች ተገድለዋል::
- የማያማሳሰላቸው መለስና ጓዶቻቸው ኢትዮጵያ የ100 ዓመት ታሪክ ያላት ይላሉ፣ ሉአላዉነት ሃገር እንዲደፈር ብቻ ሳይሆን ሃገራችን ተቆርሳ መሬታ እንዲወሰድ አድርገዋል ጃንሆይና መንግስቱ የቆየች ቀይ ባህር በማሳጣት ታሪካዊ አመጣጥ የሌለው ኢትዮጵያ የባህር በር ከማሳጣት አልፎ ሃገራችን ሃገራዊ ፀጥታ ጥገኛ እንድትሆን የወደብ ጥገኛ አድርጎዋታል::
- ልማት በሚመለከት የአፍሪካ መሪዎች ለመለስ በልማት ቁርጠኛ ብለዉታል: እንግዲህ የአንድ መሪ የልማት መለኪያው የሚመራው ህዝብ ጠግቦ ያድራል ወይ ከስደት ድነዋል ወይ የሚሉ ጥያቄዎች ማንሳት ይገባል: በመለስ ዘመነ መንግስት ኢትዮጵያ ጥቂት የመለስ ጓዶችና ከነሱ የተቋራኙ ግለሰቦች ሰምተዋል: የተማረና ያልተማረ ወጣት ሥራ አጥነት ስደት በዉጭ ተሰዶ መሞት መንገላታት አለ
- እነዛ በመንገድ ሥራ በሃይድሮ ኢሊክትሪክ ትምህርት ህክምና አንዳንድ እንድስትሪ ቢኖሩም በእርሻ የተሰራ ነገር ቢኖር የአባይ ግድብ ቢጀመር የባቡር ሃዲድ ዕቅድ ቢወጣ ይህ ተግባር አንድ ሃገር ሊመራ ነኝ የሚል መንግስት ሊሰራው የሚገባው ነው: ሃገር እገዛለሁ የሚል መንግስት መንገድ፣ ህክምና፣ ትምህርት፣ እርሻ፣ ንግድ፣ ንፁህ ዉሃ፣ መጠልያ፣ መብራት ወ.ዘ.ተ ማስፋፋት አለበት: እነዚህና

ሌሎች ካልሰራ ስልጣኑ ሊኖር አይችልም: ስለዚህ የግድ ሁሉም ዐይነት መሰረተ ልማት መስራት አለበት::

- ለአብነት ለፋሺስት ጣልያን ኢትዮጵያ ወሮ ዝምብሎ ቁጭ አላለም የቅኝ ግዛት ስርዓት ሊኖር ስለነበረበት በ5 ዓመት የግዛት ዘመኑ እየተዋጋ ኢትዮጵያ ምንም የመኪና መንግድ የሚባል ያልነበራት በማኪና መንገድ ልትገናኝ አድርገዋል: ሌሎች መሰረተ ልማትም ሰርተዋል: ይህ ማለት ግን የኢትዮጵያ ህዝብ ያገኘው ጥቅም አልነበረም: ስለሆነ መለስ የልማት ሃርበኛ ነበር ሲባል በ21 ዓመት የተሰሩ መሰረተ ልማት ወዶ ሳይሆን ልክ እንደፋሽስታዊ ጣልያን ለስልጣኑ ሲል እንደሰራው ሁሉ መለስና ጓዶቻቸውም የሰሩት ሥራ ካለ በዚህ መንግድ መታየት አለበት
- እነዚህ የአፍሪካ መሪዎች ለመለስ የያስቀመጡት አስተያየት ላይላዩ የመለስን ልታይ ልታይ አይተው ኢትዮጵያ መለስ ባገሩ እንዴት ልማት አረጋገጠ ብለው እንደማጥናት ፊንታ ሳያጠኑ አስተያየት መሰጠታቸው ትክክል አይደሉም: የአፍሪካ መንግስታት ግን በኢትዮጵያ ብዙ ስህተት ሰርተዋ ል: ለዚህ አብነት የሚሆን ኢትዮጵያ በ1997ና በ2002 ዓ.ም የፓርላማ ምርጫ ተካሂደዋል: በሁለቱ ምርጫዎች በተቃዋሚ ፓርቲዎች ብዙ ፀረ ዴሞክራሲ ሥራዎች ተፈፅመዋል: ምርጫው ፍትሃዊ አልነበረም የምርጫ ኮሮጆዎች ተሰርቀዋ ል: በዛን ወቅት የአውሮፓ ሕብረት፣ የካርተር ማእከል፣ የአፍሪካ ሕብረት ታዛቢዎች ነበሩ የአመሪካና የአውሮፓ ታዛቢዎች ምርጫው ፍትሃዊ አልነበረ ም ብለው ሲመሰክሩ የአፍሪካ ህብረት ታዛቢዎች ምርጫው ፍትሃዊ ነበር ብለው መሰከሩ: በመለስ ያለው አስተያየትም ከዚሁ አይለይም: ስለሆነ አስተያየት ሰጪዎች ያላጠኑት

እንዳለ መረዳት አለባቸው: ወረድ ብሎው በ80 ሚልዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ያለው ብዛት ቢመለከቱ ይሻል::

## ክፍል 3

- መለስ ከትጥቅ ትግል ጀምረው እስከ ህልፈተ ሂወታቸው ልታይ ልታይ ማለት ባህረያቸው ነበር: በሁሉ ሥራም የሳቸው ስም መኖር የግድ ይላል: በ17 ዓመት የትጥቅ ትግል ጊዜ አልተሳካላቸዉም
- "አዲስ ራዕይ በርእሰ አንቀፁ ገፅ 5 አዲስ አዲስ መስመር አንድ መለስ ጉዳዩ ከወሰኑ በኋላ የፁሑፍ ዝግጅት ክፍል ያደርጋሉ ጓድ መለስም በሌሎች ሥራዎች እንደሚያደርጉዋ ቸው ሁሉ ከበድ ያለዉን መሰረታዊ ጉዳይ የሚተነትኑበትን ይወስዳሉ ይላል"
- መለስ ከትጥቅ ትግል ጀምረው በጦርነት ነው የማይጠጉ እንጂ በሌሎች ሥራዎች ስማቸዉን ለማግነን በማሰብ ታጋዮች ብዙ ወራት ሳምንታት ቀናት የደከሙበት ሥራ በሆነ መንገድ ያልሰሩት ያልደከሙበት ሥራ እንዳሉት ለማሳወቅ ጣል ያደርጉበታል እንደዛ እያሉ ስመግኑን እንዲሆኑ ቀስ በቀስ እየደለቡ የመጡ ናቸው: አነደዛ በማድረጋቸው በ1982 የህ.ወ.ሓ.ት ከፍተኛ ቦታ ተቆናጠው በአዲስ ራዕይ የሳቸው ተሳትፎ መፃፋቸው ሌላ ሰው ሊፈፅመ ው የማይችል አርእስት ሆኖ አይደለም: የያቸቹ የጥንት ባህሬያቸው የሰዎች ሥራና ድካም የራሳቸውን ሥራ ሆና ታዋቂነትን ታመጣለች ያሰቧት ካላቸው ፍላጎት የመነጨ ነው
- "አዲስ ራዕይ ገፅ 5 በርእሰ አንቀፅ አዲስ መሰመር 1 መስመር 4: እኛ በልባችን ጓድ መለስን ዋና አዘጋጅ አድርገን መርጠነዋል ለሪኢ.ቶ ዓለማዊና ፖለቲካዊ ትግልና ጥራት የተለየ ቦታ የሚሰጠውና ሰዉን በአስተዳዳራዊ

*መንገድ ሳይሆን በሃሳብ በመታገልና አሳምና በመንቀሳቀስ የሚያምነው ጓድ መለስ ምናልባት በጠቅላላ ከተዘጋጁት እትሞች ከአንድ በስተቀር በሁሉም የአዲስ ራዕይ ብቻ አልተሳተፉም"*

- *በሁሉ ግን አሉ ብሎ መለስ በሁሉ ነገር እጃቸው እንደ ማያስገቡ እሳቸው ትንሽ ካልጨመሩበት የሙሁራን ሥራ እንደ ማያምኑ አነጥሮ አስቀምጠዋል: በኢትዮጵያ ደረጃ ያለው ሙሁር ይቅርና በዚያ በኢህአድ ፅሕፈት ቤትና በጠ/ሚኒስተር ቢሮ ለዚች ትንሽ መፅሄት የሚያዘጋጅና የሚተነት ን ጠፍቶ አይደለም መለስ ከላይ እንደተገለፀ ሰዎች በሰሩት ሥራ የራሳቸው ስም መኖር የግድ ይል ስለነበረ ነው::*
- *አንድ አብነት ልንገራቹሁ በትጥቅ ትግል ጊዜ የህ.ወ.ሓ.ት አስተሳሰብ አመልክቶ ለወራት ያህል የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ካድሬ ስልጠና ይሰጥ ነበር በዛ ማሰልጠኛ በበላይ አባይ ፀሃዬ በሚመራው ሆኖ ምክትል አረጋሽ አዳነ ነበረች የነበሩ የፖለቲካ ማሰልጠኛ ተፅፎ የሚሰጣቸውም በአባይ ነበር በዛ ትምህርት ቤት መለስ ዜናዊ፣ አማረ አረጋዊ፣ ዓለምሰገድ ገ/አምላክ፣ ፈትለወቅ ገ/ዝሄር፣ ሞንጆርኖ፣ አረጋሽ አዳነ፣ የዉብማር አስፋው፣ ሙሉጌታ ገ/ሂወት (ጫልቱ) ነበሩ: በዚህ ትምህርት አንደኛ ካድሬ የሚባሉ ቀለም የቆጠሩ (ትንሽ ትምህርት ያላቸው ክፍል ክፍል ለይተው የሚያስተምሩ) መለስ፣ አማረ አረጋዊ፣ ሞንጆርኖ፣ አብረሃ ደስታ፣ አረጋሽ አዳነ ነበሩ: 2ኛ ካድሬ የሚባሉ ከአርሶ አደሩና ወዛደሩ የመጡ ብዙ ትምህርት ያልቀመሱ ናቸው: እነዚህ የሚያስተምሩ ሙሉጌታ ገሂወት፣ የዉብማር አስፋው ነበሩ: በዚህ ጊዜ ከላይ የተጠቀሱ ፖለቲካ አስተማሪዎች ለወራት ያህል ሲያስተምሩዋቸው የከረሙ መለስ ያቺ የተለመደች ባህሪያቸው በካድሬው ተሰሚነት ለመፍጠር*

ትምህርቱ ሊገባደድ ሲል ገደማ በሆነ መንገድ ቆፍሮ ምክኒያት ፈጥሮ እያንዳንድ ክፍል ገብቶ ዲስኩር ያሰማ ነበር: ይህ ተግባር በሂወት ያሉ ሰዎችም ይመሰክራሉ::

- አሁን የራዕይ ፀሐፊዎች መለስ ዋና አዘጋጅ አድርገን መርጠነዋል ለረኢ.ቶ ዓለማዊና ፖለቲካዊ ትግል ጥራት የተለየ ቦታ የሚሰጠው ነው: በአስተዳደራዊ መንገድ ሳይሆን በሃሳብ ስለሚያሳምን ይላሉ::
- መለስ ያሉትን ሁሉ ዝም ብሎ የሚሰማቸው የሚያመልካቸው ሌሎች ሰዎችም እንዲያመልኩ የሚያደረጋቸው ወደ ስልጣናቸው ካልተመጣጠረ እጅጉን የተመቹ ናቸው: እንዲውም ይሸልሙታል::
- መለስ የሚቃወማቸው ሰው ይቅር ከሳቸው በላይ በህዝብ ተሰሚነት ያተርፋል ብለው የሚጠራጠሩት ካለ ሰው ይለኛል ሕግ እጥሳለሁ የሚል ዩሉኝታ በሌለው መንገድ ያሽቀነጥሩታል: በአዲስ አበባ አስተዳደር አቶ አርከበ ዑቅባይ ተሰሚነት አግኝተው አረከበ አርከበ አስብለው ነበር ነገር ግን አቶ መለስ ባሉበት ተገምግመው ምን አጋጣሚ እንዳገኛቸው በስብሰባው የነበሩ ሰዎች የሚመሰክሩት ሃቅ ነው: ስለሆነ መለስ በአስተዳደራዊ አሰራር አይሰሩም በማመን ነው የሚባለው: እንዲያዉም መለስ በጣም ብልሃተኛ ሰው ናቸው ሁሉም ነገር ይችላሉ: በሰዎች ተሰሚነት ለማግኘት ይጥራሉ ከዛ በኋላ ቀላል የሆነ ተሰሚነት ያዩ ዕለት ግን ተለያዩ መንገዶች አድርገው የመጉዳት ሙያቸው ከፍተኛ ነው::
- ለአብነት መለስ የህ.ወ.ሓ.ት ሊቀመንበር ከመሆናቸው በፊት ካድሬ በሚያስተምሩበት ትምህት ቤት ከሰራዊትም ከፓርቲው ስታፍ ታጋዮች ብዙ ደጋፊዎች አገኙ መለስም ከዛም ከዛም የሰበሰቡዋቸው ንግግሮች በማድነቅ ቀስ በቀስ በወቅቱ ለነበሩ ሊቀመንበር አባይ ፀሃዬ የህ.ወ.ሓ.ት ሊቀመንበር

ስብሃት ነጋ እየነጠሉዋቸው መጡ: መለስ ለሊቀመንበር መሀሆን አለበት የሚል ወሬ ተስፋፋ: መለስ ይህ የታጋይ መንፈስ ካረጋገጡ በኋላ በህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ዉስጥ በመግባት ድጋፍ በማግኘት በተለይ ደግሞ ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቶ ስዩ አብረሃ፣ አቶ ተወለ ወማርያም፣ አቶ ዓለምሰገድ ገአምላክ፣ አቶ ክንፈ ገመድህን ሌሎች ማ/ኮሚቴ በጎናቸው በማድረግ ለአቶ ስብሃት ነጋም ድሮዉም እንደንሰሃ አባት ያዩዋቸው ስለነበሩ እሳቸዉም ስለባረኩላቸው ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ በ1982 ዓ.ም ታህሳስ ወር አካባቢ አቶ አባይ ፀሃዬን ፈንቅለው የህ.ወ.ሓ.ትና ማለሊት ቁንጮ ሆኑ::

- መለስ ከሞቱ በኋላ አባይ ፀሃዬን ጨምሮ መለስ ለህ.ወ.ሓ.ት ፈጣሪ የሚለው አነጋገር ዉሸት ነበር: ስለመለስ በህ.ወ.ሓ.ት የነበራቸው አስተዋፅኦ በሚቀጥለው እገልፀዋለሁ: ስለአዲስ ራዕይ መፅሄት አዘጋጆች አባባል ግን የመለስን ባህሬያት በጥልቀት አወቀው ነው የፃፉት ወይ ለአድርባይነት ብለው ለሚለው በበኩልዬ አድርባዮችና ለጊዝያዊ ጥቅም ብለው የፃፉት እንጂ እንደሙሁራን መጠን ጠፍቶባቸው አይመሰለኝም::

# ክፍል 4

# መለስና ፍረደሪክ ሄግል ሲወዳደሩ

- "8ኛ ዓመት ቅፅ 4 ልዩ እትም አዲስ ራዕይ ገፅ 9 አዲስ መስመር መስመር 9: የጓድ መለስ ስብእና የሄግልን አገላለፅ በመጠቀም ልንመረምረው ስንነሳ ወደኋላ ብንመለስበትም ቢሆን ምጡቅ የዓለማዊ ስብእና ከአውሮፓ ብቻ ይመነጫል አፍሪካና የጥቁር ዘር በሙሉ ከእንሰሳዊ አረሜናዊ ባህሪ ዉጭ አይሆንም የሚለዉን ዘረኛና ፈረንጅ አምልኮ የሄግልን

አስተሳሰብ መለስ ታሪካዊ ዓለማዊ ሳይሆን ኢትዮጵያዊና አፈሪካዊ ምጡቅ ስብእና እንደሆነ በመረጋገጥ እየሞገትን ጭምር ነው ይላሉ"

- እነዚህ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ካድሬዎች (አዲስ ራዕይ) ለመለስ ፈላስፋዊ ሂግል ከሚያወዳድሩ አፍሪካ ካሉ በስብእና የተላበሱ ምጡቅ ለምን እይወዳደሩም መለስ ይቅርና የዓለም የአፍሪካ ምጡቅ ሊሆኑ የኢትዮጵያ ምጡቅ ፈፃሚ ሊሆኑ አይችሉም
- ምክኒያቱም መለስ በዴሞክራሲ በሰብአዊ መብት አጠባበቅ አይታመኑም በሃገር ሉኡላዊነት አይታመኑም: ጃንሆይና መንግስቱ ይበልጣሉ: በህዝቦች ነፃነት ዜጎች ሃሳባቸው እንዳይገልጡ ሰላማዊ ሰልፍ እንዳይወጡ እንዳይፅፉ በነፃ የመሰላቸው መሪ እንዳይመርጡ የግለሰብ መብት የማይቀበ ሉ ናቸው: ታድያ እንዴት ብለው የዘመኑ ምጡቅ ስብእና የተላበሱ ይሆናሉ: መለስ በሃሳብ የሚቃወማቸው ወይ ለስልጣናቸው አደገኛ ነው የሚሉዋቸው ዜጎች የማግለሉ በሃገራቸው ነፃ ሆኖው እንዳይኖሩ የሚያደርጉ ፕሬስ የሚዘጉ ጋዜጠኞች ፖለቲከኞች በእሱር የሚያጉሩ ናቸው: ታድያ እንዴት ብለው የኢትዮጵያ ምጡቅ ይሆናሉ: ለመሆኑ ከሚስተር ማንዴላ ተወዳድረው የስብእና ምጡቅ ለመሆን ይችላሉ እንዴት በየትኛው መለኪያ: በበኩልዬ አልቀበለዉ ም: እንደ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ካድሬዎች ይህ አባባል ሲያንሳቸው ነው ለትልቁ ነገር መለስ ምጡቅ እያለ ከ40ና 50 ዓመት በመንፈስ መሪያችን ነው መለስ በውጡት ከሚመራን አመራር ዉጭ የሚመራንም ሌላ ፍልስፍናም አንቀበልም እያላቹሁ አይደላቹሁም እንይዝላችሁም: አሁንም በፅ 9 አዲስ መስመር 3 መሰመር 7 ታለቅ የዓለም ስብእና መሆኑ ማሳየት የሚጀምረው የጎጥና የመንደር የትምህርት ቤተና የቀበሌ ችግሮችን የሚያይና የሚያስተው

ል: እነዚህንም ለመፍታት የሚያስችል ልቦናና ብቃት ሳይኖሮው ዘሎ ታላቅ የዓለም ስብእና መሆን አይችልም: እንደገና ታላቅ የዓለማዊ ስብእና ከመሆን በፊት ታላቅ ሀገራዊ ስብእና መሆን የግድ ይላል: ዘሞዶቼ በዘመነ መለስ ጠባብነት የነገሰበት ሃገር ለመከፋፈል አደጋ የተጋረጣት በቀበሌ በወረዳ ከዛ በላይ በመልካም አስተዳደር እጦት ዜጎች የሚሰቃዩበት ህዝብ በተላላፊ በሽታ የሚሰቃይበት መንስኤው በማይታወቅ ዜጎች የሚሞትበት መለስ የሃገራችን የዉስጥ ችግር አፍነው ወደ ዉጭ ብቅ ብቅ ልታይ ልታይ የሚሉ ሰው ናቸው በቡድን 8ና ቡድን 20 ከቶኒ ፕለየርና ጁርጅ ቡሽ ከኦባማ ጎን ቁጭ ቢሉ ያመጡት ፋይዳ የለም: የሃገራችን ዜጎች ከፀሃይ ከብርድ ከዝናብ የሚጠለሉበት ቤት የሌላቸው የእንሰሳ ንሮ የሚኖርበት ሁኔታ እያለ መለስ እንዴት የዓለም ይቅር የኢትዮጵያ ምጡቅ ስብእና አልነበራአዉም::

- ይህ ቀልድ ነው የአዲስ ራዕይ ፀሃፊዎች የሃገራችን ወጣት በኪንያ፣ በኡጋንዳ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ሰዑዲ ዓረብያ፣ ዱበይ፣ ኩወት፣ ሊባኖስ፣ ሊብያ፣ የመን፣ ጀቡቲ፣ ሌሎች ሃገሮች ተሰዶ የሚሞት እንደባርያ የሚሸጥ ያለው: የመለስ መንግስትም በሕጋዊ መንገድ ርካሽ ጉልበት ሰው አለኝ እያለ በየ ወሩ በሕጋዊ መንገድ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ካርጎ እየሞላ ወደ ዓረብ ሃገሮች የሚዋለው ያለ ነው: መጣሉ የሚያሳይ ደግሞ በየ ቀኑ ከዓረብ ሃገሮች እየሞቱ እነዛ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሂወት ያለው ሰው ወሰደው ሬሳ እየጫኑልን የሚመጡ የነበሩ በመለስ ዘመነ ምንግስት ነው::
- ሌላ ቀርቶ አቶ መለስ በሰሜኑ ሃገራችን ከሚኖሩበት ቀያቸው በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በሻዕቢያ መንግስት ታፍሰው በሳህል በረሃዎች የ15ኛ 21ክፍለ ዘመን የሰው ፍጡዋ ባርያ እየተባለ ግፍ ይፈፀምበት የነበረ ዐይነት አገዛዝ

የሚፈፀምባቸው ያለው በመለስ ስርዓት ነው ያየነው: ስለዚህ አንድ ሃገረዊ ፍቅር የያለው መሪ እናንተ ምጡቅ የምትሉት መሪ ለነዚህ ዜጎች ሥራ አይፈጥርም ወይ አሁንማ በሚልዮን የሚቆጠሩ አምራች ወጣት ወገኖቻችን በሁሉ የአፍሪካና የዓረብ ሃገሮች ግልፅ የባርያ አገዛዝ እየተፈፀመባቸው ነው: ታድያ ጠ/ሚኒስተር መለስ በየትኛው መልኩ ነው ምጡቅ የምትሉዋቸው: ለመሆኑ የአዲስ ራዕይ ፀሃፊዎች በትክክል ኢትዮጵያውያን ዜጎች ናቹሁ መልሱ ለእናንተው::

## ክፍል 5

## "መለስ ለሰው ልጆች ምቾት የሰራ ታላቅ ተገባራዊ ሰው"

መለስ ባለፉት 21 ዓመታት ዉስጥ እንኳን ኢትዮጵያ በህዝቦች መካከል ብዙ ክፍፍልና ሰላማዊ ሁኔታ የማይታይባት ግጭቱና ትርምስ ያልተለያት: ደም መፍሰስ ሞት ስደት መፈናቀል ያልተለያት ደህንነትና ብልፅግና ዕውቀትና ድንቅርና የብዙሃን ምቾትና የዉሁዳን ችግር የሚፈራረቁባት: ህዝቦቿ በድህነት ምክኒያ ት የሚበሉት ምግብ እንደህልም የሚታያቸው: ዜጎች የመጠለያና የልብስ እጦት ህዝቦቿ ጤንነት አጥቶ በቀላሉ ሊድን በማይችል በሽታ የሚያልቅበት: ራሳቸው ከዝናብ ከፀሃይ ከብርድ ቾነፈር የሚድኑበት ወግ ያለው ቤት አለማግኘት ንፁህ ዉሃ የማይገኝበት ሁኔታ የታየው በመለስ ስልጣን ዘመን ነው: ታድያ መለስ ለሰው ልጅ ምቾት የሰራ ታላቅ ተግባራዊ ሰው የተባለበት በየትኛው መስፈርት ነው::

በዘመነ መለስ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል አለመኖር ጥቂት ዜጎች ደልቷቸው ተንደላቅቀው የሚኖሩበት አብዛኛው ህዝብ ችግሮት ተጎሳቁሎ የሚኖርበት ነው: ይህ ሁኔታ ፍትሃዊ የሃብት የስልጣን

ክፍፍል ጥያቄ ቀስቃሽ በዜጎች ያለው የይገባኛል ጥያቄ እያነሳ ይገኛል: እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ በዘመነ ስልጣን መለስ የነበሩ ችግሮች ምንም መፍትሄ ሳያስቀምጡበት ያለፉት: አሁን የአዲስ ራዕይ ፀሐፊዎች ተላለኪዎች መለስ የዘመኑ ስብእና ታላቅነት ምጥቁነት ብተወኑን ከ80 ሚልዮን የኢትዮጵያ ህዝብ 5% እንኳን ሁሉም ዐይነት ምቾት አለ ብሎ ቢመሰክርላቹሁ ለሽልማት ለመቅረብ አለባቹሁ: ግን አዲስ ራዕዮች የምቾት መስፈርታቹሁ በናንተ የመለስ አጋሮች በቀን 3ጊዜ ቡፌ ስለምትበሉ ነው

"አዲዝ ራዕይ 15 አዲስ መስመር መስመር 6 ነው: ለሰዎች በመኖርያነት የማትመች እየሆነች ከሚሄድ እንደማትድን ለመገንዘብ ፈፅሞ የማያስቸግርበት ደረጃ ላይ ደርሰናል: እናም በዘመናችን አንድ ዓለማዊ ምጡቅ ስብእና ያለው ሰው አስተዋፅኦ በትክክል ይመዝን ከተባለ በሰዎችና በተፈጥሮ መካከል ያለውና የሚኖረውን ግንኙነት ቀና አቅጣጫ ለማስያዝ ባደረገው አስተዋጽኦ ላይ በመመስረት ጭምር ሊሆን ይገባል: ለዚህ ነው የዚህን ታላቅ መሪ ሥራዎች በሰዎችና በተፈጥሮ መካከል ያለዉን ግንኙነት ለማቃናት ባደረገው አስተዋፅኦ ለመመዘን የምንገደደው ይላሉ"

የተከበራቹሁ አዲስ ራዕይ ስለአቶ መለስ ባህረ ልንገራቹሁ መለስ ይቅርና በዓለም ደረጃ በሃገር ዉስጥም ቢሆን ወደ መድረክ የምታወጣቸው ትንሽ ነገር እንኳን ብትገኝ ለማንም አሳልፈው እንደማይሰጡ የነበሩ መሆናቸው በዚህ ፅሑፍ መጀመርያ አካባቢ ጠቆም አድርጌ አልፋለሁ: ኋላም ይቀጥላል::

ስለተፈጥሮ ጥበቃና እንክብካቤና ተፈጥሮ ከሰው ልጆች ጋር ያለው ቁርኝት በተፈጥሮ እንክብካቤና መጠበቅ ካልተደረገ ምንም እንኳን በተለያዩ ምክኒያቶች ተግባራዊ ባይሆንም በጃንሆይና በደርግ ጊዜም ደን ልማት የሚባሉ አፈርና ዉሃ ጥበቃ ሲሰሩ ነበሩ: ምን ማለት ነው በተፈጥሮና በሰው መካከል ያለው ቁርኝት አሁን በመለስ የተፈለሰፉ አይደሉም: እርግጥ መለስ በቡድን 8ና ቡድን 20 በሌላ

የዓለም መድረኮች በሚጥም ቋንቋ ጮክ ብለው መናገራቸው ይመሰገናሉ: በሌላ በኩል በሃገራችን በሰው ልጅና ተፈጥሮ ያለው ቁርኝት ግን እንዱ ያለ አንዱ ለመኖር አስቸጋሪ መሆኑ እንዲተገበሩ የሚያጠኑ ምጡቅ ተመራማሪዎች ብዙ ብርቅዬ ኢትዮጵያውያን ኑረዋል አሁንም አሉ::

ሁሉ የሚያውቃቸው ስለሰውና ተፈጥሮ ያለ ቁርኝት በሚመለከት የሚተነትኑና በተግባር በቆራጥነት የሚንቀሳቀሱ በኢትዮጵያ ደረጃ ያሉ ሊህቃን ንተወውና በ17 ዓመት የህ.ወ.ሓ.ት የትጥቅ ትግል የነበሩ ፈላስፋዎች ልጥቀስ 1ኛ መለስ በዛብህ ኢትዮጵያዊ ትውልዱ ተነቤን በአውሮፓ ከፎቅ ወድቆ ሞተ የተባለው: አሁን በሂወት ያሉ 2ኛ ዶ/ር አሰፋ አብረሃ ኢትዮጵያዊ ትውልዱ ዓድዋ: በነበረችባቸው ዕድል ተጠቅመው በዛን ቀውጢ የትግል ጊዜ ተፈጥሮ ባለመጠበቅ ሃገራችን ሰው የማይኖርባት ትሆናለች: ስለዚህ ደርግ ከመጣል ጎን ለጎን ከሚደረገው ትግል በተጨማሪ ተፈጥሮን በእንክብካቤ መጠበቅ አለብን እያሉ ሙሁራኖች አቶ መለስም የነበሩበት የህ.ወ.ሓ.ት ሥራ አስፈፃሚ (ፖሊት ቢሮ) በሙሁራን የመጣ ሃሳብ በጭፍን በመቃወም ለሙከራ ተብለው የተጀመሩ ሥራዎች በመዝጋት ለሙሁራኖች ሞራላቸው የነኩዋቸው መሆኑ: ስለሆነ መለስ ለምጥቆች የማያበረታ ቱ ራሳቸው ብቻ ልታይ ልታይ የሚሉ እንጂ ለሰው ልጆችና ለተፈጥሮ የተመቹ አልነበሩም::

አንድ ነገር ግን ልመሰክርላቸው እሱም በ21 ዓመት የግዛት ዘመናቸው የተሰሩ በሰውና በተፈጥሮ ያለ ቁርኝት በተመለከተ ብዙ ተሰርተዋል: እነዚህ ግን የመለስ ምጡቅነት የሚገልፁ ሳይሆን በሃገራችን ያሉ የዩኒቨርሲቲ የምርምር ማእከላት ጥናቶች: የሃገራችን ነባር ሙሁራኖች የሰውና የተፈጥሮ ጥበቃ ትርጉም ተረድተው ብዙ በመድከም የተፈጥሮ ጥበቃ ሥራ የሰሩት ድል ነው: ከዚህ አልፎ ግን የነዚህ ዜጎችና ሙሁራኖች ድል በመስረቅ ያልሰሩት ሥራ በመለጠፍ ጠቅለል አድርጎ ለመለስ መስጠቱ ተቀባይነት የለዉም: የዚህ

መፅሐፍ ፀሐፊዎች ሥራ የሃገራችን ብቁ ሙሁራኖች ምጡቅነት የቀማ የታሪኩ ባለቤት ላልሆነ የሸለመ ሃሳብ ነው: አንድ ነገር ግን ለፀሐፊዎች ላስተዉሳቹሁ በዘመነ አገዛዝ መለስ ዜናዊ ብቁ ሙሁር በብቃቱ ለሃገሩ የማይሰራበት ለመለስ ጎንበስ ቀና እያለ እጅ የሚነሳ በሙያው የማይተማመን ሰው የመለስ አጃቢ እየተባሉ ደልቶዋቸውና ተቀማጥለው በሙሱና በስብሰው የሚኖሩ ሰዎች ተሸክመው እየተጓዙ መለስ ምጡቅ ነበሩ ትላላቹሁ: ይህ እንኳ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚመሰክረውና የሚያውቀው ስለሆነ ሁሉም ነገር ለታሪክ ፀሐፊዎችና ለህዝብ እንተወዋለን::

## <u>"መለስ ለሰው ልጆች ሰበአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት የተፋለመ"</u>

"አዲስ ራዕይ ቅፅ 4 ልዩ እትም ገፅ 15 እስከ ገፅ 17 አዲስ መስመር 2 መስመር መለስ ለሰው ልጆች መልከ መልካሙን የሚመኝ ከምንም ነገር በፊት ሰብአዊና ዴመሞክራሲያዊ ባህረያት የተላበሰ መሆኑ: ሰዎች ወደ ፖለቲካ ትግል ከመግባያቸው በፊት የኢኮኖሚ ጥያቄዎች ን በተለይ የምግብ የመጠለያና የልብስ ጉዳዮች መመለስ አለባቸው: በተለይ በድሃና ኋላ ቀር ሃገሮች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ በቅድሚያ መልስ ማግኘት አለበት: ከጉንበት 1983ዓ.ም በፊት ዜጎች ይረገጡ ነበሩ: ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በቅድሚያ የፖለቲካ ሪፎርም ወይ የዴሞክራሲያዊ ማካሄድ አማዋጭ አልነበረ ም: ከግለሰብ መብት አኳያ የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ባልተከበሩበት አንዳችም ህዝብ በኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ሊኖር አይችልም: መለስ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የሰብአዊ መብትና የዴሞክራ ሲን ጥያቄ በቅድሚያ በመመለስ ነው የኢኮኖሚያዊ ጥያዌዎችን ወደ መመለስ የተሸጋገረሩት: መለስ ለዴሞክራሲ ያካሂደው ትግል ከሁሉም በፊት ፀረ ዴሞክራሲያውያን አገዛዝ በማስወገድ የጀመረ

ነበር: በደርግ መንግስት ተገድቦ በነበረው የሰው ልጆች በነፃ የመንቀሳቀስ መብት አስከባሪ መሪ ነበር"::

## ክፍል 6

መጀመርያ ነገር በህ.ወ.ሓ.ት መለስ ብቻውን የታገለው ህ.ወ.ሓ.ትን ገንብተው ሂወታቸውን ሰጥተው ያለፉ ለመለስ ይመሩ የነበሩ በሂወት አሉ በህ.ወ.ሓ.ት እኮ በመቶሺ የሚቆጠር ወጣት ሙተዋል: ለአብነት በትግራይ ክልል ዓድዋ አውራጃ ዓእሕፈሮም የሚባል ቦታ በህ.ወ.ሓ.ት የትጥቅ ትግል ከ20ሺ በላይ በሻዕቢያ ጦርነት ከ5ሺ በላይ ተሰልፈው ከ25ሺ ታጋይ 95% ሙተዋል: ይህ አሃዝ የኢትዮጵያ ተለቪዥን ፕሮግራም በ29/4/2005 ዓ.ም በአየር ያስተላለፈው መረጃ ይህ ብቻ አይደለም: በትግራይ 44 ወረዳዎች አሉ ከዚያ ዉጭ ከሰቆጣ አውራጃ፣ ከሰሜን ጎንደር፣ ከሰሜን ምዕራብ ጎንደር፣ ከሰሜን ወሎ፣ ከሰሜን ሸዋ የታገሉ በመቶሺ የሚቆጠሩ ወገኖች መስዋእት ከፍለዋል: እነዚህ ገለባ ናቸው የአዲስ ራዕይ ፀሐፊዎች ልብ እድርጉ በበኩሌ ይህ ፅሑፍ መፃፋቹሁ ለመለስ ታሪክ እያጋለጣቹሁ ወይስ መልካም ታሪክ እየገነባቹሁ ነው: ለመሆኑ በረከት ስምአን ኤዲት አድርጎታል::

ሌላ መለስ ለራሳቸው ጥቅምና ስልጣን ለማግኘት የተፋለሙ ነበር: አቶ መለስ በሚናገሩት በሚፅፉት የስድብ ናዳ እንዳለ ሆኖ በተለይ በተለቪዥን መስኮት ብቅ ብለው መግለጫ ሲሰጡ ለሚጠየቁት ጥያቄ አጭር መልስ ሲሰጡ ዜጎች መልስ በኪሱ የሆነ ሰው ምን ይሁንና አፉኝ ባይሆን ንሮስ መልካም ነበር ይሉታል::

ነገር ግን እኔ መለስን ስመለከታቸው በአጠቃላይ ለሃገራችን ህዝብ  በተለይ ደግሞ በዚህ ሃገር ብዙ አስተዋፅኦ ካደረጉ የትግል ጓደኞቻቸውና አብሮዋቸው ለሚሰሩ ሙሁራኖች እንደዲስፖዛል ተጠቅመው የሚጥሉ መሆናቸው ነው የማውቃቸው: ለዚሁ መረጋገ ጫ በትጥቅ ትግል ጊዜ ወዳጃቸው የነበሩ የአመራር አባላት እንደነ

አረጋዊ በርሀ ግደይ ዘርአፅዮን በዉጭ ሃገር የሚኖሩ ሌላ እንደተኙሉ ሃዋዝ፣ ዑቕባዝጊ በየነ (ረዘነ)ና ሌሎች ብዙ ታጋዮች ደብዛቸው የጠፋ: በዚህ መለስ ብቻው የፈጠረው የሚባለው ፓርቲ ነው::

በ1969፣ በ1971፣ በ1979፣ በ1972፣ በ1973፣ በ1975 ዓ.ም በህ.ወ.ሓ.ት ዉስጥ ድርጅት ለማጥራት ተብሎ ብዙ ታጋይ የታሰረበት፣ የተቀጣበት፣ የተገለለበትና የተባረረበት ፓርቲ ሲመሩ የነበሩ እንዲያው የፖለቲካ አስተማሪ የነበሩበት የተፈፀመ ሥራ ነው: ታድያ እንዴት ብለው ለሰው ልጆች ሰብአዊ መብትና ዴሞክራሲያዊ መብት ለማምጣት የተፋለሙ ይባላል::

መለስ ወደ ስልጣን ለመውጣት በተቃረቡና ስልጣንን ከጨበጡ በኋላም በጣም ወዳጆቻቸውና አስተማሪዎቻቸው ለነበሩ አባይ ፀሃዬ ሌሎች የህ.ወ.ሓ.ት ፖሊት ቢሮና የማእከላይ ኮሚቴ አባላትም በተጨማሪ ለስልጣኔ ይወዳደረኛል የሚሉት ሲቢል ባለስልጣንም አግልለዋል (ዝቅ አድርገዋል)::

የኢርትራ ጉዳይ አንቸኩል ከታሪክ፣ ከሕግ ባለሙያዎች፣ ከዕድሜ ባለፀጋዎች ሁነን ረጋ ሰከን ብለን እንነጋገርበት፣ የ100 ዓመት ዕድሜ ታሪክ ያላት ኢትዮጵያ ብለን እንናገር ሪፈረንዶም ይቆይ በጥናት የተመሰረተ ስራ እንስራ ብለው ከተከራከሩ ወገኖች በማስወገድ ከ1967 እስከ 1985 ዓ.ም የተከራከሩ ወገኖች መለስ ተገቢ መልስ አልሰጠም አሉ እስከ ህልፈተ ሂወታቸው ጠበቃ ሻዕቢያ ሆኖው አልፈዋል: ታድያ መለስ ለዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማምጣት የተፋለሙ ጠ/ሚኒስተር ለዜጎች ጥፋት የተፋለሙ መሪ ለታሪክ ፀሐፊዎች እንተዉላቸው:

"አዲስ ራዕይ ቅፅ 4 ልዩ እትም ገፅ 15 አዲስ መስመር 3 እስከ ገፅ 16 አዲስ መስመር 1: እንደሚታወቀው ሁሉ በኢኮኖሚያዊ እድገትና የጥቅም ተካፋይነት የተገለሉ ህዝቦች ሁሉ ይህንን ዕድል ለዘመናት ሳያገኙ የቆዩት ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብታቸው ስለተረገጠ ነገር ግን ከግንቦት 1983 ዓ.ም በፊት በነበረው ህዝባችን

በተጨባጭ እንደታየው የዴሞክራሲ መብት እጦት በኢኮኖሚ ዕድል መንፈግን ማስከተሉ አይቀርም: ስለዚህም የቡዙሃኑ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በቅድሚያ የፖለቲካ ሪፎርም ወይ ዴሞክራሲያዊ አቢዮት ማካሄድ አማራጭ የሌለው ነበር: ከግለሰብ መብት አኳያም የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ባልተከበሩበት አንዳችም የህዝብ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ሊኖር አይችልም ነበር"

አዲስ ረአዮች ከ1983 ዓ.ም በፊት በነበረው ስርዓት እንዳላቹሁ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ሊመጣ አይችልም ነበር: የመለስ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መንግስት ለወታደራዊ መንግስት በወታደር ኃይል ካስወገደ በኋላ ከተማ የነበረ ወታደር ይዞት የነበረ ወንበር የበረሃ ወታደር ይዞት ልክ ደርግ ኢትዮጵያ ትቅደም እያለ እንዳታለለን ሁሉ መለስም መልሱ በኪሱ እየተባለ: ሽግግር መንግስት መሰረተ የሕገ መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን አቋቋመ ሕገ መንግስቱ አፀደቀ ፓርላማ ተቋቋመ የመፃፍ የመናገር ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ታወጀ: የቡዙሃን ፓርቲ መኖር በኢትዮጵያ መኖር ታወጀ በፓርላማም ገቡ: ይህ አዋጅ ግን ለዩስሙላ ነበር: አንድ የመንግስት መዋቅር በረሃ የነበረ ወታደር ከላይ እስከ ታች ቀበሌ ተዘርግቶ ስልጣኑ ያዘው በፓርላማ ገብተው የነበሩ ተቃዋሚዎችም ለኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ማቆያ እንጂ ተሰሚነት አጡ: ስለዚህ መለስ በ1983 ዓ.ም ዴሞክራሲ አላመጣም::

"በ1983 ዓ.ም የፖለቲካ ሪፎርም ወይ ደግሞ ዴሞክራሲ አብዮት ማካሄድ አማራጭ የለዉም ነበር ይላሉ ረእዮች": መለስ ስለዴሞክራ ሲ አብዮት (ደርግ ዴሞክራሲያዊ አብዮት) አዲስ ፍልስፍና የሚለው የቻይና የማኦ አስተሳሰብ ያራምዱ ነበር: መለስ ስለየቻይና ዴሞክራሲያዊ አብዮት ከ1971 ዓ.ም ጀምረው ከሌሎች የህ.ወ.ሓ.ት ካድሬዎች እያስተማሩ መጡ በ1983 ዓ.ም ይዘዉት የመጡ ይህ የዓፈና ዴሞክራሲያዊ አብዮት ነበር::

*መለስ ከ*1983 *ዓ.ም በፊት ከነበረው ስርዓት የሚለዩት: ፋሽስት ጣልያን የባአድ ወረራው ዓላማ ለማሳካት ለመላው ሃገራችን የመሰረተ ልማት አስፍተዋል ይህ ተግባር ከህዝባዊ አመለካከት ተነስቶ የፈፀመው ሳይሆን ሃብታችን ለመዝረፍ እንጂ ለህዝብ አልነበረም: በመለስ ዘመንም ብዙ መሰረተ ልማት ተዘርግቶዋል ትምህርት ቤት፣ መንገድ፣ ህክምና ተሰርተዋል ከተማ ተሰፋፍተዋል: እነዚህ መሰረተ ልማት ድህነት ስደት ሊያድኑ አልቻሉም: የመለስ መንግስት በታቀዱ (በተጀመሩ) ፕሮጀክቶች እያንሳፈፉ (ሃይላይት በማሳየት) ለህዝብ እያደናገሩት ናቸው የመጡት::*

"*አዲስ ራዕይ ቅፅ* 4 *ልዩ እትም ገፅ* 16 *አዲስ መስመር* 2 *መስመር* 3 *መለስ ከልማታውነት በፊት ዴሞክራሲያዊ ነበር:*"

*የአዲስ ራዕይ ፀሐፊዎች ዴሞክራሲ በምን ይለኩታል መለስ እኮ ሀ ብሎ ስልጣን ከያዘ በኋላ ዴሞክራሲ የሚመስሉ አንዳንድ አዋጆች ቢያውጅም የሕግ የበላይነት የሚያረጋግጡ የሚመስሉ ጥቂት ነገሮች እንኳን ቢሞክሩም እነዛ አዋጆች ተነገሩ እንጂ የተተገበሩ አልነበሩም: ለዚሁ እንደመረጃ መለስ የማያመልክ ተቃዋሚ ፓርቲ በኢትዮጵያ ሊኖር አይፈለግም: በዘመነ መለስ ብዙ ወገኖች ተገድለዋል የፖለቲካ ፓረቲ መሪዎች ታስረዋል ነፃ ጋዜጦች ተዘግተዋል ጋዜጠኞች ታስረዋል ሃገር ለቀው ተሰደዋል ሌላ ቀርቶ መለስን አጅበው ዉጭ ሃገር የሚሄዱ ጋዜጠኞች በዛው ቀርተዋል: እነዚህም መለስ ምን መሆናቸው ስለሚያውቁዋቸው ነው: በመለስ ጊዜ ያቺ ብዙ ችግር ያላት ሕገ መንግስት በመናድ ቤተክርስቲያን መስጊድ ትምህርት ቤቶች የመለስ ፓርቲ የአባላት መመልመልያ ተደርገዋል: በሃገራችን የተለያዩ ጥያቄዎች ያነሱ ታስረዋል ብዙ ዜጎች ደብዛቸው የጠፋም አሉ: በ*1997 *ዓ.ም የአዲስ አበባ ጅምላ ግድያ በተለያዩ ክልሎች የተፈጠሩ ግጭቶች ሲፈጥሩ የነበሩበት የተወሰዱ ዘግናኝ እርምጃዎች በዘመነ መለስ የተፈፀሙ ናቸው: ታድያ የመለስ ዴሞክራሲያዊነት የት ላይ ነው: እስቲ አዲስ ራዕይ በየ ቤቱ እንደናሙና ዉሰዱና ህዝብ*

ምን እያለ ነው ብላቹሁ ብታጠኑ ድንግል የሆነ መልስ ታገኙ ነበር: እናንተ በፁሑፋቹ የምታሰፍሩት በአራት ኪሎ አንድ ዝግ ቤት ነው ስለሆነ የአካባቢው ሁኔታ የማያውቅ ፀሐፊ ወታደር ጋዜጠኛ ሰላይ ለራሱ እስረኛ ነው እንደ ሚባለው እናንተም በተዘጋ ቤት ታስራቹሁ የምትፅፉት ስለሆነ ተቀባይነታቹሁ ወድቀዋል: መለስ የግለሰብ ዴሞክራሲም አያምኑም ነበር የግለሰብ መብት ሊከበር ከሆነ በመቃብር ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ነው ይሉ ነበር:

"አዲስ ራዕይ ገፅ 16 አዲስ መስመር 3 መሰመር 1: መለስና በእርሱ የሚመሩት የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ይህን ታላቅና ከባድ ተልእኮ በከፍተኛ መስዋእት ተፋልመው ለማሳካት የበቁት የትግል መጀመርያ ፕሮግራማቸውን በሃገራችን የተሟላ ዴሞክራሲያዊን ለውጥ እዉን ለማድረግ የሚያልም ነበር"

የህ.ወ.ሓ.ት ፕሮግራም በሚመለከት ካሁን በፊት በተለያዩ አጋጣሚዎች ብዙ ተናግሬበት ነበር: አሁንም ህዝቡ እንዲረዳው እደግመዋለሁ: መለስና ህ.ወ.ሓ.ት ገና ከጅምሩ ወደ በረሃ ሲወጣ የደርግ አገዛዝ ጥለን ህዝባዊ መንግስት እንመሰርታለን ከሚል ዉጭ ይህ ነው የሚባል ፕሮግራም አልነበረዉም: ኢርትራ ከኢትዮጵያ የተለየ ራሷ የቻለች ሃገር ናት የምትለዉም በቃል እንደዝናር ታጥቀዋት የመጡ ነበሩ::

ህ.ወ.ሓ.ት መታገያ ፕሮግራም በማኒፌስቶ ደረጃ ነድፎ የወጣ በ1968 ዓ.ም መጨረሻ ዓመት አካባቢ ነው: እሱም በጠባብነት ጭቃ የተነከረ ጥያቄያችን ነፃ ሃገራዊት ትግራይ ለመመስረት ሆኖ ከቅኝ ገዢዋ ኢትዮጵያ ነፃ ለመውጣት ነው የሚል ነበር: ቀጥለዉም ኢርትራ ራሷ የቸለች ሃገር ናት የሚል ነበር: ይህ ፕሮግራም ሰነደፍ መለስ እንደነበሩ ነው: በሌላ በኩል ሊመሰርተው የሚፈልግ ስርዓት የማርኪሲዝም ለኒንዝምና የማኦ ዘዲንግ መመርያችን የሚል አሁን ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ይከተሉት ያሉ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሪእዮተ ዓለም ነው: መለስ ከኢትዮጵያውያን ፖለቲካዊ ፓርቲ ከኢ.ህ.አፓ ግገሓት

ሌሎችም ፓርቲዎች አብሮ ከመስራት ከኢርትራ ድርጅቶች አብረው ለመስራት ይፈልጉ ነበር: መለስ ጓዶቻቸው በህ.ወ.ሓ.ት ድርጅትም የዉስጠ ዴሞክራሲ የማስከበር የታደሉ አልነበሩም በጣም አፋኝ ነበሩ: ሲየፍኑ ግን በመከፋፈል የአካባቢ የኃይሎች በማናናቅ ነበር ፀረዴሞክራሲ መሆናቸው መረጋገጫ በሰሜን ኢትዮጵያ ህ.ወ.ሓ.ት የሚቀነቀን ፓርቲ ካለ በእንጭጩ እናጥፋው የሚል አስተሳሰብ ነበራቸው: መለስና በፀረ ዴሞክራሲ ሥራ በጣም ሙያተኛ ናቸው ከ1983 ዓ.ም በኋላ ለተፈጠሩና ከዛ በፊት የነበሩ ነባር ፓርቲዎች እንደ ኦነግና ሌሎች ፓርቲዎች አብረን የሽግግር መንግስት ንመስርት ሲሉም በትክክል የፓርቲ ብዙሁነት በኢትዮጵያ አምነው ሳይሆን ለዐለም አቀፍ ፖለቲካ በተለይ ከም ዓረባውያን ትርፍ ለማግኘት እንጂ ከልብ አምነውበት አልነበረም::

ምክኒያቱም መለስ በ1983 ዓ.ም ታህሳስ ወር ህ.ወ.ሓ.ት ከኢህደን አብሮ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የሚል ስም በመያዝ በተንቤን ማርያም ቆራር በተባለው ዋሻ አንደኛ ጉባኤው ሲያደርግ መለስ ለጉባኤተኛው ከወጁት ይላሉ::

እኛ እስከ አሁን ኮንሰስት ሪኢቶ ዓለም እየተከተልን እስከ አሁን ቆይተናል: ነገር ግን የኮሞኒስት የኃይል አሰላለፍ በምዕራብ ሪኢቶ ዓለም ተመትቶ ተፍረክርከዋል: ስለሆነ በአሁኑ ጊዜ ከእንፐርያሊዝም የድንጋይ ተራራ ለመጋጨት አይቻልም: አሁን ማድረግ ያለብን የነበረን የኮሞኒስት አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሪእዮተ ዓለም ካባችን ዉስጥ በመደበቅ ላይላያችን የካፑታሊዝም ነጭ ካባ ለብሰን ለምዕራባውያን በማታለል ብቻ ነው ልንጓዝ የምንችለው: ነገር ግን የኮሞኒስት አሰላለፍ ፈርሰዋል ከነጭራሹን ተንደዋል ብለን የኮሞኒስት ሪኢዮትና ተግባር ትተነው ማለት አይደለም: ኮሞኒስት አይፈርስም ዘለቂ ነው ብለው አወጁ: በጉባኤተኛው ብዙ ተቃቅሞ ነበር ነገር ግን ምን ይሁን የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ በመአዝኑ ሁነው ዲስኩራቸው ስለ አወረዱበት ጉባኤተኛው ፀጥ አለ: ስለሆነ መለስ

አንባገነኑ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ከጥንቱ ጀምረው ይዘዉት የመጡ ናቸው::

አዲስ ራዕይ እኔ የ38 ዓመት ትግል ሁሉም ነገር መለስ እንደሰራው መለስ የወታደራዊ ሳይንስ መሃንዲስ፣ የልማት መሃንዲስ፣ የአባይ መሃንዲስ፣ የዴሞክራሲ መሃንዲስ ምጡቅ የክፍለ ዘመኑ ፈላስፋ አድርጋቹታል ይህ አባባል ፍትሃዊ አይደለም: በኔ እምነት በ17 ዓመት የትጥቅ ትግል ጊዜ ከመለስ የሚበልጡ ብዙ ፈላስፋዎች ነበሩ: ለመለስ ያስተማሩ የህ.ወ.ሓ.ት አብዛኛዎቹ በተለይ ነባሮች ጓዶቹ አብረው ሲሰሩ ነበሩ: አንድ ቀንጨብ በማድረግ ብንወስድ መለስ ከወታደራዊ ሳይንስ ምንም ግንኙነት አልነበረዉም: ተዋግቶ አዋግቶ አያውቅም ጭራሹም የመድፍ የአየር ድምፅ ሊሰማ ፍቃደኛ አልነበረም የአነስተኛ ነፍጥም ተኩሶ አያውቅም: ይህ ሃሳብ በቀጣዩ ምዕራፎች በስፋትና በጥልቀት መልስ ይሰጠዋል::

በ21 ዓመት የሰላም የስልጣኑ ዘመንም መለስ በመድረክ ወጥቶ ሲናገር ሲከራከር ተስጦ ነበረው: ባለፉት 21 ዓመት ግን መንጋ ሚኒስትሮች መንጋ ሙሁር አማካሪዎች ከክልል እስከ ሃገር በየ ደረጃው ያለው ባለሙያ የሰራው ሥራ ሁሉም ነገር መለስ እንደሰራው ብቻው ሌት ተቀን ሲሸቅል በድካም ምክኒያት አረፈ ብላቹዋል: እኔ ደግሞ የምለው መለስ ብቻቸው ለብቻቸው አንባገነግ ሆነው ከሳቸው የሚበልጡ ሙሁራን የማያስጠጉ ለስልጣን የሚሳሱ መሪ ናቸው እላለሁ::

መለስ በሃገራችን ዴሞክራሲ ሊሰፍን ነው ብለው ወደ ሽግግር መንግስት ለገቡ ፖለቲካዊ ፓርቲዎች ከገፅ መሬት እንዲጠፉ መለስ ትልቅ ልምድ ነበራቸው ይህም ለኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከሙርከኞችም ከምንም ሰብስቦ ለጣጥፎ በገንዘብ በንብረት ካደራጀ በኋላ ሆነው እየገፉ ብሎም በሰራዊት እያጀቡ አስፈላጊ ከሆነም በጦርነት ኦሆዴድ እግር ተክሎ እነ ኦነግ እንዲነቀሉ አድርገዋል::

በዓፋርም በህ.ወ.ሓ.ት ታጋይ ሆኖ ክፍሊ ባህል የነበረ እስማዒል ዓሊ ሰሮ የሚመራው በማስተባበር ለ20 ዓመት የቆየ የነ ዓሊሚራሕ ፓርቲ በማድቀቅ የራሳቸው ተላላኪ አድርገው አስቀመጡ: በጋምቤላ ፣ በሶማል፣ በደቡብ ህዝቦች ተመሳሳይ ተጠፍጥፈው ተሰርተው ተቀመጡ: በአጠቃላይ መለስ በሃገር ደረጃ ለነበሩ መለስ ለማያምንባ ቸው ፓርቲዎች ተፃራሪ ፓርቲዎች በመፍጠር ነባር ፓርቲዎች ከመድረክ እንዲጠፉ ወይ ደግሞ ሃገር እንዲለቁ ወይ ሴራ በመፍጠር የወንጀል ድራማ በመስራት አሸባሪ፣ አልቃዒዳ፣ አልሸባብ፣ አልእቲሓ ድ፣ የሻዕቢያ ቅጥረኛ፣ የትምክህተኛ የጠባብ ኃይሎች፣ ነውጥ ፈጣሪዎች፣ የጥፋት ኃይሎች እየተባሉ መጥፎ ስም እየለጠፈ እንዲደቁ አደረጋቸው: በአንፃሩ መለስን የሚያመልኩ ተወላዋይ ኃይሎች የሃገራችን አንጡራ ሃብት ባጀት በመመደብ ለዓለም አቀፍ ፖለቲካ ትርፍ ይጠቀምባቸዋል፣ ስለዚህ መለስ የሚመራቸው ፓርቲ ግልፅ የሆነ የፓርቲ ፕሮግራም ታክቲክና እስትራተጂ ያልነበረው በወቅቱየ ትግራይ ኢትዮጵያ አይደለችም ከአምሓራ ቅኝ ገዢዎች ነፃ ለመውጣት ነው የምንታገለው፣ ኢርትራ ቀይባሕርን ይዛ ትገነጠል ብሎ ኢትዮጵያ የባሓር በር የሌላት ያስቀረ ኋላም በየ ጊዜው ፕሮግራም እየቀየረና እየተገላበጠ የመጣ መሪ ነበር: ይህ  የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉ ያወቀዋል በተለይ ደግሞ የህ.ወ.ሓ.ት ታጋይና የትግራይ ህዝብ ያውቀዋል: ስለዚህ የአዲስ ራዕይ አዘጋጆች የምትፅፉት ልሳን አሁንም ከአራት ኪሎ ወጣ ብለቹሁ ሃቂን ነገር ሰብሰብ አድርጋቹሁ ብትፅፉ ይሻላል::

መለስና ጓዶቻቸው ነፃ ሃገር ለመመስረት ከቅኝ ገዢዎች አማራ ነፃ ለመውጣት ነው የምንታገለው ብለው ፕሮግራም ነድፈው ሲታገሉ ቆይተው ለምን እንደገና ኢትዮጵያዊ ፓርቲ ሆኑ?

መለስ የወጣለት ጠባብነት ጭቃ የተነከረ ፕሮግራም በመፅሐፍ መልክ ታትሞ ሃገር ዉስጥና በዉጭ ከተሰራጨ በኋላ ከባድ ተቃዉሞ

አጋጠመው በተለይ በትግራይ በታጋዮች፣ በደጋው ከተማዎች፣ ገጠር ገበሬ ሳይቀር እንደእሳት ተቀጣጥሎ ተቃዉመውን አነሳ: በሰሜን የነበሩ ፓርቲዎች ኢ.ህ.አ.ፓ፣ ኢ.ድ.ዩ ጠንክረው ተቃወሙት: ደርግም የህ.ወ.ሓ.ት ጠባብነት ለመምታት በትግራይና በሃገር ደረጃ ላሉ የትግራይ ተወላጆች በተለይ ቀሰቀሰበት::
የመለስ ፓርቲ ተደናገጠ: በፓርቲ ወስጥ ጥያቄው የእሳት ሰደድ ሆኖ ተስፋፋ: በነ መለስ የተሰጠው መልስ ማሰር ከከቀላል እስከ ከባድ በጅምላ ተፈረደበት: ሁኔታው አልበረደም ከኢ.ድ.ዩ፣ ከኢ.ህ.አ.ፓ ጋር ጦርነት ቀጠለ:ጦርነቱ በ20 ወራት ተጠናቀቀ በቃ ህ.ወ.ሓ.ት የትግራይ ንጉስ ሆነ: እንቅስቃሴውም በረታ: ለህ.ወ.ሓ.ት መፍትሂ ሊያስቀምጥ የሚያስገድደው ሁኔታ ተፈጠረ::

ህ.ወ.ሓ.ት በጭንቀት እያለ ኢ.ህ.አ.ፓ በጎንደርና በትግራይ ወልቃይትና ፀለምት የነበረው ኃይል ፈራረሰ ከ200 በላይ የሚሆኑ እነ ታምራት ላይነና ሌሎች የሉባቸው ሙሁራኖች ወደ ህ.ወ.ሓ.ት ተጠጉ: እነዚህ ሙሁራኖች ለህ.ወ.ሓ.ት ጠባቦች ናቹሁ ኢ.ትዮጵያዊነታቹሁ የካዳቹሁ ናቹሁ አሉዋቸው ሌላ ሂስም አቀረቡ: በዴሞክራሲ በሰብአዊ መብት ያለው ሁኔታ ወቀሱ: ለአንድ ወር ያህል ከህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች ተወያዩ: ህ.ወ.ሓ.ት ነፃ ሃገር ትግራይ ለመመስረት የሚል በዉስጡ የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ ብቻ የሚያውቁት አቋም የወሰደ ይመስል ነበር: በኢ.ርትራ ጥያቄ አልተሰማሙም: እነ ታምራት ላይነም ኢ.ህ.አ.ፓን ናድሳለን ብለው ትግል ለመጀመር ወሰኑ ከ200 በላይ የነበሩ ከ15 በላይ አንታገልም ብለው ወደ ሱዳን ሄዱ: ኢ.ህድን በህ.ወ.ሓ.ት ተጠፍጥፎ ተሰራ እነ መለስ የነበራቸው የጠባብነት ጭቃ ለመጥረግ በኢ.ትዮጵያ ውያን በተለይ በትግራይ ህዝብ ተሰሚነት ኢ.ህድን የአሁኑ በአደወን ለመሰራት ከህ.ወ.ሓ.ት ፖሊት ቢሮ በወታደራዊ ስየ አብረሃ በፖለቲካ አባይ ፀሃዬ ስብሃት ነጋ መለስ ተመደቡ: በተራ እየሆኑ ለኢ.ህድን ስራት: ኢ.ህደን ከ30 የማይበልጡ ህ.ወ.ሓ.ት ነፃ ባወጠው

ሰቆጣ አውራጃ ተመሰረተ: ኢ.ህደን ከተመሰረተ በት ጀምሮ የሚጠብቀው ሰራዊት ተመድለት መጀመርያ ሁለት ሻምበል ሰራዊት ከ10 የህዝብ ካድሬዎች ተመደቡ::

ከሁለት ዓመት በኋላ ሁለት ሻለቃ (በጦሎኒ) ሰራዊት ከ20 በላይ ካድሬዎች ተመደቡ: ኢ.ህድን ተቀባይነት አልነበራቸዉም የህዝብ አስተዳደር ፍትህ በሚመለከት በህ.ወ.ሓ.ት ካድሬዎች ነው የሚሰራው: ትጥቅ ስንቅ ንብረት ልብስ ህክምና የሚሰጣቸው በህ.ወ.ሓ.ት ነበር: ኢ.ህደን ህ.ወ.ሓ.ት ጠባብ ነው የሚለው በመጠኑም ቢሆን ለህ.ወ.ሓ.ት አማፂ ሆነ: በጦርነት ጊዜ ከኢ.ህደን መስራች እንዳይሞቱ ጥንቃቄ እንዲደረግ በአካባቢው ለነበሩ የህ.ወ.ሓ.ት ሰራዊት አዛዦች ለእነ ኃይለ ስላሴ (ወዲ እንበይተይ) የአሁኑ ጀነራል ለኪዳነ ማርያም (ሻምበል) የአሁኑ ኮነሬል ወለገብሪኤል (ሞደርን) ለነጋሽ ኒኖ ወ.ዘ.ተ ልዩ መመርያ ይሰጣቸው ነበር::

በሌላ በኩል የኢ.ህደን መሪዎች (ከመለስ) የሚለያቸው አንድ ነገር ተፈጠረ: መለስና ጓዶቹ የማይወዱት ነገር: እሱም ኢ.ህደን የኢ.ርትራን መገንጠል አያምኑም: የቢሄር ቢሄረሰብ የራስህን ዕድል ራስህን መወሰን እስከ መገንጠል የሚል: መገንጠል የሚል ሃረግ አይቀበሉም በነ መለስ ዴሞክራሲ የለም የሚሉ ነበሩ::

ይህ ለህ.ወ.ሓ.ት (ለመለስ ጓዶቹ ከባድ ራስ ምታት ነበር) በተደጋጋሚ ውይይት ተደረገ: አባይ ፀሃዬ፣ ስብሃት፣ ስየ፣ ክንፈ ገ/መድህን: መለስ አሁንም የኢ.ህደን አቋም ለመቀየር በተደጋጋሚ እስከ ሰቆጣ ተላ ተላጀ ሂደው ተወያዩ ነገር ግን ሊቀየሩ አልቻሉም: በነ መለስ ክንፈ ስብሃት ማስጠንቀቅያ ተሰጣቸው: ከ1973 ህደር ወር እስከ 1980 ዓ.ም ነሐሴ ወር አቋማቸው አልቀየሩም: በ1980 ዓ.ም ነሐሴ ወር ግን የመለስ ፖሊት ቢሮና የኢ.ህደን ማ/ኮሚቴ ለአንድ ወር በደጀና ወልቃይት ውይይት ተደረጎ የኢ.ህደን ማ/ኮሚቴ አብዛኞቹ ተንበረከ ኩ የመለስና ጓደኞቹ ፍፁም ተላላኪ ሆኑ:

ከኢህደን ሙሉዓለም በ1984 ዓ.ም ጎጃም ላይ በፈንጂ ሙተዋል ተባለ: ሃውጃለ በ1983 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ራሳቸው የመቱት: ኃይለ ጥላሁን ጀነራል ጥሮታ ተቃውሞ ነበራቸው: እነዚህ ሰዎች በነ መለስ አቦይ ስብሃት ይጠሉ ነበሩ: የሻዕቢያ ዋና ሎሌዎች የነበሩ ታምራት ላይነ፣ ህላዊ ዮሰፍ፣ አዲሱ ለገሰ፣ ተፈራ ባልዋ፣ ታደሰ ካሳ (ጥንቅሽ) ወ.ዘ.ተ ነበሩ::

ኢኢህደን ደርግ እስከ ተደመሰሰ ድረስ በመለስ ባላ ተደግፎ የመጣ መለስ እጅህ አወጣ ካለው የሚያወጣ እስካሁን በመለስ ስንባ እየተነፈሰ የሚገኝ ፓርቲ ነው: አሁንም መለስና ጓዶቹ ፀረ ዴሞክራሲ ናቸው በተለይ ደግሞ ከ1967 እስከ 1971 ዓ.ም እነዛ ማ/ኮሚቴ የነበሩ ስዩም መስፍን፣ ስብሃት ነጋ፣ ግደይ ዘርአፅዮን፣ አረጋዊ በርሀ፣ አባይ ፀሃዬ ሲሆኑ በዛን ጊዜ ሕገደንብ ህ.ወ.ሓ.ት ንደው በማ/ኮሚቴ አማራር ተወክለው ሊመሩ የተቀመጡ መለስ ዜናዊ፣ ዶ/ር አታኽልቲ ቀፀላ፣ አውዓሎም ወልዱ፣ ስየ አብረሃ በደረጃቸው ፈለጭ ቆረጭ ነበሩ: አዲስ ራዕይ እብደምትሉት ከሆነ መለስ እስከ 1982 ዓ.ም የነበረ ጊዜ የብቻው ራዕይ አልነበረዉም: በአጠቃላይ የቀድሞ ኢህህደን የአሁኑ በአዴን ከተመሰረተ እስከ አሁን ነፃነት የሌለው ፓርቲ ነው::

## <u>ምዕራፍ 7</u>

## <u>"መለስ ዴሞክራሲያዊና በተራማጅ አስተሳሰብ የሚመራ ድርጅት ገንቢ"</u>

ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በመለስ ብቻ የተገነባ ድርጅት: የአዲስ ራዕይ አርእስት በመምረጥ በመቶሺዎች የሚቆጠሩ ጀግኖች ሂወታቸው ያለፈበት ብዙ ጀግኖች ፍልስፍና በማመንጨት የሰሩትና የገነቡት ፐርቲ እያለ መለስ ገንብተውታል ብላቸሁ ያልነበራቹሁበት ታሪክ ስትፅፉ በጠጅ ቤት በውስኪ ቤት ወይ ደግሞ በኮረፌ ቤት ሁናቹሁ ናቹሁ የፃፋቹሁ::

ሐቂን ልገልፅላቹሁ እሞክራለሁ: የህ.ወ.ሓ.ት የ17 ዓመት የትግል ታሪክ የምናውቀው ያየነው በአካል የነበርነው ለመለስም የመሪነት ብቃት እንዲኖረው ያደረግን ብዙ ሰዎች አለን: ይቅርና እንደአዲስ ራዕይ 6 ሚልዮን መፅሐፍ ብናሳትም ነገ ጢት ይህ ትውልድ ወደ ፊት አሳትሞ ሐቀኛ ታሪክ እንዲያውቅ ብለን ፅፈን ያስቀመጥነው አለ: ታሪክ ነገ ተጋላጭ ነው:

"አዲስ ራዕይ ቅፅ 4 ልዩ እትም ገፅ 18 አዲስ መስመር 2 ጓድ መለስ ከትግል አጋሮቹ ጋር ሆኖ የገነባው ድርጅት ከትንሽ እስከ ትልቅ ደረጃ ያደረሰው በዚህ አኳሃን ተገንብቶ ነው: የመለስ የመጀመርያው ድርጅት ህ.ወ.ሓ.ት ነበር በሂደት ደግሞ ህ.ወ.ሓ.ትና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግን በጋራ በመሆን ኢ.ህ.አ.ዴ.ግን መሰረቱ ኦሆድድና ደኢ.ህደንም ብዙም ሳይቆዩ ተቀላቀሉ: ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ከትልቆቹ የሃገራችን ክልሎች የሚገኙ ህዝቦችን በሚመሩ አራት ድርጅቶች መልክ ተዋቀረ: መለስ ከህ.ወ.ሓ.ት እስከ ሂወቱ ፍፃሜ ድረስ በመራው ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በአመራርነት ታግሎ እያታገለ መሪ::"

አዲስ ራዕይ ጓድ መለስ ከትግል ጓደኞቹ ጋር ሆኖ ህ.ወ.ሓ.ትን እንደገነባ አስቀምጣቹለታል: ወረድ ብላቹሁ ደግሞ መለስ ከህ.ወ.ሓ.ት እስከ ሂወቱ ፍፃሜ ድረስ በመራው ወ.ዘ.ተ...ብላቹሃል: እዚህ ላይ ለአዲስ ራዕይ ሐቁን አውቃቹሁ የፃፍነው መፅሓፍ ዉሸት ነበር እንዴ ብላቹሁ ራሳቹሁ እንድትጠይቁ በተጨማሪ የሃገራችን ህዝብ ሐቁን እንዲያውቅ አጠር ያለ የመለስ የትግል ታሪኩ ለመግለፅ ልሞክር: ስለመለስ ታሪክ ስገልፅ ግን ከ1967 ዓ.ም እስከ ዛሬ ያለው ጉዞው ለመግለፅ እሞክራለሁ::

## የመለስ የትግል ታሪክ ባጭሩ

መለስ በጥር ወር 1967 ዓ.ም መጀመርያ: ማገብት አስቀድሞ ከሻዕቢያ ጋር ድርድርና ስምምነት አድርጎ 50% የተማሩ 50% ያልተማሩ 20 ወጣቶች ወታደራዊ ስልጠና ወሰደው ትጥቅ ይዘው

ወደ ትግራይ እንዲመጡ ተብለው መለስ ከዘጠኝ ሰዎች አስመራ ገቡ: አስመራና አካባቢዋን በደርግና በኢርትራ (ጀብሃና ሻዕቢያ) በአንድ ገፅ በሌላ በኩል የደርግ ሰራዊት በጦርነት እየታመሰች ናት: የህ.ወ.ሓ.ት ሰልጣኞች 9 ሰዎች አስመራ ገብተው በአንድ ቤት ተደብቀው ከረሙ: አንድ ወር ሙሉ ከአስመራ ሊወጡ አልቻሉም: በጥር ወር መጨረሻ ግን ሁኔታው ጋፕ ብሎ ሊወስዳቸው የመጣ የሻዕቢያ ታጋይ የነበረ ከዛ በኋላ ወደ ህ.ወ.ሓ.ት ለመቀላቀል ኢሳያስ አፈወርቂ ስለፈቀደለት እንሂድ ሲላቸው የነበሩ ሁሉ ሲዘጋጅ በማኸሉ መለስና ዑቅባዝጊ በየነ (ረዘነ) ሁነው ሲጋራ ልንገዛ ብለው ተለይተው ሳይመለሱ በዛው እንደወጡ ተሰወሩ: እነዛ አብሮዋቸው የነበሩ ጨለማን ተገን በማድረግ ከአስመራ ወጥተው ከብዙ ቀን አድካሚ ጉዞ ወደ ሻዕቢያ ወታደራዊ ማሰልጠኛ በረሃ ደረሱ: እነዛ ወደ ሻዕቢያ የሄዱ እንዴት ሰለጠኑ ምን ችግርስ አጋጠማቸው?: የሚለው በጋህዲ 2 መፅሸፍ ተገልፀዋል::

መለስ አሰመራ ላይ ከተሰወሩ በኋላ በአያታቸው (የእናታቸው አባት) ቤት በመንደፈራ አውራጃ ዓዲ ኳላ በሚባል ቦታ ተደብቀው ቆይተው በማዝያ ወር 1967 ዓ.ም ወደ ሽራሮ ሄደው በሽራሮ ከተማ ካሕሳይ ስዩም የሚባል በተሃዱ እርሻ ልማት ይሰራ የነበረ የህ.ወ.ሓ.ት ህቡእ አባል ተቀብሎ ወደ ታች ተከዘ ይዞዋቸው ሄደ: አቶ ገሰሰው አየለ 6 ሰዎች ይዘው ሄደው ከተከዘ ተቀብለው ትግል ወደ የተጀመረበት ደደቢት ይዘዋቸው ሄዱ: የተቀበሉዋቸው ሰዎች አቶ ገሰሰው አየለ (ሱሑል)፣ አስገደ ገስላሴ፣ ተወልደ ረዳኸኝ (ብርሃነ)፣ ገመድህን ተፈሪ (ሰመረ)፣ ካሕሳይ በላይ (ሃፍቶም)፣ አረጋዊ በርሀ (በሪሁ) ናቸው::

የተከበራቹሁ አንባብያን መለስ ከሞቱ በኋላ እነ አባይ ፀሃዬና ስዩም መስፍን ሲናገሩ: መለስ አስመራ ተሰውረው ቀርተው ወደ ሃገራቸው ተመለስ እያሉ ከነ አባይና ስዩም ግን መለስ ኢርትራ ከሄዱ አብረው ሂደው አስቀድመው ስልጠና ወሰደው ደደቢት ሂደው እዛው

ከነበሩ ፖለቲካ ንቃት ሊሰጡ ታዘው ሄዱ ብለዋል: ምን ዐይነት ነጭ ዉሸት ነው ያሰለጠኑዋቸው: አስገደ በነሩ ከስብሃት ነጋ አብረው ነበር የሰለጡ: ስብሃት ነጋ ለመለስ በ15 ቀን ቀድመው ወደ ደደቢት የገቡ::

መለስ ደደቢት እንደገቡ ቦታው ሙቀቱ ከ42 ድግሪ በላይ ስለነበረ የዉሃ ጥም አይችሉም ነበር ዉሃ ተሎ ተሎ ስለሚጠጡ ድሽ የሚል ስም ነበራቸው: በሌላ በኩል ከከተማ ይዘዉት የመጡ በሽታ አጥቅቶዋቸው ስለነበረ የድርጅቱ ሃኪም አስገደ ነበሩ መድኃኒት ከከተማ ገዝተው አምጥተው ከታከሙ በኋላ ድነው ወታደራዊ ስልጠናቸው ቀጠሉ: በዛን ጊዜ በህ.ወ.ሓ.ት ከጀማሪዎች አንዱ አስገደ በኢስራኤላውያን ለ2 ዓመት ወታደራዊ ስልጠና የወሰዱና የጤና ረዳት (አድቫንስ ድሬሰር) እንደነበሩ የሚታወቅ ነው::

መለስ ስልጠና እየወሰዱ እየያሉ ኢርትራ የሄዱ ዘግይተው ስለነበር ደርግም ማደን ስለጀመራቸው ደደቢት ላይ ከ30 የማያንሱ ሰዎች ነበሩ: በነዛ ሰዎች ማኸል የመጨናነቅ ሁኔታ ስለነበር በሶስት ጉሩብ ተከፈሉ: አንደኛው ጉሩብ ወደ ሱዳን እንጠጋ ከዛ እየተንደረደርን እየገባን እየወጣን ንታገል አሉ: አንድ ቡድን ከበረሃ ደደቢት አንወጣም የሚሉ ገሰሰው አየለ፣ አረጋዊ በርሀ፣ ግደይ ዘርአፅዮን፣ አስገደ ገስላሴና ሌሎችም ነበሩ: አንድ ቡድን ደግሞ መለስ ዜናዊ ያሉበት ወደ ኢርትራ ፓርቲዎች ተጠግተን እንቆይ አሉ: ሆኖም ደደቢት ነው የምንቆይ ያሉ አሸነፉ::

መለስ ዜናዊና ስብሃት ነጋ ከ1967 ዓ.ም ደደቢት ከተገናኙበት ቀን ጀምሮ ደርግ እስኪወገድ ኋላም እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ የነበራቸው የአባትና የልጅ ግንኙነት ዐይነት ነበር: ስብሃት ነጋ በትግሉ ዘመን ለመለስ ያጋጠማቸው ችግር ይጣበቁላቸው ነበሩ: መለስም በስብሃት ነጋ አያስችላቸዉም ነበር::

መለስ ደደቢት ከነበሩበት ጊዜ ስብሃት ነጋና ከሽሬ ገበሬዎች ተጣልተው ቀውስ ሲፈጥሩ በሙሁኖች አጠቃላይ በሽሬ ታጋዮችና

ዓድዋ አክሱም ከመጡ መከፋፈል ተፈጠረ: ክፍፍሉ የፈጠሩት ደግሞ ስብሃት ነጋ ናቸው: መለስ በዛን ጊዜ ከስብሃት ጎን ተሰልፈው ነበር: ሆኖም ግን መለስ ሳቂና ከሁሉ መደባለቅ ባህሬቸው ስለነበረ ተንኮለኛ መሆናቸው አይታወቅባቸውም ነበር::

መለስ በ1967 ዓ.ም ነሐሴ ወር በአድያቦ ዊደኽ በሚባል አካባቢ አሁንም ስብሃት በፈጠሩት ፀረ ገሰሰው አየለና የአድያቦ የመሳፍንት ልጆች ከነ ሐየሎም አርአያ፣ ተስፋይ ወለስላሴ፣ ብርሃነመስቀል ማግለል አለብን በሚል አረጋዊ በርሀና ስብሃት ከሌሎች በማበር አደገኛ ቡድን ፈጥረው ነበር: ነገር ግን ገሰሰው አየለ፣ ስዩም መስፍን፣ ሙሴ፣ አግአዚ ሆኖው ጉዳዩ በጥንቃቄ ያዙትና በሰላም እንዲፈታ አደረጉ: መለስ አሁንም ወጣሁ ወጣሁ ልታይ ልታይ ባይ ነበሩ::

መለስ በ1968 ዓ.ም ጥቅምት ወር አሁንም ከነ አፅበሃ ዳኘው ሆኖው በማይረባ ነገር ፀረ ገሰሰው አየለ ተነስተው ነበሩ: በዚህ ሴራም ስብሃት ነጋ ነበሩበት: አሁንም ሌሎች ታጋዮች ተቃወሙትና ከሸፈ::

መለስ በ14/3/1968 ዓ.ም በኢሮፕ ወረዳ ዓሲንባ በሚባል ቦታ ሓረዛ በህ.ወ.ሓ.ት ፖለቲካ ክፍል ተመደቡ: በዛን ክፍል ተካ ካሽሳይ (መቀሌ) ኃይለስላሴ ገመድህን (መሐመድ) ፍሰሃ አፈወርቂ (መቀሌ) ዓወት ተሰፋይ (ተንቤን) መለስ (ዓድዋ) ተመደቡ: በነዚህ ቡድን መለስ በፈጠሩት ችግር ስምምነት አጡ: ኋላ እንዲበተኑ ተደረጉ: የችግሩ መንስኤ የመለስ ስልጣን ፍላጎት የፈጠረው ነበር: ያቺ ቡድን ከተበታተነች በኋላ ቆይተው መለስ ቦታው ላይ እንዲመለሱ::

መለስ በአብዛኛው ታጋይ ተቀባይነት ያጡ ነበር: በየካቲት 1968 ዓ.ም በተደረገው ጉባኤ ገሰሰው አየለ እንዳይመረጥ መለስና ስብሃት ዋና ተንቀሳቃሽ ነበሩ: ከጉባኤ በኋላ ተመድበውበት የነበሩ 04 ፖለቲካ ክፍል ፈረሰ ምክኒያቱም በዚያች ቡድን የነበሩ ሰዎች በማ/ኮሚቴ ተፈላጊዎች ስለነበሩ::

የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ በነ አግአዚና ሙሴ ሞት 5 ማ/ኮሚቴ ቀሩ በመጀመርያ ጉባኤ ሰፋ ይበል ብቁ ሰዎች አሉ ተብሎ ታጋይ ቢከራከር በማ/ኮሚቴ ያሉ አቅም ያላቸው ብዙ ሰዎች ስለነበሩ ለዛ ቡድን ሊበልጡት ስለሚችሉ ሰግተው ጠባብ እንዲሆን አደረጉ: በ1969 ዓ.ም መጀመርያ ሕገወጥ በሆነ መንገድ 4 ሰዎች የአንድ ማ/ኮሚቴ ሆነው ሊመሩ ወኪል ማ/ኮሚቴ ተብሎ ስም ተሰጣቸው: ከነሱ መለስ ዜናዊ ነበሩ: የዚህ ስልጣን አሳጣ ብዙ ታጋዮች ተቃወሙ: ለሚቀጥለውም በሙሉ ሕንፍሽፍሽ ፈጣሪ (አንጃ) የሚል ስም ተሰጠው: ይህ ችግር ከሌሎች ጥያቄዎች ተጨምሮ በህ.ወ.ሓ.ት ዉስጥ ትልቅ ችግር ተፈጠረ: መለስ በቅርብ የሚገናኙ ከስብሃት ነጋ ነበር: እንደቀድሞው አባትና ልጅ ይመስሉ ነበር: መለስ ያቺ ስልጣን ካገኙ ወጣሁ ወጣሁና ልታይ ልታይ ጀመሩ::
ለመልስ የምታስርቅ (ከመድረክ የምታገል) ቀን ተፈጠረች: በ1969 ዓ.ም እሷም የዓድዋ ባንክ ለመውረር እነ አረጋዊ በርሀ የሚመሩት ሰራዊት ገባ: መለስም በውግያ ወቅት ምድብ ቦታ ተሰጣቸው: ነገር ግን በተመደቡበት ቦታ አልተገኙም ጦርነቱ ድልን አልተጎናፀፈም መለስ ተሰወሩ: ከ 5 ቀን በኋላ ወደ ሰራዊቱ መጡ: መለስ በጦርነቱ ተሰወሩ ግዳጃቸው አልፈፀሙም የሚል በሁሉም ታጋይ ተነሳ: በዛን ጊዜ የህ.ወ.ሓ.ት ሕግደንብ ከጦርነት የሸሸ የሞት ፍርድ ይቀጣል የሚል ሕግ ነበር: ይህ ሕግ ከዛ በፊትም ከዛ በኋላም በሌሎች ታጋዮች ተግባራዊ ተደረገዋል: የመለስ መስወር በሁሉም የህ.ወ.ሓ.ት ታጋይ ተሰተጋባ: ለነበረ ችግር አባባሰው: እነ ስብሃት ነጋ ለችግሩ ሕንፍሽፍሽ (አንጃ) አሉት ከዛም አልፎ አውራጃዊ ችግር አሉት: በዛ ወቅት ከመለስ ጋር ከአስመራ ተሰውረው ተመልሰው አብሮዋቸው የመጡ ዑቅባዝጊ በየነ (ረዘነ) በኢ.ድ.ዩ ጦርነት ተከበው ከከበባው ሰብረው መውጣታቸው እንደሸሹት ተቆጥሮ በእሱር ቤት ገቡ ኋላም አልታዩም: መለስ በታጋይ ሁሉ ተጠሉ: መለስ ተናጋሪ ነበሩ የሚሰጡት አስተያየት ሁሉ የማ/ኮሚቴ ሃሳብ ነው የሚደግፍ::

መለስ በሰራዊቱ ፊት መታየት አቆሙ ስብሃት ባለበት አካባቢ ይቀመጡ ነበር: መለስ ያቺ በዓድዋ የተበላሸች ስም ለማደስ በ1970 ዓ.ም በነሐሴ ወር መጨረሻ ከኃይል (22ኛ) ሻምበል ሆነው ዓዲዳዕሮ ከደርግ በተደረገው ጦርነት ገብተው ነበር: መለስ በዛን ጊዜም ከኃይል 22 ተሰወሩ: እንግዲህ መለስ በ17 ዓመታት በትግል የተሳተፉባቸው ጦርነቶች በዓድዋና ዓዲዳዕሮ ነበሩ እነሱም አልተሳኩም: ከዛ በኋላ በጦርነት ተሳትፈው አያውቁም: መለስ ከዓዲዳዕሮ ጦርነት በኋላ 04 ፖለቲካ ክፍል ተወሸቁ: በታጋይም ትልቅ ተቃዉሞ ተነሳ: ነገር ግን የነ ስብሃት ነጋ ቡድን ተጠናክሮ ስለነበረ ተልባ ቢንጫጫ በአንድ መውቀጫ እንደሚባለው ሆነ: እንዲያዉም ስለመለስ ከጦርነት መሰወር ያነሱ ታጋዮች ቀውሰኛ አውራጃዊ እየተባሉ ታሰሩ ደብዛቸው ጠፉ: ስለዚህ እንደማስረጃ ለመጥቀስ ኪዳነማርያም በለይ ቀበሮ ከአክሱም ተስፋይ ሕንፍሽፍሽ ከዓድዋ አበራ ማንካ ከመቀሌ ኪዳነ ግርማይ ከመቀሌ ታደሰ ከመቀሌ ዳዊት ገብሩ (ገ/ዝሄር) ከስሄታ ከበደ ገ/መድህን ከዋጀራት ይገኙበታል::

መለስ ይባስ ብለው በ1971 ዓ.ም የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ ሆነው በጉባኤ እንዲመረጡ ተደረገ: በዛን ጊዜ ለመለስ የሚቃወሙ የነበሩ ጠንካራ ታጋዮች ፀረኢ.ህ.አ.ፓ ኢ.ድ.ዩ በተደረጉ ጦርነቶች ሞቶዋል: የቀሩም የታሰሩ የተቀጡ ሞራላቸው የወደቀ ነበሩ: የቀረው በነ ስብሃት ነጋ የተመለመለ አድርባይ የጉባኤ ተሳታፊ ነበር::

መለስ ከ1971 ዓ.ም የህ.ወ.ሓ.ት ጉባኤ በኋላ የህ.ወ.ሓ.ት ካድሬ አሰልጣኝ ነበሩ ገ/መስቀል ኃይሉና አባይ ፀሃዬ ስር ሁነው ነው:: በዛን ወቅት የህ.ወ.ሓ.ት ርእዮተ ዓለም ወደ ማኦ የከረረ ነበር: መለስ ስለቻይና ሬቮልዩሽን ሲተነትኑ እዛ በቻይና ሬቮልዮሽን ተሳታፊ የነበሩ ነው የሚመስሉ::

መለስ ሲያስተምሩት የነበረ አብዛኛው አብዛኛው የመለስ ማንነት አያውቁም ነበር: መለስ ተናጋሪ ስለነበሩ በካድሬ ስልጠና እየተሳሉ

ሂዱ: ያቺ ከጦርነት መሰወርም እየተረሳች ሂደች: ነገር ግን አሁንም ተዋጊ አውሮፕላን የመድፍ ተኩስ ሊሰሙ አይፈልጉም::

መለስ ህ.ወ.ሓ.ት ከአንድ ሪኢቶ ዓለም ወደ ሌላ ሪኢቶ ዓለም ሲገላበጥ አብረው የሚገላበጡ ነበሩ: ለማስረጃ ያህል ህ.ወ.ሓ.ት መጀመርያ የቻይና ሪኢዮተ ዓለም አምላኪ በነበረበት በአባይ ፀሃዬ ተፅፎ የተሰጣቸው ማስተማርያ ፅሑፍ ወደ ካድሬ በማስተላለፍ የታወቁ ነበር: እንዲያዉም ስለቻይና ሲያስተምሩ ልቅሶም ይጨምሩበት ነበር::

ህ.ወ.ሓ.ት ቆየት ብሎ ከ1974 ዓ.ም ጀምሮ የቻይናን ሪኢዮተ ዓለም እንደቁሻሻ ጣል አድርገው የአልባንያ ሪኢዮተ ዓለም አማኝ በመሆን ለማኦ እየጨፈጨፉ ለእንቨርሆጃ አመለኩ: መለስም ስለቻይና ሪቨልዩሽን ሲያስተምሩ ቆይተው ገልበጥ ብለው የአልባንያ ዳዳስ ሆነው አሁንም በአባይ ፀሃዬ የተዘጋጀ ፅሑፍ እንደልማዳቸው እንደሳክሰፎን ማስተማር ጀመሩ: በወቅቱ መለስን ተከትለው የካድሬ አስተማሪዎች አረጋሽ አዳነ የዉብማር አስፋው አለምሰገድ ገ/ኣምላክ አብረሃ ደስታ ፈትለወርቅ (ሞንጀርኖ) አማረ አረጋዊ ገ/መስቀል ኃይሉ ወረደ ገሰሰ ሙሉጌታ ገ/ሂወት (ጫልቱ) ሌሎችም ነበሩ::

ህ.ወ.ሓ.ት ከማርክሲስት ለኒንስት የወዛደር ፓርቲ እመሰረታለሁ ብሎ መንቀሳቀስ ጀመረ: በዛን ጊዜ በህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ የሪኢቶ ዓለም ልዩነት ተፈጠረ: የኸዉም አረጋዊ በርሀና ገደይ ዘርአፅዮንና ተከታዮቻቸው በአንድ በኩል: በሌላ በኩል ደግሞ አባይ ፀሃዬ መለስ ዜናዊና ሌሎች ማ/ኮሚቴ የነበረ ልዩነት ለረጂም ጊዜ ተፈጥሮ የቆየ: የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ ፀረ እነግደይ የሆነ ሪኢቶ ዓለም (የአልባንያ) በሺ የሚቆጠሩ አንደኛ ካድሬና 2ኛ ካድሬ ሰለጠኑ: በዛ ወቅት የሚማረው ካድሬ እነግደይ የያዙት አስተሳሰብ ተቀባይነት እንዳያገኝ አባይና መለስ ግንባር ቀደም ተሰለፉ: መለስም ለነግደይና አረጋዊ እንድአስተማሪዎቻቸው እንደታላቅ ወንድም ነው የሚያዩቸው የነበሩ: በፖለቲካ ልዩነት ምክኒያት እንደጠላቶቻቸው ማየት ጀመሩ:

መለስ ለጓደቻቸው በትንሽ ነገር ተሎ ብለው በጠላትነት ማሰለፍ መለያ ባህሬያቸው ነበር::

ህ.ወ.ሓ.ት በአልባንያ ጥምቀት የተጠመቀ ካድሬ ይዞ የማለሊት ጉባኤ በ5/11/1977 ዓ.ም ወደ ወርዒ በረሃ ጠራ: ጉባኤ 18 ቀን የፈጀ ነበር: በጉባኤው ብዙ አጀንዳዎች ነበሩ: እነ ግደይ የሪኢ.ቶ ዓለም ልዩነታቸው ለጉባኤ አቀረቡ: ጉባኤተኛው ግን ለአንድ ዓመት ሙሉ በየ 2 ወር ፀረ የግደይ ሃሳብ ካድሬ ሰልጥኖ ስለነበር: የግደይ ሃሳብ ተቀባይነት አልነበረዉም: አባይና መለስ ቀናቸው ወጣላቸው: መለስ ከጦርነት በመሰወራቸው በስጋት የበታችነት ይሰማቸው የነበረ አሁን የሞራል ድግራቸው 100% ሞላች: እነዛ ያስተማሩዋቸው ካድሬዎች ማድነቅ ጀመሩ: መለስም ወጣ ወጣ አሉ አስተማሪያቸው ለነበረው አባይ ፀሃዬ እያናናቁዋቸውና እየነጠሉዋቸው ሄዱ::

በማኸሉም ህ.ወ.ሓ.ት እንድልማዱ በሪኢ.ቶ ዓለም ተገለበጠ: መለስም ስለማኦ ስለኢ.ንቨ.ርሆጃ ሪኢ.ቶ ዓለም ሲያስተምሩ ቆይተው አሁን ህ.ወ.ሓ.ት ትክክለኛ ሪኢ.ቶ ዓለም ብሎ ሲቀየር አሁንም በአባይና በሌሎች ተዘጋጅቶ የተሰጣቸው መማርያ መፅሐፍ በማንበብ 3ኛው ሪኢ.ቶ ዓለም ለማሳመን ለሊትና ቀን ተንቀሳቀሱ አስተማሩ: በሥራቸውም የሳቸው ተቀጥያ ለመሆን የሚሯሯጡ እንደአማረ አረጋዊ፣ ዓለምሰገድ ገ/አምላክ፣ ሙሉጌታ ገ/ሂወት፣ ፈትለወርቅ ሌሎቹም ነበሩ: ልብ ብሎ ያ ካድሬ የሚሰለጥን ያለው የማኦን የአልባንያ ኢ.ንቨ.ርሆጃን ሪኢ.ቶ ዓለም ለመጨበጥ የሰለጠነ የስታሊ.ን ሪኢ.ቶ ዓለም ይማር ያለው ያው እሱ ነው: ሌላ ደግሞ መለስና ህ.ወ.ሓ.ት ይዘዉት የነበሩ ሪኢ.ቶ ዓለም ቀይረው ሲገላበጡ የመጀመርያው ወይ ደግሞ የሁለተኛው ሪኢ.ቶ ዓለም አልቀበልም ለሚለው ሰው ከጊዜው የማይሄድ ጭቃ ጭንቅላት ተብሎ ይገለላል: ተቀባይነት እንዳያገኝ ይደረጋል ጭራሹም ይሰወራል ወይ ስልጣን ካለው ስልጣኑ ይነጠቃል: በዚህ የሪኢ.ቶ ዓለም መገላበጥ ምክኒያት በየ መድረኩ ብዙ ጀግና ታጋይ ተጎድተዋል ደብዛቸው ጠፍተዋል::

መለስ ከማለሊት ጉባኤ በኋላ የ 04 ፖለቲካ ክፍል ኃላፊ አባይ ፀሃዬ ስለነበሩ ከማለሊት ጉባኤ በኋላ የማለሊት ሊቀመንበር ሆኖ ስለተመረጠ መለስ የፖለቲካ ክፍል ምክትል ኃላፊ ሆኑ: ቆየት ብሎው ጭራሹን የህ.ወ.ሓ.ት ኃላፊ ሆኑ: መለስ በዛ ፖለቲካ ኃላፊ መሆን የረኩ አልነበሩም የጥይትና የሜግ ተዋጊ አውሮፕላን የማይሰሙበት ዉጭ ጉዳይ ሆኖው የስዩም መስፍን ስልጣን ለመያዝ ፍላጎት ነበራቸው: ነገር ግን አልሆነም ሆኖም የህ.ወ.ሓ.ት የፖለቲካ ሊቀመንበር ሆኑ: እነ ዓለምሰገድ በምትካቸው ተቀመጡ በብቃት አማረ አረጋዊ ነበር ግን በነዛ ቡድን አልነበረም::

መለስ ያቺ የፖለቲካ ሊቀመንበርነት ከያዙም በኋላ ካድሬ ማስተማሩ አልተዉም: እነ አማረ አረጋዊ 3 ወይ ከዛ በላይ ወራት ካስተማሩ መለስ ስልጣናቸው ተጠቅመው በማጠቃለያ ብቅ ብለው ለካድሬው ደስኩራቸዉን ያሰማሉ: መለስን ያላወቀ ካድሬ አንጀቴ ይህ ሰው ያኑርልን ይላል: መለስ የሚፈልጋትም እቺ ተሰሚነትና ተወዳጅነት መፍጠር ነበረች: አንዳንድ ጊዜም ጦርነት በሌለበት ጊዜ መርጠው ወደ ተዋጊ ሰራዊትም ብቅ ብለው ለአስተማሩዋቸው ካድሬዎች ታማኝ ለሆኑ በማግኘት ፀረ አባይ ፀሃዬ ያደራጁ ነበር::

መለስ ለካድሬዎች ብቻ አይደሉም በማ/ኮሚቴና በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ዉስጥም ፀረ አባይ ፀሃዬ ማደራጀት ጀመሩ: መጀመርያ ዓለምሰገድ ገ/አምላክ ክንፈ ገ/መድህን ሙሉጌታ ገ/ሂወት ጀነራል አበበ ተ/ሃይማኖት ሰበኩ: በ2ኛ ደረጃ ስየ አብረሃ ተወልደ ወ/ማርያም ቢተው በላይ ከሰራዊት አዛገሮችም እነ ሳሞራ የኑስ ስብሃት ነጋ ወ.ዘ.ተ አሰልፈው በግልፅ ምንም መሸማቀቅ የሌለው ዐይኑ ያፈጠጠ የስልጣን ጥም ገፍቶዋቸው አባይ ፀሃዬ ብቁ መሪ አይደለም ብለው መጀመርያ በወሬ በሁሉም የህ.ወ.ሓ.ት አካላት አሰራጨት: ከዛ በኋላ በህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ ስብሰባና 6 ወር የፈጀ ግምገማ በክንፈ ገ/መድህንና አለምሰገድ ገ/አምላክ አባይ ፀሃዬ የአመራር አቅሙ ሚጥጦ ስለጨረሰ በመለስ ዜናዊ ይተካ የሚል ሃሳብ ቀረበ:

ሌሎችም ጨመሩና ትልቅ ክርክር ተደረገ ለረጂም ጊዜ ፈጀ በመጨረሻ በ1982 ዓ.ም ታህሳስ ሕገደንብን በሚጥስ መንገድ ተከትሎ መለስ የህ.ወ.ሓ.ት የማለሊት ሊቀመንበር ሆኑ::

ልብ በሉ መለስ እስከ 1982 ታህሳስ በፖለቲካ ትምህርት ቤት ካልሆነ በወታደራዊ ሳይንስ ምርምር ከመጤፍም አስተዋፅኦ አልነበራቸዉም: ስለዚህ መለስ ከሞተ በኋላ መለስ ህ.ወ.ሓ.ት የፈጠረ ወታደራዊ ሳይንስ ታጋዮችን አንፆ ደርግን ያስወገደ ምጡቅ ዘመን የወለደው ማለታቹሁ ዉሸት ነው: እኔ የሚገርመኝ አባይ ፀሃዬ ሁሉም ነገር እያወቁ ሃቅ አለመናገራቸው ነው::

መለስ የህ.ወ.ሓ.ት ሊቀመንበር ከሆኑበት እስከ ደርግ ተወገደበትም በወታደራዊ ሳይንስ ፍልስፍና አንድም አስተዋፅኦ አልነበራቸዉም: መለስ የህ.ወ.ሓ.ት ቁንጮ ከሆኑም በወታደራዊ ምርምር የሚመሩት ኮሚቴ ነበሩ: እነሱም የህ.ወ.ሓ.ት ወታደራዊ አዛዥ ስየ አብረሃ ምክትላቸው ፃድቃን ገትንሳኤ ሓየሎም አርኣያ አባል: እነዚህ ሶስቱ ኮሚቴ ነበሩ: በወታደራዊ ማሰልጠኛ በተለይ በምርምሩ ሓለፎም ቸንቶ ኃይለ ስላሴ ገኪዳን (መሐመድ) ነበሩ: ከመጀመርያ ጀምሮ በወታደራዊ ማሰልጠኛ የጀመረውና የቀጠለበት አስገደ ገስላሴ የአሰልጣኝ ስልጠና የሰጣቸው: ከደርግ ከድተው የመጡ ወታደሮች እንደነ ሓድጉ ከበደ ግርማይ ጃብር ሻንበል ካሕሳይ አባይ ኋላም እነ ሓለፎም ቸንቶ ተስፋይ ቸንቶ ሰመረ ቸንቶ ነበሩ: ከደርግ የተማረኩ የደርግ መከነኖችም ትልቅ አስተዋፅኦ ነበራቸው: ለዚህ ሁሉ አስተባባሪው የመምራት ስልጣን ነበራቸው: ከ1967 እስከ 1968 ዓ.ም ወታደራዊ አዛዥ የነበረ ገሰሰው አየለ: ከ1967 እስከ 1969 ዓ.ም መስከረም ሙሴ ተኽለ (መሐሪ ተኽለ) ከ1969 እስከ 1977 ዓ.ም ሐምሌ አረጋዊ በርሀ ስየ አብረሃ በምክትልነት: ከ1977 እስከ 1984 ዓ.ም ስየ አብረሃ ነበሩ: ስለሆነ መለስ በወታደራዊ ምርምር ቦታ አልነበራቸዉም ወታደራዊ ዶክተሪኑ ከተዘጋጀ በተግባር ሲውል መጀመርያ በህ.ወ.ሓ.ት ፖሊት

ቢሮ ቀጥሎ ደግሞ በመላው ማ/ኮሚቴ ይወያዩነታል ከዛ ዉጭ መለስ የሰራው ስራ አልነበረም: በወታደራዊ ሳይንስ ብቻ ሳይሆን በማ/ኮሚቴ የሚታይ የፖለቲካዊ የህዝብ ጉዳይ የኢኮኖሚ የዉጭ ጉዳይ መመርያዎች ማኒዋሎች ዕቅዶች በየ ግላቸው ካዘጋጁት በኋላ ወደ ተግባር ከመሸጋገሩ ማ/ኮሚቴ ሁሉ ተወያይቶበት ካፀደቁት በኋላ ነው: ስለዚህ መለስ በሁሉም ነገር ለህ.ወ.ሓ.ት ተሸክሞ መጣ የሚል አነጋገር ከሃቅ የራቀ ዉሸት ነው::

አንድ ነገር አለ መለስ በዚያች የፖለቲካዊ ኮሚቴ ለራሱ ታዋቂነት ሲል በሚገባ ሰርተዋል: እርግጥም ሰራዊቱ ህዝቡ፣ ህ.ወ.ሓ.ት በሪኢ.ቶ ዓለም ሲጋላበጥ አብሮ እየተገላበጠ ብዙ ታጋይ በማሳመን አታግለዋል::

መለስ በሴቶች እኩልነት የነበረው እምነት በጣም የወረደ ነበር: መለስ በሴቶች እኩልነት ፈፅሞ አያምንም ነበር: እነ አረጋሽ አዳነና የዉብማር አስፋው ሕሪቲ ምሕረትአብ መብራት በየነ ሮማን ገ/ስላሴ ያሉበት የሴተች ታጋዮች በህ.ወ.ሓ.ት የሴቶች እኩልነት አልተረጋገጠም: ህ.ወ.ሓ.ት ፀረ ሴቶች መብት ነው: ከማእከላይ ኮሚቴ እስከ ታችኛው ታጋይ የሴቶች መብት ይነካል: ወንድና ሴት እኩል ስህተት ከፈፀሙ ቅጣቱ ለሴት ይብሳል::

በህ.ወ.ሓ.ት ፆታዊ ግንኙነት የሚገድብ ከፈፀመ ግን ሞት ፍርድ የሚል ሕግ ለ10 ዓመት ያህል ቆይተዋል: በዛን ወቅት ሴት ታጋይ ከባለ ስልጣኞች ፆታዊ ግንኙነት ሲፈፅሙ ለባለስልጣኑ ላለመቅጣት ሴቷ ደብዛቸው ይጠፋል እሱ ይኖራል: ይህ ብዙ ሰዎች ያደረጉት ነው::

ሌላ መለስ ለነዛ ለሴቶች እኩልነት ጥያቄ ያነሱ ታጋዮች እንደ ጠላት ይቆጥራቸዋል: መለስ እስከ ሚሞት ሴቶች 50% ስልጣን ማግኘት አለባቸው በትምህርት መታገዝ አለባቸው:ለሴቶች ለማገዝ ተብሎ በዝቅተኛ ነጥብ ዩኒቨርሲቲ ይግቡ እያለ ሲደሰኩር: አሁንም የሚሰራው ያለ ሴቶች ተወዳዳሪ ሁነው ተምረው ብቁ እንዲሆኑ:

ለብቃታቸው እንቅፋት የሚፈጥር ነገር አስወገደ ብቁ እንዲሆኑ እንደማድረግ ፈንታ ተንበርካኪዎች እንዲሆኑ ማድረግ: አሁንም ፀረ የሴቶች እኩልነት ነው የነበረው: ስለዚህ መለስ እስከ ህልፈተ ሂወቱ ፀረሴቶች እኩልነት ነበር: የመለስ ፀረ የሴቶች መብት መሆን አሁን ያሉት የቀድሞ የህ.ወ.ሓ.ት ነባር ታጋይ ሴቶች አድርባይ ናቸው እንጂ ስንት በነገሩን ነበር::

## መለስ ብቁ ሙሁራኖች ወደ ጎኑ አያስጠጋም ነበር

በትጥቅ ትግል ጊዜ ብዙ ሙሁራኖች ይመደቡለታል ነገር ግን መለስ በተለያዩ መንገዶች ካጠገቡ ያርቃቸዋል: በዚያን ጊዜ ሙሁራኖች ከሚባሉ እየታሰሩ እየተፈቱ አብሮ የቆየ አማረ አረጋዊ በአሁኑ ጊዜ የሪፖርተር ጋዜጣ አዘጋጅ ብቻ ነው: እሱም 3ጊዜ ታስረዋል::

አንድ ጊዜ ዓመተ ምህረቱ 1982 ሓምሌ ወር ነው መለስ በሕገወጥ ስልጣን ከያዘበት ከ 6 ወር በኋላ በህ.ወ.ሓ.ት የነበረ ሙሁር በህ.ወ.ሓ.ት አመራር ደስተኛ ስለአልነበረ ተልግ ምታንፀባርቅ ነበር: በሰራዊትም በስታፍ መለስ ወደ ስልጣን መምጣቱ ደስተኛ አልነበረም: መለስ ብልሃተኛ ነው ሙሁሩ ወደ ጎኑ ለማሰለፍ አሰበ: ሙሁሩ ሊሰለፍለት ከሆነ ከሱ በፊት የነበረ አመራር መምታት የግድ ይለዋል: የሚመቱ ደግሞ አባይና ስብሃት ነበሩ: በስብሃት አይጨክንም: ሆኖም ግን ነባሩ አመራር በሙሁሩ ላይ ጥሩ አመለካከት እንዳልነበረው በሙያው እንዳላሰራው ለመናገር ወሰነ: ፀረሙሁር ግን እሱ ነበር: ከዚያ በኋላ ወለም ቀለም የቆጠረ ሙሁር ሃገረ ሰላም ተሰበሰበ: መለስ ያነሳው ጥያቄ ግልፅ በግልፅ እንወያይ ያለፈው አመራር በድሎናል የምትሉ ሃሳባቹሁ ግልፅ ተብሎ ነበር በ1981 ዓ.ም ጉንበት ሰኔ ብዙ ሙሁራች 06 (የህ.ወ.ሓ.ት የጫካ እሱር ቤት) ታስረው ነበር እነሱም ተፈትው በስብሰባው ተቀላቀሉ: ሙሁራኑ ያዩት የሰሙት ሁሉ ሐቅ መሰላቸው እነሱም የሚገምቱት ሁሉ ዘረገፉት: ለቀናት ያህል የሚታይህን ሁሉ ግለፅ አሉት:

ውይይቱ የፈጀው ከወር በላይ ነው: መለስ ለነ አባይ ሲጠሉ ለራሱ ተወዳጅነት አተረፈ: የኛ ሙሁር ደስ ብሎት በማንጨብጨብ ተለያዩ: መለስ የሰጣቸው ሁሉ እንደሚፈፀሙ ምለው ዘመቱ::

መለስ ፍርድ ቤትም ነበሩ: በህ.ወ.ሓ.ት ብዙ ታጋዮች: ህዝብ የሚታሰሩበት ወህኒ ቤት (06) የሚባል ነበር የታሰሩት ጉዳያቸው ከተጣራ በህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ ነበር: መለስ ስልጣን ከያዙበት በፊት አባይ ፀሃዬ፣ ስብሃት ነጋ፣ ክንፈ ገ/መድህን፣ አበበ ተ/ሃይማኖት፣ ተወለ ወ/ማርያም፣ መለስ ራሳቸው፣ ዓለምሰገስ ገአምላክ፣ ሐሰን ሺፋ ወ.ዘ.ተ ነበሩ: ኋላ ግን ለይስሙላ የሕግ ሙያ የሌላቸው ጠበቃ እንዲደረጉ ተደረገ: መለስ ማንነው ዳኛ ማንነው ጠበቃ ህ.ወ.ሓ.ት በ17 ዓመት የትጥቅ ትግል ዘመን ሰዎች የሚፈረዱ በሕግ ግምገማ የብዙሃን አስተያየት ስለአረፈበት ተብሎ ከቀላል እስከ ከባድ ቅጣት ይቀጣሉ: መለስ በዚያች ሁለት ዓመት ጊዜ ብዙ የጅምላ እስራት ተፈፅመዋል:: ታገል ተብሎ እንቢ ያለ ወጣት: ልጆቻቹሁ ያላታገለቹሁ ተብሎው ለራሳቸው ታስረው ሃብታቸው ተወረሰ: ስንት ወንጀል በህዝብ ላይ ተፈፀመ: ይህ ወንጀል በትግራይ ብቻ አይደለም በስመ ኢህደን በሰሜን ጎንደር፣ ፀለምት፣ ጃንአሞራ፣ በቆላወገራ፣ ፀገዴ፣ አርማጭሆ፣ በበለሳ፣ በጋይንት፣ ንፋስ መውጫ፣ ሰሜን ሸዋ፣ በሰቆጣ ላሊበላ፣ ሰሜን ወሎ ልክ በትግራይ የተፈፀመው ጭካኔ ተፈፅመዋል: ይህ መለስ የህ.ወ.ሓ.ትና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪ በነበሩበት ነው::

መለስ እጅጉን ጨካኝ ነበሩ: አንድ ጊዜ የማለሊት ከፍተኛ ካድሬዎች ታማኝ የሆኑ አብዛኛው ማ/ኮሚቴ ተሰብስበው ወጣቱ ወደ ትግል ማሰለፍ ይብቃ በተለይ የትግራይ ወጣት ከአንድ ቤት ከ 2 እስከ 6 ከዛም በላይ ታግለዋል: አሁን ያለው ወጣት ካፈስነው ወላጆች ባዶ ይቀራሉ የሚል ተቃዉሞ መጣ መለስ የሰጡት መልስ አሁን ያለን ሰራዊት በሳይንስ ተረድቶ የሚዋጋ ቢሆን በቂ ነበር ነገር ግን አሁን ያለን ሰራዊት ዝም ብሎ እንደገለባ እየተቃጠለ ለጠላትም

እያቃጠለ መጨረሻ ተቃዋሎ ይቀራል ህ.ወ.ሓ.ትም ትቃጠላለች ስለሆነ ያለን ገለባ ተቃዋሎ ከማለቁ በፊት እሱን የሚተካ ብዙ ገለባ እየሰበሰብን አሰልጥነን ማዘጋጀት አለብንን ለደርግ ልናሸንፈው የምንችለው ገለባ በማብዘት ነው አሉ: አንድ አንድ ማ/ኮሚቴና ካድሬዎች መቃወም ሞክረው ነበር አለገፉበትም: ስለዚህ መለስ እጅጉን ጨካኝ ምንም ዐይነት ወታደራዊ ሳይንስ የማይከተሉ ሰው ነበሩ: በፀረ ሻዕቢያ ጦርነት የተከፈለ ዘግናኝ ሞትም ከገለባ ማብዛት አለብን ከሚለው የመለስ ወታደራዊ ፍልስፍና የሚመነጭ ነበር::

## መለስ ለግለስልጣናቸው ለመርካት ወዳጃቸዉን ይበላሉ

መለስ በ17 ዓመት የትጥቅ ትግል ዘመን እንዴት ብለው በማን ተደግፈው እንደመጡ በስፋት አይተናል ከጉንበት 1983 ዓ.ም እስከ ህልፈተ ሂወታቸው መጨረሻ እንዴት ተጓዙ::

መለስ ጉንበት 20/1983 ዓ.ም የደርግ የመጨረሻ ዉድቀት እንግሊዝ ሃገር ለድርድር ሂደው ነበር: ጦርነቱ የመሩት በትግራይ ሃገረ ሰላም ዋና ማዘዣ በማእከል ኮማንድ ፖስት ሆኖው አተ ስየ አበረሃ ከዛ ካለው ሴንትራል ኮማንድ ማእከላዊ አመራር ለቀዳሚ መምርያ ኮማንድ ፖስት በጎንደርና በጎጃም ያለው ኃይል ዋና ኮማንድ ፖስት ማ/አመራር ሃየሎም አርአያ በሰሜን ሸዋ በጣምራ በር ወሎ ጭፍራ ለነበረ ማእከላዊ አመራር ፃድቃን ገ/ትንሳኤ የዛሬው ጀነራል ነበር: ግንኙነታቸው ከስየ አብረሃ በሃገረ ሰላም ነበር: ስለዚህ መለስ በወታደራዊ ምንም ቦታ አልነበራቸዉም::

ደርግ ወድቆ ስልጣኑ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ያዘው: የደርግ የነበረ ቢሮክራሲ ባለስልጣኑ ታሰረ ከሃገርም ሸሸ: የቀረው በየ ሥራ ምድቡ ዝቅ ብሎ 2ኛ ዜጋ ሆኖ እንዲሰራ ተነገረው: በኢትዮጵያ ደረጃ ያሉ ቁልፍ የስልጣን ቦታዎች ሁሉ በህ.ወ.ሓ.ት ታጋዮች ተያዙ: የቢሮክራሲ ሥራ ደግሞ ምንም ሙያ አልነበረዉም: አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ሃገር ወዳዶች ስለሃገራቸው በመቆርቆር ምን መሆን እንዳለበት ምክር

ለመለገስ ቢሞከሩ በመለስ ቡድን ተቀባይነት አጡ: በህ.ወ.ሓ.ት መለስ ዉጭ በመጨረሻ የደርግ የሚኒስተር መስርያ ቤት የነበረው በህ.ወ.ሓ.ት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተያዘ: መከላከያ ሚኒስተር ስየ አብረሃ፣ ፃድቃን ወ/ትንሳኤ፣ የማነ ኪዳነ እስከ ያነሰች መምርያ በታጋዮች ተያዘች: በዉጭ ጉዳይ ስዩም መስፍን ህ.ወ.ሓ.ት ተቀዳ ዓለሙ የደርግ የቀረው መዋቅር ህ.ወ.ሓ.ት ጥቂት በኢ.ህ.ዴ.ን የደህንነት ሚኒስተር (ባለስልጣን) ክንፈ ገ/መድህን መዋቅር በሙሉ ህ.ወ.ሓ.ት ከ17 ዓመት የትጥቅ ትግል የህ.ወ.ሓ.ት ወህኒ ቤት (06) የፀጥታ ሰራተኞች የነበሩ: ፋይናንስና ጉምሩክ ወንድወሰን ህ.ወ.ሓ.ት የአሁኑ በአዴን ከነ መዋቅሩ: ሌሎች የሚኒስተር መስርያ ቤቶችም አልፎ አልፎ ሚኒስተርና ምክትል ከነ መዋቅራቸው ሲኖሩ በሌላ በኩል በሚኒስተር መዓረግ ሲቪል ሆኖው በሥራቸው ደግሞ በታጋዮች ተያዘ: በዛን ጊዜ ፓርቲ ነን ብለው ህ.ወ.ሓ.ት ሲጠፈጥፉዋቸው የነበረው ለኦሮሞ ሰለሞን ተስፋይ የሚያስተባብረው የህ.ወ.ሓ.ት ካድሬ ብዛታቸው በመቶ የሚቆጠሩ: በደቡብ ቢተው በላይ ኃይለስለሴ ባህታ የሚመሩት ብዛት ያለው የህ.ወ.ሓ.ት ካድሬ: በአፋር አብረሃ ማንጁስ በደሪዳዋ ፍሰሃ ዘሪሁን (ማእሲ) ተመደቡ: በአማራም የኢ.ህ.ዴ.ን የሚያማክሩና በአመራሩ ሆነው የሚሰሩ ከህ.ወ.ሓ.ት ሥራ አስፈፃሚ እስከ ተራ ካድሬ ተመደቡ: እነዚህ ሁሉ የሚያስተባብሩ አባይ ፀሃዬ ነበሩ: መለስ በሁሉም ክልሎች ለነበሩ ለደርግ ይቃወሙ የነበሩ አሁን ፓርቲ ፈጥረው በሽግግር መንግስት ገብተው ግን ደገሞ ከህ.ወ.ሓ.ት በሪኢ.ቶ ዓለምና በተለያዩ ፖለቲካዎች በሰብአዊ መብትና ዴሞክራሲ ፍፁም ከህ.ወ.ሓ.ት የማይስማሙ በመሆናቸው ህ.ወ.ሓ.ትም እነዚህ ለማፍረስ በየ ቢሄሩና ቢሄረሰቡ ገብቶ ወጥመድ ማስቀመጥ የግድ ይል ነበር: በመለስ ዐይን ባገር ቤት ለቆዩ ሙሁራን ይንቁዋቸው ነበር::

በሌላ በኩል በቤተ መንግስት በአማካሪነት ተወለ ወማርያም ዓለምሰገድ ገአምላክ ሲቀመጡ የቤተ መንግስቱ መዋቅር የፀጥታና

ደህንነት የፋይናንስ መዋቅር በሙሉ ህወሓቶች ነበሩ: በቤተ መንግስት ከሌሎች ቢሮዎች የታምራት ላይነ ብቻ ነበሩ: አንድ አስገራሚ አብነት ልገልፅ: መለስ ለይስሙላ የተለያዩ ሙያ ያላቸው አበይት ሙሁራን አማካሪዎች ብለው ወደ ጠሚኒስተር ቢሮ አስጠግቶዋቸው ነበሩ: እነዛ ሙህሁራኖች ግን ለስም እንጂ በሙያቸ ው ለሃገሪቱ አስተዋፅኦ እንደማድረግ ወንበርና ጠረጴዛ ሰጥተው ቁጭ አደረጉዋቸው እንዳዉም የኋላ ኋላ ተላላኪ አደረጉዋቸው ለዚሁ አብነት ዶክተር (ፕሮፌሶር) ተኮላ ሓጎስ ከሚሰሩበት ሥራ ከአመሪካ አምጥተው ከመለስ አጠገብ ቁጭ አደረጉዋቸው ያለ ሥራ ብዙ ጊዜ ቆይተው ሲሰለቻቸው ለመለስ ነገሩዋቸው ብቁ መልስ አላገኙም: ተመልሰው አመሪካ ገቡ: ሌሎችም ተደናግጠው ተመልሰው ወደ ስደት ገቡ::

ይህ የስልጣን አመዳደብ በብዙ የህ.ወ.ሓ.ት ታጋይ ተቃዉሞ ነበር: ብዙ ጥያቄዎች ተነሱ በዴሞክራሲ በስልጣን በአመዳደብ ማዳላት ስለኢ.ርትራ መገንጠል ዉስጠ ዴሞክራሲ ስለሪኢ.ቶ ዓለም በስፋት ተነሱ: በዛን ጊዜ መለስ ከየት እየመነጨ ሃሳብ ነው የሚል ጥርጣሬ ነበራቸው: ጥያቄው ያመነጭ ያለው ከአንዳንድ የህ.ወ.ሓ.ት አመራር ሳይሆን አይቀርም የሚል ነበር: ህ.ወ.ሓ.ት በዉስጡ በተቃዉሞ ተናጠ: መለስ ከሁሉ የህ.ወ.ሓ.ት ታጋይ የመከላከያ ሚኒስተረም መቀሌ ከ2ሺ በላይ ኮንፍረንስ ተጠራ: ኢ.ትዮጵያ ከሁሉም አቅጣጫዎች ተሰባስበ ው መቀሌ ገቡ::

የኢ.ህ.ዴ.ን ማ/ኮሚቴ ተሳትፈው ነበር: ፀረ ዴሞክራሲ ሥራ ሊማሩ መድረኩ ተከፈተ ኮንፍረንሰኞች ጥያቄያቸዉን አፈሰሱ: መድረኩ መለስና ተወልደ ሌሎችም ይመሩት ነበር: ጥያቄዎች ረጋ ብለው እንደመመለስ መለስ የስድብ ናዳቸውን ለቀቁት: በዛን ጊዜ ማ/ኮሚቴ ሁሉ በአንድ ቃል ጥያቄ ያነሳ ታጋይ ከዳተኛ ነህ ተባለ እንዲያዉም በድርጅቱ የማጣራት ሥራ እንሰራለን ተብሎ ተወሰነ: ኮንፍረንሰኛ ሁሉ ስጋት ላይ ወደቀ::

መለስ የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ ሁሉ ታማኝ ካድሬዎች በመመልመል የህ.ወ.ሓ.ት ታጋይ ወዳለበት በሁሉም አቅጣጫ አሰማራ: ለዚህ ስብሰባ የሚያስተባብሩና የሚፈርዱ ተመደቡ::

በአዲስ አበባ ታደሰ በርሀ (ጋውና)፣ ኮነሬል አብረሃ (ካርተር)፣ ወዲሙዕሮ፣ ጌታቸው አሰፋ ታችኛው ካድሬ

ላይኛው ኮሚቴ፣ ስየ አብረሃ፣ ተወልደ ወማርያም፣ ዓለምሰገድ ገአምላክ፣ ፃድቃን ገትንሳኤ::

በኮሮችና እዝዎች፣ በእዝ፣ በኮር፣ በክፍለጦር፣ በብርጌድ፣ ፈራጅና አጣሪ ኮሚቴ እንድደራጅ ተደረገ::

በትግራይ ክልል ላየኛው ኮሚቴዎች ገብሩ አስራት የሚመራው: ታችኛው ኮሚቴ: ሃለቃ ፀጋይ በረሀ፣ አባይ ወሉ፣ ካሕሳይ ቆራይ (06) በሁሉም ዞኖች በነዛ መሪዎች የሚመራ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለክልል መስተዳደር ተዋቀረ::

በኢትዮጵያ ደረጃ የስልክ የሬድዮ መገናኛ ተዘረጋ በሃገር ደረጃ ግንኙነት አላቸው ተብለው የሚጠረጠሩ በአንድ ሰዓት (ቀን እንዲታዩ) ይደረጋል: በየ ሰዓቱ እገሌ ስለእገሌ ምን አለ እየተባለ መረጃ በስልክ በሬድዮ መገናኛ ይተላለፋል: አንድ አንድ ቦታም በመደረክ ቁሞ የሚጠየቅ ሃቁን አውጣ እገሌ ባህርዳር ወይ ሌላ ቦታ ለራሱ አጋልጦ አንተም ጠቁሞሃል በማለት ሽብር መፍጠር ነበር: ሰው ተጨነቀ::

በየ ክልሉ በሃገር ደረጃ የሚደረረገው ስብሰባ ዉጤቱ በከፍተኛ ኮሚቴ ተጨመቆ ማታ ማታ ሁሉ ጊዜ ሪፖርት ለመለስ ይቀርብለታል: የህ.ወ.ሓ.ት ታጋይ ባልሰራው በማያውቀው ነገር ተጨነቀ: በጥርጣሬ ከ32ሺ በላይ ከተራ ታጋይ እስከ ከፍተኛ ካድሬ ታሰረ: በተለይ በ17 ዐዓመት የትጥቅ ትግል ጊዜ የተለያዩ ጥያቄ ያነሱ የነበሩ በተለያዩ የህ.ወ.ሓ.ት አቋሞች፣ ፖሊሲዎች ኢርትራን የሚመለከት ይከራከሩ የነበሩ አብዛኞቹ ታሰሩ: በሆለታ ገነት የጨለማ እሱር ቤት ብቻ ከ3ሺ በላይ ከፍተኛ ካድሬዎች ጦር

መሪዎች ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመት ተኩል ያለ ፍርድ ቤት እውቅና ታስረው ያለ ቅርታ ተፈቱ አንዳንድ ሰዎችም የት እንደቀሩ አይታወቅም: ብዙ ታጋይ አዲስ አበባ ብራንዳ ላይ ወደቀ ሴት ጀግና ታጋዮች በሴተኛ አዳሪነት ተሰማሩ: ብዙ የገበሬ ልጆች እድል ያገኙ ወደ ሃገራቸው ተመለሱ: የቀሩ ተበታተኑ: ወደ ሃገር ቤት ተመልሰው በዘመድ አዝማድ እንዳይኖሩም ሬድዮ ድምፅ ወያነ ትግራይ በነ ፀጋይ በርሀ ካድሬዎች የቀበሌ ተላላኪዎች እነዚህ ከሰራዊት ተባርረው የመጡ እንዳ ያታልላቹ እንዳታስጠጉዋቸው ተብሎ ታወጀ: ትናንትና በጎማ ጫማና በቁረጭ አቡጀዴ አንሶላ ለብሰው ደርግን እየጠራረጉ አዲስ አበባ አራት ኪሎ አስገብተው ለነ መለስ በሞቀ ወንበር ያስቀመጡ ጀግኖች እንደዚህ ዐይነት ግፍ እንዲፈፀምባቸው ማድረግ: እነ መለስና ጓዶቹ ምን ያህል ጨካኞች እንደነበሩ ያሳያል::

ከመለስ ጀምሮ የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ ሲባል የነበረ ልንገራቹሁ ይላሉ: ይህ የገበሬ ሕብረተሰብ ወታደር እኩልነት አለህ ብለን ያመጣነው አሁን ባለበት የበረሃ እኩልነት: እናስተናግድህ ብለን ልቅ ከሰደድነው በህዝብ ፊት ገበያ አውጥቶ ስለሚያጋልጠን ሩቅ ሳይጓዝ ማስታገሻ ማድረግ አለብን: የሚም በነ መለስ ዓለምሰገድ ገአምላክ ስብሀት ነጋ ክንፈ ገመድህን ተወልደ ወማርያም ስየ አብረሃና ሌሎች አጋሮቻቸው ሃሳብ ይሰነዝሩ ነበር: በተለይ ዓለምሰገድ ገአምላክ እንደዛሬው በነ መለስ ተገፍተው በስደት የሚኖሩ አይመሰሉም ነበር::

መለስ ይህ ሰራዊት መበተን ዓላማ ነበራቸው የሀዉም በህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ በሰራዊት ተቀባይነት የነበራቸው እንደስየ አብረሃ አባይ ፀሃዬ ሌሎችም ስለነበሩ: የተበታተነው ታጋይ የነስየ ኃይል እንደመድከም ተደርጎ የተወሰደ እርምጃ ነበር: መለስ ቀጥሎ ያደረገ ው ለሚጠረጥራቸው ከፍተኛ መሪዎች በጦርነት የተጎዳች ትግራይ እናልማ በሚል ሽፋን አባይ ፀሃዬን የሚያክል ህ.ወ.ሓ.ት 17 ዓመት

የመራ በትንሽ አንድ የተማረ ኤክስፐርት ማናጀር ሆኖ ሊመራት የሚችል ሰርተን ስየ አብረሃ ለህ.ወ.ሓ.ት ስራዎች 20 ዓመት (ሃያ ዓመት በላይ) የመራ በአንድ ኢኮኖሚስት (መሃንዲስ) ሊመሩ የሚችሉ የትእምት ድርጅቶች ከሚኒስተርነት አውርዶ ወደ ትግራይ ማሽቀንጠር: ለተወልደ ወማርያም ዓለምሰገድ ገአምላክ አማካሪዎች በሚል ሽፋን ወንበርና ጠረጴዛ በቂ ደሞዝ ሰጥቶ ቁጭ ማድረጉ መለስ ምን ያህል ለራሱ ብቻ ለብቻው እንደሚያስብ አንድ ማስረጃ ነው: ስለዚህ መለስ ብቻው ያለ እረፍት ለሃገር ልማት ደክሞ የሞተ መለስ በማለት በ1993 ዓ.ም የህ.ወ.ሓ.ት መሰናጠቅ ወቅትም የነበረው የጠላቶችን አመታት ስልት ከረጂም ጊዜ አካብቶት የመጣ ልምድ ነበር: እነ ስየ ገብሩ አስራት ተወልደ ሌሎችም በዚህች ሃገር ካሉ ስልጣኔን አትቀጥልም ብሎ በማሰብ ነበር: ምንም እንኳ እነዛ ተነጥለው የወጡ መውጣት ያልነበራቸው ቢሆንና የራሳቸው አንኳር ስህተት ቢኖራቸው መለስ ግን ሁሉም ነገር ዉስጥ ለዉስጥ በፀጥታ ኃይሎችና ካድሬዎች አዘጋጅቶ በመቆየት መድረክ ረግጠው እንዲወጡ ማድረግ ሆን ብሎ አስቦበት ያደረገው ጨካኝ ተግባር ነው: መለስ የተገነጠለው ማ/ኮሚቴ ብቻ አልነበረም የመታ አሁንም ከነዛ የተገነጠሉ ጓዶች ግንኙነት ይኖራቸዋል ያላቸው ወይ ለወደፊት ጠንቅ ይሆናሉ ያላቸው ብዙ የህ.ወ.ሓ.ት ታጋይ ካድሬዎች ስቪል አባልና ካድሬዎች በሰበቡ ጠራረጎ ጥሎቸዋል::

## መለስ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባል ድርጅቶች በአጋር ድርጅት መሪዎች ካድሬዎች ጨካኝ ነበሩ

መለስ የቾኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባል ድርጅቶችና አጋሮች አመራር አባላት: በየ ክልላቸው ሄደው በህዝብ ታዋቂነትና ተወዳጅነት ከፈጠሩ ቅናት ስጋት በማሳደር ከህዝባቸው በመነጠል (በመወንጀል) ቆፍረው ቆፍረው ይነቅሉታል: ለአብነት አንድ ሁለት ልጥቀስ፦

1. ታምራት ላይኔ በሙስና እንደተጨማለቁ አስቀድመው ያውቃሉ: ታምራት ላይኔ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ከታምራት በላይ ከነ ዘር መንዘራቸው በሙስና የተነከሩ ነበሩ: ሆኖም ግን ለስልጣናቸው አደገኛ ስለአልሆኑ ችላ ብለው ታምራት ላይኔ ግን በጊዜው በመድረክ በመውጣት ልታይ ልታይ የሚል መንፈስ ለሳዩዋቸው በብዙ ሙሁራኖች ከዲፕሎማሲ ታዋቂነትን ስለአተረፉ መለስ ደብቀዋት የቆዩ ቀይ ካርድ በየስሜን መድረኩ በማቅረብ ወህኒ ቤት ወረወሩዋቸው
2. አባተ ኪሾ ታማኝ ነበሩ ነገር ግን ከነ ቢተው በላይ፣ ገብሩ አስራት፣ ሰለሞን ተስፋይ በአጠቃላይ ከህ.ወ.ሓ.ት መሰናጠቅ ከነበረው የኃይሎች አሰላለፍ ተጠርጥረው በዛው እንደ መሰናበት ለደህድን አመራር በዉስጣቸው በመሰናጠቅ ከፋፍለው ለአባተ ኪሾ በመጨፍፀፍ ወደ እሱር ቤት ወረወሩት
3. በኦሮሞ አባዱላ ገመዳ ታዋቂነት አግኝተው ምን ይሁን ምን ብዙ ሰው በጎናቸው አሰልፈው ስለነበሩ በፓርላማ ምርጫ ለፌደራል ስልጣን አማካኝተው አፈጉባኤ አድርገው ቁጭ አደረጉዋቸው እሳቸው ከሆኑ በኋላ በአባዱላ ገመዳ ዘመነ ስልጣን የዛን የወረዳ የክልል ባለስልጣኖች የነበሩ በሙስናና በሌሎች ምክኒያት በመፍጠር የመዋቅር ለውጥ አደረጉ: በዚሁ ከኦሮሞ ሳንወጣ በጁነዲን ሳዶ፣ ኩማ ደመቅሳም ብዙ ሰርተዋል: ዶር ነጋሱ ጊዳዳ በጥሩ አቋማቸው ወንጀለኛ ተደርገው ተባርረዋል
4. በአማራ ክልልም ብዙ ታዋቂነት ያገኙ አሉ ያሉዋቸው ብዙ ሰዎች ዝቅ እንዲሉ አደረጉዋል: ቀደም ሲል የታወቀው ሽኮር ቀማሹ ታምራት: ወንድወሰን ከበደ ኃይለ ጥላሁን ተፈራ ባሉዋ አሁን ከመለስ ሞት በኋላ ወጣሁ ወጣሁ የሚሉ ያሉ በረከት ሰምኦን ታደሰ ካሳ (ጥንቅሽ) ዝቅ አደረጉዋቸው

5. ከምርጫ 2002 ዓ.ም በኋላ ከፍተኛ ሚኒስትሮች የነበሩ እነ ተሾመ ቶጓ፣ ሽፈራው ጃርሶ፣ ስዩም መስፍን፣ ግርማ ብሩ፣ ተቀዳ ዓለሙ፣ ሌሎችም: መጀመርያ የሰሩት ሁሉ ሪከርድ ይዘው በመቆየት ስልጣን መተካከል በሚል ሰበብ ጠራርገው አወጡዋቸው: ከዛ በኋላ ጥሩ ሉሌ ይሆኑልኛል ያሉዋቸው በክፍተቱ ሰገሰጉት መተካከል ግን አላደረግኩም::

የተከበራቹሁ አንባብያን እነ ኩማ ደመቅሳ አባዱላ ሌሎችም ከሙስና ነፃ ናቸው ማለት አይደለም: መለስ ለሰዎች በከባድ ዱላ ከመቱ በኋላ ዱላው ተቀብለው ሰጥ ብለው የተገዙ እንደገና አሻሽተው ወደ ስልጣን ይመለሱቸዋል እነዛ የተመለሱ አሜን ብለው ይገዙላቸዋል ለዚሁ እንደ ምስክርነት አባይ ፀሃዬ ኩማ ደመቅሳ አዲሱ ለገሰ ሌሎችም: መለስ በሂወት አሉ ያልተነካ የተካ ካላቸው የአማራና ምክር ቤቱ ተጨምሮበት አያሌው ጎበዜ ብቻ ናቸው: መለስ በሶማል፣ በጋምቤላ፣ በጉሙዝ እጃቸው አሳርፈዋል::

በአጠቃላይ መለስ 38 ዓመት ሙሉ ስልጣን ሳይኖራቸው ይሁን ስልጣን ይዘው ከፋፍለህ ገዛ የሚል የኋላቀር ስርዓት ኤክስፐርት ነበሩ::

በአጠቃላይ መለስ ተሰሚነት አምልኮት የሚያገኙለት ነገር ከተገኘች ለማንም አሳልፈው የማይሰጡ ለሕግ ለደንብ የማይገዙ ነበሩ::

በ1975 ዓ.ም ጥቅምት ወር ለመለስ ትንቢት ሲያስቀምጥ ኪሮስ ሓጎስ (ወዲ ሓጎስ) ይባላል: ይህ ሰው ኢትዮጵያዊ በዓድዋ ከተማ የተወለደ ያደገ የመለስም አብሮ አደግ ነው: በዛ ባስቀመጥኩት ጥቅምት ወር ወርዒ በሚባለው መለስ አማረ አረጋዊ ዓለምሰገድ አረጋሽ አዳነ አባይ ፀሃዬ ካድሬ ያስተምሩ ነበር: በዛን ጊዜ የህ.ወ.ሓ.ት ሴት ታጋይ መብታችን ተነካ ብለው አድማ የጀመሩበት ነበር: በዛ አካባቢ ከ 15 ማ/ኮሚቴ ነበሩ ለሴቶች እየሰበኩ ሲያወያዩዋቸው ከረሙ ሊያሳምኑዋ ቸው አልቻሉም::

አንድ ቀን ግን መለስ ከሁሉም ተማሪዎች ካድሬ በመመልመል 30 የሚሆኑ ተሰበሰቡ: መለስ ለሴቶች ለማሳመን ብዙ ተናገሩ: ከ8 ሰዓት ንግግር በኋላ ሴቶች አምነናል ተሳስተናል አሉ ግን ካንገት በላይ ነበር: ኋላ አገርሽቶበታል: ሆነው ግን ወዲ ሐጎስ ያለ ቢኖር ይህ ዉሸታም ሰዉየ ሲወሰልት ቀን እቺ ሃገር ይሸጣታል አለ (በትግርኛ እዙ ሑልኩስ ወዲ እዙይ ክውስልት እንተሎ መዓልቲ ዓዲ ከጥፍእ እዩ: ይትረፍ ነዓና ንዓለም እዉን ከታልልዩ): ይህ ለማስረጃነት የጠቀስኩት መለስ ለሁሉም ነገር ይጠቀሙበታል: ወዲ ሓጎስ ሐቀኛና ጀግና ነበር ከሌሎች ጀግኞች እኩልየሚሰለፍ ነበር::

እስከ አሁን በማኸል የመለስን የትግል ታሪክ እንደመንደርደሪያ ማስቀምጥ አንባብያን ለሚቀጥል የአዲስ ራዕይ 8ኛ ዐመት ቅፅ 4 ልዩ እትም 2005 ዓ.ም መለስን አስመልክቶ ተፅፎ ያለው ታሪክ ሃቅ ወይም ዉሸት ብላቹሁ ትረዱ ዘንድ በማሰብ ነው የመለስ ታሪክ: ተግባራቸው ሁሉ ለመፃፍ ብዙ መፃሕፍት ሊወጣው ይችላል እሱ ታሪክ ተመራማሪዎች ይፃፉት እኔ ግን መግቢያ እንዲሆንላቹሁ ለመግለፅ ብቻ ነው::

# ክፍል 8

# 8ኛ ዓመት ቅፅ 4 ልዩ እትም በገፅ 18 አደዲስ መስመር 3

"በቅድሚያ መለስ ህ.ወ.ሓ.ትና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የተራማጅ አስተሳሰብ ባለቤቶች እንዲሆኑ ያደረገዉን ትግል እንመልከት: መለስ የድርጅቱ ፖለቲካዊ ሪኢ.ቶ ላለማዊ መሪ ለመሆን ያበቃው ከሁሉ በፊት ራስን እጅግ ተራማጅ በሆነው አስተሳሰብ በመገንባቱ ነበር: መለስ የሚመሩበት አስተሳሰብ የሕብረተሰብን ችግሮች በትክክል ለመለየት አልፎ ተርፎም ለመፍታት የሚያስችል አስተሳሰብ ነበር"::

መለስ ህ.ወ.ሓ.ትና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የተራማጅ አስተሳሰብ ባለቤት አድርጎታ ል የሚል ሃሳብ ለመለስ ብቻ መሸለም ትክክል አይደለም: መጀመርያ ህ.ወ.ሓ.ት ከመመስረቱ በፊት በስድሳዎቹ ዓ.ም ከነበሩ የተራማጅ ተማሪዎች ማሕበር ጋር ነበር: በዛን ወቅት የነበሩ አስተሳሰቦች እንደ ፋሽን ይታይ የነበረ የማርክሲዝም ለኒንዝምና የማኦ መስመር እንከተላለን የሚል ነበር: በተጨማሪ ዘውዳዊ ስርዓት በማፍረስ በህዝብ የተመረጠ ህዝባዊ መንግስት ይመሰረት የመሳሰሉ የቢሂር ጥያቄ ነበሩ::

ህ.ወ.ሓ.ት የመሰረቱ ግለሰቦች ደደቢት ወርደው አዲስ ተራማጅ ሃሳብ አልነበራቸዉም: በሰነድ የተነደፈ አዲስ ተራማጅ ሃሳብ አልነበራቸዉም: የባሰው ግን በጣም የወረደና ታሪካዊ መነሻ የሌለው ነፃ ሃገረ ትግራይ እንመሰርታለን: ትግራይ የኢትዮጵያ አካል አልሆነችም የሚል ሃሳብ በመያዝ በፕሮግራም ነድፈው ማኒፌስቶ ፅፈው በዓለም ደረጃ ያሰራጩ ናቸው: መለስ ማኒፌስቶ ከፃፉት የኮሚቴ አባላት አንዱ ነበሩ: ስለዚህ መለስ ከጅምሩ ተራማጅ ሳይሆኑ የነበሩ እጅግ ኋላ ቀር የሆነው የጠባብነት ሃሳብ አራማጅ እንደነበሩ ነው ታሪካቸው የነበረን::

መለስ ለራሳቸዉም ቢሆን በተራማጅ አስተሳሰብ የታነፁ አልነበሩም እስከ ህልፈተ ሂወታቸው ለራሳቸው ያደረጉት ግንባታ ከ80 ሚልዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ለመከራና ለአሳር ያደረጉ እንጂ ያመጣው ፋይዳ የለም: ሕብረተሰቡ አንድነቱ ላልቶ ብቻ ሳይሆን እንዲገነጠል በጠላትነት እንዲተያይ ሆኖዋል::

በፖለቲካዊ አስተሳሰብ ሪእዮተ ዓለም አዲስ ተራማጅ ሃሳብ ያመጡት የለም ያ ከ 40 ዓመት የነበረ የማኦ ሃሳብ ነው ደጋግመው እየሰሩ የመጡ: ስለዚህ መለስ ዴሞክራሲያዊ ተራማጅ አልነበሩም::

"በገፅ 19 አዲስ መስመር 2: መለስ ተራማጅ የሚባል አስተሳሰብ ያዳበረው መለስ ብጥናትና ምርምር ሥራዎች ያመጣቸው ኣዳዲስ ሃሳቦች በማንም ላይ በግድ እየጫነ የማይጓዝ ሰው ነበር ይላል::"

መለስ የራሳቸው ተራማጅ ሃሳብ አፍልቀው ያመጡት ሃሳብ አልነበረም: ቀደም ሲል የአባይ ፀሃዬ ሃሳብ አስተላላፊ ነበሩ: ስልጣን ከያዙ በኋላ መለስ የሰዎችን ሃሳብ ወሰደው የራሳቸዉን ሃሳብ አድርገው የማቅረብ ችሎታ ስላላቸው ባለፉት ዓመታት የሙሁራን፣ የተማሪዎች፣ የአስተማሪዎች፣ የነጋዴዎች፣ የገበሬዎች፣ የወዛደሮች፣ የሴቶች፣ የሃይማኖት አባቶች ስብሰባ ያዘወትራሉ: በስብሰባው የፈለቁ ሃሳቦች የተሰጡ አስተያየቶች ሁሉ በቪድዮ ካሜራ እየቀረፁ ከያዙ በኋላ አይተው ተመልክተው የሚያስፈልጋቸው ሃሳብ በመውሰድ ቆየት ብለው የራሳቸው ሃሳብ አድርገው የማቅረብ (የመጥለፍ) ችሎታቸው ትልቅ ነበር: መለስ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሃሳብም: ለጊዜው ሃሳባቸው በመቃወም በብዙሃን መገናኛዎች ሳይቀር ሲመቱዋቸው ይቆዩና የተወሰኑ ወራት ወይም ዓመት ቆይተው የሚቃወሙት የነበረ ሃሳብ ተመልሰው የራሳቸው ፍልስፍና አድርገው ያቀርባሉ: ስለዚህ የሰዎችን ሃሳብ የመጥለፍ እንጂ ሃሳብ አፍላቂ አልነበሩም::

ሌላ መለስ ከ1979 ዓ.ም ጀምረው መፃህፍት ጋዜጦች መፅሄቶች ያነባሉ: ከንባባቸው ብዙ ነገር ሊማሩ እንደቻሉ ይነገርላቸው ነበር: እርግጥ ያነባሉ ግን ደግሞ በመሰረታዊ ፍልስፍና የሚያተኩሩ ሳይሆን እሳቸዉን መድረክ ጋር ሊያስተውቁኝ ይችላሉ ብለው የገመቱት ቀንጨብ አድርገው በቃላት ተንጠልጥለው ነው የሚናገሩ: በዛን ጊዜ አጀቤ መለስ ይባልላቸዋል::

"በገፅ 19 አዲስ መስመር 3: የመጀመርያ አብነት ህ.ወ.ሓ.ት ከ1977 ዓ.ም በኋላ በዉስጡ የተቀሰቀሰዉን ጠንካራ የሃሳብ ልዩነት ያስተናገደ በት አገባብ ነው: በዛን ወቅት የህ.ወ.ሓ.ት ሊቃነመናብር ት ፀሃፊ የነበሩት አረጋዊ በርሀና ግደይ ዘርአፅዮን ናቸው: ሁለቱም አዲሱ የህ.ወ.ሓ.ት ተራማጅ ሃሳብ መቀበል ስላቃታቸው የቆየ የኋላቀር አስተሳሰቦች የሙጥኝ ብለው ይዘው ነበር: በአዲሱና ጊዜ በሻረው አስተሳሰብ መካከል በተካሄደው ሰፊ የሃሳብ ትልል መለስ

አዲሱንና ተራማጅን አስተሳሰብ በማምጣት እነርሱ ደግሞ የቆየዉን አመለካከት ለማስጠበቅ በሞሞከር በተካሄደ ው ዴሞክራሲያዊ ትግል ህ.ወ.ሓ.ት ዉስጥ የአዲሱ አመለካከት የበላይነት ጎልቶ ወጣ: ይላሉ የአዲስ ራዕይ ፀሐፊዎች::"

የአዲስ ራዕይ ፀሐፊዎች እየፃፋቹሁ ያላቹሁ የመለስ ታሪክ ማጉላት ነው ወይስ የመለስ ታሪክ ማበላሸት ለሚለው ጥያቄ በበኩሌ ዐይንን የኳሉ መስለው ዐይንን ማጥፋት ነው የሚመስለኝ: ምክኒያቱም በ1977 ዓ.ም መለስ ያመጡት አዲስ ሪኢ.ቶ ዓለም ፖሊሲ አልነበረም: ህ.ወ.ሓ.ት ከተመሰረተበት እስከ አሁን ይዞት ያለ የቻይና አንባ ገነን ኮመኒስት ሪኢ.ቶ ዓለም ነው: በመለስ አጭር ታሪክ እንደ ገለፅኩት ህ.ወ.ሓ.ት ከመጀመርያ ጀምሮ ማርክሲዝም ለኒኒዝም መሰረተ ሃሳብና የማኦ አዲሱ ዴሞክራሲ ፕሮግራም ተከትሎ ነው የመጣ: ታድያ የመለስ አዲሱ ነተራማጅነት የት ላይ ነው: በ1977 ዓ.ም ህ.ወ.ሓ.ት የማርክሲስት ለኒንስት ሊግ (የወዛደር ፓርቲ) ያስፈልጋል አሉ ያው ለነበረው ሪኢ.ቶ ዓለም: በወዛደር አመራር ይመራ ማለሊት ለሁሉም መደቦች አፍና ትምራ ነው ያሉ: ይህ ደግሞ የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መንጠቅ ማለት ነው::

እነ ግደይ ዘርአፅዮን ይዘዉት የነበረ ህ.ወ.ሓ.ት ፀረ ዴሞክራሲ ነው: በአሁኑ ጊዜ ከግለሰብ እስከ ብዙሃኑ መብት የሚያስከብር ካፒታሊዝም ዴሞክራሲ ነው: ስለዚህ ህ.ወ.ሓ.ት መደባዊ ይዘቱም ሆነ ይዞት ያለው የጠባብነት የማርክሲዝም ለኒንዝም ሃሳብ ይዞ ዓለም አቀፍ የወዛደር ስርዓት ሊመጣ አይችልም ነው ያሉት: ሌላ በአረጋዊ በርሀም ተመሳሳይ ነበር: ለየት ያለ ቢኖረው በግንባርና በደጀን (በቤዝ ኤርያ): በማዘዣ ጣብያ በግንባር የጦርነት አሰላለፍ የሚል ልዩነት ነበር በመሰረቱ ግን አዲስና ጊዜው የሚጠይቀው ልዩ ሃሳብ የነበራቸው ግደይና አረጋዊ በርሀ ናቸው: መለስ ባለህበት ሂድ (እንደ ወታደራዊ ሰልፍ) ዐይነት የንግግር ድንፋታ ስለነበራቸው ብቻ ነው:

በተጨማሪ መለስና ሌሎች የህ.ወ.ሓ.ት አመራር በጉባኤ የነበረ ካድሬ አስቀድመው ከ3 እስከ 4 ወር የአንድ ወገን ሃሳብ አሰልጥነው ስለቆዩ እንደ ሰዓት (የድሮ ሮሜር) የተሞላ ካድሬ በዉሸት ቅስቀሳ እጁ ስለአወጣላቸው እንጂ መለስ ይሁኑ ሌሎች ተራማጅ ሃሳብ አልነበራቸዉም: እንዲያው በጉባኤ የነበረ ታጋይ የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴና የነሱ አጋሮች የነበሩ ካድሬዎች ተፅእኖና ዓፈና ሳይበግረው ለአረጋዊ በርሄና ግደይ ዘርአፅዮን ወደ ማለሊት ማ/ኮሚቴ መረጡዋቸው: የማለሊት ፖሊት ቢሮም ተመረጠው ነበር: መለስ ያሉበት የማለሊት ማ/ኮሚቴ ግን በዉስጡ አንድ ማ/ኮሚቴ ስህተት ፈፅሞ ከተገኘ ለፓርቲው ቁጥጥር ኮሚቴ ክስ ቀርቦለት እሱም ክሱ አይቶ ሊወስን እየተገባው እነ መለስ ግን ፀረ ሕገደንብ ማለሊት በመሄድ ለነ ግደይ ከፖሊት ቢሮና ከማእከላይ ኮሚቴ ስልጣናቸውን አሽቀንጥረው ጣሉዋቸው: አዲስ ራዕዮች ሃቁ ግን መለስ ምንም ተራማጅ ሃሳብ ያልነበራቸው: እሳቸውና ጓዶቻቸ ው ፀረ ዴሞክራሲና ዓፋኖች መኖራቸው ነው እማውቀው: ስለዚህ መለስና ህ.ወ.ሓ.ት በ1977 ዓ.ም በነበረ ጉባኤ ልዩነት ያስተናገደበት ጉባኤ ሳይሆን ህ.ወ.ሓ.ት የመጨረሻ ዓፋኝና አንባ ገነን መሆኑ የተጋለጠበት ነበር: ሌላ አዲስ ራዕዮች በ1977 ዓ.ም ግደይና አረጋዊ አዲስ የህ.ወ.ሓ.ት ተራማጅ ሃሳብ መቀበል ያቃታቸው ነበሩ ትላላቹሁ: ምን ማለታቹሁ ነው መለስ እኮ አዲስ ሃሳብ አልነበራቸዉም: አዲስና ተራማጅ ሃሳብ የነበራቸው እኮ እነግደይ ዘርአፅዮንና አረጋዊ በርሀ ነበሩ: በዛን ወቅት ደግሞ የህ.ወ.ሓ.ት ተራማጅ አስተሳሰብ ሳይሆን ጎልቶ የወጣ መለስና ህ.ወ.ሓ.ት ማለሊት ዓፋኝ መሆናቸው ጎልተው መድረክ ላይ የወጡበት ነበር::

"ገፅ 20 አዲስ መስመር ሁለት: እንደገና በ1993 ዓ.ም ከኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አመራር የተነሳው ልዩነት ከመፍታት አኳያ የመለስን ዴሞክራሲያዊ አካሄድ እንመልከት: በአንድ በኩል የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ የተንሰራፈበትን አንጃ በሚወክሉ እነ

ተወልደ፣ ስየ፣ ገብሩ አስራት በሌላ በኩል ልማታዊ ዴሞክራሲያዊነት አስተሳሰብን በሚወክለው መለስና ጓዶቹ መካከል የተካሄደው የአስተሳሰብ ትግል በወረቀትና በእስክሪቶ በድርጅት መድረኮችና ጉባኤዎች የተካሄደ ነበር ይላሉ::"

አዲስ ራዕዮች በማታውቁት በስማቹሁ በተሞላቹሁ አልበቃም ብላቹሁ ለምን የሌሎች ዜጎች ታባላሽላቹሁ: እኔ ለማንም ሰው አልወግንም ሃቁ ግን ልመስክር::

መለስ ፀረ ኪራይ ሰብሳቢና ሙስና አልነበሩም: ምክኒያቱም በሃገራችን ያሉ ኪራይ ሰብሳቢዎች በሙስና የተጨማለቁ ባለስልጣኖች ጥቂት ባለሃብቶች ሁሉም የመለስ አጋሮች ናቸው: የሚመጣ ሰው ግን ብዙ ስሞች በመለጠፍ ከገፀ መሬት ያጠፉታል::

መለስ ከህ.ወ.ሓ.ት የተገነጠለው ቡድን የኪራይ ሰብሳቢ ወኪሎች ብለው ስም ለጥፈዋል: እኔ እንደማውቀው ግን በስልጣን የነበረ ህ.ወ.ሓ.ት የቀማ አንጃና ተገንጥሎ የወጣ አንጃ ልዩነታቸው እነ ገብሩ የነበራቸው ልዩነት፦

የሉኡላዊነት ጉዳይ ሆኖ ለሻዕቢያ ጨርሰን በመጥረግ ዓሰብን በመቆጣጠር ድሮ የፈፀምነው ስህተት ነስተካክል ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እናድርግ: ከኢርትራ ጋር በአልጀርስ የተደረገ ድርድር የሃገራችን ሉኡላዊነት የማያከብር ስምምነት ነው: ጭራሹም እኛ ሉኡላዊነታችን አሳልፈን ለሻዕቢያ ተንበርክከን ተጉዘናል: አሁንም ሻዕቢያ በዉስጣችን መንግስት መስርቶ ይመራን እንዳለ ነው የሚረዳን: በመሰረቱ ስለኢትዮጵያ ብቻችን የፈፀምነው ስህተት ነው የሚል ነበር: አሁን የኢርትራ ጠረፍ በሚመለከት እንደአዲስ ይታይ ለሻዕቢያም ጨርሰን እናስወግደው ነበር: በተጨማሪ ከሻዕቢያ ያደረግነው ድርድርና ስምምነት ሁሉ ሃገራዊ ኃላፊነት የሌለው 80 ሚልዮን የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲንበረከክ ያደረገ ነው ብለው ነው የተከራከሩ::

መለስ ግን እናንተ የሚትሉት ያላቹሁ ፀረ ዴሞክራሲና የህዝቦችና ቢሄር ቢሄረሰቦች መብት የሚያስከብረው ሕገ መንግስት እየናዳቹሁ ነው ያላቹሁ: ጭራሹም እናንተ የኪራይ ሰብሳቢነት ጠበቃ ናቹሁ:: ወደዳቹሁም ጠላቹሁም ኢርትራ ነፃነቷ አግኝታለች አፍንጫቹሁ ንከሱ በማለት ለሻዕቢያ ወገንነታቸውን አረጋገጡ::

ሌላ አንጃዎች መለስን ለመርታት ሲሉ ታች ወደ ዘረኝነት በመውረድ መለስ ኢርትራዊ ዝርያ ስለሆኑ ለኢትዮጵያ ጥቅም ያልቆሙ መሆናቸው አስመስለው ፈርጀዋል ትላላቹሁ::

በበኩሌ መለስ ከታገሉበት ጉንበት ወር 1967 ዓ.ም እስከ ህልፈተ ሂወታቸው ለኢርትራውያን ለሻዕቢያ በመጣበቅ ይቅርና ኢትዮጵያ ውያን ኢርትራውያን ራሳቸው የሻዕቢያ ታጋዮች ሳይቀሩ የሚያውቁት ነው: ስለዚህ አንጃዎች በትክክል ካሉት ትክክል ነበሩ::

ለነዛ ከህ.ወ.ሓ.ት ተገንጥለው የወጡ አንጃዎች በበኩሌ ስህተት ፈፅመዋል የምላቸው እነ መለስና ቡድኖቻቸው ከትጥቅ ትግል ጀምረው ከመታገል ፈንታ እነሱ በንቃት ሻዕቢያ እንዳይሞት ለማዳን በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ለሻዕቢያ በመስጠት ቀበሮ ጉድጓድ ገብተው የነ ኢሳያስ ቂጥ ሲጠብቁ የተሰዉ ወገኖች በመቃወም አለመታገላቸው የህ.ወ.ሓ.ት ታጋይና በአጠቃላ ይ የኢትዮጵያ ህዝብ ሙሁራኖች የዉጭ ሃገር መንግስታትና ግለሰቦች የኢርትራ ሪፈረንዶም ሰከን ብላቹሁ ተመልከቱት ብለው አስተያየት ሲሰጡ እነ መለስ ለትግራይ ህዝብና ታጋይ ሲያስሩት ሲያንገላቱት በትግል የመጣ ነው የኢርትራ ነፃነት ለጠባብና ትምክህት ኃይሎች አሳልፈው የሰጡ ከዳተኞች ብለው ሲያስሩዋቸው ና ሲሰውሩዋቸው ለዉጭ መንግስታትና ዲፕሎማቶች መለስ በመቀሌ ማዘጋጃ ቤት ቆሞው የዉስጥ ጠባቦች ተወላዋይ ኃይሎችና የኢሰፓ ትርፍራፊ የኢ.ህ.አ.ፓ መሳፍንቶች ኢምፕርያሊስቶች 30 ዓመት እንደገና ከኢርትራ ሊያዋጉን የኢርትራ ጉዳይ የመገንጠልና ኢትዮጵያ የባህር በር የሌላት ትቀራለች: ስለሆነ የነበራቹሁ አቋም

ቀይሩ እያሉ ቀውስ ይፈጥራሉ: እኛ ግን እንዲያው ኢትዮጵያ ዙርያ መለስ ትዘጋ ባህር በር ለማግኘት ብለን በኢርትራ የነበረን የነፃነት አቋም አይቀየርም: ኢርትራ ነፃነት አይገባትም ብሎ የሚመጣ ካለ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መቃብር ብቻ የሚፈፀም ይሆናል አሉ መለስ: ይህ የተናገሩት ከ2000 በላይ ኮንፍረንሰኛ 31 የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ 4 የኢ.ህ.አ.ዴ.ግን ማ/ኮሚቴና ካድሬዎች በተገኙበት የተነገረው ነው: ከዛ በኋላ በአስር ሺ የሚቆጠር የህ.ወ.ሓ.ት ታጋይ ታሰረ: የትግራይ የዕድሜ ባለፀጋዎች ወጣቶች ታሰሩ ተቀጡ ተሰወሩ: እዚህ ላይ ከህ.ወ.ሓ.ት የተገነጠሉ ማ/ኮሚቴ በመቃወም ፈንታ መለስ ለፈፀሙት ወንጀል በመሳተፍ ዋና መቺ ኃይል ነበሩ: እዚህ ሁሉ ሰው ሊረዳው የሚገባው አንጃዎች ቀድመው ለነ መለስ አስተሳሰብና ፖሊሲ ስለተቃወሙና ስለአላጋለጡ ከመለስና ጓዶቹ እኩል ወንጀለኞ ች ናቸው አልልም ኋላ የወሰዱት አቋም ችላብለው ያለፉት ካሳ ሆኖ ነው የሚረዳኝ: በተለይ ደግሞ አሁንም ከተቃውሞ ጎራ ተሰልፈው የሚታገሉ ያሉ ገብሩ አስራት፣ አውዓሎም ወሉ፣ አረጋሽ አዳነ፣ የዉብማር አስፋው፣ ስየ አብረሃ ትልቅ ክብርና ካርድ ይገባቸዋል: ሌሎች የመለስን አቋም በመቃወም የወጡ ግለሰቦችም ከመለስ አብረው 26 ዓመት የፈፀሙት ስህተት ይብቃ ብለው መተዋቸው ምንም እንኳ እንደነ ገብሩ አስራት መታገል ይገባቸው ቢኖርም ከሁሉም ነገር ታቅበው ዝምታ መርጠው በግል ሥራቸው ሰርተው መኖራቸው አንድ እርምጃ ወደ ፊት አድርጌ ነው የምመለከተው: በሌላ በኩል መለስን ተቃውመው ከወጡት እንደገና ለሆዳቸው ሲሉ ወደ መለስ ተንበርክከው ያለፈዉን የፈፀሙት ሃገራዊ ክህደት በመድገም የሻዕቢያን ሎሌ የነበሩና ያሉ የነ አባይ ፀሃዬ ቡድን መጥፎ ቀን ዉለዋል እላለሁ::

## **"በገፅ 20 አዲስ መስመር 2 መስመር 14"**

"በመሆኑም መለስ አንደአንድ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ብቁ መሪ አዳዲስ ሃሳቦችን አምጥቶ በመጫን ሳይሆን በዴሞክራሲያዊ አኳኋን ተከራክሮ፣ አሳምኖ፣ የሁሉም ሃሳብ እንዲሆን በማድረግ የተጓዘ ጥልቅ ዴሞክራሲነት የነበረው ስብእና ነው: ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ያለ ማቋረጥ እያደገና እየተለወጠ እንዲሄድ ያደረገው የመለስ አመራር ተራማጅ ብቻ ሳይሆን ጥልቅ ዴሞክራሲያዊነት የነበረውም ነው የምንለው ከዚህ በመነሳት ነው::"

እኔ እስከ አሁን መለስ እንደማውቃቸው የዉጭ እውቀት እንደነ መካቬሊ፣ ማኦ፣ እንቨርሆጃ በሃገር ዉስጥም የአንዳንድ ሙሁራኖች ሃሳብ በመጥለፍ በቃላት ቃኝቶ ከማቅረብ ዉጭ መለስ ተራማጅ ነበር (የተራማጅ ፍልስፍና ነበረው) አልልም በኢትዮጵያ ፍትህ መልካም አስተዳደር የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሃሳብን በነፃ የመግለፅ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፣ የሕግ የበላይነት፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መኖር፣ ነፃ የህዝብ ተሳትፎ፣ ነፃና ፍይሃዊ ምርጫ፣ መብቶች አልተከበሩ: ታድያ የአዲስ ራዕይ መፅሐፍ ፀሐፊዎች የመለስ ተራማጅነት የት ላይ ነው: የመለስ ዴሞክራሲ ለ80 ሚልዮን ህዝብ ሞዳ እንግሊዝ ነው::

መለስ ሃሳቦቹን አመንጭቶ በማጨን ሳይሆን በማሳመን በመከራከር ነበር የሚመራው ብላቹሁ አፋቹሁ ሞልታቹሁ እየተናገራቹሁ ነው: በኔ እምነት ከመለስ 19 ዓመት በቅርብ አብሬ ንሬያለሁ: እንዳላቹሁ መለስ ተናጋሪ ተከራካሪ ናቸው ነገር ግን አብዛኛው ጊዜ የሚሰሩት በሃገራችን ህዝብ ብዙ ችግሮች መፍታት የሚገባቸው እያሉ እጅግ ብዙ የህዝብ ረሮዎች እያሉ ለነዛ ብዙ ችግሮች መሰረታዊ መፍትሄ እንደማምጣት ለሁሉም ነገር በመሸፈን ለሃገር ዉስጥ ወገኖች ለዉጭ መንግስታት ሳቢ የሆኑ (ሃይላይት) በአየር ላይ የሚያንሳፍፍ አዲስ ነገር የፈጠሩ መስለው እነጋጋሪ አጀንዳ ያመጣሉ: ለአብነት ያህል ፓርላማ ሚኒስቴሮች ምክር ቤት ያልወሰኑት የሶማል አልሸባብ ኢትዮጵያ ሊወር ስለተዘጋጀ ወደ ሶማል ሃገር ገብተን እንመታለን:

ሻዕቢ.ያ በሁሉ አቅጣጫ ሊወረን ማለት ነው እኛም ማስታገሻ እርምጃ እንወስዳለን: ቆየት ብሎ ሻዕቢ.ያን ከእንግዲህ ወድ.ያ አንሸከመዉ.ም እናስወግዳለን: የአባይ ግድብ እንገድባለን 2 ሺ ኪሎሜትር ባቡር ሐዲድ እንሰራለን 15 የሱካር ፋብሪካዎች እንገነባለን: ህዝባችን በዓመት 3 ጊዜ በልቶ ጠግቦ ሊ.ያድር ነው: ሙስና ከስሩ ንነቅላለን፣ አዲስ አበባ ባግዳድ እነደርጋለን ወ.ዘ.ተ የሚሉ አበይት ነጥቦች በማንሳት የ80 ሚልዮን ህዝብ ቀልብ (አቅጣጫ) የሚስቡ ናቸው::

እዚህ ላይ ማንም ኢ.ትዮጵያዊ እብድ ካልሆነ በስተቀር አሸባሪ እንዲወረው ሻዕቢ.ያ ሲወረው ሻዕቢ.ያን እናስወግዳለን ሲሉ አብሮ የሚሰለፍ እንጂ የሚቃወም የለም: የአባይ ግድብ 2ሺ ኪሎሜትር ባቡር ሐዲድ የሱካር ፋብሪካዎች መስራት 3ጊዜ በቀን መብላት ህዝብ ሁሉ ይፈልጋል: ነገር ግን እነዚህ አነጋገሮች የመለስ ማታለ.ያ ስልቶች ናቸው: ምክኒ.ያቱም እነዚህ የመለስ ህዝብን የሚ.ያንሳፍፉ ዕቅዶች ግባቸዉ.ም የሚመቱ ከሆኑ ህዝቡ ቤትና ሆዱ .ያሉ ችግሮች መፍትሄ አግኝተው ህዝቡም በሙሉ ልቡ ተሳትፎባቸው መሰራት ነበረባቸው: አለበለዚ.ያ ፈርጣማ ጡንቻ .ያለው ወጣት ገበሬ ወጣት ሙሁር ሥራ አጥቶ በሚልዮን የሚቆጠር ጠረፍና ወንዝ ባህር ተሻግሮ በማ.ያውቀው በረሃ እየሞተ እየታረደ ጉበቱና ኩላሊቱ ሌላው የአካላቱ ብልት ለዓረቦች ተሸጦ የቀረው ስጋ የአሞራና የቀበሮ ቀለብ እየሆነ 3ጊዜ በልቶ ጠገቦ የሚባለው እንዴት አድርጎ ይህ ማንም ኢ.ትዮጵያዊ አይቀበለዉ.ም::

መለስ ተራማጅ ብቻ ሳይሆን ጥልቅ ዴሞክራሲ.ያዊነትም ነበረ: ምን ማለት ነው ተራማጅ ጥልቅ ዴሞክራሲ ፈላስፋ ነበረ አላቹሁ: በየት አድርጎ በየትኛው መስፈርት: አሁንኮ የኢ.ትዮጵያ ህዝብ ከህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ብዙሃን መገናኛ ዉ.ጭ አይሰማም: የኢ.ትዮጵ.ያ ወህን ቤቶች በጋዜጠኞችና በሰላማዊ ፖለቲካ ትግል የሚ.ያራምዱ የፓርቲ መሪዎች ሞልተዋል: የመንግስት የፀጥታ ፍትህ ደህንነት አካላት ለህ.ወ.ሓ.ት ብቻ የሚ.ያገለግሉበት ሁኔታ አለ:

የሃገራችን መሪዎች ልጆችና ዘርማንዘራቸው በመንግስት ባጀት ያለ አንዳች የትምህርት ዉድድር በቻይና፣ በአመሪካ፣ በአውሮፓ፣ በደቡብ ኮርያ ከፍተኛ ትምህርት የሚማሩበት ፍትሃዊ የሆነ የሃገር ሃብት ክፍፍል በሌለበት የሃገራች ሃብት በህ.ወ.ሓ.ትና ግብረአበሮቹ ባለቤትነት የተያዘበት ባለበት ህዝብ መጠለያ የማግኘት መብት የታገደበት ሕብረተሰብ በሙሉ በግድ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባል ካልሆነ የማይኖርበት ሃገር ሆና እያለች፣ የትምህርት ነፃነት በሌለበት የትምህርት ማእከላት ሁሉ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባላት መመልመያና ማደራጃ በሆነበት ዘመን፣ የሴፍት ኔት የድርቅ ወይም የበረዶ ወይም የቃጠሎ እርዳታ ለህ.ወ.ሓ.ት አባልነትና ደጋፊዎች የሚሰጥበት፣ ከዛ ዉጭ 2ኛ ዜጋ የሆነበት ሁኔታ እያለ: መለስ እንዴት ብሎ ጥልቅ ዴሞክራሲያዊና ተራማጅ ሊባል ይችላል: ለመሆኑ አዲስ ራዕዮች ጥልቅ ዴሞክራሲያዊ ነበር ስትሉን ምን ማለት ነው ህዝብኮ ለናንተም ለመለስም መስታወት ነው: ከላይ የተዘረዘሩ ፀረ ዴሞክራሲ ነጥቦች ተጨባጥና ያሉ ናቸው::

በ1997 ዓ.ም ድህረ ምርጫ በአዲስ አበባ የጉዳና ነውጠኞች ተብለው ከ200 በላይ ሰዎች የተገደሉ በየ ክልሉ ምክኒያት በመፍጠር የተገረፉ የታሰሩ የተገደሉ በጋምቤላ የተጨፈጨፉ ወገኖች በ2002 ዓ.ም የፓርላማ ተወዳዳሪ የነበረው የዓረና መድረክ ፓርቲ አባል አረጋዊ ገብረሃንስ ባልታወቁ ባንዶች በጩቤ ተቆራርጦ የተገደለው: በሱማል መንደሮች ሲቃጠሉ: በጂማ በየጊዜው ሲገደሉና ሲታሰሩ በዓፋር በየጊዜው የሚገደሉ: በደቡብ ህዝቦች የደረሰበት ዓፈና ምክኒያት ራሱን በበንዚን አቃጥሎ የሞተው አስተማሪ: የመለስን ተራማጅነትና ጥልቅ ዴሞክራሲያዊነት ሳይሆን የሚያሳየው የመለስ ፀረ ዴሞክራሲያዊነትና አንባገነን ዲክቴተር ነው የሚያመለክተን: ስለዚህ አዲስ ራዕይ ፀሃፊዎች አሁንም ህዝብ ምን ይለናል ብላቹሁ ብታስቡ መልካም ነው::

የሃገራችን ሃብት በመንግስት ሌቦችና ጥቂት ግብረአበሮቻቸው ከመለስ ቤት ጀምሮ በሙስና እየተወረረች ህዝቦቿ ሲበታተኑ የመለስ ጥልቅ ዴሞክራስያዊነት ሳይሆን ፀረ ዴሞክራሲ መሆናቸው መረጋገጫ ነው::

መለስ 21 ዓመት የስልጣን ዘመናቸው በመድረኮች ሁሉ አዳዲስ የስድብ ፋብሪካ እየፈበረኩ ነው ነውጠኞች፣ ጠባቦች፣ ትምክህተኞች፣ አሸባሪዎች፣ ጥግተኞች፣ ቁሻሻዎች፣ ገረድዎች፣ ኪራይ ሰብሳቢዎች፣ ነፍጠኞች አረ ስንት ቁሻሻ ስድቦች ሲሳደቡ አይተናል: ታድያ እነዚህ ቁሻሻ ስድቦች ከአንድ ተራማጅና ጥልቅ ዴሞክራሲያዊነት አለኝ የሚል መሪ ሊነገር ይገባል በበኩሌ ትክክል አይደለም ነው የምለው: መለስ እጅጉን አንባገነንና ዲክቴተር መሆናቸውነው የሚያሳየን::

## ክፍል 9

## "መለስና ለዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግስት የተካሄደው ትግል ገፅ 20 8ኛ ዓመት ቅፅ 4 ልዩ እትም"

አሁን ላለው የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ከመራራ ትግል ተፋልመው ታግለው ያመጡት በሚልዮን የሚቆጠሩ የሃገራችን ህዝቦች እያሉ በሚልዮን የሚቆጠሩ ወጣት ታጋዮች ተሰውተው ሰዉነታቸው ተቆራርጠው ያመጡትን ሕገ መንግስት ለመለስ ሚጥጦ መስጠት ፍትሃዊ አይደለም: ይቅርና መለስ አንድ ሰው ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግም ለ 400ሺ ታጋይና ከግማሽ ሚልዮን በላይ የታጠቀ ምልሽያና የገጠር ካድሬ አሰልፎ ብዙ መስዋእት ተከፍሎ በቢልዮን የሚቆጠር ሃብት አውድሞ ደርግን ያስወገደ እያለ ያረቀቀውና ያፀደቀው ሕገ መንግስ ት ነው ተብሎ የሚሰጥ አይደለም: አዲስ ራዕዮች ግን አሁን ያለው ሕገ መንግስት መለስ ብቻቸው ታግለው

አምጥተው የሰጡን ሕገ መንግስት ነው የምትሉን ያላቹሁ: ይህማ ትክክል አይደለም የህዝብን ድል መስረቅ ነው::

የተከበራቹሁ አንባብያን በኔ እምነት የኢትዮጵያ ህዝብም የሚያውቀ ው ለዘውዳዊ ስርዓትና የደርግ ስርዓት ለመጣል ህ.ወ.ሓ.ት የያዘው ቡድን ብቻ አልነበረም: መጀመርያ ትግሉ የተፋፋመው በነበሩ ጥቂት ሙሁራኖች መሪነት ተጀምሮ ወደ ገበሬው ወዛደር የመንግስት ሰራተኛ ወደ ታችኛው ሙሁሩ ተማሪ ተስፋፍቶ ህዝባዊ ማዕበል ተቀሰቀሰ ከዛ ህዝባዊ መዕበል ብዙ የተለያዩ ፖለቲካዊ አቋም ታጥቀው የተነሱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተፈልፍለው አብዛኛቹ በረሃ ወጥተው በትጥቅ ትግል ለደርግ ሲፋለሙ አንዳንዳቸዉም በስዉር ሆኖው በመታገል ደርግን በማዳከም ትልቅ አስተዋፅኦ ነበራቸው: ከነሱ ዉስጥ ለመጥቀስ ኢ.ህ.አ.ፓ፣ ኢ.ድ.ዩ፣ ኦነግ፣ የኦጋዴን ነፃነት ግንባር፣ የዓፋር ዓሊሚራሕ፣ የጋምቤላ፣ የሜኤሶን፣ የኢርትራ ጀብሃ፣ የኢርትራ ሻዕቢያና ሌሎች በደቡብ ህዝቦች የነበሩ ህ.ወ.ሓ.ት፣ ግገሓት የነበሩ: እነዚህ ፓርቲዎች በመጀመርያ ጊዜ በያሉበት ለደርግ በመክበብ በዉስጥም በደጅም አዳክመዋል: ይሁን እንጂ እነዚህ ፓርቲዎች እርስ በራሳቸው ተስማምተው ለዋና ጠላት አሸንፈው ስርዓት እንደመቀየር እርስ በራሳቸው በመጫረስ ነፍጥ አንስተው ተፋጁ: ከነዛ ነፍጥ አንስተው ያለኔ ሌላ አታምልኩ የሚሉ ነበሩ እንደ ህ.ወ.ሓ.ት በሰሜን ኢትዮጵያ የነበሩ ፀረደርግ ኃይሎች ሲያጠፉ ደርግም በአንድ በኩል ህ.ወ.ሓ.ት ለሚመታቸው የነበረ በኋላ በመምታት በሌላ በኩል: በደቡብ በምስራቅ በምዕራብ ለነበሩ ታጋዮች አደከማቸው ለአንዳንድም አከሰማቸው: ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ለራሳቸው እየተዳከሙ ለደርግም አዳክመዋል: በተለይ ደግሞ በደርግ ቢሮክራሲ ሰርገው በመግባት ብዙ አዳክመዋል: ለእግረ መንገዳቸው ለህ.ወ.ሓ.ትም አግዘዋል: ስለሆነ አሁን ያለው ሕገ መንግስት የመለስ ብቻቸው ሳይሆን ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግም ሳይሆን የመላው

የኢትዮጵያ ህዝቦች የትግል ዉጤት ነው: ሓቁ ይህ እያለ ህ.ወ.ሓ.ት እስከ አሁን ያላመነው ያለው 60ና 70 ሚልዮን የኢትዮጵያ ህዝብ የትግል ዉጤት በመካድ ሳይቀበል ቆይቶ አሁን ደግሞ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ታጋይና የትግራይ ህዝብ መስዋእትም ክዶ ሁሉም ነገር ለመለስ ሸለማቸው ቁጭ አለ: ይህ ተግባር ደግሞ ለአዲስ ራዕዮችና ለህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች እጅጉን የወረዳቹሁ መሆናቹሁ አንድ ማረጋገጫ ነው::

"ገፅ 21 ቅፅ4 ልዩ እትም 2005 ዓ.ም: በዚህ አኳኋን የፀደቀው ያፀደቀው ሕገመንግስት በጥልቅ ዴሞክራሲያዊ ፅንሰ ሃሳቦችና መርሆዎች ላይ የተዋቀረ ነው: የሃገራችን ሕገመንግስት ከዴሞክራሲ ያዊነት አኳያ በዘመናችን ካሉ ከአብ ዞኞቹ ሕገመንግስቶች በእጅጉ የላቀ ነው: ብዙዎቹ የበለፀጉ ሃገሮች ሕገመንግስት ጨምሮ ብዙ የዓለማችን ሕገመንግስታት ህዝብን የሉኣላዊ ስልጣን ባለቤት ያደረጉ አይደሉም ይላሉ::"

ጂብ በማያውቁት ሃገር ሂዶ አኅዛ አንጥፉልኝ አለ እንደሚባለው አዲስ ራዕዮች ይህ ፅሑፍ የት ሆኖው ለየትኛው ህዝብ እንደፃፉት የሚረዳቸው ያለ አይመስለኝም: የኢትዮጵያ ህዝብ በአሁኑ ጊዜ በመረጃ አሰባሰብ ወደ ፊት መጥቆ እንደሂደ አይረዳቸዉም ያለ: አሁን ያለ የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት እርግጥ ከደርግና ከጃንሆይ ከነበሩት ሕገ መንግስቶች የተሻለ መሆኑ እኔም እስማማበታለሁ: ሆኖም ግን ከዘመናችን ካሉት በዴሞክራሲያዊነት የላቀ ነው ሲሉን ማንን ነው የሚያታልሉ ከአመሪካ፣ ከጀርመን፣ ከእንግሊዝ ወ.ዘ.ተ ይበልጣል ነው የሚሉን ያሉ: ሌላ ቀርቶ ከነ ጋና ሃገር ሕገ መንግስት ም አይሻልም: እርግጥ ሕገ መንግስቱን በነ አቶ ክፍሌ ወዳጆ ሙሁራዊ ጥረት የሆነ መለስ ህ.ወ.ሓ.ት ተፅኖ ሳይበግረው የተሻለ ሕግ መንግስት እንደፀደቀ ሁሉ ሰው የሚያውቀው ነው: እኔ የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ከዓለማችን የበለጠ እንዲሆን እመኛለሁ ለወደፊት ከዓለማችን ካሉት ዴሞክራቲክ ሃገሮች ባይበልጥም

የመለስን ስርዓት በሰላማዊ መንገድ አስወግዶ አሁን ካለው ሕገ መንግስት የተሻለ ሕገ መንግስት እንደሚፀድቅ እምነቴ ነው::

"በዓለማችን ያሉ ሕገ መንግስታት ህዝብን የልእላዊ ስልጣን ባለቤትነት ያረጋገጡ አይደሉም ይላሉ::"

የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ሆን ብሎ ኢርትራን ገንጥሎ የሃገራችን ሉአላዊነት አሳልፎ የሰጠ: የሃገራችን ህዝቦች የፀጥታ የደህንነት የኢኮኖሚ ዋስትና የሚያሳጣ የባህር በር ባለቤትነት ያሳጣ እያለ: በዓለማችን ያሉ ሕገ መንግስታት የህዝብ ሉአላዊ ስልጣን ባለቤትነት አያረጋግጡም ብለው አፋቸው ሞልተው ሲናገሩ በጣም አሳፋሪ ነው: ሕገ መንግስቱን በየ ቀበሌው ወረዳ ህዝብ ተወያይቶበት ብላቹዋል: ይህ ጉዳይ ሲሰራ እኛም እኮ አለነበት ይሰራ የነበረ የመለስና ጓዶቹ ጠባብ አቋሞች ሳይሸራረፍ ተግባራዊ መሆን አለበት እየተባለ: ለዛ አቋም የሚቃወም እንደጠላት የሚታይበት ሁኔታ ነው የነበረ: ሕጉ ሲረቀቀም'ኮ ለአቶ ክፍለ ወዳጆ በህ.ወ.ሓ.ት ካድሬዎችና እንደ ዳዊት ዩሃንስ ያሉ የመለስ ተላላኪዎች ተከበው ነው ያረቀቁት::

እኔ አስታዉሳለሁ የሕግ መንግስት አፅዳቂ ሸንጎ ከአንድ መቶሺ ህዝብ አንድ ሰው ሲወከል ቢያንስ 75% ተወካይ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሆን አለበት የሚል ግድ ይል ነበር: ምክኒያቱም ምልአተ ጉባኤ የበላይነት መለስና ጓዶቹ ካላገኙ ሕገ መንግስቱ ህ.ወ.ሓ.ት በሚፈልገው መንገድ ሊፀድቅ አይችልም: እዚህ ከተሸነፍን ተመልሰን በረሃ መግባታችን ነው ተብሎ ከ 4ሺ በላይ የህ.ወ.ሓ.ት ከፍተኛ ካድሬዎች በመቀሌ በአዲስ አበባ በስብሰባ ተነግረዋል: በመላው የኢትዮጵያ ክልሎች የነበሩ የህ.ወ.ሓ.ት አባላትም ቅስቀሳ ተደርገዋል: በዛን ጊዜ ኦሆዴድ፣ ደቡብ ህዝቦች፣ ዓፋር፣ ሱማል ለስሙ እንጂ ትርጉም ያላቸው ሰዎች አልነበሩም: በአዴን ለስሙ በአመራር ደረጃ ነበሩ እንደ ስር መሰረት አልነበራቸዉም: እርግጥ ከሱማል እንደ ዶ/ር ዓብደልመጂድ ሑሴን ያሉበት በጣት የሚቆጠሩ ሙሁራኖች ከሱማል ከደቡብ ከኦሮሞ

ከአማራም ነበሩ: በማፅደቁ ግን ብዙ ቦታ የሚሰጣቸው ሰዎች አልነበሩም: መለስ ግን ብልሃተኛ ስለነበሩ በመድረክ እያወጡ እንደሽፋን ይጠቀሙባቸው ነበሩ: በወቅቱ ለነበሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሚደረጉ ክርክሮች ዕድል አለመስጠት: ስማቸው በማጥፋት ከህዝብ ለማግለል መለስና ህ.ወ.ሓ.ት ሌት ተቀን ተንቀሳቅሰዋል::

ሌላ ቀርቶ ሕገ መንግስትን ለማፀደቅ ሁለት ወር ሙሉ በአራት ኪሎ አዳራሽ ክርክር ሲካሄድ መለስና ጓዶቹ ቀን በአዳራሽ ሲከራከሩ ዉለው ለሊት ደግሞ መለስ ከካድሬዎች ሆኖ ቀን በተቀዋሚዎች ሲፈልቁ የዋሉ ጠቃሚ ሃሳቦች እንዴት እናፍርሰው በድምፅስ እንዴት እናሸንፍ: ከህ.ወ.ሓ.ት አባልነት ዉጭ ያሉ እንዴት ወደኛ ድምፅ እናሰልፋቸው በማለት የመለስ ቡድን እያንዳንዱ እንዲሰብክ ተደርጎ ነበር: በዛን ጊዜ ብዙ መቶ ሚልዮን ገንዘብ ወጪ ሁነዋል: ስለዚህ መለስ ከሳቸው አስተሳሰብ ዉጭ ሕገ መንግስት እንዳይፀድቅ ትልቅ ስጋት ስለነበራቸው በተለይ ደግሞ የኢርትራ ሪፈረንዶም ነፃነት በሚመለከት ስጋት ነበራቸው: ከ1967 እስከ 1987 ዓ.ም ለ 21 ዓመት ኢርትራ ነፃ ሉአላዊት ሃገር ናት ብለው ሰጥቶዋቸው የቆዩት በዛ የኢትዮጵያውያን ሕገ መንግስት ማፅደቅ ለማንም ያልተፈቀደ ኢሳያስና አጃቢዎቹ መለስ ኢርትራ ለመገንጠል ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ሲከራከሩ የኢሳያስ ሎሌነታቸው ሲያረጋግጡ ኢሳያስ ፈገግ ይል ነበር: ስለሆነ ሕገ መንግስቱ ኢርትራ ለመገንጠል መለስ የታገሉበት የኢርትራ ሉአላዊ ባለቤትነት ያረጋገጠ ነበር::

"ገፅ 23 አዲስ መስመር 2: አሁን አሁን በዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት ሽፋን ከለሽና ፈራጅ ሲሆኑ የምመለከታቸው አውሮፓውያንና አመሪካውያን ከዚህ የመለስ ዴሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ ግንባታ አካሄድ በጣም በተለየ አኳኋን ዛሬ የሚገኝበት ደረጃ ላይ የደረሱት ከስንት መንፋቆቅ በኋላ እንደ ሆነ ታሪካቸው ያጠና ሁሉ የሚገነዘበው ነው: ዛሬ በዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት ሲመፃደቁ የምናያቸው

ትናንትና ከትናንት ወድያ ብቻ ሳይሆን ዛሬም ጭምር እኛን አፍሪካውያን ከእንሰሳት ባልተለየ ሁኔታ ሲያንገላቱን የምንመለከታ ቸው ዴሞክራሲን ከሃብታሞች ከዚያ በስንት አስርት ዓመታት በኋላ ለጥቂሮች ይሉናል::"

መለስ የዓለማችን የዴሞክራሲ የሰብአዊ መብት ጳጳስ አድርጋቹሁ ከምትነግሩን: የመለስ ፍልስፍና የትኛው ሕገ መንግስት ነው: የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት እኮ ከሌሎች ሃገሮች ቅጅ የሆነ ነው: ሌላ ቀርቶ የኢትዮጵያ ፍታቢሄር ሕግ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በሙሉ ከእንግሊዝ ፈረንሳይና አመሪካ ኮፒ የሆነ ነው: ሌላ ቀርቶ የኢትዮጵ ያ የንግድ ሕግም በቀጥታ በዉጭ ተተርጉሞ የሚሰራበት ያለ ነው: ታድያ እነ አመሪካ አውሮፓ መንግስታት የትኛው የመለስ ሕግ ነው የከለሱት: ሌላ ቀርቶ መለስ ራሳቸው ሲነግሩን የኢትዮጵያ የምርጫ ስነ ምግባር ሕግ (ከድኦፍ ኮንዳክት) በዓለም ደረጃ የተፈተነ የስዊድን የምርጫ ሕግ ነውያመጣነው ብለውናል::

እኔ የማውቃቸው መለስ ከሆነ ከ1972 ዓ.ም ጀምረው እስከ ህልፈተ ሂወታቸው የህ.ወ.ሓ.ት መስመር ነው ትክክል: ዓለም በሁለት ኃይሎች በመከፋፈል ምዕራብ አውሮፓ፣ አመሪካ፣ ካናዳ፣ አሱስትራልያ ወ.ዘ.ተ በኢምፐርያሊዝም በፋሽዝም ጎራ ሲያሰልፍ በሌላ በኩል የማኦ፣ የቻይና፣ የቲቶ ይጎዝላቪያ፣ የኩርሽቾብና በርዥነብ ጎርባቾቭ የራሻ ክላሸን በማለት ከአንድ ወደ አንድ እየተገላበጡ እንደመጡ: በዚህ ዓለማችን ያለ ህ.ወ.ሓ.ት የጠራ ኮሞኒስት መስመር የለም ብለው ነበር: ቆየት ብለው አዲስ አበባ ሊገቡ ወራት ሲቀራቸው ያ ወዳጃቸው ስታሊንም ፋሽስት ነበረ ወደ ማለት አዝማሚያ አምርተው ነበር: ለነገሩ አዲስ ራዕዮች በመግቢያ ፅሑፋቹሁ በለስን ከሄግል ጎን አሰልፋቹታል ምናልባትም የህወሓት ካድሬዎች እንደሚሉን መለስ አልሞተም መለስ ሙቶውም እየመሩን ነው ብለው ከጌታ እየሱስ ክርስቶስ ጎን እንዳሰለፉት ሁሉ እናንተም

መለስም ከእህዚአቢሄር ጎን እናሰልፈዋለን ብላቹሁ እንዳትሰብኩ እሰጋለሁ::

ዴሞክራሲ ለሃብታሞች ይሉናል: አሁንም እኔ የማውቃቸው መለስ ቀደም ሲል ፀረ ሃብታም፣ ባለሃብት፣ ሃብታም ገበሬ ከፍተኛ ሙሁራኖ ች ከፋሽዝም ኢምፐርልያሊዝም ጎን እኩል በሚሰለፉ በጠላትነት ፈርጀው በትግሉ ወቅትም እየመቱዋቸው እንደመጡ አውቃለሁ::

ከጦርነቱ በኋላ ደግሞ የአንባ ገነን የቻይና አስተሳሰብ በዉስጣቸው በመቅበር ካፒታልዝም ስርዓት ነው የምንከተል በማለት ወደ ምዕራብና አመሪካ ጎንበስ ቀና ጀመሩ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ያለመ: ሃገር ያለ ባለሃብት አታድግም የሃገር ዉስጥ ይሁን የዉጭ ሃገር ባለሃብት ከመጣልን ግማሽ መንገድ ሂደን እንቀበላለን አሉ: ግን ይህ ዉሸት ነበር: የነበራቸዉን የኃይሎች አሰላለፍ የሙሁር ኃይልም ለማስጠጋት ፍቃደኛ አልሆኑም: የሚያስጠጉት ባለሃብትም በዘመድ አዝማድ ከባለስልጣናት የተጠላለፈ ባለሃብቶች በሙስና የተሳሰሩ ሃብታሞች ብቻ ሆነ: በተረፈ ግን የመለስ ባለሃብቶች፣ የትእምት፣ ጥረት፣ ድንሾ ወ.ዘ.ተ የፓርቲ ሃብታሞች በቻይና ቅጅ የተደራጁ በመከላከያ ስር ያሉ 130 ኩባኒያዎች ሌሎች የመንግስት ኮርፖረሽኖ ች ናቸው: አሁንም መለስ የጀመሩት አሁን ያሉ የመለስ ለጋሲ (ዉርስ) የሚከተሉ የሚያራምዱት ፖሊሲ ነው::

"ገፅ 23 አዲስ መስመር 2 መስመር 15: ዛሬም ሲያሻቸው በቆዳ ቀለም እየመረጡ የሰው ልጆችን ከሚለዩ ነገር ግን በዴሞክራሲ ስም ከሚምሉ ከሚገዘቱ ምዕራባውያን በፍፁም በተለየ ሰብአዊ መሰረት ላይ የተገነባው የመለስ ዴሞክራሲ ፍፁም ሰብአዊና ሲቪል ነው: እናም መለስ ከምንም ነገር በፊት ሰብአዊና ዴሞክራሲ ነው ስንል በዚህ ረገድ ከማንም ጋር ቀርበን ለመከራከር ሆነ ለመርታት ድፍረታችን በመግለፅም ጭምር ነው::"

ራዕዮች ለመሆኑ የዴሞክራሲ መስፈርቶች ምንድናቸው: አታውቁም እንዳልላቹሁ ከማወቅም አልፎ በአዲስ ራዕይ አድርጋቹሁ ከ80 ሚልዮን የኢትዮጵያ ገበሬው፣ ነጋዴው፣ ሙሁሩ፣ ሰራተኛው እየሸወዳ ቹሁ እያላቹሁ ግንኮ የዴሞክራሲ መስፈቶች ልንገራቹሁ፣ የተሟላ መልካም አስተዳደር ሁሉም ዐይነት ሰብአዊ መበቶች፣ የፕረስ ነፃነት፣ የመምረጥና የመመረጥ መብቶች፣ በሃገሩ በነፃ መንቀሳቀስ፣ መጠለያ፣ ዉሃ፣ ትምህርት፣ መበራት፣ በአጠቃላይ ለንሮው የሚያስፈልጉ ማግኘት መሪዎች የማውረድ ወደ ስልጣን የመውጣት መብት የሕግ እኩልነት ወ.ዘ.ተ ነው::

በሌላ በኩል የሕግ በላይነት የፀጥታ ኃይሎች፣ ፖሊስ፣ ደህንነት፣ አቃቢ ሕግ፣ ዳኞች፣ የሃገር መከላከያ ሰራዊት፣ የአንድ ፓርቲ አጃቢ መሆን የለበትም: ሕግ አርቃቂ፣ ሕግ ተርጓሚ፣ ሕግ አፅዳቂ ሁሉም እንዲዋቀሩ መድረግ ወ.ዘ.ተ ናቸው: እነዚህ የተዘረዘሩና ሌሎች በመለስ ዘመነ አገዛዝ አለነበሩም አሁንም የሉም: በነ አመሪካ አውሮፓ ግን አሉ በምታምኑት አምባ ገነን ቻይና የሉም ዓፈናው አጠናክረው ነው የሚሰሩበት::

መለስ ፍፁም ዴሞክራሲ ሲቪል እንደነበረ ተማምነን እንከራከርለት አለን እያላቹሁ ነው: አሁንም ደገሜ ሊዘረዝር አልችልም: ባለፉ ክፍሎች ተዘርዝረዋል: ጠቅለል አድርጌ ለመግለፅ በኔ እምነት መለስ ከመንግስቱ ከጃንሆይ የማይለዩ ሆነው ግን በአነጋገር ለመንግስታት ለህዝብ በማደናገር በማታለል ግን እጅጉን ከሁሉም የላቁ ሰው ነበሩ ጥር የምትል ዴሞክራሲ የላቸዉም: በሚልዮን የሚቆጠር የኢትዮጵያ ሙሁር ወጣት ሴት ወንድ የመለስ ህ.ወ.ሓ.ት ፀረዴሞክራሲ ተግባር ነው ወደ ስደት የዳረገው::

መለስ ያ በህዝብ የፀደቀ ሕገ መንግስት የምትሉ አያግዳቸውም መለስ ሊያጠቁት የሚፈልጉ በአንድ ለሊት ሕግ አርቅቀው የፈረዱ ፈርደው ጧት እሳቸው ያሉት ሁሉ ተቀብሎ የሚያፀድቅ ፓርላማ አላቸው አፅድቅ ሲሉት የሚያፀድቅ: አፍርሰው ሲሉት የሚያፈርስ አላቸው:

ለዚህ አብነት የሚሆን ብርቱካን ደሜቅሳ ለስየ አብረሃ በሕጋዊ መንገድ በዋስ ስትለቀው ወድያዉኑ በሙስና የተጠረጠረ የዋስ መብቱ እንዳይጠበቅ የሚል ሕግና አዋጅ አፀደቁ ተብሎ በ24 ሰዓት ሕግ አወጁ: ለተቃዋሚ ፓርቲ ማጥፊት (ማኅሳቆል ሲፈልጉ) ፀረ አሸባሪነት ሕግ አረቀቁ አፀደቁ: የምርጫ ስነ ምግባር አረቀቁ አሳወጁ: የተቃዋሚ ፓርቲዎች የመቀስቀሻ ፅሑፎች ተፈትሸው በሬድዮ በተለቪዥን እንዲሰራጩ ሕግ አወጡ: አረ ስንት ተብሎ የመለስ ጉድ ሊገለፅ: ስለዚህ መለስ ሰብአዊ መብት የማያከብሩ ሕገ መንግስት የሚንዱ አንባገነን ዲክቴተር ሰው ነበሩ::

"መለስ በፆታ በብሄር በዘርና በቀለም በሃይማኖት ልዩነት ላይ ያል ተመሰረተ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብት በማስከበር አኳያ እኔ ነኝ ያለ የዴሞክራሲ ጠበቃ የመለስ የዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት አከባበር በሁለትና ሶስት መቶ ዓመታት ተረት ሳይሸፈን ለማነፃፀር ዝግጁ እስከ ሆኑ ድረስ ደረታችንን ነፍተን ልንከራከርና ልንረታበት የምንችል አድርገን በመተማመንም ነው: መሪያችን ዴሞክራሲያዊ ብቻ ሳይሆን በጥልቅ ሰብአዊነት ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊነት የነበረው ነው የምትለው::"

መለስ ከጥንት ጀምረው በጠባብነት ጠበል ታጥበው እንደመጡ ታሪካቸው አይታቹሃል: የመለስ የክልል አወቃቀር ካለፉት ስርዓቶች በከፋ በቋንቋና በባህል የተደረገው የክልል አወቃቀር ቢሄር ከቢሄር የሚያጋጭ ዘረኝነትን እንዲስፋፋ ያደረገ የመለስ የመንግስት አወቃቀር የተሳሳተ አሰራር ነው: በዘመነ ጃንሆይና ደርግ እንኳን ማንም ኢትዮጵያዊ በፈለገው ክልል ሄዶ ይሰራል የተገለለ ስሜት አልነበረም የቋንቋ የምንስየ ልዩነት አልነበረም ትግራይ ኦሮሞ ሃገሩ ነው ኦሮሞ ዓፋር ሄዶ ሃገሩ ነው አማራ ኦሮሞ ጉራጌ ጋንቤላ ሃገሩ ነው: በዘመነ መለስ ግን ኦሮሞ ትግራይ ሄዶ ሊሰራ የምንሰራው በትግርኛ ቋንቋ ስለሆነ ሥራ የለም ትግራይ ኦሮሞ ከሄደም የሚያጋጥመው ተመሳሳይ ነው: ወይ ጉራጌ አማራ ወይም ትግራይ

ሂዶም ተመሳሳይ እጣ ነው የሚያጋጥመው: ስለዚህ የቢሄር ቢሄረሰብ አንድነት በዘመነ መለስ እየላላ ሄደ እንጂ አንድነት የለም: እንዲያው ዘረኝነት እየሰፋ ነው የመጣው የመለሰና ጓዶቻቸው ተገባር የትግራይ ተጠሊ ሆኖዋል አማራ ከጉራጌ ኦሮሞ ግጭቶች እየበዙ ይታያሉ: ሃይማኖት በሚመለከትም መንግስት በሁሉም ሃይማኖቶች እጁ እያስገባ በአሁኑ ጊዜ በሙስሊም ሕብረተሰብ ጣልቃ በመግባት ብዙ ችግር ፈጥሮ ይገኛል: በኦርቶዶክስም ጣልቃ በመግባት ቤተ ክርስቲያን በትልቅ ቀውስ አስገብቶዋል: በሌላ በኩል መለስ ጥልቅ ሰብአዊነትና ዴሞክራሲያዊነት የነበረው ነው ብላቹዋል: መቸም ለሁሉም ነገር ለአንድ ስርዓት መስታወቱ ህዝብ ነው: በኔ እምነት መለስ ጥልቅ ዴሞክራሲያዊነት የተላበሱ ሳይሆን የኖሩትስ ትንሽ የዴሞክራሲ ጫፍ እንኳ ነበራቸው ከተባሉ ሙተው እያሉም ለሽልማት መቅረብ አለባቸው: መለስ ግን የወጣላቸው ዲክቴተር ነበሩ::

መለስ በሰበአዊና ዴሞክራሲ አከባበር 300 ዓመት ፊት ተጉዞ ተረት ተረት ያደረገ የዴሞክራሲ ጀግና እያሉን ነው: በኔ እምነት የአዲስ ራዕይ አነጋገር ቢሆንልን ደሰታው አልችለዉም: ግን 300 ዓመት ወደ ፊት መጥቆ መሄድ ይቅርና እነዛ ጥሩ ዴሞክራሲ አላቸው ከሚባሉ ጅራት ወደ ኋላ 40ና 50 ዓመት ሃገራችን ብትቀመጥ ደሰታየ መጠን የለዉም: ስለዚህ አታጋንኑ::

አንድ ነገር ግን ልጠይቃቹሁ አመሪካ አሁን ደርሰዉበት ያሉ የዴሞክራሲ ደረጃ ከ 400 ዓመት በላይ ነው የፈጀባቸው: መለስ በ 21 ዓመት የ300 ዓመት እድሜ እድገት ሂደዋል ስትሉን የት ሆናቹሁ ነው: ህ.ወ.ሓ.ት በ17 ዓመት የትጥቅ ትግል ወቅት እርግጥ ብዙ ችግሮች ነበሩት በዉሸት ግን አይታማም ነበር: ጠቅለል ባለ መልኩ ግን መለስና ጓዶቹ ፍፁም የለየላቸውዲክቴተሮች ነበሩ::

## <u>ክፍል 10</u>

## መለስ ብዙሃንነትን በአግባቡ ያስተናገደ የእኩልነትን አራማጅ

"ገፅ 25 አዲስ መሰመር 2: ጓድ መለስ ብዙሃንነትን በተመለከተ እንከን የለሽ አቋምና ተገባር የነበረው ታላቅ ሃገራዊና ዓለማዊ ስብእና ነበር: በሰዎች መካከል በርካታ ልዩነቶች መኖራቸውን የተቀበለና የሚያከራክር ሰው ነበር: ከዚህም በመነሳት የሰው ልጆችን ብዙሃነት ከማይቀበሉ የሃገር ዉስጥና የዉጭ ኃይሎች ጋር በሃሳብና በተግባር ተፋልመዋል: በሃገር ዉስጥ ኢትዮጵያ ሃገራችን ብዙሃንነ ት ስላላት ይህንን በአግባቡ ስለማስተናገድ አስፈላጊነት መስበክ የጀመረው ከልጅነቱ በተለይም ከዩኒቨርሲቲ ቀናቶቹ ጀምሮ ቢሆን ብዙሃንነትን በአግባቡ የማስተናገድ አቋሙ በተደራጀና ተጨባጭ ለውጥ በሚያመጣ የፖለቲካ አቋም መልክ የተገለፀው ህ.ወ.ሓ.ትን በማደራጀት ለትግራይ ህዝብ መብት መከበር መታገል በጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነው---- ይላሉ አዲስ ራዕዮች::"

መለስ ከመጀመርያ ጀምሮው በሰዎች መካከል ልዩነት አይቀበሉም ነበር ዉሸት ነው: ለመረጃ ያህል በህ.ወ.ሓ.ት ዉስጥ በ1067 ዓ.ም በደደቢት የተፈጠረ ልዩነት: በ1967 ዓ.ም በዊዳኸ የነበረ ልዩነት: በ1968 ዓ.ም በበለሳ: በዛን ዓመት በዲማ ጉባኤ: ከ1969 እስከ 1970 ዓ.ም ሕንፍሽፍሽ (አንጃ) ህ.ወ.ሓ.ት ያናወጠ: በ1977 እስከ 1979 ዓ.ም ከነ አረጋዊ በርሀና ግደይ ዘርአፅዮን የነበረ ልዩነት: በ1982 ዓ.ም አባይ ፀሃዬን ለመፈንቀል የነበረ ልዩነት: በ1985 ዓ.ም 32ሺ ታጋዮችና በሚልዮን የሚቆጠር ህዝብ በኢርትራ ሪፈረንዶምና ሉኣላዊነት በተመለከተ የነበረ ልዩነት: በ1983 ዓ.ም በህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ የነበረ ልዩነት: እንዲሁም በ17 ዓመት የትጥቅ ትግል ጊዜ ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የነበረው ልዩነት: ከ1983 እስከ ህልፈተ ሂወታቸው በኢትዮጵያ በሰላም ከሚታገሉ ፖለቲካዊ ፓርቲዎች የነበረ ልዩነት መለስ አንድ ቀንም በሰላም ግርጭቶችን

ለመፍታት በተግባር ሳይቀር ፍፁም ነተሳሺነት አልነበራቸዉም: እነዚህ የጠቀኩዋቸው ልዩነቶች በሙሉ ለማለት ይቻላል በማሰር በመግደል: በጦርነት ስም በማጥፋት በማግለል ወይም ከሃገር ተሰዶ እንዲጠፋ በማድረግ የተፈቱ ናቸው: ስለዚህ መለስ ባለፉት 38 ዓመታት ጊዝያቸው በሰዎች መካከል የነበረ ግንኙነት ለማስተካከልና ለመቀራረብ መልካም ግንኙነት እንዲኖር የሚጥሩ የነበሩ ሳይሆን በሰዎች በህዝቦች መካከል መልካም ግንኙነት እርቅ ሰላም እንዳይኖር የሚያራርቁና ችግሮች የሚያባብሱ ሰው ነበሩ: መለስ ለአፍሪካም ለዓለም ሳይቀር በአህጉሮች ህዝቦች መልካም ግንኙነት ለማድረግ ስብእና የተላበሱ ብላቹሃል::

መለስ በሃገራቸው ዉስጥ ለሰዎች መልካም ግንኙነት ያልታገለ: በዉጭ የሚያደርጉት ልታይ ልታይ ባህሪያቸው መጥቀው እንዲታዩ ስለፈለጉ እንጂ: መለስ ለሰው ልጆች መልካም ግንኙነት የሚሰሩ ቢሆን ንሮ በሃገራቸው ዉስጥ በሰሩ መለካም ነበር::

መለስ እኔም እንደማውቃቸው በበረሃ ትግል ወቅት ካድሬ ያስተምሩ ነበሩበት ጊዜ ያካበቱት የንግግር ችሎታ ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላም በሃገርም በዉጭም ብዙ መድረኮች በማግኘታቸው የነበራቸዉም መድረክን የመቀጣጠር ልምድ ታዋቂነትን ፈጥሮላቸዋ ል: በትክክል የመናገር ችሎታቸው ይቅርና ሓቅነት ያላቸው ዉሸትም ቢኖር ሓቅ አድርገው የማሳመን ችሎታቸው እኔም አድናቂያቸው ነኝ: መለስ ሲናገሩ ለነገ አይሉም ዉጤት ተሰሚነት አገኝባታለሁ ካሉ ልክ እንደመካቪሊ ይጠቀሙበታል: መለስ የመካቪሊ መፅሐፎችም አንባቢ ነበሩ::

መለስ ብዙሃንነትን ማስተናገድ የጀመሩት ገና ከልጅነታቸው በዩኒቨርሲቲ ቀናቶች ጀምረው ነው ብለዋል: መለስ የብዙሃንነት እምነት ከዩኒቨርሲቲ ጀምረው እምነት ከነበራቸው በረሃ ደደቢት ከወጡ በወራት ዉስጥ የኢትዮጵያ መሰረት የሆነች ትግራይ ጠ/ግዛት ነፃ ሃገር ስለሆነች የምንታገለው ያለን ከቅኝ ገዢዎች አማራ ነፃ

ወጥተን ነፃ ሃገራዊት ትግራይ እንመሰርታለን ብለው ማኒፌስቶ ከፃፉት አንዱ መለስ ነበሩ ብየ አለሁ::

መለስና ጓዶቹ ነፃ ሃገራዊት ትግራይ ለመመስረት የሚል ዓላማ የማያዋጣ መሆኑ ከተረዱ በኋላም ብዙሁነትን አያምኑም ነበር: ብዙሃንነት የሚቀበሉ ቢሆን ንሮ ከግንባር፣ ከኢ.ድ.ዩ፣ ከኢ.ህ.አ.ፓ፣ ከኦነግ፣ ከዓፋር ነፃ አውጪ፣ ከሱማል ኦጋዴን ፓርቲዎች የነበረ ግንኙነት ለምን ጦርነት አስፈለገ: ብዙ ህዝብ አልቀዋል ንብረት ወድመዋል የብዙሃንነትን ግርጭት አፈታት የሚያምኑ ከነበሩ ከዚህ በላይ ችግር አልነበረም:ደርግን ፀረብዙሃንነት ነውብለው ሊታገሉ በረሃ የወጡ ገና በዩነቨርሲቲ እያሉ ብዙሃንነትን የሚያምኑ ከነበሩ ያ ፍላጎት ለምን አልተገበሩትም ኢትዮጵያ ሃገራችን መለስ በፈጠሩት ልዩነት አንድነት አደጋ ላይ ወድቀዋል:ብዙሃንነትን የሚያምኑ ቢኖሩ የኢርትራ ሪፍረንዶም ከ70 ሚልዮን ህዝብ ተወያይተው ለምን አልፈቱትም: ህ.ወ.ሓ.ት በ1993 ዓ.ም በሁለት ሲሰናጠቅ መድረክ ከፍተው በብዙሃን ድምፅ ለምን አልፈቱትን 21 ዓመታት የአገዛዝ ዘመናቸው በሙሉ በኢትዮጵያ ሃገራችን ብዙሃንነት ባለመረጋገጡ እስከ አሁን በግርጭቶች እየተናጠች ትገኛለች::

መለስ ደርግ ከተወገደ በኋላስ በሰዎች መካከል ያለው ልዩነት የአፈታት ስብእና ቢኖራቸው ንሮ ከ1983 ዓ.ም እስከ ህልፈተ ሂወታቸው ሕገ መንግስት በሚፈቅድላቸው በሰላም የተደራጁ እንዲሁም በመለስ እምነት አጥተው ነፍጥ አንስተው በረሃ የወጡ ፓርቲዎች ነበሩ አሉም: መለስ ካለፉት ገፆች እንደተገለፀው ካሉት የተቃዉሞ ኃይሎች ሰፊ መድረክ ከፍተው ተወያይተው ልዩነታቸው አጥብበው አብረው እንደመጋገር ብረት ካነሳ በብረት ልዩ ሃይል በደፈጣና ፀረደፈጣ ዉግያ እንዲጠፍ ተደረገዋል: በሰላም ለሚታገሉ የምርጫ ሃይሎችም ነፃ የፖለቲካ ሜዳ እንደመፍጠር ሕብረተሰብ የመማያውቃቸው ለመለስና ለህ.ወ.ሓ.ት የሚመቹ ግለሰቦች በመመልመል ፀረነዛ ከሕብረተሰብ ብሶት የፈለቁ ፓርቲዎች

በህ.ወ.ሓ.ት በመበስበስ በቂ ገንዘብ ቁሳቁስ በመመደብ ለሚቃወም ህዝብም በማስፈራራት በማሰር ለትክክልኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለሚደግፍ ከሁሉ ዜጎች ሊጠቀሙበት ከሚገባቸው ነገሮች በመንፈግ በማግለል አባሎቻቸው በማሰር በመግደል ሃገራቸው መርገጫ እስከ ሚያጡበት እንቅፋት ይፈጥራል: ታድያ አዲስ ራዕዮች የመለስ የብዙሃነትን ጠበቃ መሆን የቱ ነው::

እስከ አሁን በፅሑፍ ሁሉ ያልተገለፀ የመለስና የህ.ወ.ሓ.ት ስልት (ታክቲክ) ይህ ተግባር ህ.ወ.ሓ.ትና መለስ ከተፈጠሩበት ጊዜ በኢትዮጵያ ከነበሩትና ካሉት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሐቀኛ ዴሞክራሲያዊ ዉድድር ተደርጎ ተቃዋሚ ፓርቲ በምርጫ አሸንፎ ስልጣን ተረክቦ ሃገር ሊመራ መለስም ያሸነፈ ፓርቲ ሊመራቸው ፍቃደኛ ሆነው ይኖራሉ ተብሎ አይገመትም: ግን መለስና ጓዶቹ ከጥንት ጀምሮው የሚጠቀሙበት ስልት በመድረክ ካሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እርቅ የሚባል ነገር አይኖርም: ግን ባለን የብዙሃን መገናኛና በካድሬዎች ወደ ህዝብ በመግባት በፅሑፎች ሰላም ፈላጊዎች መስለን እንቀሳቀሰ: ሽማግለ በማድረግም ድርድር ማድረግ በድርድሩ ሊያግባባ የማይችል ሃሳብ በማቅረብ የዉግያ ሃይላችን ማዘጋጀት: ከነዛ ተቃዋሚዎችም ተቃዋሚዎቻቸው ማጠናከር: በተጨማሪ እነሱ የሚያደርጉዋቸው ትናንሽ ስህተቶች በማጉላት ከሕብረተሰብ እንዲ ነጠሉ ማድረግ ወ.ዘ.ተ የሚል አሰራር የመለስና ጓዶቹ ነበር: ይህ ተግባር ከኢ.ድ.ዩ፣ ከግንባር፣ ከኢ.ህ.አ.ፓ፣ ከጀብሃ፣ ከኦነግ የጀመረ እስከ የመለስ ህልፈት ነበር አሁንም አለ: ሌላ መለስና ጓዶቹ ተገደው ለድርድር ሲቀርቡም ቅድመ ሁኔታ በመፍጠር ተቃዋሚዎች እምቢ ብለዋል ብለው ስም በማጥፋት ይንቀሳቀሳሉ ከዛ በኋላ ነፍዋ አንስተው ይማቲ ነበር::

ሁለት ያህል አብነትዎች ለመግለፅ መጀመርያ ከግንበር በአንድ በኩል የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ ድርድር ያደርጋል በሌላ በኩል ለታጋዩ የማጥቃ ት ትእዛዝ ተሰጥተዋል: ግንባርም ተጨፈለቀ: ከኢ.ድ.ዩ

ጠረናፊትም ህዝብ የሃይማኖት መሪዎች የኢርትራ ፓርቲዎች ሽማግሌ ሆኖው እንዲያስታርቁ ተገኝተው እያሉ በሌላ በኩል ደግሞ እነሱን ለመደምሰስ ተዋጊ ሰራዊት ተሰባስቦ እርቁ ከተፈፀመ ከ 3 ቀን በኋላ ኢ..ድ.ዩ ጠረናፊት ተደመሰሱ: የኢ.ህ.አ.ፓ ለኦነግም እንደዚሁ ተደርገዋል: ስለዚህ የመለስ በሰዎች መካከል የነበረ ልዩነት ለመፍታት የሚያደረጉት ጥረት ተቃዋሚዎች ለመምታት ጊዜ ለመሸመት ነው እንጂ ሰላም ከመፈለግ የመነጨ አልነበረም::

"ከገፅ 25 እስከ ገፅ 26 መስመር አንድ: መለስ ብዙሃነትን በማስመልከት የነበረው ፍፁም ዴሞክራሲያዊ አቋም ግን በፅሑፎች ጥያቄ ብቻ የታጠረ አልነበረም በሃገራችን የሃይማኖት ብዙሃነት ዙርያ ለዘመናት የታየው የአያያዝ ችግር በፍፁም ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫ ለመፍታት የሚያስችል ሃሳብና ተግባር የነበረው መሪም ነበር: መለስ ኢትዮጵያ የብዙ ቢሄሮች ብቻ ሳይሆን የበርካታ ሃይማኖቶች መናሃርያ የሆነች ነገር ግን ደግሞ የሃይማኖታዊ ብዙሃነትን በአግባቡ መስተናገድ ተስናት የቆየች ሃገር እንደሆነች በጥልቀት የተገነዘብና ተንሰራፍቶ የቆየዉን ሃይማኖታዊ አድሎና ጭቆና ለመፍታት የሚያስችሉ በቂ ሃሳቦች በማፍለቅ ታግሎ ያታገለ የእኩልነት አራማጅ መለስ ነበር ወ.ዘ.ተ---- ትላላቹሁ አዲስ ራዕይ::"

መለስ የሃይማኖት ብዙሃነትስ ይቅር የኢትዮጵያ ሃገራችን የ3 ሺ ዓመት ታሪክ በ100 ዓመት ቀይረው ያነበቡና ወደ መድረክ ብቅ ያሉ ሰው ነበሩ: የኢትዮጵያ ሃይማኖቶች ስናነሳ ከኢትዮጵያ ታሪክ የተያያዘ መሆኑ ማራጋገጥ አለብን: የኢትዮጵያ ሃይማኖት ከክርስቶስ ልደት በፊት 2ሺ ዓመት ቀደም ብሎ ብሉይ ኪዳን እንደነበረ ከዛ በኋላ አዲስ ኪዳን እንደሆነ ይታወቃል: የሙስሊም ሃይማኖትም ከ1400 ዓመት በፊት ወደ ኢትዮ እነደገባ አባቶቻችን አውርውናል: የኢትዮጵያ ታሪክም ከሃይማኖት ታሪክ ተያይዞ የመጣ ነበር: መለስ ግን ትናንትና ኢትዮጵያ የምትባል ሃገር 100 ዓመት እድሜ ነው

ያላት ብለውናል ይህ የመለስ ብቻ እንዳይመስላቹሁ የመለስና የህ.ወ.ሓ.ት ዋና ሃሳብ ነበር::

በሌላ በኩል ኮመኒስት አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ሁሉም ዓይነት ሃይማኖት አያምኑም ብቻ ሳይሆን ሁሉም ሃይማኖት አርካሾች ናቸው በማለት ለአማንያን ያራክሱሉ: እነ ለኒን፣ ስታሊን፣ ማኦ፣ አንቨርሆዥ ሃይማኖትን አያምኑም ነበር መንግስቱ ኃይለማርያም ጭምር ሃይማኖት አያምንም ነበር: እንዲያው የኢሳፓ አባል የሚሆን ከሃይማኖት ንክክ ነፃ መሆን አለበት ይባል ነበር::

መለስና ህ.ወ.ሓ.ትስ በሃይማኖት የነበራቸው አቋም ምን ይመስል ነበር: መለስና ህ.ወ.ሓ.ት ከመጀመርያ ጀምሮ ሙስሊም ይሁን ክርስቲያን ሃይማኖት አያምንም ነበር: እርግጥ ነው ፀረ ሃይማኖት ነን ብሎ በአዋጅ አላወጀም: ነገር ግን ወቅቱ የትግል ጊዜ ስለሆነ ታጋይ ሁሉ ያገኘው መብለት መጠጣት አለበት በሚል ሽፋን በህ.ወ.ሓ.ት ሃይማኖት የሚባል አልነበረም: በተለይ ከ1967 ዓ.ም እስከ 1971 ዓ.ም የታገለው ወጣት 99.9% ቀለም የቆጠረ ስለነበረ: ፍፁም ኦርቶዶክስ ሃይማኖት አማኝ የሆነ ቤተ ክርስቲያን አይስምም ሰራዊት ተሰልፎ ሲጓዝ ቤተ ክርስቲያን በመንገዱ ካለና ብዙ ህዝብ ካለ ለመታለል ተብሎ በትእዛዝ ስሞ እንዲያልፍ ይደረጋል: ሙስሊም ዜጎቻችንም አይሰግዱም ነበር: በኋላም ከሁሉም ሃይማኖት ተከታዮች ወደ ትግል የተቀላቀሉ ገበሬዎች ወይም ወዛደሮች የከተማ ነዋሪም ስለነበሩ የቆያቸው ታጋይ ሃይመማኖት ስላልነበረው ኋላ የመጡም በእምነታቸው መሳም መስገድ አሳፍሮቸው ከሃይማኖት ዉጭ ሆኑ: ወደ ህ.ወ.ሓ.ት የተሰለፊው 386ሺ ታጋይ ሃይማኖት አይከተልም: አንድ አንድ ግለሰብ በየ ሃይማኖታቸው ሲያመለኩ ሲታዩ ታጋይ ይንቃቸው ነበር: ስለሆነም በረው የሚጠፉም ነበሩ::

መለስ የማርክሲዝም ለኒንዝም ሪኢቶ ዓለም ከሚያምኑ ካድሬዎች አንዱ ነበሩ: የማርክስዝም፣ ለኒንዝም፣ የማኦ፣ የኢንቨርሆዥ፣ ስታሊን ሪኢቶ ዓለም የሚያምኑ በየ ደረጃው ከ100ሺ በላይ ካድሬ

አሰልጥነዋል እሳቸው ያሰለጠኑዋ ቸው ለሌላው ታጋይና ምልሻ የገጠር ካድሬ በአጠቃላይ ለህዝብ አሰልጥነዋል: በመለስ ሲያሰለጥኑ የስልጠናው ሲሰጡ ዳይለክቲካል ማተርያሊዝምን ፍልስፍና መንደርደርያ አድርገው ሲያሰለጥኑ አይዲያሊዝም (አማንያን) መምታት ያለመ በመሆኑ አይድያሊዝምን አድርገው ለሁሉም ሃይማኖቶች እንደየእድገት ጎታች አታላይ ቁሻሻ በማለት ይመቱዋቸው ነበር::

መለስ ለሃይማኖት እንደጠላት ሲያሰልፉት ከእምፕርያሊዝም፣ ፊዩዳሊዝም፣ ባህታዊ፣ መነኩሴ፣ ጠንቋይ፣ ደብተራ፣ ሁሉም ዓይነት ለማኞች፣ ድኩማን፣ የቆሎ ተማሪ፣ የገዥዎች ወታደር፣ ሴተኛ አዳሪዎ ች፣ የከተማ ቦዘኔ፣ ቄሶች ወ.ዘ.ተ አምራች ያልሆኑ መጣጭ ጥገኛ ትል (ፓራሳይት) ብለው በጠላትነት ያስቀምጡዋቸው ነበሩ: ወገኖች መለስ ስለሃይማኖት ሲያስተምሩ ለነዛ ላይ የተጠቀሱ አካላት ማንነታቸው ሲያባሳብሱዋቸው የሰማ ታጋይ ከሳቸው በላይ ይጣሉዋ ቸው ነበር: መለስን ካነሳን መለስን ተከትለው ያስተምሩ የነበሩ ዓለምሰገድ ገ/አምላክ፣ ገ/መስቀል ሃይሉ፣ ሙሉጌታ ገ/ሂወት፣ ፈትለወርቅ ገ/ዝሄር (ሞንጆርኖ)፣ አማረ አረጋዊ፣ አረጋሽ አዳነ፣ የዉብማር አስፋውና ሌሎች ማ/ኮሚቴ ወ.ዘ.ተ ነበሩ: ለፖለቲካ ካድሬ መማርያ አዘጋጅ የድሮ ፈላስፋው አባይ ፀሃዬ ወ.ዘ.ተ ነበሩ: ምናልባት አስገደስ ምን ታምን ነበርክ ብትሉኝ የባስኩ ፀረሁሉም ሃይማኖቶች ነበርኩኝ: አሁን ደግሞ አማኒ ነኝ የሁሉም ሃይማኖት እምነት አክባሪ ነኝ::

እንገዲህ አጀንዳዬ መለስ ከልጅነታቸው ለሃይማኖት ብዙሃንነት ጠበቃ ነበሩ ለሚለው በልጅነታቸው የነበራቸው እምነት አላውቅም መረጃም አልነበረኝም: አባታቸው አቶ ዜናዊ አስረስ ወዳጅ ነበሩ: ወደ መቀሌ ሲመጡ ቤቴ ነው የሚያርፉ: ስለመለስ የልጅነት ታሪክ ይነግሩኝ ነበሩ ስለሃይማኖት ግን ተጫውተን አናውቅም::

መለስና ህ.ወ.ሓ.ት ግን ምንም ሃይማኖት አያምኑም ነበር: ስለማያምኑ ደግሞ የትግራይ ቄሶች የተንቤን አውራጃ የዓድዋ የአክሱም የሽሬ አውራጃዎች: የሳምረ ግጀት ቦራ አፅቢ ወንበርታ ወረዳዎች በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ቄሶች ደያቆኖች መለኩሴዎች ፀረ ህ.ወ.ሓ.ት በመነሳት ለገበሬው ስለሰበኩት ወጣት አልታገልም አለ: የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች ተጨነቁ::

የኋላ ኋላ ግን አንድ ብልሃት መጣ በህ.ወ.ሓ.ት ዉስጥ በቤተ ክህነት መንፈሳዊ ኮለጅ የተማሩና ሌሎች የተማሩ የትግራይ ቄሶች ኮንፍረንስ በመጥራት ብዙ ስብሰባ ተደረገ እነ መለስ ምንም አማራጭ አልነበራቸዉም መድረክ ላይ እየወጡ ሂስ አደረጉ: በተለይ አባይ ፀሃዬ ስብሃት ነጋ ሌሎችም ሂስ አደረጉ: ቄሶችም በረድ አሉ ሙስሊሞቹም እንደዚሁ: ብዙ ቄሶችም የህ.ወ.ሓ.ት ካድሬ ሆኖው ተሰለፉ: ብረት አንስተዉም ከሰራዊት ጋር ተቀላቀሉ: ይሁን እንጂ ሕብረተሰቡ በህ.ወ.ሓ.ት እያመነ በሂደ ቁጥር አብዛኛው ወጣት ፀረ ሃይማኖት ሆነ ታግዶ የነበረ የወሲብ ግንኙነት መጋባት ከተፈቀደ በኋላ ሙስሊሙ ክርስቲያን ያገባል ክርስቲያኑ ሴት ሙስሊምን ታገባለች በቃ ተዋለዱ::

ደርግ ተወገደ ታጋይ ከተማ ገባ ሙስሊም ክርስቲያ ባል ይዛ ወደ ቤተሰቧ ሄደች ወንድ ክርስቲያንም ሙስሊማ ሚስት ይዞ ሄደ: ሁሉም ተፋቱ: በአሁኑ ጊዜ ሳይፋቱ የሚገኙ አንድ ሰው አውቃለሁ: እሱም ሐሰን ሽፋ ነው: በዚህ መሰረት መለስ የሃይማኖት ብዙሃነት አያምኑም ነበር: የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴና በመቶ ሺ የሚቆጠር ካድሬ አማኝ አልነበረም: አዲስ ራዕይ የምትሉት ዉሸት ነው::

መለስ ከ1983 ዓ.ም እስከ ህልፈተ ሂወቱ የነበረው እምነትስ ምን ነበር: ከተማ ከገቡ ሃይማኖት (እምነት) ምን ያህል ሃያልነት እንዳለ ውም እየተረዱ መጡ: ያለ ሃይማኖት ስልጣናቸው ስር መሰረት እንደ ማይኖሮው አወቁ: በህዝብ ተፅኖም በሕገ መንግስት ጥርት ብሎ መስፈር የግድ ይል ነበር: በተለይ የጃንሆይ ስርዓት ለሙስሊም

*ሃይማኖት ያላላ ለክርስቲያን ሃይማኖት ሰማይ የሚሰቅል ሌሎች ሃይማኖቶች የሚያገል ስለነበረ: የደርግ ስርዓትም ጭራሹን ሁሉም ዓይነት ሃይማኖት ያፈነ ስለነበር: በዘመነ መለስ የሁሉም ዓይነት አማኒያን ነፃነት በሕግ መንግስት በመስፈሩ አማኒያን ደስ ብሎዋቸ ው ነበር: ሆኖም ግን እነ መለስ በግልባጩ መንግስት በሃይማኖት ሃይማኖት በመንግስት እጃቸው ማስገባት የለባቸዉም የሚለው ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ መለስም ሃይማኖት መሪዎች ጥሰዉታል::*

*ይህም መለስ የሃይማኖት በዓላት የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎችና ካድሬዎች መጫወቻ ሜዳ የፖለቲካ ማስረፅያ (ማጥመቂያ) ሲያደርጉት የሁሉም ሃይማኖት መሪዎች ጳጳሳት ዑለማዎች ሃይማኖት በሚመለከት ለአማኒያን እንደመስበክ ፀሎት እንደማድረግ ፈንታ የፖለቲካ ዲስኩራቸው ያሰራጩበት ነበሩ አሉም: ሁለቱም በኢትዮጵያ ህዝብ የፀደቀ ሕገ መንግስት ጥሰዉታል በተለይ የክርስቲያን ሃይማኖት ጳጳሳት በተለየ መንገድ የካድሬ ሥራ ይሰሩ ነበር አሁንም ይሰራሉ::*

*መለስ ግን ምንም እንኳ የሃይማኖት መሪዎች ይጠቀሙባቸው እንጂ እስከ ህልፈተ ሂወታቸው ዋዜማ የሃይማኖት እምነትም አልነበራቸዉ ም የሃይማኖት ብዙሃነትም አያምኑም ነበር: በቀብራቸው ዋዜማ ግን መለስ ከሚስታቸው ጋር ሳይሆን ለብቻቸው ቆርበው እንደቆዩ በቤተ መንግስት አካባቢ ይነገር ነበረ: ምናለባትም እነለኒን ስታሊን ሲሞቱም የመጨረሻዋ 11ኛ ሰዓት እግዝአቢሄርን እንዳስታወሱ መለስ አስተምሮውኛል: መለስም እንደጌቶቻቸው ለኒንና ስታሊን በ11ኛዋ ሰዓት ወደ እግዚአቢሄር አስታዉሰው ቆርበው እንደሚሆኑ እጠረጥራለሁ::*

*"በገፅ 26 አዲስ መስመር 2 መሰመር 1: መለስ ብዙሃነትን ከልጅነቱ ጀምሮ ያከበረና ለማክበርም የተፋለመ ሰው እንደነበር በተግባሩ ከማሳየቱም በላይ ሃሳብ በመንደፍ ደረጃም የነበረዉን አቋም በተለያዩ ፅሑፎች አረጋግጠዋል: ለህዝብ ባስማቸው ንግግሮችም*

ይህንኑ የሚያንፀባርቁ አቋሞችን በብዘት ማግኘት ይቻላል ----አዲስ ራዕይ::"

አዲስ ራዕዮች መለስ የሃይማኖት ብዙሃነት አማኝ እንዳልነበሩ ከላይ በስፋት ተገልፆ ነበር: ይቅርና ለአማንያን ወግነው ሊፋለሙስ ይቅር የሃይማኖት ብዙሃነት የእድገት እንቅፋት ናቸው: ጭራሹም የሃይማኖ ት አማንያን የአድሃርያን መሳርያ ነበሩ ብለው የሚያምኑ እንደነበሩ ተቀምጠዋል: ሌላቀርቶ በህልፈተ ሂወታቸው ዋዜማ 10 ወር በፊት በሙስሊሙ ሕብረተሰብ ጣልቃ በመግባት ለነባሩና አብሮን የቆየ የሙስሊም ሃይማኖት በማግለል በሃገራችን የማይታወቅ ከመለስ ፖለቲካ ቁርኝት ያለው አልአሕባሽ የሚባል ሃይማኖት ከ1400 ዓመት በላይ የቆየው የሃገራችን ሙስሊሞች እምነት በበላይ በማስቀመጥ ለሙስሊሙ ሕብረተሰብ ችግርና ቀውስ ፈጥረው እንዳለፉ ነው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያውቀው: መለስ የፈጠሩት ችግር አሁን ያሉ መሪዎችም የመለስ መንገድ እየተከተሉ ይገኛሉ የኢትዮጵያ ሙስሊም ሕብረተሰብ ወደ አሸባሪነት ተቀይረዋል ተብለው ስጋት ላይ ይገኛሉ::

ሌላ መለስ ለሃይማኖት ብዙሃነት ሲሉ በፁሑፍን በንግግርም ለመላው ዓለም ገልፀዋል ብላቹሃል: መለስ ስለማንኛውም ነገር ትናንት የተናገሩ ለዛሬ ወይ ለነገ ቀይረው ሲናገሩ ሃቅ ባይሆንም የማሳመን ችሎታቸው የንግግራቸው ችሎታ እኔም አውቃለሁ ህዝብም ያውቃል: መለስ ልክ በትጥቅ ትግል ጊዜ ከአንድ ሪኢቶ ዓለም ወደ አንድ ሪኢቶ ዓለም እየተገላበጡ እንደመጡ ሁሉ ባለፉት 21 ዓመትም እየተገላበጡ እንደመጡ ሁሉ የሚያውቀው ነው::

"ገፅ 27 አዲስ መስመር 2 ቅፅ 4 ልዩ እትም አዲስ ራዕይ ከሱማልያ እስከ ሱዳን: ከቡሩንዲ እስከ ሩዋንዳ: ከለይበርያ እስከ ኢርትራ የራስን ማንነት በማክበርና በማስከበር ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ ወይም ሰላማዊ ስርዓት ይመሰረት ዘንድ ድምፁን ከፍ

አድርጎ ከማሰማቱም በላይ በተግባርም የነዚህ ህዝቦች ትግል በመደገፍ ተንቀሳቅሰዋል መለስ::"

አዲስ ራዕዮች ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀደም ሲል በዘመነ ጃንሆይ በኮንጎ ከዛም አልፎ አፍሪካን ተሻግረው በደቡብ ኮርያ ሰላም በማስከበር አህጉራዊ ግዳጃቸው ፈፅመዋል: መንግስቱ ኃይለማርያም ደግሞ ለደቡብ አፍሪካ ታጋዮች ለዝንባብዌ በተለያዩ መንገዶች በማገዝ አፍሪካዊ ግዳጅን ይፈፅም ነበር: በተጨማሪ ለደቡብ ሱዳንም ያገዝ ነበር: አሁን መለስ ያደረገው የሰላምን ማስከበር ካለፉት ስርዓቶች የተለየ ምን ስራ ሰራ::

እንዲያው መለስ የሚታሙት በርዋንዳ፣ ላይበርያ፣ ቡሩንዲና ሌሎች ሃገሮችም የተደረገው ሰላም ማስከበር ተግባር ለቢዝነስ የዉጭ ምንዛሬ ለማግኘትና ብሎም ሰራዊትና ቁሳቁስ በማሰማራት ለሰላም አስከባሪ ሰራዊት የተሰጠው ገንዘብ ሂወቱ ለሰዋ ሰራዊት ልክ እንደሌሎች ሃገሮች የላባቸው ዋጋ እንደመክፈል ፈንታ በግዳጅ የተሰማራ ሰራዊት በተባበሩ መንግስታትና አፍሪካ ሕብረት የሰጣቸው ገንዘብ 90% በመቁረጥ ወደ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መንግስት ኪስ ገቢ ስለሆነ በሁሉም ቦታዎች ሰላም ለማስከበር የዘመቱ የኢትዮጵያ ሰራዊት ጠንካራ ተቃዉሞ እንዳሳዩ ሁሉ ህዝብ የሚያውቀው ነው: በተለይ አንድ ሻለቃ ግዳጁ ፈፅሞ ከመጣ በኋላ የላባቸው ዋጋ ሊሰጠን የተባለ ገንዘብ ይሰጠን ብሎ በአዲስ አበባ አካባቢ ምሽግ መሽጎ ሊያነጋግሩት ለሂዱ ባለስልጣኖች በማሰር ተቃዉሞ ስላሳየ በስንት ጥረት እንዲለሳለሱ በማድረግ አንድ ሻለቃ ሰራዊት ትጥቁ እንዲያወርድ ተደርጎ በሙሉ ታስሮ ወደ ትግራይ ምስራቃዊ ዞን ዉቅሮ ከተማ አካባቢ አስመጥተው አስረዉት እንደነበር ይታወቃል: ከዚያ በኋላ ሰራዊቱ የት ገባ ለሚለው መለስና ጓዶቹ (እግዚአቢሄር) ያውቃሉ: ስለሆነም መለስ ሰራዊት ወደ ሰላም ማስከበር መላካቸው ቢዝነስን ዓላማ ያደረገ ነበር ነው የተባለው: ባይሆን ንሮ የህንድና የሌሎች ሃገሮች ከሚከፈላቸው ገንዘብ ውሎ አበልን ሳይጨምር 70% እስከ

90% ለሰራዊታቸው በእጅ ዶለር ተሰጥቷቸዋል: በሌላ በኩል አነዛ አድማ ያደረጉ ወታደሮች ገንዘባችን ይሰጠን ተወረናል ያሉ ገንዘባቸው የተነጠቁ መሆናቸው መረጋገጫ የሚሆነው አንደኛ ከነሱ በኋላ ወደ ቡሩንዲና ላይበረያ የሄዱ እጅግ ብዙ ገንዘብ ይዘው መጥተው ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው ተቋቁመዋል: ሁለተኛ በአሁኑ ጊዜ በዳርፎርና በአብየይ ያሉ የሰላም አስከባሪዎች ልክ ለሌሎች ሃገሮች ወታደሮች እንደሚሰጣቸው በየ ደረጃቸው በመቶ ሺና በሚልዮን የሚቆጠር ገንዘብ አግኝተዋል: ይህ የሚያሳየው የኢትዮጵያ ሰራዊት ሚስጢሩ ሳያውቅ እንደተበላና አሁን ግን ሰግተው ይሰጡዋቸው እንዳሉ ነው የሚታወቀው::

አዲስ ራዕዮች መለስ ለኢርትራም ሰላም አስከባሪ እንደሰጣት አዳብላቹሁ አስቀምጣቹታል: ግን አዲስ ራዕዮች ለምን ታጭበረብሩ አላቹሁ: መለስና ህ.ወ.ሓ.ት ሻዕቢያን ከደርግ ጥቃት ለማዳን ብሎም ኢርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠልና ኢትዮጵያ የባህር በር ለማሳጣ ት ከ1972 እስከ1977 ዓ.ም መጀመርያ ዓመት የተሰጠ የሰራዊት እርዳታ መለስና ጓዶቻቸው የኢትዮጵያ ሉአላዊነትና አንድነት ለመበታተን ተብሎ ከ20ሺ በለይ የኢትየጵያ ወጣቶች ሂወታቸው እንዲያልፍ የተደረገው ነው: አዲስ ራዕዮች ግን የነ መለስና ጓዶቻቸው ወንጀል ለመሸፈን መለስ ከአህጉራዊ ብዙሃነትን አመለካከት የመነጨ በኢርትራ ሰላም አስከብረዋል ብላቹሁ ስታታልሉን ምን ያህል ሃገር ሽያጮች መሆናቹሁ ያሳያል:ይህ ማታለል ከአሁን በፊት አንዳንድ ፀሐፊዎች የሚባሉ እንደታጋይ ነባር ብስራት አማረን ወለገብሪኤል ታደሰ ሕቡር ገኪዳን የመሳሰሉ ሰዎች ሻዕቢያ ለማዳን ኢርትራን ለመገንጠል ከ20ሺ በላይ ወጣት ሞተ ከዛ የማያንሱ ቆሰሉ እያሉ ሻዕቢያ ለማዳን የተሰዉ ኢትዮጵያውያን ከ400 አይበልጡም ብላቹሁ ሲታስቀምጡ ምን ዓይነት ሰዎች ናቹሁ: እርግጥ እነዛ ሰዎች በ17 ዓመት የትጥቅ ትግል ጊዜ አንድ ቀን አንድ ጥይት ተኩሰው የማያውቁ ጊዜያቸው

እየተደበቁ ያሳለፉ ናቸው: በአጠቃላይ መለስ በዚህ ሰላም የማስከበርም ብዙሃነትን ለማዳን ካላቸው እምነት ሳይሆን ለቢዝነስ (ዶላር ለማግኘት) ያደረጉት የማስከበር ስራ ነበር: የኢርትራ ጉዳይ ከሆነ የተሰጠው እርዳታ ሃገር በመሸጥና መለስና ጓዶቻቸው የሻዕቢያን ሎሌነታቸው ለማረጋገጥ የሰሩት ነው::

ጠቅለል ባለ መልኩ መለስ ለሃገር ዉስጥም ይሁን ለዉጭ ህዝቦች ብዙሃነትን መብት ለማስከበር ወይም ለመጠበቅ ካላቸው እምነት ሳይሆን ለዉጭ ህዝብ ግንኙነት ልታይ ልታይ በማለት ተወዳጅነት ለማግኘት የሚያደርጉት ነበር እንዲያዉም አብዛኛው ህዝብ መለስ ለዉጭ ሰዎች የተመቹ በተለይ ደግሞ ለኢርትራ አጅጉን የተመቹ መሆናቸው ለሃገር ህዝብ ግን በሁሉ መልኩ የማይመቹና መለስ ለብቻቸው ብቻቸው ወደ መድረክ ብቅ ያሉ እቺ ሃገር የመበታተን አደጋ አሻራ አስቀምጠውበታል እንደአለፈነው የሚታማ ነው::

## ክፍል 11

## መለስና የሴቶች እኩልነት

"ገፅ 28 አደዲስ መስመር 3: ታላቁ የህዝብ ልጅ መለስ በሴቶች እኩልነት ጥያቄዎች ላይ እንከን የለሽ አቋምና ተግባር ነበረው: መለስ በሴቶች የእኩልነት ጉዳይ ላይ ፍፁም ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ አቋም ነበረው: የሴቶችን እኩልነት የማስጠበቅ ጉዳይ አንድና ሁለት አዋጅ በማስወጣት ብቻ ሳይሆን በራሳቸው በሴቶች ትግል ጭምር መሰረታዊ የሕብረተሰብ አወቃቀር ለውጥ በማምጣት የሚያረጋግጥ ነው ብሎ የሚያምኑት መለስና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ከ20 ባልበለጡት ዓመታት በኢትዮጵያ መሰረታዊ የሕብረተሰብ አወቃቀር የሚመጣበት ጠንካራ መሰረት አንጥፈዋል: መለስ ትጥቅ ትግል በጀመሩበት በትግራይ ከዚያም አልፎ በኢትዮጵያ ደረጃ የሴቶችን እኩልነት በራሳቸዉም ተሳትፎና ተግባራዊ ትግል ለመረጋገጥ

በተደራጀ አኳኋን በአካሄደው ጥረት እነሆ የሃገራችን ሴቶች ከድህነት በመላቀቅ በጎዳና እየገሰገሱ ይገኛሉ::"

መለስ ስለሴቶች እኩልነት በተመለከተ የነበራቸው አቋምና እምነት ባለፉት ገፃት የመለስ አጭር ታሪክ በሚል አርእስት ነካ ነካ አድርጌ አልፌው ነበር: መለስና ጓዶቻቸውና ህ.ወ.ሓ.ት በማኒፌስቶ ደረጃ ባይፃፍም የሴቶች እኩልነት እንደሚያምኑ ይናገሩ ነበሩ: በታጋይም በህዝብም ቅስቀሳ ያደርጉበት ነበሩ: ይሁን እንጂ በተግባር ግን በፀረ የሴቶች እኩልነት በግንባር ቀደምት መለስ ይሰለፉ ነበር::

ሴቶች በህ.ወ.ሓ.ት የነበራቸው ተሳትፎ ከ1967 እስከ 1969 ዓ.ም በጣም ጥቂት ሴቶች ነበሩ: ከ1969 እስከ 1972 ዓ.ም ከሰራዊቱ 15% በላይ ተሳትፎ ነበራቸው ከ1974 በኋላ ከ 25% እስከ 32% ደርሰው ነበሩ: በህ.ወ.ሓ.ት የተሰለፉ ሴቶች የተማሩና ያልተማሩ ሳይለይ እኩል ከወንዶች በወታደራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ በህዝብ አስተዳደር ንቁ ተሳትፎ ነበራቸው: ወታደራዊ አዛዦች ሆነው አዋግተዋል ፖለቲካ መሪዎች ነበሩ: በህዝብ አስተዳደርና ፍትህ በማሕበራዊ አገልግሎት በብቃት ሰርተዋል::

ሴቶች በራሳቸው ጥረት እኩል ይታገሉ እንጂ በነ መለስና ጓዶቻቸው ግን ተቀባይነት አልነበራቸዉም: በህ.ወ.ሓ.ት ከተራ ወንድ ታጋይ እስከ ላይኛው ለሴቶች ማናናቅ መሪዎች ለግል ፍላጎታቸው ሊጠቀሙባቸ ው መፈለግ: ሴት ለሁሉም ነገር አሳሳች ናት ወ.ዘ.ተ ብዙ አስቀያሚ አመለካከቶች ነበሩ::

በሴቶች ይቀርቡ የነበሩ ጥያቄዎች በአቅም ከወንዶች እኩል እያለን እኩል ስልጣን አይሰጠንም: የበታች አድርጋቹሁ ታዩን አላቹሁ: በአጠቃላይ ህ.ወ.ሓ.ት በአፍ የሴቶች እኩልነት አምናለሁ ይላል እንጂ በተግባር ፀረ የሴቶች እኩልነት ነው ብለው ጠንካራ ተቃዉሞ በማሳየታቸው የህወሻት ማ/ኮሚቴ ሁሉ ፀረ የሴተች ጥያቄ ተነስተዋል: በህ.ወ.ሓ.ት ድርጅት በሁሉም ዞኖች ወረዳዎች በሰራዊት የሚገኙ ታጋይ ሴቶች አንድ ልብ ሆኑ: በተለያዩ

ሰሚናሮች መሪ አካል ናቸው ለሚባሉ ከፋፍለው መወያየት ጀመሩ: ያወያዩ ከነበሩ መካከል መለስ ናቸው: እንዳዉም በሀ.ወ.ሓ.ት የሴት ፌሚኒስቶች ተፈጥረዋል የነዚህ አንቀሳቃሾች እነ አረጋሽ አዳነ የዉብማር ፈትለወርቅ መብራት በየነ ሕሪይቲ ምሕረትአብ ሮማን ገ/ስላሴ ሌሎቹም ተፈረጁ በተለይ ቀለም የቆጠሩ ሴቶች: በመለስና አባይ ፀሃዬ ዐይን ገቡ: ሌሎቹም እንደዓለምሰገድ ክንፈ ገ/መድህን ከሰራዊት አዛገሮችም ፀረ ሴቶች ተነሱ::

ሁኔታው እየተባባሰ ስለሄደ በመቶ የሚቆጠሩ የሴቶች ካድሬ በወርዒ በረሃ ለሳምንታት በአንድ በኩል የሴቶች ካድሬ በሌላ በኩል የሀ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴና አጋሮቻቸው የሆኑ አድርባይ ካድሬዎች ነበሩ: ዉይይቱ ተጧጧፈ ነገር ግን ስምምነት ላይ አልተደረሰም: በውይይቱ መለስ ዋና ተሳዳቢና ዘለፋ ያበዙ ነበር ያለ ስምምነት ተበተነ: ቆየት ብሎ በተንቤት አካባቢ የሴቶች 1ኛ ኮንፍረንስ ተጠራ: በዛን ኮንፍርንስ በርከት ያሉ ወንዶች ታማኝ ካድሬዎች ነበሩ: ሆኖም ግን በኮንፍርን ሱ ወሳኝ ባልሆኑ ነጥቦች ቢስማሙም መሰረታዊ መግባባት ሳይደረሱ ኮንፍርንሱ ተበተነ::

እንደገና ሁኔታው እየተባባሰ በመሄዱ 2ኛ ኮንፍርንስ በደጀና ተጠራ: ኮንፍረንሱ በጣም የሞቀና እነ መለስ በተለይ ከነ አረጋሽ አዳነ ከፍተኛ ካድሬዎች በማስፈራራት እጅግ አስነዋሪ የሆነ ስድብ በመሰንዘር እስከ ለመምታት የተሞከረ ነበር: ይህ ፍፃሜ መለስና ጓዶቻቸው ነበሩ::

ሌላ በትጥቅ ትግል ጊዜ ወሲባዊ ግንኙነት ለ10 ዓመት ታግዶ ስለነበረ በዛን ወቅት በሴተች ወሲባዊ ጥቃት ሲደርስ ለሴቶች አሳሳቶች በማለት ሴቶች ሲቀጡ ወንዶች ግን በተለይ መሪዎች ከሆኑ ይፋ ሁኖ እንዳይታወቅ ይሸፈን ነበር: ወሲባዊ ግንኙነት ከተፈቀደም ሴቶች የወንዶች ወሲባዊ እርካታ ምቾት እንዲሆኑ ከመታገል ተገልለ ው የወንዶች ጥገኛ ሆነው እንዲቀሩ ተደረጉ: በተለይ የመሪዎች ሚስቶች ከሆኑ ከስራ ገበታቸው ተፈናቅለው በወንዶች ፍላጎት የቤት

እመቤት ሆኑ: ህ.ወ.ሓ.ት ከተመሰረተ እስከ 1983 ዓ.ም ደርግ እስከ ተወገደበት አንዷት ሴት ማ/ኮሚቴ ነበረች ከድርጅቱ ማ/ኮሚቴ ካሉት ወንዶች አብዛኛቸው በሁሉም አቅም የሚበልጡ ሴት ታጋዮች ነበሩ: ግን የነ መለስ በሴቶች ላይ የነበራቸው ንቀት ሴቶች ወደ ስልጣን ሊመጡ አልቻሉም ነበር::

የህ.ወ.ሓ.ት ሴት ታጋዮች ግን አንዳንድ ሴቶች ለግል ጥቅማቸው የምቅበዘበዙ ወደ ጎን በመተው አብዛኞቹ ግን ፀረደርግ ጠንክረው ከታገሉት የማያንስ ለመብታቸው ጠንካራ ታጋዮች ነበሩ: እስከ አሁን መለስ ለሴቶች መብት የቆሙ አልነበሩም: አዲስ ራዕዮች መረጃ ያንሳቹዋል: ግን አይመስለኝም አሁንማ እየጠረጠርኩዋቹሁ ሂድኩኝ::

"መለስ የሴቶች የአወቃቀር ለውጥ ለማምጣት ከትግራይ አልፈው በመላው ኢትዮጵያ የሴቶች እኩልነት በራሳቸው ትግል ብቁ እንዲሆኑ ተደርገዋል: የሃገራችን ሴቶች ከድህነት ተላቀዋል ይህ የመለስ ስብእና ዉጤት ነው ብላቹዋል ራዕዮች::"

በትጥቅ ትግል ጊዜ የነበረ የሴቶች እኩልነትና መለስ ለሴቶች እኩልነት የነበራቸው አስተዋፅኦ ቀደም ሲል ተቀምጠዋል: መለስ የሴቶች አወቃቀር በሚመለከት ሰርተዉት ያለፉ ሁሉ ሴቶች ከነበሩበ ት ሁኔታ የሚያዳክም እንጂ የሚያሻሽል አልነበረም በመለስ አስተዳደር ጊዜ: ይህም ሴት በዝቅተኛ ነጥብ ዩነቨርሲቲ እንድትገባ ስትመረቅም በዝቅተኛ ነጥብ እያላት የስራ ዕድል ታገኛለች: የ8ኛ የ10ኛ የ12ኛ ክፍሎች መልቀቅያዎች በዝቅተኛ ነጥብ ማለፍ የሚል አሰራር ሴቶች ጠንክረው ተምረው ከወንዱ በልጠው ተመራማሪዎች እንዳይሆኑ የሚያደርግ በመሆኑም አልፎ ተንበርካኮች እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው: የመለስ የእኩልነት ፖሊሲ::

"የኢትዮጵያ ሴቶች በተደራጀ አኳኋን ባካሄዱት ጥረት እነሆ የሃገራችን ሴቶች ከድህነት በመላቀቅ በድገት ጎዳና እየገሰገሱ ይገኛሉ ይለሉ ራዕዮች::"

ሴቶች በእድገት ጎዳና እየገሰገሱ ናቸው አይደሉም እያልን ከምንከራከር ሴቶች በተጨባጭ ምን ደረጃ ላይ አሉ፡ የኢትዮጵያ ሴቶች በሚልዮን የሚቆጠሩ ቀለም የቆጠሩና ያልቆጠሩ በዝሙት አዳሪነት የተሰማሩ አሉ፡ በሕጋዊና ሕጋዊ ባልሆነ ወደ ሰዑዲ ዓረብ፣ ኩዌት፣ የመን፣ ሱዳን፣ ኬንያ፣ ጀቡቲ፣ ዱበይ፣ ኳታር፣ ሊባኖን፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ሊብያ አውሮፓ አመሪካ ካናዳ ወዘተ ተሰደው መከራ አሳራቸው ተሚበሉ፡ ከፎቅ እንደ ቁሻሻ የሚጣሉና የሚታረዱ በሚልዮን የሚቆጠሩ ናቸው፡ ተምረው የጎዳና ተዳዳሪዎች የሆኑ ህዝብ ይቁጠራቸው፡ ሥራ ለመቀጠር ክብረ ንፅህናቸው ሸጠው የሚቀጠሩ እንዳሉ ታውቃላቹሁ፡ በዘጠኝ ክልሎችና አዲስ አበባ ሚግሬሽን መስርያ ቤት ፓስፖርት አውጥተው በየ ቀኑ ወደ ስደት የሚጎርፉ ለአዲስ ራዕይ አዘጋጆችና ለአዲሱ ለገሰና በረከት ሰምኦን የተደበቀ አይደለም፡ በተሳሳተ የመለስ ፖሊሲ መጋቢ እንድስትሪ ባለመኖሩ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ተደራጅተው ከስረው በጎዳና የወደቁ ስንት ናቸው፡ ምነው አዲስ ራዕዮች ምንም የሌላቸው በባዶ ሆዳቸው ተናገሩ እየተባሉ በኢትዮጵያ ተለቪዥን በግድ የሚዋሹ ሴቶች እያሳያቹሁ ለሃገራችን ህዝብና ለዓለም እያደናገራቹሁ ትኖራላቹሁ፡ ስለዚህ በመለስ ዘመነ ስልጣን የሴቶች መብት ያልተጠበቀበት ሴቶች በሁሉም ነገር የተዋረዱበት ዘር ማንዘራቸው በዓለም የተዘራበት ነው፡ ሐቁ አሁን አልፎላቸውና እየናጠጡ የሚገኙ የቻይና የዱባይ የጃፓን የአውሮፓና አመሪካ ገበያ ተቆጣጥረው ንሮዋቸው በአየርና በዓለም ከፍተኛ ሆቴሎች ምቾታቸው ተጠብቆ የሚኖሩ ያሉ የሀ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎች ሚስቶችና አብአብረው የተጠጉ ቤተሰቦች ናቸው፡ የሃገራችን ሴቶች ምንኛ የእንሰሳ ንሮ ይኖሩ እንዳሉ ለማረጋገጥ ከፈለጋቹሁ አዲስ ራዕዮች ከ 3 ሰዓት በኋላ በአዲስ አበባ በሁሉም አካባቢዎች፣ ባህርዳር፣ ናዝሬት፣ ደሴ፣ መቀሌ፣ ድሬዳዋ፣ ሃረር፣ ጅጂጋ፣ ጎንደር፣ ሑመራ፣ ሽሬ፣ ዓዲግራት፣ ሰመራ በአጠቃላይ የመከላከያ ሰራዊት

በሚኖሩባቸው ጠረፎች የሚገኙ ሴቶች የእንሰሳ አኗኗር ራሱ ማስረጃ ነው::

## "አዲስ ራዕይ 8ኛ ዓመት ቅፅ 4 ልዩ እትም"

"ገፅ 29 አዲስ መስመር 2: መለስ በትጥቅ ትግል ጊዜ ለሴቶች የመሬት ባለቤትነት እንዲሆኑ አድርገዋል: ሴቶች በትግራይና በከፊል አማራ ክልል ገጠሮች የመሬት እኩል ተጠቃሚዎች ሆነዋል: ሴቶች የመረሬት ተጠቀቃመሚነት ጣእም ለመማወቅ የቻሉት በመለስ መሪነት በተካሄደው አኩሪ አመራር የእኩልነት ትግል ነው::"

ራዕዮች እርግጥ በትጥቅ ትግል ጊዜ መሬት ተሸንሽኖ በወቅቱ የነበሩ እድሜ ደረስ ሴቶች መሬት አግኝተዋል: ያን ሥራ ግን 1ኛ መለስ የአማራር ቁንጮ ባልነበሩበት ነው: ቢኖሩም ግን የህ.ወ.ሓ.ት ሥራ እንጂ መለስ የፈፀማቸው ሥራ አልነበሩም::

መሬት የተሸነሸነው በ1983 ዓ.ም ነበር: በዛን ጊዜ እድሜ ደረስ የሚባለው ወንድ የ21 ወይም 22 ሴት ደግሞ 19 ወይም 20 ዓመት ነው: በዛን ጊዜ ወንድ የ22 ዓመት ወጣት መሬት አግኝተዋለ: የ21 ዓመት ዕድሜ ወጣት መሬት አላገኘም በአሁኑ ጊዜ የ44 ዓመት ዕድሜ ደርሰዋል ሚስት አግብቶ 4 ወይም 5 ልጆች ወልዶዋል ነገር ግን መሬት የለዉም: የ20 ዓ.ምት ዕደሜ ኮረዳ በ1982 ዓ.ም መሬት አግኝታለች: የ19 ዓመት ዕድሜ ኮረዳ መሬት አላገኘችም በአሁኑ ጊዜ ዕድሜዋ 42 ዓመት አድርጋለች በሳይንሱ መሰረት በዛሬ እንኳ አይቻልም: ግን ወልዳ ልትጨርስ 3 ዓመት ቀርታቷል: ከነዚህ ሰዎች ዕድሜ በታች መሬት ሊያገኙ አልቻሉም: በዛን ጊዜ የ 1 ዓመት ዕድሜ የነበረ አሁን ዕድሜው 21 ዓመት ነው: ታድያ ይህ ወጣት ሴት ይሁን ወንድ ከነ ልጆች የት ነው ያሉት: መለስ ይህ ጥልቀት ያለው ጥናት እያሳየናቸው ነበር: ሃይላይት እያመጡ በአየር ናቸው ያንሳፍፉን የነበሩ: ይህ አሰራር የመለስና ጓዱቻቸው የሚፈጥሩት ነው::

*አሁንም የኢትዮጵያ ሴቶች የመሬትን ጣእም ለማወቅ የቻሉት በመለስ ዘመነ ስልጣን አልነበረም: በመለስ ዘመነ ስልጣን ለማወቅ የቻሉት መሬት ሳይሆን ስደት ሞት መንገላታት ልጅና አባት እናት ለየብቻቸው ወደ ስደት መበታተን ነው ያገኙት: ወዳጆቼ የሃፀይ ኃይለስላሴና የደርግ የመለስ ስርዓቶች የሶስቱ ስርዓቶች ሲወዳደሩ ስደት ረሃብ ሥራ አጥነት በዘመነ መለስ የከፋ ነው: አሁንም እባካቹሁ አዲስ ራዕዮች ህዝብን አታዳናግሩ::*

*አንድ ነገር ግን ግልፅ ማድረግ ያስፈልጋል: እስከ አሁን ያላቹሁን ቢኖር መለስ ከትጥቅ ትግል ጀምሮ እስከ ህልፈተ ሂወቱ ብቻው ሰው ሳያስጠጋ ሰው ሳይፈራ ሃገር ጥሏት ሄደ እያላቹሁ የምትሳደቡ ያላቹሁ እንዴት አድርጋቹሁ ነው የምትመለከቱት ያላቸሁ: ለመሆኑ እስከ አሁን ያየነው በረከት ስምኦንና አዲሱ ለገሰ ሬድዋን አይተዉታል እስኪ ልቀጥልና ግምገማ እያሳረፍነ ልሂድ::*

## ክፍል 12

## "መለስ ሳያውቁ የጣሉት ሲያውቁት ደግም ያጡት የወጣቶች ሮል"

*"መለስና ድርጅታችን ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ሃገራችንና ዓለምን የተሻሉ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረትና አስተዋፅኦ ከአደረጉላቸው መስኮች አንዱ የወጣቶችን ህ.ወ.ሓ.ት ከመቀየር ባደረጉት ጥረት የሚገለፅ ነው: ዓለማችን ለሴቶች የማትመች እንደሆነች ሁሉ ለወጣቶችም የማትመች ከሆነች ከርማለች::"*

*ራዕዮች የኢትዮጵያ ህዝብና ወጣቱም ጭምር ለመለስ አበጥረው ያውቁታል ከሚያውቁበት አንዱ አንደኛ መለስ እተገብራቸው አለሁ የሚሉ የሚሉዋቸው ሕብረተሰብ የሚያንሳፍፍ እንጂ የሕብረተሰብ መሰረታዊ ችግሮች ስራ አጥነት ስደት መበታተን አላዳኑም: ሁለተኛ መለስ ወደ ስልጣናቸው የሚጠጋቸው የማያስጠጉ ለመጪው*

ትውልድ ተኪ መሪ ለማፍራት ፍቃደኛ ያልነበሩ ብቻቸው ልታይ ልታይ እያሉ ይሮጡ የነበሩ መሆናቸው አበጥሮ ያውቃል::

መለስ የዉስጣቸው ችግር የተመቻቸ ዴሞክራሲያዊ መድረክ ከፍተው ከዜጎቻቸው ያለው ግርጭት በዉይይቱ በሃገራቸው ያለ ዴሞክራሲያዊ ዓፈና ያላስወገዱ በሃገራችን የብዙሃን ፓርቲ (ማልት ፓርት ሲስትም) ዘግተው ለብቻቸው ስልጣን በሞኖፖሊ የሙጥኝ ብለው የያዙ ናቸው: ያለኔ ሌላ አታምልኩ ብለው ብቻቸው ለብቻቸው እየሮጡ መተካካት እንደመፈክር አንግበው እየዘመሩ ምንም ተግባራዊ ያላደረጉ ከህልፈተ ሞታቸው በኋላ የተጋለጡ መሆናቸው ያሳያል: ይህ ሁሉ የመለስ ባህር የኢትዮጵያ ህዝብ ተቃዋሚዎች የዉጭ ሃገር ዜጎች ያውቁት ነበር: በተለይ ወጣትና ሙሁራኑ በጋዜጣ በእንተርኔት በዉጭ ብዙሃን መገናኛ ይጠቀሙ ነበር: በተጨማሪ የአውሮፓ ህብረት የአመሪካ አንባሳደራት ችግራቸው ይነግሩዋቸው ነበር: መለስ ግን ከጥንት ጀምሮው እንደ ባህል የያዙት የሰዎች ሃሳብ አለመቀበል ነው: እንዲያዉም አስተያየ ት የሰጣቸው ሰው ወደ ጠላትነት ይመድቡታል::

ሌላ ሲያውቁት ያጡት የሚል የሃሳብ ድራማ ነበር: የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎች መለስ ሞተው እያሉ ለመጪው የህዝብ ግንኙነት ስራቸው ሊጠቀሙበት በማሰብ በዋናነት ግን ለወደፊት የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ዓላማዎች ለማሳካት ለአስርቱ ዓመታት አገዛዛቸው ይጠቅማቸው ዘንድ በማሰብ አስከሬኑ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት ለሳምንታት ያህል የኢ.ህ.አ.ዴ.ግና ህ.ወ.ሓ.ት ወጣት ሊግ የፓርቲ አባላት አደራጅተው በመቆየት ለዓመታት የሚያቆይ መፈክሮች አዘጋጅተው የቆዩት የሃዘን ድራማ ነው የነበረው::

ወጣቶች እኮ በዘመነ መለስ ያገኙት ጥቅም አልነበረም: ከኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አመራር ቁርኝት የነበራቸው የአመራር ልጆች ወይም ዘመድ አዝማድና የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ልጆች ናቸው ተጠቃሚዎች: በመለስ ቀብር የነበሩ ወጣቶች ከቻይና፣ ሂንድ፣

አመሪካ፣ እንግሊዝ፣ ኮርያ የመጡ ነበሩ: ሁሉም ለማለት ይቻላል አስተናጋጆች ነበሩ: ሌላው ወጣት ለድራማ በተለያዩ መነገዶች የተሰባሰቡ ነበሩ: ስለዚህ አዲስ ራዕዮች አሁንም ለኢትዮጵያ ህዝብ እያታለላቹሁ ናቹሁ: ለመሆኑ ፁሑፋቹሁ በረከት ሰምኦን ሬድዋን አዲሱ ለገሰ አይተዉት ነበር: አይተዉት ከሆነ ፁሑፍ የመለስ ሃቀኛ ታሪክ የሚገልፅ ወይስ መጥፎ አሻራ እየለጠፉባቸው ነው: ለታሪክ ተመራማሪዎች ይግባኝ ብያለሁ::

## ክፍል 13

## መለስና የመድበለ ፓርቲ ስርዓት

"ገፅ 34 አዲስ መስመር 1: መስመር 2: መለስ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በኢትዮጵያ ፖለቲካ መልከዓ ምድር ዉስጥ ያመጡት መሰረታዊ ለውጥ መካከል አንዱና ዋናው በፖለቲካ የመሳተፍና የመደራጀት መብትን በተመለ ከተ ያመጡት ለውጥ ነው: ለማንም ግልፅ የሚሆን በሃገራችን የፖለቲ ካ ተሳትፎ ሁሉም ቢሆን ለጥቂት ገዢዎች ብቻ የተፈቀደ ነበር: የመደራጀት መብትም በተመሳሳይ መልኩ ለጥቂት ገዢዎች ብቻ የተሰጠ ትርፍ ነበር: የርቁን ትተን የቅርቡ ብናስታውስ በደርግ ዘመን ኢሰፓ የተባለ ፓርቲ የፖለቲካ መልከዓ ምድሩን በብቸኝነት ተቆጣጥሮት ስለነበር ሌሎች የተደራጁ ኃይሎች እጅግ በሚዘገንን ጭፍጨፋ ከሃገሪቱ ምድረ ገፅ እንዲጠፉ ወይም ብረት አንስተው ብቻ ለመኖር እንዲፍጨረጨሩ ሲገደዱ ቆይተዋል::"

አዲስ ራዕዮች ደርግ የኢትዮጵያ ፖለቲካ መልከዓ ምድር በማጥበብ ደርግን ለሚቃወሙ ሁሉ ሲፈታው የነበረ አዋጅ በማስተጋባት በመጨፍጨፍ በማሰር ጭራሹን ተቃዋሚ ነኝ ባይ በሃገር ዉስጥ የማይኖርበት አድርገዋል: የመለስ ዋና ችግር የነበረው በሕገ መንግስ ት የሰፈሩ አንቀፆች ከሞላ ጎደል ዴሞክራሲያዊ ይዘት የተላበሱ

ነበሩ: በተግባርም ከሽግግር መንግስት ጀምሮ በኢትዮጵያ ብዙ የተለያዩ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች የየራሳቸው ሪኢቶ ዓለምና ፖሊሲ ይዘው መንቀሳቀስ ጀምረው ነበር: የኢትዮጵያ ህዝብም በሃገራችን የብዙሃን ፓርቲ (መድበለ ፓርቲ) መኖር ተበሰረዋል ብሎ እየተጠራጠረ ደስታና ፍርሃት እየተፈራረቁበት ተቀብሎ በወቅቱ መለስ ሲያውጁ የነበሩ ዴሞክራሲያዊ የሚመስሉ አዋጆች በጥርጣሬ እያየ ተቀበላቸው::

መለስ ግን በተገባር ለነዛ ከእንግዲህ ወድያ መድበለ ፓርቲ በኢትዮጵያ ትንሳኤ ሙዉታን ሁነዋል ብለው ደስ ብሎዋቸው እየተጠራጠሩ መንቀሳቀስ የጀመሩ ፓርቲዎች ነበሩ::

ድሮ እንደተለመደው በመለስ ሳንባ የሚተነፍሱና በሪሞት የሚቆጣጠሩዋቸው የነበሩ አጋር ፓርቲዎች አድረጎ ለነዛ አዲስ ፓርቲዎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመመስረት አፈረሳቸው: ጠንከር ላሉትም እንደኦነግ ጋምቤላ አብነግም ለኦሆዴድ በማጀብ በጦርነት አድክመው ኦሆዴድን በሃይል የኦሮሞ ምስል አስይዞ ፓርላማ አስቀመጣቸው: ለሌሎች በድለላ እርስ በራሳቸው በማጋጨት እንዲበታተኑ አደረገ: በቃ በኢትዮጵያ መድበለ ፓርቲ መኖር በወረቀትና በአየር በሬድዮና ተለቪዥ'ን መናገር ብቻ ሆነ በሁሉም ክልሎች የመለስ ህ.ወ.ሓ.ት አባል ፓርቲዎችና አጋር የሚባሉ ፓርቲዎች በመለስ እንደጭቃ ተጠፍጥፈው የተሰሩ: ፓርቲዎች የበላይነት አግኝተው በመለስና ጓዶቹ እንደየድሮ ሮሜር ሰዓት እየተሞሉ ህዝቡ በግዴታ ያዙት::

መለስ የፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃ የመንቀሳቀስ የመደራጀት መብት ካለፉት ገዢዎች የሚለየው የደርግና የጃንሆይ ገዢዎች ግልፅ በሆነ ለህዝባዊና ፖለቲካ ተቃዉሞ ጭራሹን በጠራራ ፀሃይ ሲያፍኑት፣ ሲገድሉት፣ ሲያስሩት፣ ከሃገር በሮ እንዲጠፉ ሲያደርጉት፣ ለማታለል ተብሎም በወረቀት በሚድያ በአዋጅም ትንፍስ አይሉም ለሁሉም ነገር በግልፅ ነበር የሚያፍኑት::

መለስ ከነባሩ መንግስታት የሚለየው ሁሉም ዐይነት ዴሞክራሲያ ዊ መብቶች በማኒፌሰቶ በሕገ መንግስት አዋጅ በህዝብ የተመረጠ መንግስት ለስሙ አቋቁሞ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲወዳደሩ ፈቅዶ በዓለም አጀብ ሊባልለት በሃገር ዉስጥም በዉጭም ብዙሃን መገናኛ ዓለም እንዲያውቀው ድብልቅልቅ በማድረግ ምርጫ ሲመጣም የዉጭ ታዛቢዎች መጥተው ይታዘቡ: እና ሐቀኛ ተቃዋሚ ስለ የሌለ ነው እንጂ የተለየ ሃሳብ ይዞ ሊወዳደር የሚፈልግ ካለ: ግማሽ መንገድ ሂደን እንቀበለዋለን በማለት በማደናገር ይናገር ነበር::

መለስና ህ.ወ.ሓ.ት ግን በ17 ዓመት የትጥቅ ትግል ጊዜ ነፍጥ አንስተው በጦርነት ያጠፉዋቸው እነ ኢ.ድ.ዩ ኢ.ህ.አ.ፓ ኦነግ ምስክሮች በአካል እያሉ የህ.ወ.ሓ.ት ታጋይና የትግራይ ህዝብ የፀለምት የሰሜን የፀገዴና አርማጭሆ የሰቆጣ ህዝብ እያለ: የድመት ልጅ አይተዉም የዝሪያው የአያቱ ሽለመጥማጥ ባህርያት እንደሚባለው ሁሉ: መለስና ህ.ወ.ሓ.ትም ከተማ ከገቡ በኋላ ለሚይደበቀው ባህሪያቸው ይዘው መድረክ ወጥተው መድበለ ፓርቲ (ብዙሃን ፓርቲዎች) መኖር በኢትዮጵያ ተበስረዋል: ሁላችን ኢትዮጵያውያ ን የተለያየ አማራጭ ሪኢቶ ዓለምና ፖሊሲ ይዘን እንቅረብ በሚያስማሙን አብረን በመስራት በምንለያይበት እያጠበብን ወደ ህዝብ ቀርበን ህዝብ ይፍረደን ብለው ተናግረዋል: ይህ ብለው ሲያበቁ ግን መለስ ባለፉት 21 ዓመታት በአስር የሚቆጠሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በጦርነት በተለያዩ ሴራ (ተንኮል) በመቆፈር እንዲከስሙ አድርገዋል: ታድያ የነ አዲሱ ለገሰና በረከት ስምኦን ሬድዋን ተላላኪዎች መለስ በኢትዮጵያ መድበለ ፓርቲ ስርዓት እንዲስፋፉ ያደረጉ ፈላስፋ ነበሩ ስትሉን በየትኛው መስፈርት ነው: በበኩሌ አዲስ ራዕዮችና አለቆቻቹሁ ያልተፃፈ ነው የምታነቡ ያላቹሁ: የሚገርመው ግን በረከት ስምኦንና አዲሱ ለገሰ ከ1970 እስከ 1974 ዓ.ም ኢ.ህ.አ.ፓ በ4 ዓመት ጦርነት ድባቁ የገባ መሆኑ እያወቃቹሁ ራሳቹሁም ህ.ወ.ሓ.ት በኢ.ህ.አ.ፓ ላይ

በፈፀመው የማጥቃት እርምጃ ተደናግጣቹሁ ወደ ህ.ወ.ሓ.ት እጃቹሁ የሰጣቹሁ እያላቹሁ ከደርግ ዉድቀት በኋላም በጎጃም ከነበው ኢ.ህ.አ.ፓ እርቅ እንደማድረግ አወጃችሁ እንደገና ጦርነት አገርሽቶበት ብዙ ሂወት አለፎ እያለ እንዳዉም በ1984 ዓ.ም በሱዳን ጠረፍ በጎጃምና በጎንደር በረሃዎች በሻውራ ቋራም በተደረገው ጦርነት እጅግ ብዙ የኢ.ህ.አ.ፓ ታጋይና በአስር የሚቆጠሩ የኢ.ህ.አ.ፓ ከፍተኛ አመራር ተማርከው ደብዛቸው የጠፋበት አለ: መለስ የመድበለ ፓርቲ በሃገራችን መኖር ዳዳስ ነበር ስትሉ ምን ማለት ነው: በኔ እምነት አሁንም መለስና ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በኢትዮጵያ መድበለ ፓርቲ ስርዓት እንዳይኖር ታጥቀው የሚታገሉ የነበሩና ያሉት ናቸው: የአዲሱ ለገሰና በረከት ስምኦን ሌሎች ይህ መፅሐፍ መለስ የሰራውና ያልሰራው ታሪክ ስትፅፉለት ለራሳቹሁ ከመለስ ጋር የነበራቹሁ መቃቃር በትክክል ፍቃቹሁ ነው የፃፋችሁት::

በሃገራችን የፖለቲካ ተሳትፎ ሁሌም ቢሆን ለጥቂት ገዢዎች ብቻ የተፈቀደ ነበር ይላል: ባለፉት ስርዓቶች የነበረ ፖለቲካ ተሳትፎ የገዢዎችና መዋቅራቸው ብቻ እንደነበረ ከአዲስ ራዕዮችና እነ በረከት ልዩነት አይኖርም: እኔ የምለው ያለሁ እኮ በዘመነ መለስ ህ.ወ.ሓ.ትና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ያለው ፖለቲካ ተሳትፎ ስንመለከትም የፖለቲካ ተሳትፎ ካለፉት ስርዓቶች በወረደ የመለስ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ማ/ኮሚቴና ልጆቻቸው ዘርዝራቸውና ዘመድ አዝማድ ከዛ አልፎ ለኢ.ርትራ ዝርያ ተሳትፎ የፈቀደ ስርዓት ነው::

"ገፅ 36 አዲስ መስመር 2 መስመር 1: በመለስ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አመራር የተገነባው ስርዓት ዉበት በፓርቲዎች መካከል ለማሸነፍ የሚካሂደው ትግል አስተዳደራዊ ድጋፍ ሳይኖሮው እንዲካሄድ መደረጉ ነው: በተጨማሪ የዚህ ስርዓት ሌላ ዉበት ፅንፈኛ አቋም ያላቸዉን ጨምሮ የተሳሳተ አመለካከት ያላቸው ፓርቲዎች ለዴሞክራሲያዊና ነፃ የሃሳብ ትግል ተጋልጠው የአመራር ኃላፊነት

የሚጨብጡበት ሁኔታ መፈጠሩ ነው: እንደገና በመለስ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የተገነባው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚመራባቸው ፖሊሲዎች እስትራተጂዎች በዚህኛዉን በዛኛዉን የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል በሚካሄዱ የሰለጠነ ዴሞክራሲያዊና ሕግ መንግስታዊ ትግል በሕብረተሰብ ደረጃ የበላይነ ትን ለማግኘት መቻላቸው ነው::"

መለስና ህ.ወ.ሓ.ት ስልጣን ከያዙበት ዘመን ጀምረው ዉበት ያለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ዉድድር ከመለስ አስተዳደራዊ አመራር ዉጭ የተሰራ ጭራሹን አልነበረም: ከነዛ ለይስሙላ ተብለው በአንድ በኩል ነፃ አደረጃጀት ነፃ የፓርላማ ምርጫ ዉድድር ፈቅደናል ብለው በሃገርና በዓለም ደረጃ ሲያታልሉና ሲያደናግሩ: በሌላ በኩል ደግሞ የሃገራችን የምርጫ ምህደራ ከፌደራል ምርጫ ቦርድ እስከ ቀበሌ የነበሩትና ያሉት የምርጫ ቦርድ ኃላፊዎችና መዋቅራቸው እስከ ታዛቢዎች የአንድ ፓርቲ አባላት ዘርግተው ምርጫዉን አስተዳዳራዊ ብቻ ሳይሆን ፍፁም ዓፋኝና ለተቃዋሚ ፓርቲዎች የዴሞክራሲያዊ ምህዳር ዓፍነው በመያዝ የተፈፀመ የምርጫ ዉድድር ነበር::

ሌላ የመለስ ዉበት ያስብለው ቢኖር ፅንፈኛ አቋምና የተሳሳተ አመለካከት ያላቸው ፓርቲዎች በዴሞክራሲያዊና ነፃ የሃሳብ ትግል ከማጋለጥ ከሕብረተሰቡ እንዲገለሉ ማድረጉ ነው: አዲስ ራዕዮች ያለፉት 21 ዓመታት 4 ምርጫዎች ተካሂደዋል: በነዚህ ምርጫዎች የመለስ የዴሞክራሲ ዉበት በተላበሰበት አኳኋን ተፈፀሞ ነበር ማለታቹሁ ምን ያህል ከ80 ሚልዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ደግማቹሁ ደጋግማቹሁ የምታታልሉት ያላቹሁ መሆናቹሁ የኢትዮጵያ ህዝብና ዐለም የሚያውቃቹሁ መሆኑ አለማወቃቸሁ ነው ችግራቹሁ::

ሐቁ ግን በመለስ ስልጣን ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ሃገራችን ከጥይት ጭሆትና ሰው በግደልና መገደል: ከሃገር ሃብት ዉድመት በዜና አታወጡት: የሃገራችን ወህን ቤቶች ጦርነት ባወጁትና በሰላም የሚታገሉ ፓርቲዎች አባላትና መሪዎቻቸው በጋዜጠኞች ሞልተው ተጣበው ይገኛሉ: የመለስ ዉበት እነዚህ ዜጎች በእሱር ቤት ማጎር

ከሆነ: ይህ ዉበት ሳይሆን ዉበታችን አያድርገው: በአሁኑ ጊዜኮ በምስራቁና በደቡብ ሃገራችን ኦነግ አብነግ የኦጋዴን ሶማል ፓርቲዎ ች በምዕራብ ደገሞ የጋምቤላና የኦነግ ፓርቲዎች: በሰሜን ሻዕቢያን ተጠግተው አማራጭ አጥተው ሃገራቸዉን የሚያደሙ ያሉ ደምሂት ሃርነኞች ከፋኝ: እንዲሁም የኦሮሞ ፓርቲዎች በየ ቀኑ ይዋጋሉ ይገድላሉ ይሞታሉ ሀብት ያወድማሉ: ታድያ ይህ የመለስ ዴሞክራ ሲያዊ ዉበትን ያረጋግጣል: በኔ እምነት መለስና ድርጅታቸው ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የደርግን ፋሽስታዊ ስርዓት አስወግደን በመቃብር ፋሽስቶች ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ያብባል እያለ የዴሞክራ ሲ ጮራ አለ እያለ በ100ሺ የሚቆጠር ህዝብ ቀብሮ የተመለሰ: የደርግን ስርዓት እንዲያብብ መደረጉ የፋሽስቶች ሌጋሲ ዉበት ተከትሎ እቺን ሃገር በጣጥሷት የሉአላዊነቷና ነፃነቷ ተበላሽቶ አንድነት የላላ ዉበበት ኣላብሷት ነው ያለፈው: አዲስ ራዕዮችና የአዲስ ራዕይ ፀሐፊዎች እነ አዲሱ ለገሰና በረከት ስምኦን በሃገራችን የሌለ ዉበት ህዝቡ ለሚያውቀው ራሱ የጭቆና የርሃብ የስደት ቀማሽ ሆኖ ፍዳው እያየ ቁልጭ ብሎ እንደመስታወት እየታየው ልታታልሉ ት መሞከራቹሁ ሁለተኛ በ80 ሚልዮን ህዝብ ግፍ እየፈፀማቹሁ እንዳላቹሁ ነው የሚገባኝ::

አንድ ነገር በግልፅ ልንገራቹሁ: የፅንፈኝነት የደፈጣ ተዋጊዎች መፈልፈያ በዓለማችን ብዙሃንነትን የሚጨፈልቁ ሰዎች ሲኖሩ ብቻ ነው በሃገራችን ያሉ ነፍጥ አንስተው የሚዋጉ ደፈጣ ተዋጊዎች በመለስ ትርጉም ፅንፈኞች፣ አሸባሪዎች፣ ነውጠኞች፣ ኪራይ ሰብሳቢዎች፣ የኒዮሊብራሊዝም አራማጆች፣ ጥገኞች፣ የሻዕቢያ የጥፋት መልእክተኞ ች፣ የጉንበት ሰባት ተላላኪዎች የሚሉ ስሞች በመለጠፍ በሰላም ሃሳባቸውን በማራመድ ለሚታገሉ ዜጎች ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ በሰላም እንደመስተናገድ ሆን ተብሎ በመገፋፋት፣ የሚያበሳጩ ንግግሮች፣ ስድቦች፣ ዓፈናዎች፣ የወንጀል ወጥመድ በማጥመድ፣ በወንጀል እንዲከሰሱ፣ እንዲገረፉ

ማድረግ፣ ለሚያቀርቡትን ሃሳብ ሚድያ በእጁ ተቆጣጥሮ ያደረጉና ያላደረጉት ድርጊት በማጋለጥ፣ በደጋፊዎቻቸው ሽብርና ማስፈራራት፣ በመፍጠር፣ ከሕብረተሰቡ እንዲገለሉ ማድረግ፣ ሃገር ዉስጥ ከኖሩ ለስልጣኔ አስጊ ናቸው የሚሉዋቸው ሙሁራኖች የፓርቲ መሪዎች ጋዜጠኞች በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ ለመለስና ለፓርቲያቸው እንዲምበረከኩ ወደ ስደት እንዲበተኑ ግማሾች በማስፈራራት ሽብር የሚለቁ ግማሾች ፓስፖት አውጥተው ቪዛ በማስመታት ሁሉም ዐይነት ፕሬሶች በመጨረስ ከሃገር እንዲጠፉ ያደርጋሉ::

አንዳንድ አብነቶች ልንገራቹሁ: በመለስ የሽግግር መንግስት ዘመን ወድያዉኑ ከጫካ እንደገቡ በሃገር ዉስጥ በዉጭ በጫካ በዱሩ ያላቹሁ ፀረደርግ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች የነበራቹ በየላቹሁበት እንዲሁም ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ደርግን አስወግዶ ኢትዮጵያ ከተቆጣጠረ በኋላ የተፈጠራቹ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ነን ይምትሉ ሁሉ: እቺ ሃገር የሁላችን ስለሆነች የሆነ የተለየ ሃሳብ ይኑር ልዩነታችን እንደለሽግግር መንግስት አቋቁመን እየተግባባን ሕገ መንግስት በማርቀቅና በማፅደቅ እቺ ሃገር ከመበታተን እናድናት ተባለ: ይህ አዋጅ እጅግ ጥሩ ነበር: ትልቅ ቦታም መሰጠት ነበረበት::

ነገር ግን የአዋጅ በወቅቱ ጠንካራና ለ17 ዓመታት ከህ.ወ.ሓ.ት በጦርነት ለተፋለመው ኢ.ህ.አ.ፓ አይጨምርም ነበር: ይህ የሚያሳይ ኢ.ህ.አ.ፓ ብዙ ከፍተኛ ሙሁራን ነበሩት አሁንም አሉ: መለስና ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በረሃ ከረገጡበት ጀምረው ይቅርና በፓርቲ ደረጃ የተደራጀ በህ.ወ.ሓ.ት ዉስጥም ለነ መለስና ለህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች ይበልጣል የሚባል ሙሁር ቦታ አልነበረዉም::

ስለዚህ መለስና ህ.ወ.ሓ.ት በሽግግሩ መንግስት ወቅት በመልካም አዋጅ እንዲሰባሰቡ ካደረገ በኋላ የፈፀመው ወንጀል ቢኖር ባለፉት

ገፃቶች እንደተገለፀው ሁለት ወንጀሎች ፈፅመዋል: አንደኛ በሽግግር መንግስቱ ለገቡ ፓርቲዎች ለማክሰም የመለስና ህ.ወ.ሓ.ት ተቀጥያ በሆኑ ፓርቲዎች በሙሉ ወታደራዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ማሕበራ ዊ ሞራላዊ ድጋፍ በመስጠት በመጠናከር እንዲበታተኑዋቸ ው አደረጉ: ለኦነግና ለአብነግ ሌሎቹም በኢትዮጵያ ለነበሩ ፓርቲዎች በጦርነት አደቀቁዋቸው እስከ አሁንም ጦርነቱ መወናጀል አለ: እነዚህ ፓርቲዎች በጦርነት አዋጅ ብቻ አይደለም የተመቱ ከጦርነቱ ጎን ለጎን ከአሸባሪዎች ከአልታሃድ አልቃዒዳ ከአልሸባብ መርበብ ከአሸባሪዎች ከፅንፈኞች ግንኙነት አላቸው እየተባሉ ዜጎች ወደነዛ ፀረአሸባሪዎችና የአልቃዒዳ መርበብ የሆኑ ተጠቂ የሆኑ ሃገሮች አመሪካ ምዕራብ አውሮፓ ካናዳ አዉስትራልያ ተጠልለው ሃገራቸው በዐይናቸው እየዞረች የኣሳር እንጀራ እየበሉ ይኖራሉ::

ሁለተኛ በሃገር ዉስጥ ያሉ ደፊጣ ተዋጊዎች ጥያቄያቹሁ ምንድንው ብለው ለሰላማዊ ዉይይት ጠርተው በመወያየት ልዩነታቸው በማጥበብ ለሰላም በመቆም አዲስ ስም በመለጠፍ ድራማ በመስራት የነሱ ደጋፊዎች ለሆኑና ዘመድ አዝማድ ማሰር: ማንገላታት ዜግነታቸዉን መንጠቅ ይታያል: ሌላ ቀርቶ ሕገ መንግስትን አክብረው በሰላም ለሚታገሉ የምርጫ ኃይሎች ጋዜጠኞችን ምክኒያት በመፍጠር እየወነጀለ እሱር ቤት እያጎሩዋቸው ነው የነበሩ::

መለስ በ21 ዓመት ወታደራዊ ስልጣናቸው ያለ እሳቸው ፍልስፍና ለዚች ሃገር የሚጠቅም ሪእዮተ ዓለምና ፖሊሲ የለም በማለት የቻይና አንባ ገነን ኮሞኒስት መንግስት የሙጢኝ ብሎ በመያዝ በህዝብ ላይ አሸበራነት የሚፈፅም የነበረ መንግስት ነው::

ጠቅለል ባለ መልኩ ሁሉም ዐይነት ዴሞክራሲያዊ መብቶች በማፈን በሃገራችን ደፈጣ ተዋጊዎች አሸባሪዎች የፈጠሩዋቸው መለስ ነበሩ: በተጨማሪም አሁን እየተፈጠሩ ያሉ ደፈጣ ተዋጊዎችና በመለስና ጓዶቻቸው አሸባሪዎች የአልቃዒዳ መርበብ ይፈጠሩ ያሉ

የመለስ ሊጋሲ ተከታዮች በሆኑ ጓደኞቻቸው ነው: ስለሆነ መለስ በሽግግር መንግስት ይሁን ከዛ በኋላ እስከ ህልፈተ ሞታቸው: ለብዙሃንነት ያልቆመ ለተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ያልተመቹ: በዚህች ሃገር የመለስ አስተሳሰብ የማያመልክ ሰው የማይኖርባት ሃገር: ከላይ እንደተገለፀው የብዙሃንነት አንድነት ሊላላ ያደረገ መለስ ራሳቸው ለራሳቸው የተመቸ ነበረ::

"አዲስ ራዕይ ገፅ 39 አዲስ መሰመር 2 መስመር 2: በአራት ታላላቅ ሃገራዊ ምርጫዎች በዴሞክራሲያዊ ዉድድር አሸናፊ ላለፉ ሃያ ዓመታት ሃገርን ያስተዳደረ ፓርቲ መሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ ተቃዋሚዎች በራሳቸው መሰረታዊ ድክመቶች በዴሞክራሲያዊ ዉድድር ሊያሸንፉ አለመቻላቸው በግልፅ ያረጋገጠበት ብላቹዋል::"

አዲስ ራዕዮች መለስ ህ.ወ.ሓ.ት በአራቱ ሃገራዊ የፓርላማ ዉድድሮች የሃገር ዉስጥና የዉጭ ታዛቢዎች ያረጋገጡት ፍትሃዊ ዴሞክራሲያዊ ታማኝ እንዳልነበረ የምርጫ ኮሮጆዎች በግልፅ በወታደሮች የተቀማበት መለስ ጭራሹን የተርበደበደበት በመስቀል አደባባይ መለስ ሰልፍ መርቶ በተሰበሰበው ሰልፈኛ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መለስን ለመደናገር ሰልፉን አደመቁት: ማን ሊሰርቁት ነው ተብላቹሃል ብሎ እንደነገራቸው የማይታረቅ በስርቆት ብቻ ነው የምናሸንፈው ያላቸው ይመስል መለስ ቆባቸው በእጃቸው በመያዝ ይህ የህዝብ ማዕበል እያለ እንዴት ይጭበረበራል ተብሎ ይገመታል ብለው አስፈሪ የጭንቀት ንግግር የተናገሩበት መድረክ ነበር::

በነጋታው ተቃዋሚ ፓርቲዎች መለስ ከጠሩት ሰልፍ ቢያንስ 4 እጥፍ ብዛት ሰልፍ ወጣ: ከዛ በኋላ መለስና ጓዶቻቸው እንቅልፍ አጡ በትልቅ ጭንቀት ተዋጡ: ወድያው በፍጥነት በሃገር ደረጃ እንዴት ምርጫ እንደሚያፍኑት በሺ የሚቆጠሩ ታጋይ ካድሬዎችና የፀጥታ ሃይሎች ተሰማሩ::

ምርጫው ደረሰ አዲስ አበባ 20 ወንበሩን ተቃዋሚዎች አሸነፉ 100% በጎንደር፣ በጎጃም፣ በሰሜን ሸዋ፣ በመላው ኦሮሞ ሶመል

ዓፋር ወ.ዘ.ተ ተሸነፉ ስልጣናቸው አደጋ ላይ ወደቀ: መለስ በተቻለ መጠን 50+1 እንዳያጡ ዓፍነዉም ቢሆን የምልአተ ጉባኤ ሸንፊት እንደ ማይቀበሉ በተቀዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ሸብርተኛነት አወጁ ከፍተ ኛ የክልልና የፌደራል ባለስልጣኖች ወደ ኮሮጆ መስረቅ ተሰማሩ: እሱም ተደርጎ ምልአተ ጉባኤ አላሸነፉም: እንደገና በብዙ የምርጫ ጣብያዎች ተቃዋሚዎች ኮረጆ ስለሰረቁት ቆጠራ ስለተበላሸ እንደገና ምርጫ ይካሄድ ተባለ: ተቃዋሚዎች አልተቀበሉትም: ገለልተኛ ያልሆነ ምርጫ ቦርድ በነዛ መለስ የተሸነፈባቸው ቦታዎች እንደገና ምርጫ ይካሄዳል ብሎ ወሰነ ብዙ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ማ/ኮሚቴ የተሸንፈዉበት የምርጫ ጣብያዎች በሁለተኛ ምርጫ አሸንፊው ተብለው ምልአተ ጉባኤው ሞላ መለስም ኡፈይታ አገኙ: ስለሆነ መለስ ባለፉት 4 ታላላቅ ምርጫዎች አላሸነፉም ብቻ ሳይሆን የወጣለት ፋሽሽታዊ ግፍ በመፈፀም የምርጫ ወረቀት በመስረቅ በስልጣን የቆዩበት ዘመን ነበር::

መለስ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አሸንፈናልና ድምፃችን ይጠበቅልን ብለው ከመረጣቸው ህዝብ አደባባይ ወጡ: መለስ በወቅቱ የአድማ በታኝ ፖሊስ ስለአልነበራቸው ከሃገር መከላከያ ሚኒስተር ወታደሮች እንደአግአዚ ክፍለጦርና ሌሎች ክፍለጦሮች በትላልቅ ከተሞችና ገጠር ተሰማሩ: በተለይ አዲስ አበባ ለመለስ የፈንጂ ወረዳ ሆነች: ብዙ ሰው በጅምላ ተገደለ በጭነት ማኪና እየተጫነ ዝዋይና ሸዋሮቢት ብርሸለቆ ጦላይ ታጠቅ ጦር ሰፈር በጎንደር ጎጃም በትግራይ ኦሮሞ ደቡብ ህዝቦች እጅግ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ታሰሩ ተገረፉ አካላቸው ጎደለ::

እንግዲህ አዲስ አበባ የነበረ ህዝብ ከብዙ ክልሎች የተሰበሰበ ስደተኛ ወዝአደር ነጋዴ ወ.ዘ.ተ ነው: በአዲስ አበባ የሞተው ወጣት ከ200 አይበልጥም ነው ያሉን: የሞተ ሰው ወደ አዲስ አበባ ለንግድ ለስራ ለኮንስትራክሽን ሸቅል መጥቶ በዛው የቀረ እናቱ ትቁጠረው እንጂ ምንም የሚታወቅ ነገር የለም: በየክልሉ ቁጥራቸው

የማይታወቅ የታሰሩ የተገደሉም ነበሩ: ታድያ መለስ በ4 ምርጫ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተወዳድረው አሸንፈው ሃገር የመሩ ይላሉ: እዚህ ላይ መንግስቱ ሰው ገዳይ ነበር መለስም ብዙ ሰው ገድለዋል: ታድያ መለስ ምን ዐይነት ስም ይሰጣቸው: የተከበራቹሁ አንባብያን በትግራይ ክልል እንኳ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ተመራጭ ባልነበራቸው ቦታዎች መለስና ፓርቲያቸው የተሸነፉበት ነበር: እንደ አብነት ለመጥቀስ በዋጀራት 13ሺ መራጭ በመሆኒ 25ሺ መራጭ በአላማጣ 8ሺ መራጭ በዓድዋ 460 በመቀሌ ቀበሌ 03 ዓይደር 04 4ሺ መራጭ በሽሬ 3400 በሰሐርቲ ሳምረ በተንቤን በአክሱም በማይፀብሪ በሑመራ በወልቃይት በሙቶሺ የሚሆን ህዝብ ተወካይ ባልነበራቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች መርጠዋል: ስለዚህ በ1997 ምርጫ ይቅርና በሌሎች ክልሎች በትግራይ እንኳ በብዙ ተመርጠዋል::

ሌላ መለስ በ1997 ዓ.ም ምርጫ ዘረኝነት ቅስቀሳ አካሂደዋል: ይህ እንደአብነት ተቃዋሚዎች ይህ አደረጉ ኢንተርሃሞኝ በኢትዮጵያ ይፈጠራል ብለው ቀስቅሰዋል እቃ ወደ ቀበሌ ትግሬ ወደ መቀሌ አሉ ብሎ መፈክር ማን መሆኑ አይታወቅም: ይህ ታሪክ ያጋለጠው ይሆናል ሌላ ለትግራይ ተወላጆች በልዩ ቅስቀሳ በማድረግ የትግራይ ህዝብ በሌሎች ቢሄሮች ተጠርጣሪ እንዲሆን አድርገዋል: ይህም ታሪክ ለወደፊት ያጋለጠው ይሆናል: መለስና ጓዶቻቸው በአዲስ አበባ ለምርጫው ደላላ ታክሲዎች ነጋዴዎች ሌሎች ሕብረተሰብ የግብር ቅጣት እንዳይከፍሉ በአርከበ ዑቅባይ ታውጀዋል: ሌላ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባል አዲስ አበባ ከነበሩና ከሌሎች ክልሎች እየሳቡ መሬት በመሸንሸን አንድ ሰው ከ5 በላይ ቦታ እየያዘ ለመለስ ደጋፊ እንዲሆን ተደርገዋል: ይህ ደግሞ ትልቅ የመለስን ሙስና ነበር::

መለስ በ2002 ዓ.ም በተቃዋሚ ፓርቲዎች በተለይ በመድረክ በሃገር ደረጃ በትግራይም የመድረክ አባል ድርጅት የሆነው ዓረና ትግራይ በብዙ ቦታዎች አሸንፈዋል: ነገር ግን መለስና መዋቅራቸው

አፍንዉ.ታል: ብዙ ሰው ታስረዋል የመድረክ ተወዳዳሪዎች በማይታወቁት ባንዳዎች ተገድለዋል: ይህ ደግሞ የሃገር ዉስጥና የዓለም ታዛቢዎች ያረጋገጡት ነው::

ከ1997 ዓ.ም በፊት የነበሩ ሁለት የምርጫ ዘመናትም ለተቃዋሚ ፓርቲ ለፅሕፈት ቤት ኪራይ ያካራየ ለተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አብሮ የሄደ የበላ የጠጣ በሃዘንና በደስታ የተሳተፈ ሰው ሁሉ ተገሎ እንደጠላት ታዩ: ከሁሉም ዐይነት ጥቅማ ጥቅሞችን ከሴፍት ኔት የድርቅ እርዳታ የአረጋውያን እርዳታ ከመስጠት የተገለሉ ነበሩ: ስለሆነ አዲስ ራዕዮች የመፅሄት ስትፅፉ ህዝብ በዐይኑ ያየው የሚያውቀው በተግባር ግፍ የተፈፀመበት በሂወት እያለ እንዴት ትሽፍኑት አላቹሁ::

አንዳንድ ጊዜ አዲስ ራዕዮች በቤት ዊስኪ 30 (50) ሽብር በሚገዛው ብለው ለበል ጎጭ ያደረጉ የሰንጋ ቁርጥ እየበሉና ጎጭ እያደረጉ ነው የፃፉት: እያልኩኝ ተጨነኩ: ወይ ደግሞ ለመለስ ያደነቁ መስለው መለስ ወንጀለኛ ነበር ብለው እያጋለጡት ያሉ የሚል ጥያቄም ብቅ ይለኛል: እንደገና በአሁኑ ጊዜ አዲስ ራዕይን የመለስ ሌጋሲ ተከትለው ይምራት እያሉ በረከትና አዲሱ ለገሰ ሬድዋን ናቸው እኒህ ሰዎች መለስ አስቀይሙቸው ይኖራል ምናልባትም ግንኝነት እንዳልነበራቸው የተረዳሁት: በመሆኑ ግማሽ ያህል ከፈተሽኩ በኋላ በጥልቀት ለመታዘብ ወሰንኩ ከእንግዲህ ወድያ በዝርዝር ለመፈተሽ እሞክራለሁ ተከታተሉኝ: ቀጠል አድርገው አዲስ ራዕዮች ያሉት ቢኖር ተቃዋሚዎች በራሳቸው መሰረታዊ ድክመቶች በዴሞክራሲያዊ ዉድድር ሊያሸንፍ አለመቻላ ቸው በግልፅ አለመረጋገጣቸው ነው ብለዋል::

አዲስ ራዕዮች ተቃዋሚዎች መሰረታዊ ድክመቶቻቸው በዴሞክራሲ ያዊ ዉድድር አለመቻላቸው በግልፅ ማረጋገጥ ይቻላል የሚለው አልስማማም እነዚህ ሰዎች በአጭር ጊዜ ህዝባዊ ማዕበል ፈጥረው በሰላማዊ መንገድ ታግለው ለመለስና ፓርቲው ማቆምያና መርገጫ

አሳጥቶዋቸው ነበር: እዚህ ላይ ምንም ድክመቶች አልነበሩም እነዚህ ሰዎች መለስና መዋቅራቸው ሁሉም ዐይነት ብዙሃን መገናኛዎች የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ማኪናዎች ትናንሽና ትላልቅ: የመንግስት ገንዘብ በሁሉም አካላት የመንግስት ሰራተኛ: በመንግስት የህትመት ድርጅቶች በትእምት ድርጅቶች በጥረትና ድንሾ ድርጅቶች በቢልዮን የሚቆጠር ገንዘብና ቁሳቁስ እየተጠቀሙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ግን በጣም ጥቂት ገንዘብና ቁሳቁስ ይዘው ለመለስ ስርዓት ማንቀጥቀጣቸው እጅግ ጠንካራዎች ነበሩ::

የመለስ መንግስት እኮ የተቃዋሚ ፓርቲና ደጋፊዎቻቸው ድምፃችን ተሰርቀዋል ይመለስልን ብለው ሲቃወሙ ለመሪዎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ነው: ተቃዋሚዎች በማሰር በቃሊቲና በክልሎች ወህኒ ቤቶች ታጎሩ: መለስ በዛን ወቅት ከመንግስቱ ኃይለማርያም የባሰ የአንባ ገነንነት ፋሺስታዊ ገፅታ ነበራቸው: የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ዕድሜ ልክ ተፈረደባቸው: በወህኒ ቤትም ከዘመድ አዝማድ እንዳይገናኙ በጨለማ ቤት ተዘግተዋል: ከዛ በኋላ ጠንካራ ታጋዮች ከየት ከየት ይመጣሉ: እኔ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ስህተት የሚለው መለስ ምልአተ ጉባኤ ሞምላቱ (50+1) ከተረጋገጠ በኋላ አሸነፍንችሃል ብሎ የፈቀደላቸው አዲስ አበባ ጨምሮ ይዘው ፓርላማ ገብተው ቦታ በመያዝ መታገል ነበረባቸው: ድርቅ ማለት አልነበረባቸውም: ሆን ብለው ዘረኝነት ያስፋፉ የነበሩ ሰዎች (ባንዳዎች) ለይተው እያወቁ ዝም ብለው ይነዱ ነበር: ሌላ ቀርቶ በእስር እያሉም አብረው የታሰሩ ባንዳዎች ነበሩ::

1. ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመላው ኢትዮጵያ የታሰሩ የተገደሉ ደብዛቸው የጠፋ አያውቃቸዉም ነበረ
2. ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጥራታቸው ያልጠበቁ ነበሩ: የነበረው ቅንጅት ትልቅ አካሉ የመለስ አካል ነበር
3. ያደርጉት የነበረ ሰላማዊ ሰልፍ የተማእከለ አልነበረም መለስና ጓዶቹ መጠቀምያ ተጠቅመውበታል በተጨማሪ

እንዳንድ የተቃዉሞ መሪዎች ትእግስትና ማስተዋል ይጎድላቸው ነበር፡ ባልተማከለ መንገድ የመግለጫ ድንፋታ ያበዙ ነበር

4. በሰላማዊ ሰልፍ ጊዜ ሰልፉ በልዩ ቦታና የመንግስትና የህዝብ ሃብት በሚያወድም መሆን አልነበረበትም በዚህ ላይ መለስ ተጠቅመውበታል
5. ከታሰሩ በኋላ ከመንግስት (ከመለስ) መደራደር አልነበረበት ም ቢሞቱም ይሙቱ በትእግስት መቆየት ነበረባቸው፡ የሃገራችን ህዝብና የዓለም መንግስታት አብሮዋቸው ነበሩ፡ በተረፈ 1997ና በ2002 የተቃዋሚ ጥንካሬ እንደአዲስ ራዕዮችና አለቆቻቸው እንደሚሉት ደካማ አልነበሩም፡ እንዲያዉም ይህ ትውልድ ከነሱ ተምሮ ሌጋሲያቸው ሊከታተል የሚችለው ጀግንነት የፈፀሙ አባቶች ናቸው፡ ልናመሰግናቸውና ልናከብራቸው ይገባል፡

## ክፍል 14

## "ሶስት ጊዜ በቀን መብላት በአጭር ጊዜ ያሳካ መሪ"

"አዲስ ራዕይ ገፅ 40 8ኛ ዓመት ቅፅ 4 ልዩ እትም 2005 መለስ ወደ ስልጣን ከመጡ በአንድ ወቅት በአስር ዓመት ዉስጥ ምኞታቸው ሲገልፁ የኢትዮጵያ ህዝብ በቀን 3 ጊዜ በልቶ ጠግቦ እንዲያድር መጠለያ ጥሩ ልብስ እንዲኖሮው እናደርጋለን ሲሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቀዋል፡ በአርእስቱ ላይ የሚገልፀው ያለ ደግሞ 80 ሚልዮን ህዝብ ሶስት ጊዜ በልተው እንዲያድሩ ያሳካ መሪ ይላሉ ራዕዮች፡፡"

ሁኔታው ሃቅ ነው ዉሸት እንየው፡ መለስና ጓዶቻቸው ወደ ወንበር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ በከተማም በገጠርም ንሮ ዉድነት ደርግ ከነበረበት ወቅት እየባሰበት፡ የኢትዮጵያ ብር የመግዛት አቅሙ እያሽቆለቆለ የመጣ በመሆኑ ደግሞ ሥራ አጥነት ተስፋፍቶ የገጠርና

የከተማ ህዝብ ያታ በማይለይ ወደ ስደት እንደጎርፍ የሚሄድ ነው ያለው::

መለስ ለነበረው ረሃብና ሰቆቃ ለመፈታት በፓርላማ ስብሰባ በተለያዩ መድረኮች በሃገራችን ድህነት ሊጠፋ ከተፈለገ ቅድሚያ በገጠር ያለው ድህነት ማጥፋት አለብን: በገጠር ያለው የገበሬ ጡንቻ በዘመቻ መልክ ወደ ልማት እናስገባው ብለው መናገራቸው ይታወቃል ያ ንግግር ግን ንግግር ከመሆን አልፎ የሃገራችን የግብርና ሙሁራኖች ተመራማሪዎች ሳይንቲስቶች የኢኮኖሚ ተንታኞች የተሳተፉበት ሳይሆን መለስ ብቻቸው በተለቪዥን መስኮት የሚያስተላልፉት ዲስኩር ነበር: ሌላ ቀርቶ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የአመራር ጓዶቻቸው እንኳን አያማክሩም ነበር::

መለስ ደርግ ከወደቀ ማግስት የገጠር ገበሬ ራሱ አይቀበልም አገሬው አያጠግብም የሚል ሃሳብ የመጣ በመለስ ስልጣን አልነበረም: መለስና ጓዶቻቸው ታሪክ ለሰሩት ሰዎች ማጎለት እርማቸው ስለሆነ ነው እንጂ ለኢትዮጵያ ህዝብ የምግብ ዋስትና ሊረጋገጥ ከሆነ መጀመርያ የተፈጥሮ ሃብት መንከባከብ አለብን: አሁን መጀመር አለብን ብለው ሃሳብ ያመነጬ በ1978 ዓ.ም በዉጭ የነበሩ የእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ባለሙያዎች ነበሩ: ከነሱ ዉስጥ እነ ታጋይ መለስ በዛብህ ዶ/ር አሰፋ አብረሃ በተለይ መለስ በዛብህ በትግራይ ክልል በአበርገሌ ወረዳ ሸዋጣ በተባለ ምድረ በዳ ልዩ ሳንስ ተጠቅሞ ከሄክታር 60 ኩንታል ማሽላ እንዲመረት ያደረገ ነበር: ያሉበት ስብስብ ነበር: እነዚህም እኛ እንጀምረው በሚል በአውሮፓና አመሪካ አንድ ማሕበር በማቋቋም በትግራይ ክልልና በሰሜን ጎንደር ፀለምት ሰቆጣ የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ እንጀምር ብለው በወቅቱ የነበሩ ደኖች እንዳይወድሙ በማሰብ ለህዝቡ ማስተማር የአፈርና ዉሃ ጥበቃ እንዲደረግና ተራራዎች ሁሉም እርከን መስራት ኋላም እስከ ሜዳ ወርደህ እርከኑ መስራት የሚል ነበር: ለዚሁ ለመስራት በሚልዮን

የሚቆጠር መቆፈርያዎች ዶማ አካፋ መላኪዖ በእርዳታ ገብቶው ለያንዳንዱ ገበሬ ተሰጠው::

አንድ ዶማና አንድ አካፋ እንዲሁም አንድ መላኪዖ ለ 5 ሰዎች እንዲሰዋ ተደረገ: በዛ መሰረት ከጦርነት ጎን ለጎን ነፃ በወጡ ቦታዎች በመጠኑ ተጀመረ: የገባ ዶማና አካፋ ለጦርነቱ የመኪና መንገድ መስርያና ለምሽግ መቆፈሪያ ተጠቀሙበት: በዛን ጊዜ መለስ በህ.ወ.ሓ.ት ሊቀመንበር አልነበሩም በፖለቲካዊ ኮሚቴ ሁነው የፖለቲካ ካድሬን አሰልጣኝ ነበሩ: በ1983 ዓ.ም ደርግ ከተወገደ በኋላ መለስ ስልጣን ይዘው የክልል መዋቅር ተዘርግቶ የግብርና ሙያ መዋቅር በወረዳ ደረጃ ከተዘረጋ በኋላ የዉሃና አፈር ጥበቃ በሰሜን ኢትዮጵያ በትግራይ ብቻ በትግሉ ወቅት ተጀምሮ የቆየው ደርግ ከህ.ወ.ሓ.ት በፊት በምስራቃዊ ዞን በስፋት ጀምሮት ስለቆየ የመለስ ስረዓትም ቀጠለበት::

የመለስ ስርዓት የአፈርና ዉሃ ጥበቃ ቢቀጥልበትም በትግራይ ብቻ ካልሆነ በሌላ ክልል ብዙ አይሰራበትም ነበር: በትግራይ ክልል ግን የትግራይ ተወላጆች የሆኑ ሙሁራኖች እንደና ዶክተር ሙሉጌታ በዛብህ በሳይንሳዊ ጥናት የተደገፈ አብዛኛው የኢትዮጵያ ታራሽ መሬት ድርቅ ስለሚያጠቃው ክረምት በመጠበቅ ሰብል ዘርተህ በቂ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ አይቻልም: ስለሆነ ህዝብ የምግብ ዋስትና ሊረጋገጥለት ካተፈለገ በጋም በመስኖ በማልማት ክረምትን ጨምሮ ሁለት ጊዜ የእርሻ ስራ በመስራት ሰብል ማፈስ አለበት አሉ: ስለዚህ በሁሉም ተፋሰስ ያለባቸው ቦታዎች በጋና ክረምት የሚፈሱ መካከለኛና አበይት ወንዞች በመገደብ ህዝቡ ወደ መስኖ ስራ ከገባ ብቻ ነው የሚል ሃሳብ አቅርበው በተጨማሪ ብዙ ግድቦች ከተገደቡና መስኖ ከተስፋፋ የእህል ሰብል ብቻ ሳይሆን ሌሎች የገቢ ምንጭ ሊያመጡ የሚችሉ የእንሰሳ ሃብትም በማራባት ጥሩ ዉጤት ይኖሮዋል ብለው ፕሮጀክት ቀርፀው ያለአንዳች ክፍያ አጥንተው ለትግራይ ክልል አስተዳደር አቀረቡ: ያን ጥናት የክልሉ ስራ

አስፈፃሚ ተቀብሎ ለመለስ አቀረበ: መለስ ከብዙ ጊዜ በኋላ ይቀጥል ብለው ፈቀዱ: ከፈቀዱ በኋላ በትግራይ ክልል ሳርት የሚባል ድርጅት በ15 ዓመት 500 መካከለኛና ትናንሽ ግድቦች እንዲሰሩ በተጨማሪም ትላልቅ ግድቦችና ጥልቅ ጉድጓዶች በጀት ተመድቦባቸው እንዲጠኑ ታዘዘ: በሌሎች ክልሎችም ያ የዶክተር ሙሉጌታ በዛብህ ጥናት እንዲሰራጭ ተደረገ ለዚሁ በልዩ ታይቶ አባይ ፀሃዬን እንዲመሩት ተደረገ: እነዛ ሃሳቡን ያመነጩ ሙሁራኖቹም ለክልሉ የገባ ብርና ባለሙያዎች ከህዝብ የተውጣጡ ንቁ ገበሬዎች ስልጠና ሰጥተው ካበቁ በኋላ ለዚሁ ስራ የሚሰሩ ብዙ መሃንዲሶች ተመደቡ: ግድቦች በህዝብ ነፃ ጉልበትና በጥቂት ማሽነሪ ተጀመሩ: ለሙከራ ያህል በመቀሌ በዉቅሮ በአክሱም በሽሬ በአድያቦ በሰሐርቲ እያንዳንዳቸው ከ80 እስከ 100 ሄክታር በመስኖ ሊያጠጡ የሚችለሉ ግድቦች ተሰሩ: እነዛ ግድቦች ስራ ሲጀምሩ ሁሉንም ለማለት ይቻላል ከ250 ሄክታር በላይ ታራሽ መሬት እያጠጡና ገበሬው በዓመት ሁለት ጊዜ ምርት እያፈሰ የንሮ ለውጥ ለማምጣት አልፎ ብዙ ገበሬዎች ሃብታም ሁነዋል::

የነዛ ሙሁራኖች ጥናት ስልጠና ሲሰጥ የትግራይ ሰዎች ብቻ አይደለም ያሰለጠኑ የአማራ ክልልና የኢርትራ ሙሁራኖችም ነበሩ: የኢርትራ ሰዎች ለምን ሰለጠኑ ለሚለው መልሱ መለስ ስለ ፈቀዱላቸውና ወደውላቸው ነው::

ሳርት ተቋቁሞ ብዙ ግድቦች ከገደቡ በኋላ በየ ዓመቱ 33 ግድቦች በ15 ዓመት 500 ግድቦች ለመገደብ ዕቅድ ወጥቶ በሬድዮ በተለቪዥ ን ታወጀ በክልሉ ጉባኤም ፀደቀ: ብዙ ተባለ ከግድቡ ጎን ለጎን የራያ ሜዳማ ቦታ (ራያ ቫሊ) የሚባል በመስኖ ለመስራትም በ40 ሚልዮን ብር ባጀት ተመድቦ ጥናት ተጀመረ: የትግራይ ሙሁራኖች በነፃ ያጠኑት የተጀመሩ ግድቦች ዉጤት ስለተገኘበት በአማራ ክልልም ተጀመረ: ኢርትራ የወሰዱዋትን ስልጠና ተሎ ብለው ወደ ተግባር በመግባት ብዙ ግድቦች በመገደብ ብዙ የመስኖ ስራ አስፋፉ::

ድህነትን ለማጥፋትና የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ በትግራይ ተወላጅ ሙሁራኖች ጥናት በክልሉ መሪዎች ፍላጎትና ጥረት ከተጀመረ ጥቂት ቆይቶ በ1993 ዓ.ም የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ መሰናጠቅ ተያይዞ ይመስላል የሳርት የግድብ ስራ እንዲዳከም ተደረገ: ቆየት ብሎ ዉጤት የሌለው የነ ገብሩ አስራት በግብታዊነት ጠባብ አመለካከት የተመሰረተ ድርጅት ተብሎ በሳርት የነበሩ ብዙ መሃንዲሶች በመሰናበት ወደ መዘጋት ወሰኑ: ልብ በሉ ይህ የዉሃ መገደብ ጉዳይ በአመራር ተጀምሮ እስከ አሁን እየሰራ እያለ በዛን ጊዜ መለስ ከራሳቸው ቂም ተነስተው የገብሩ አስራትና መሰለቹ ፍልስፍና ነው ብለው ለሃገራችን ስትራተጂካዊ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ድርጅት ዘጉት፡፡

መለስ ሳርትን የሚያህል በሳይንሳዊ ጥናት የተመሰረተ የምግብ ዋስትና ሊያረጋግጥ የሚችል ድርጅት ዘግተው በግብታዊነት ተነስተ ው ወደ ኋላቀር ዉሃ ማቆር (ሆረየ) የሚባል ለአርሶ አደሩ የሚያዳክ ም ሃሳብ አምጥተው ገበሬው በየ ማሳው ጉድጓድ ቆፍሮ የክረምት ዝናብ በማቆር መስኖ በማስፋፋት ድርቅ በመቋቋም የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ይቻላል ብለው አወጀ የመንግስትና የፓርቲዎች ብዙሃን መገናኛ የሆረዮ ጠቃሚነት ለህዝቡ ለማሳመን ሌት ተቀን ዲስኩራቸውን እየነዙ ሰነበቱ: ሆሮየ ዉሃ ማቆር አንድ ዓመት ሳይቆይ ጠቃሚነቱን ወደ በክረምት ይዞት የቆየ ዝናብ አቆመ ሳምንት ሳያስቆጥር ወደ ሰማይ ተነነ: ይህ ሁኔታ ለመለሰና ጓዶቻቸ ው የምጥ ህመም ፈጠረባቸው: አሁንም ይህ ሁኔታ ህዝቡ ሳያውቀ ው መላ እናስፈላልግ ብለው የሆሮየ ዉሃ ወደ መሬት ስለሰረገ ዉሃው እንዳይሰርግ የሚከላከል ላስቲክ ከህንድ እንግዛ ተብሎ ለትግራይ ብቻ ያለ ሙያቸው በግብታዊነት በእነ ተክለወይኒ አሰፋ የትግራይ እርዳታ ማሕበር (ማረት) ዳይሪክተር በ200 ሚልዮን ብር ተገዛ: ሃገር ቤት ገብቶ ገበሬው በብድር በወለድ የሚታሰብ በደደቢት ብድርና ቁጠባ ተመዝግቦ ላስቲኩን እንዲወስድ ተገደደ፡፡

ላስቲኩም ዉሃው ወደ መሬት ለማስረግ ቢከላከልም ትነቱ ግን የባሰውን አቃላጠፈው: አርሶ አደሩም ምንም ሳይጠቀም ዉሃ ዘግኖ ቀረ: መለስም በትግራይ የደረሰ በግብታውነት የታጀበ ኪሳራ አልበቃ ም ብሎዋቸው በአማራ በኦሮሞ በደቡብ ክልሎች የህንድ ላስቲክ እንዲገዙ አድርገው ለኪሳራ ዳረጉዋቸው: ብዙ ገንዘብ ወጪ ሁኖ የተገዛ ላስቲክ በአሁኑ ጊዜ በቤት መጠለያ የሰርግና ሌሎች ዳስ መስርያ ሆኖ ይገኛል: ገበሬዉም በብድርና ቁጠባ ባንኮች ከንቱ ከስሮ ቀረ::

ይህ ኪሳራ አልበቃም ብሎ እያንዳንድ ገበሬ የዉሃ ባንክ መኖር አለበት ተባለ: ጥናት የጎደው ስላለ ይህም ከሸፈ: በቃ ምን ይደረግ መለስና ጓዶቻቸው ወደ ጭልምልም ገቡ::

መለስ ተመልሰው በትግራይ ተጀምሮ የነበረ የሳርት ፕረግራም የነ ገብሩ አስራት በግብታውነት የታጀበ ብለው የኮነኑት ሳርትም አፍርሰው ወደ ሌላ ስራ አሰማርተዉት የነበረ እንደገና ይቋቋም ተብሎ እየወደቀ እየተነሳ እየሰራ ይገኛል::

መለስ የልማት ፈላስፋ ነበሩ ድህነት በማጥፋት ህዝቡ ለአንድ ጊዜ በልቶ የማያድር የነበረ በመለስ ጥረት በቀን 3ጊዜ በልቶ እንዲያድር ያደረገ የተሳካለት መሪ ስትሉን የቱ ላይ ነው: በአሁኑ ጊዜ ይቅርና 3ጊዜ ለመብላት ይቅር ቁርስ ምሳ ራት ቁምራ አመጋገብ አይደለ እየተጠቀመ ያለው: 3ጊዜ በልቶ እንዲኖር ያሳካ መሪ ስትሉን ራዕዮች: መስፈርታቹሁ ምንድነው ምናልባት እናንተ በቤተ መንግስት አካባቢ ስላለቹሁ ምርጥ በሆኑ ኩክስ (የምግብ ሰራተኛ) የተሰራ በአስር የሚቆጠር የምግብ ዓይነት ጠረጴዛው ሙሉ ቀርቦ ስትበሉ ቢራ ማወራረጃ አፕሬትቭ ወይን ዊስኪ ሃይላንድ ዉሃ ይሻላል እያላቹሁ እያማረጣቹሁ ስትበሉ ስትጠጡ ነው ወይ: የእናንተ ጓደኞች በሆኑና አብሮዋቹሁ ሲበሉ ሲጠጡ ስታዩ የኢትዮጵ ያ ህዝብም እንደዚሁ ነው የምትሉን ያላቹሁ: አሁን የኢትዮጵያ ወጣት

የገጠር የከተማ ሙሁር ነጋዴ አምራች ኃይል የሚበላ አጥቶ መጠለያ ያጣ የወደፊት እጣ ፈንታው የጨለመበት ነው ያለው::

"ኢ.ህ.አ.ዴ.ግና አርሶ አደሩ ባካሄዱት ርብርብ በኢትዮጵያ የርሃብ መቅሰፍት መውረድ ካቆመ 20 ዓመታትን ተቆጥረዋል: በድምሩ በ10ሺዎች የሚቆጠሩ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ካድሬዎች በመቶሺዎች የሚቆጠሩ የግብርና የጤና የአነሰተኛና ጥቃቅን ኤክስቴንሽን ሙያተኞች አሰተማሪዎች የገጠር ብድር ሰራተኞች ወ.ዘ.ተ: በሕብረት ባካሄዱት ሰፊ የለውጥ እንቅስቃሴ አስከፊ ድርቅ ባለበት ጊዜም ሳይቀር 3ጊዜ ሳይበላ የሚያድር ኢትዮጵያዊ ቁጥሩ እጅጉን ቀንሰዋል::"

የርሃብ መቅሰፍት ወርደዋል ስትሉ እንዴት ነው ደጋግሜ እንደ ጠቀስኩት የኦሮሞ የሱማል የአማራ የጉራጌ ከንባታ ሃዲያ ጋምቤላ ትግራይ ሴትና ወንድ ወጣቶች አዛውንቶች ሳይቀሩ የት ነው ያሉ ኪንያ ጀቡቲ ሱዳን ኡጋንዳ ግብፅ ኢስራኤል ደቡብ አፍሪካ ዓረብ ሃገሮች አውሮፓ አመሪካ ወደ ሌላ የገባው ህዝብ የሚበልቱም የሚቀምሱም የሚለብሰው የሚጠለልበት ታሞ የሚታከምበት ስለአጣ አይደልም በየአህጉሩ የተሰደደው የጠፋው: ልዩ ልዩ የአካላቱ ለሃብታሞች እየተሸጠ ደላላዎች ብዙ ገንዘብ የሚያተርፋ ያሉ: ለዚህ ሁሉ ችግር የወለደው ነው: በሃገር ዉስጥ ያለስ በሚልዮን የሚቆጠር በሰፍት ኔት የታቀፈው የበሰበሰ ስንዴ የሚቀለብ ያለው::

"አረ አዲስ ራዕይ 8ኛ ዓመት ቅፅ 4 ልዩ እትም አዘጋጆች (ፀሃፊዎች) የምትኖሩት ሃገር የት ነው::"

በድርቅስ መለስ ስልጣን ከያዙበት ቀን ጀምሮ የኢትዮጵያ ህዝብ ከእርዳታ መቸ ተላቆ ያውቃል: በሶማል፣ ነዓፋር፣ በትግራይ፣ በሰቆጣና ላሊበላ፣ በደቡብ፣ በወሎ ተርቦ የማያውቅ በጎንደር፣ ፀለምት ፣ በለሳ፣ ጋይንት፣ በጎጃም በረሃብ የሚማቅቅ ያለው ስንት ነው: ሌላ ቀርቶ በትግራይ  በኢሮብ ምስራቅ ትግራይ አብዛኛው፣

ዋጅራት፣ ራያ፣ ሰቆጣና ላሊበላ፣ ፀለምት፣ በዓፋር፣ ኦጋዴን ይህ ሁሉ በእርዳታ አይደል የሚኖረው::

በአስር ሺ የሚቆጠሩ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ካድሬዎች ስለልማት የሰሩት ነገር የለም: በሚልዮን የሚቆጠሩ የመለስ ካድሬዎች ከገቢያቸው አቅም በላይ ፎቆች ቪላዎች ሲያሰሩ ሃብት ሲያካብቱ፥ ልጆቻቸው በልዩ ትምህርት ሲያስተምሩ 80 ሚልዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ከህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አመለካከት ዉጭ እንዳያስብ የሚያደርጉ የነበሩና ያሉ ናቸው::

እነዛ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ የግብርና የሕክምና ባለሙያዎች ወደ ሳይንሳዊ የእርሻ ዘዴ ከመሄድ ፈንታ ከሳይንስ ዉጭ በካድሬዎችና በቀበሌ በወረዳ መሪዎች ምንም ሙያ የሌላቸው ይህ አድርግ በተባለው የሚሄድ የግብርና ባለሙያ ነው ያለ: በተጨማሪ ህዝብ ያለፍላጎቱ እንደመዳበረያና የእርሻ ግብአቶች ውሰድ አልወስድም ገበሬዎችን በንሮዋቸው መጎሳቆል እየፈጠሩለት ይገኛሉ: በተጨማሪ የእርሻ ባለሙያ ለሙያው ቅድሚያ ከመስጠት ለህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ፓርቲ ስራ ተጠምዶ የካድሬ ስራ እየሰራ ለመኖር እየተገደደ ነው: በግብረና ስራ ለተወሰኑ ወገኖች ለውጥ ቢያመጣም ከረሃብና ስደት አላዳነም::

የብድርና ቁጠባ ድርጅቶችም ምንም እንኳ ከድሮ መሳፍንቶች አራጣ የተሻለ ቢሆንም ሁለት ችግሮች ግን በገጠርና ከተማ ፈጥረዋል: ይህም 1ኛ ወለድ ከባንክ 3ጊዜ እጥፍ ነው: 2ኛ ድርጅቶች ሲያበድሩ ተበዳሪው የተበደረው ገንዘብ ምን ላይ እንቨስት አድርጎ ምን ያህል ያተርፋል: የገበያ ሁኔታ አያጠናም: ሌላ ደገሞ ተበዳሪዎች ሁሉ ወደ አንድ የስራ መስክ ስለሚያሰማሩዋቸው ምርታ ቸው በአንድ ጊዜ ገበያ ሲወረዱ ገዢ አጥቶ ለኪሳራ ይዳረጋል: ስለዚህ ተሎ ይከስማሉ: ሌላ ብድሩ አበዳሪዎች ለግብርና ለተበዳሪዎ ች ስለሆነ የሚደረግ የብድር መተላለፍ ተበዳሪዎች የማያውቁት

የባኬጅ ገገርዎች ይፈፀማል: ጭራሹን ለሙሰና ይጋለጣል ገበሬው ደሂቶ ለስደት ይዳረጋል::

ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋሞች በመቶሺዎች የሚቆጠሩ ተቋቁመው ሃገራችን በአንድ ጊዜ ትለወጣለች በማለት መለስና ጓዶቻቸው በብዙ መድረኮች በየ ክልሎች ዞኖች እየሄዱ ብዙ ብለዋል: በየአካባቢው ያሉ አስተዳዳሪዎች ደግሞ ሃብታም ያልሆኑ ሀብታም ሁኖዋል እያሉ በተለቪዥን መስኮት የዉሸት ሃብታም እያሳዩ ህዝብ አደናግረዋል: እነዛ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ሊወድቁ የቻሉበት ለነሱ የሚመግ ብ እንድስትሪ ባለመኖሩ ነው: ይህ መለስ ሳይቀበሉት ቆይተው እንዲያዉም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሲተቹት መለስ በማንቋሸሽ ሲያጣጥሉት ቆይተው በህልፈተ ሂወታቸው ዋዜማ ጥቃቅንና አነስተ ኛ ተቋማት ያለ ትላልቅ እንድስትሪ ድጋፍ አይሆንም የሚል ይተቹ የነበሩ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሃሳብ የራሳቸው ሃሳብ አድርገው ደሰኮሩበት: መለስ የሰዎች ሃሳብ ፍልስፍና ጠልፈው የራሳቸው ሃሳብ በማድረግ ችሎታ ነበራቸው::

አስተማሪዎችም አንደኛ መመዘንያቸው ሙያ ልምድ ሳይሆን ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ያምናል አያምንም ነው: ሌላ አስተማሪዎች የማስተማር ስራቸው ትተው ለተማሪዎችም በህዝብም የመለስን አምልኮት ነው ሲያስተምሩ የነበሩት: ከመለስ ህልፈት በኋላም በተጠናከረ መንገድ እየሰሩበት ይገኛሉ: የትምህርት ጥራት ጠንቅም የመለስ ፖሊሲና የአስተማሪዎች ብቃት አለመኖር ነው: ትምህርት ቤቶች የሚገመገሙ ፔዳጎጂ በሚያወቁ ሙሁራኖች ሳይሆን በቀበሌ ተላላኪዎች ነው የሚገመገሙ: በአጠቃላይ በመለስ ዘመን ሁሉም ዓይነት ወረደዋል::

ከላይ የተዘረዘሩ ሃሳቦች በሙሉ ለሃገራችን ካለት በታች ከሞቱት በላይ ያደረጋት የመለስና የጓዶቻቸው የተሳሳተ የአንባገነኖች ፖለቲካ አስተሳሰብና የመለስ የተበላሸ የልማት ፖሊሲ ነው: ስለሆነ መለስ የኢትዮጵያ ህዝብ በቀን 3ጊዜ በልቶ ጠግቦ እንዲኖር፣ መጠለያ፣

ልብስ አግኝቶ እንዲኖር ያሳካ መሪ የሚባል ሳይሆን ለዚህ ህዝብ ለድህነት ለረሃብ ለስራ አጥነት ዳርጎ የጠፋ ያልተሳካለት መሪ አንባገነን ዲክቴተር ነበሩ::

## ክፍል 15

## መለሰ ቤት አልባነት እንድያከትም ፈር ቀያሽ መሪ

"ገፅ 43 ተራ ቁጥር 19 8ኛ ዓመት ቅፅ 4 ልዩ እትም እስከ ገፅ 46 አዲስ መስመር 1

መለስ ለከተሞች የመኖርያ ቤት ችግር ለመቅረፍ የተረባረበ የመኖርያ ቤት ችግር ከገጠር በከተማ የባሰ ችግር መኖሩ በገጠር ግን የሳር ቤት የሌለው ገበሬ ሊኖር አይታሰብም: ሽንት ቤት መብራት ዉሃ የሌለው ደሳሳ ሳር ቤት ይዘው ቤት አለን ብለው የሚመኩ ገበሬዎች አሉ: በከተሞች ግን መሬትና ገንዘብ ስለየሌላቸው ብቻ ቤት አልቦ የሆኑ በአንድ ቤት ብዙ ሰዎች ታፍገው የሚኖሩ በተደፈኑ ስንት ቤት ላይ የሚኖሩ በርካታ ሰዎች ነበሩ: በየ ጎዳናው ላስቲክ ካርቶን ለብሰው ተጠልለው የሚኖሩ ነበሩ: ከ1992 ዓ.ም ወዲህ በመለስ አመራር በመላው ሃገራችን ከ300 ሺ. በላይ ቤቶች ተሰርተው ለድሆች ታድለዋል::"

"የቀድሞ መንግስታት በ115 ዓመታት ግዛታቸው እንኳን ይህ ያህል ቤቶች አልሰሩም: ይሰሩዋቸው የነበሩም ጥራት አልነበራቸዉ ም: መለስ ግን በአዲስ አበባ ብቻ በአንድ ዓመት 95ሺ. ቤቶች ሰርቶ ለድሆች አስረክበዋል: መለስ ለሰው ልጆች ምቾት ሲል በሌሎች የበለፀጉ ሃገሮች ድሃ ቤት የማያገኝበት ደረጃ ደርሶ እያለ መለስ ግን በሁሉም ክልሎች ዘመናዊ ቤቶች በመስራት ለድሆች ቤት ሰረተው የቤት ባለቤት እንዲሆኑ አድርገዋል: በበለፀጉ ሃገሮች የቤት ችግር ምክኒያት ድሃና ሃብታም አሽከርና ጌታ ግንኙነት ሲኖራቸው መለስ ግን ለለሰው ልጆች ምቾት ባለው ስብእና ድሆች በከተማ ማኽል

አየወጡ ዳር እንዳይኖሩ በከተሞች ማኽል ቤት በመስራት ከሃብታሞ ች ተሰባጥረው እንዲኖሩ ኮንደሚንዮም በመስራት ትልቅ ተግባር የሰራ::"

"የመለስ ቅኝት ቤት ሰርቶ ለሴቶች ቅድሚያ ያለ እጣ 30% በመስጠት 70% ደግሞ ለወንድ እጣ በመውጣት ቤት እንዲያገኙ አድርገዋል: ይህ ፍትህሃወዊ 12 ክፍፍል ያመነጨው መለስ ነበር: ከሁሉም የኢኮኖሚ ክፍፍል ተነጥለው የነበሩ እናቶችም ተጠቃሚ ሁነዋል::"

መለስ በትጥቅ ትግል ጊዜም ሴቶች የመሬት ባለቤት እንዲሆኑ እንዳደረገው ሁሉ በከተማም ቤትና መሬት እንዲኖራቸው አድርገዋ ል: ህዝቡም 30% ቤቶች ያለ እጣ ለሴቶች ሲሰጥ ተቃዉሞ አልነበረዉም ይላሉ የራዕይ አዘጋጆች: እንግዲህ መለስ ለድሆች ቤት አልቦነት እንዲያከትም ፈር ቀያሽ መሪ ከሆኑ እስቲ ልብ በሉ በ21 ዓመት የመለስ የስልጣን ዘመን የመሬትና የቤት አሰጣጥ እንዴት ነበር ብለን ለሚያውቀው ህዝብ ደግሜ ልጠቁመውና ህዝቡ ይፍረድ::

መለስ ድሆች ቤት አልባ እንዳይሆኑ ፈር ቀያሽ መሪ አልነበሩም: መለስ ከበረሃ ከገቡ ጀምረው እርግጥ በስማቸው የተሰራ ቤት የማውቀው ቤት የለም: ሆኖም ግን እሳቸው የሚመሩት ህ.ወ.ሓ.ት አዲስ አበባ እስከ የመለለስ ህልፈተ ሂወት የነበረ የቤት የማግኘት ዕድል እንዴት ነበር በማለት የነበረው ሁኔታ ሃቁን ልመስክር::

ህ.ወ.ሓ.ት ደርግን አስወግዶ ስልጣን ይዞ ሁሉም የሃገራችን ከተሞች ከተቆጣጠረ በኋላ በሁሉም ከተሞች የነበሩ የመንግስት የኢሰፓ የደህንነት አባላት ቤቶች በሙሉ ከህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ከከፍተኛ እስከ ዝቅተኛ የስልጣን እርከን የነበሩ ቤቶች ተቀራምተው ያዙዋቸው በዉስጣቸው የነበሩ የቤት ቁሳቁስ ጭምር: በዛን ጊዜ መለስ ይቅርና ለድሃ ሰዎች ሊያስበና ለ17 ዓመት እየታገለ በእግሩ ተጉዞ አዲስ አበባ የገባ ተራ ታጋይ እንኳ በንፋስ በፀሃይ

የሚጠለልበት ቤት እንኳ አልሰጡትም: ትንሽ ስልጣን ያላቸው የትኛው ቪላ ፎቅ ይሻላል የትኛው ማኪና ትሻላለች ብሎ ለራሱ ቤትና ንብረት ለመያዝ ይችል ነበር: መለስ ከድርጊቱ የሚቃወሙ ሰዎች ስህተት ትሰሩላቹሁ ብለው ሲነገሩዋቸው የሚቀበሉ አልነበሩም: እስከ አሁን በኢትዮጵያ ከተሞች ሁሉ ያሉ የመንግስት ቀበሌና ኪራይ ቤቶች የድሮ ባለስልጣ ናት ቤቶች በህ.ወ.ሓ.ትና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ባለስልጣናት ካድሬዎችና የነሱ ጥገኞችና ዘመድ አዝማድ ሃብታሞች ይዘዉት ይገኛሉ: የሚገርመው ደገሞ እነሱ በመንግስትና በቀበሌ ኪራይ ቤት እየኖሩ: መለስ በቸሩላቸው ምርጥ ምርጥ ቦታዎች ቪላዎችና ሰማይ ጠቀስ ፎቆች በመስራት በየ ወሩ በመቶሺ የሚቆጠር ብር ኪራይ ይሰበስባሉ: በተጨማሪ የቀበሌና የኪራይ ቤት የመንግስት ቤቶች ለራሳቸው መኖሪያ ከመጠቀም አልፈው እየከፋፈሉ አከራይተው ገንዘብ ይሰበስባሉ: ይህ ተግባር መለስና ጓዶቻቸው የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቃል: ለዚህ ተገባር አዲስ አበባ እንደሞዴል ወስደን ማረጋገጥ ይቻላል::

መለስ የሰዎች ቤት አልቦነት ለማክተም ፈር ቀያሽ ሲባሉ በየትኛው መስፈርት ነው: ባለፈው ፓራግራፍ እንደተመለከትነው ቅድሚያ ምርጥ ምርጥ ለታማኝ ጓዶች የሚያስብ እንጂ ለድሆች ደንታ አልነበራቸዉም ነው የሚያመለክት: ኋላስ ምን አደረጉ: መለስ በኔ እምነት ህዝቡም እንደሚያውቀው ለድሆች አሳቢና ተቆርቋሪ ድሃ ሰዎች መጠለያ ልብስ ሕክምና ትምህርት ማግኘት አለባቸው ብለው የሚያስቡና የሚመኙ አልነበሩም: ለዚህ ማረጋገጫ ይሆነን ዘንድ መለስ መጠለያ እንዲኖራቸው አስቀድመው የተረባረ ቡ ለስልጣናቸው ቀዳምነት አንደኛ ሚኒስትሮች ሁለተኛ ለከፍተኛ ጦር መኮነኖች ሶስተኛ ለአንባሳደሮች አራተኛ ለክልልና የትልልቅ ቢሮ ሃላፊዎች መምርያ ሃላፊዎች ከዛም ውረድ ተዋረድ ታማኝ የመንግስት ሰራተኞች ወረድ ብሎም በየ ደረጃቸው የሚመጥናቸው ምርጥ መሬት በመስጠት ቪላዎችና ትላልቅና መካከለኛ ህንፃዎች

ፎቆች ሰርተው በየወሩ በመቶሺ የሚቆጠር ገንዘብ ያገኛሉ: መሬት እየሰነጠቁ ለሁሉም ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ እደግፋለሁ ላለው ጥገኛ ስቪል ህዝብ ወይም ወታደሮች የደህንነት ሰዎች የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባላት ካድሬዎች እየሸነሸኑ ሰጡዋቸው: የአምቼ ቦታዎች ይዞታ የነበረው መገናኘኛ አካባቢ ያለው ምርጥ ቦታ በሲአም ሲ ምርጥ ቦታ በዋናው መንገድ በገርጂ የሚገኙ ጥሩ ቦታዎች በቦሌ መድሃኒዓለም የፖሌ ትምህርት ቤት የተሰጠ በፖሌ ምሊንዮም አዳራሽ አካባቢ የሚገኝ የኢትዮጵያ ሲቪል አቭየሽን የነበረ በሉቢ ምዕራብ አዲስ አበባ የሚገኝ በቀለበት መንገድ ከነዋሪ ህዝብ የተቀማ: በሳሪስና ጎፋ ማዞርያ: በሲ ኤም ሲ ሲቪል ሰርቪስ ኮለጅ አካባቢ: የአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞች በግልፅና በድብቅ በባለስልጣኖች በትእዛዝ የተሰጡ ምርጥ ቦታዎች::

የሃገራችን ክልሎች ዞኖች ወረዳዎች ከተሞች የመለስ ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባላትና ከነሱ የተጠጉ ባለሃብቶች በምቾት የሚኖሩበት የመለስ ሃገር ናት መሬት መስጠተና ቤት መስራት ዋጋው ከአንድ ሚልዮን እስከ አስር ሚልዮን የሚቆጠር ገንዘብ ነው: እኚህ ቤት ሰሪ የመለስ ምሰሶዎች ደሞዛቸው ከ3ና 6ሺ አይበልጥም ልጆች ያስተምራሉ ያለብሳሉ ምርጥ ምግብ መጠጥ ይጠቀማሉ በየቀኑ ይዝናናሉ: ያ ሁሉ በሚልዮን የሚቆጠር ገንዘብ ከየት መጣ መልስ እንደመስታወት ለሚታዘበው ክቡር ህዝብ ልተወው: እነዛ የተሰሩ ኮንድሚኒዮም ግልፅ በሆነ ምክኒያት የያዙት የመለስ ወገኖችና ታማኝነታቸው አሁን እኮ በሃገራችን ክልሎች ዞኖች ያለ ህዝብ በአንድ ጠባብ ቤት 10ና ከዛ በላይ ሰዎች ታፍገው ነው የሚኖሩት: ታድያ መለስ ለራሳቸው ምሶሶዎች የመኖርያ ቤት የማግኘት ፈር ቀያሽ ሆኑ እንጂ ድሃውማ የት ያገኘዋል::

"መለስ የገጠሩ ህዝብ ምንም እንከን መብራት ዉሃ ባይኖበረው ደሳሳ ጎጆ በሳር የተሰራች የኔ ናት የሚላት አለቸው: የከተማው ህዝብ ግን ክፉ ንሮ ይኖራል ብለዋል አዲስ ራዕዮች::"

አዲስ ራዕይ አሁንም ስለገበሬ ንሮ ስትገልፁት ሓቀኛ መረጃ የላቹሁም: እኔ የማወቀው የኢትዮጵያ የገጠር አርሶ አደር ከ 70% በላይ የሚያርሰው መሬትም ቤት ሰረቶ የሚኖርበት ስፋት 5x5 ሚተር ትንሽ መሬት ጎድኑን የሚያሳርፍበት መሬት የለዉም: ይህ 70% ህዝብ ከወላጆቹ ጥገኛ ሁኖ የሚኖረው ያለው::

አንድ ነገር ለአንድ ለአንባብያን መረጃ ሊሆንላቹሁ በሰሜን ኢትዮጵያ በጎንደር ትግራይ አገው ምድር የሰቆጣና ላሊበላ ዞኖች: ሰሜን ሸዋ ሰሜን ወሎ በ1983 ዓ.ም በዚህ ፅሑፍ መጀመርያ አካባቢ እንደ አስቀመጥኩት ወንዱ በ22 ዓመት ዕድሜ ሴት በ19(20) ዓመት ዕድሜ 100x50 =5000 ሚተር ካሬ ታራሽ መሬት አግኝተዋል: በዛን ወቅት ከ20 እስከ 22 ዓመት ዕድሜ የነበሩ በአሁኑ ጊዜ 42 እስከ 44 ዓመት ዕድሜ አላቸው: ከነዚህ ዕድሜ በታች የነበሩ ደሳሳ ጎጆም የላቸዉም: የወጣት ጡንቻቸው የሚያሳርፉበት የስራ መስክ መሬት የላቸዉም: አርቀው ተሰደው ሰርተው እንዳየኖሩ የስራ ዕድል የለም: በሌሎች ክልሎችም መሬት ከተሸነሸነበት ጊዜ ጀምሮ ሕጉ ከሚፈቀደው ዕድሜ በታች የነበሩ መሬት መጠለያ ቤት የላቸዉም: ስለሆነም የገጠር ህዝብ በመኖርያ ቤት ማግኘት የተሻለ ነው የምትሉት ፍፁም ዉሸት ነው: እስት ወደ የገጠር ህዝባችን ገብታቹ ሁ ንሮዉን ፈትሹ::

የከተማ ነዋሪ ህዝብ ገንዘብና መሬት ስለየሌላቸው በአንድ ቤት ታጉረው ተፋፍገው የሚኖሩ ለሰገራ ቤት በተጻፈነው ጉድጓድ የሚተኙ አሉ ብላቹዋል: እዚህ ላይ ሐቅ ተናግቹዋል: አሁንም በአዲስ አበባ የባሰበት ሁኔታ በሁሉም የክልል የዞን ወረዳ የሚኖሩ ህዝቦች ከ 50% በላይ መጠግያ ያጣ ህዝብ ነው የሚገኝ::

"ዝቅ ብላቹሁ መለስ ሃገራችን በ115 ዓ.ምት ያለፉት ገዢዎች ያልሰሩት መለስ ፈር ቀያሽ ከ300ሺ ቤት ሰርቶ በየዓመቱም 95ሺ ቤት ሰርቶ ለድሃ ሊያስረክብ ነው ብላቹሃል::"

መጀመርያ ነገር ለምን በስብሰው ከወደቁ 115 ዓመት ወደኋላ ተመልሳቹሁ ከሞቱት ትዋዳዱሩላቹሁ: በአሁኑ ጊዜኮ ይቅርና የአውሮፓና አመሪካ ሃገሮች የአፍሪካ ሃገሮች አብዛኞቹ መጠለያ የሌለው ህዝብ ብዙ ነው: በሃገራችን ደገሞ መለስ ዜናዊ የበለፀጉ ሃገሮች የመጠለያ ችግር ያልፈቱ እያሉ እኛ ግን 300ሺ ቤት በመስራት የመኖሪያ ቤት ችግር ቀርፈናል ብላቹናል: ይህም ዉሸት ነው በአዲስ አበባ ይሁን በክልሎች በዞኖች የተሰሩ ኮንደሚኒም ቤቶች ሃሜት ለመከላከል ጥቂት ቤቶች ለድሆች መሰጠት 90% ከዛ በላይ: ምርጥ ምርጡ ለመለለስ ምሰሶዎችና የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ካድሬዎች ወይም ወዳጆቻቸው የተሰጡ ናቸው: ድሃው አላገኘዉም ቢያገኝም የወር ገቢ የለዉም ከየት አምጥቶ ይከፈለዋል::

የበለፀጉ ሃገሮችኮ በነፃ ኢኮኖሚ ፖሊሲያቸው መሰረት ህዝቡ መኖርያ ቤት በባለሃብቶች ይሰራል: ስራና ገንዘብ ያለው ተከራይቶ ይኖራል: ስራ የሌለው ድሃ ሰው መንግስት ተከራቶ ያስቀምጠዋል: መኖርያ ቤት ብቻ አይደለም ድሆች ስራ እስኪያገኙ ሊያኖራቸው የሚችል የገንዘብ ዱጎማ ያደርጋል::

መለስና ጓዶቻቸው ግን ቤት ሰርተው ለህዝብ ንሸጣለን ቢሉ ችግሩ ሊፈቱት አልቻሉም መፍትሄ ሊሆን የሚችል የመለስ የተበላሸ ዲክቴተርና አንባገነን የኮሞኒስት ፖሊሲ ሳይቀየር የድሆች መጠለያ ችግር ሊቀረፍ አይችልም::

በሰማይ ነብሳቸው ይማራቸው ፈር ቀያሽ መለስ የኢትዮጵያ ህዝብ 17 ዓመት ታግሎ በነ አቶ ክፍለ ወዳጆ ጥረትና ከፍተኛ ክርክር የፀደቀ ሕገ መንግስት የህዝቦች መጠለያ ቤት፣ መሬት፣ ዉሃ፣ መብራት፣ ትምህርት ወ.ዘ.ተ የማግኘት ሕገ መንግስታዊም ዜግነታዊ መብት ነው ብሎ የረጋገጠው ፍፁም ንደዉታል::

ሕገ መንግስት ባረጋገጠው መብት መሰረት መለስም ወደ የከተማ መሬት ፖሊሲ ቀይረው ደንብ ወጣለት: የከተማ መሬት ለመጠለያ በማሕበር በመደራጀት በእጣ ለመኖርያ ቤት ለድርጅት በምሪት

የሚል የመሬት አሰጣጥ አዋጅ አውጥተው የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባል ሁሉና ጥቂት ሲቪል ነዋሪዎች ተቀብለው ሰርተዋል: በሌላ በኩል ደግሞ በተለይ በትግራይ ክልል ተቆርቋሪ (ግዱሳት ተጋሩ) በሚል አድሎ ያለበት አሰራር በመቀሌ ከተማ 500 ሚተር ካሬ ለቤት መስርያ ተሰጥተዋል: ይህ ሁሉ ካደረጉ በኋላ በማሕበር መሬት በእጣ መጠለያ መስጠት ተሰረዘ: በሊዝ ወይም በኮንደሚንየም ግዙ ተባለ: የሚገርመው ነገር ደግሞ በሁሉም ክልሎች በማሕበር ተደራጅተው ገንዘባቸው በባንክ አከማችተው መሬት ይሰጠን ብለው እየተጠባበቁ ድንገት መሬት አይሰጥም ገንዘባቹሁ ውሰዱ ተብለው በትልቅ ችግር ወደቁ: ለመረጃ ያህል በመቀሌ ከተማ ብቻ 280 ማሕበራት 7600 ሰዎች መሬት ይሰጣቹሃል ተብለው ተነግሮዋቸው ሲያበቃ ከ4ና 5 ዓመታት በላይ በባንክ የቆየ በሚልዮን የሚቆጠር ገንዘብ መለሱላቸው: በሌላ በኩል በዚሁ በመቀሌ ከተማ የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴና አጋሮቻቸው ባለሃብቶች በመቀሌ ህዝብ አፓርታይድ መንደር በሚል ስም የሚታወቅ ሰፈር የራሳቸው ትምህርት ቤት የገበያ ማእከል መዝናኛ መዋእለ ህፃናት ክልኒክ ያሉበት ከተደራጁ ሰዎች ማንም ሰው ሊገባው የማይችል በሕግወጥ ለከተማው ዉበት ተብሎ በልኡል ራስ መንገሻ ስዩም የተከለለ መሬት የነበረው እፅዋት በማውደም በአንድ ዓይነት ፕላን 1.25 ብር ለሚተር ካሬ ሊዝ የተሰጠ መጠለያ ፈር ቀያሽ መለስ ያውቁታል: እንደዚህ ዓይነት ምርጥ ምርጥ ቦታዎች ለመለስና ጓዶቻቸው መሰጠት ከፍ ብየ እንደገለፅኩት ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የመለስ ህልፈተ ሂወት እየተሰራበት የመጣ ማዳላት የተላበሰ አሰራር ነበር: ይህ አሰራር መለስ አበጥረው ያውቁ ነበር: ሌላ ቀርቶ በአዲስ አበባና በሌሎች ክልሎች ያሉ የተሰሩ ህንፃዎች የማን ባለስልጣን ወይም ዘመድ መሆኑ አበጥረው ያውቁ ነበር::

መለስ ድሆች ኮንዶሚንየም ተሰርቶ ስለተሰጣቸው በማኸል ከተማ ከሃብታሞች ተቀላቅለው ይኖራሉ ብለዋል አዲስ ራዕዮች::

ፈር ቀያሽ መለስ ከተሰሩ የኮንደሚንየም ቤቶች 30% ለሴቶች ያለ እጣ እንዲሰጣቸው ከ70% ሴቶች ከወንዶች እጣ እንዲያወጡ አድርገዋል ብለዋል: ለመሆኑ እነዛ 30% ቤት የወሰዱ ድሃ ሴተች ማን ነው የመለመላቸው: በትክክል ህዝብ በሚያውቀው ግልፅነትና ፍትሃዊነት ባለበት የተወከሉ አይደሉም: ሆን ተብሎ ሴቶቹ የህዝቡ 50% ሴቶች ስለሆኑ ለመለስና ጓዶቻቸው የፖለቲካ መሳርያ ለማድረግ የተሰራ ድራማ ነው: ምክኒያቱም መለስ የሴቶች መብት ሲያነሱ ምርጫን ግምት ዉስጥ ያስገባሉ የሃይማኖት መብት ሲያነሱ የማሕበራት የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የወጣት መማህራን ማሕበራትና እናከብራለን ሲሉ ለምርጫ ትርፍ ለማግኘት ተብሎ የሚደረግ ነው: ከዛ ዉጭ መለስና ጓዶቻቸው ጥቅምና የስልጣን ዕድሜ የማራዘም ከልሆነ መለስ አይሰሩትም: ይህ ደግሞ የድሮ ባህሪያቸው ነው::

መለስ በትጥቅ ትግል ጊዜ ሴቷን የመሬት ባለቤት እንድትሆን ያደረጉ ብልህ መሪ ነበሩ ተብለዋል: የገጠር መሬት እኮ መሬት ለአራሹ የሚል የትግል መፈክር ሆኖ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና ሙሁራን ለፊዩዳላዊ ስርዓት ያነሱት ጥያቄ ነበር: ይህ መፈክር ለነበረው ስርዓት ለመገርሰስ የተነሳ የትግል ማዕበል ነበር: ደርግ ስልጣን ከያዘ በኋላ የመሬት ሽንሽናው የተፈፀመው በደርግ ነበር: ህ.ወ.ሓ.ት ደርግ ላደረገው የመሬት ሽንሽና ማስተካከል (ክለሳ) ነው ያደረገው: ይህ ደግሞ የመለስ ሰራ አልነበረም በመሬት አስተዳደር በመጀመርያ ግደይ ዘርአፅዮን ነበር: እሱ ከወጣ በተወልደ ወልደማርያም ነበር የተሰራው እስከ 1986 ዓ.ም በተወልደ ነበር: ስለዚህ መለስ መሬት ለሴቶች የሚል ሃሳብ ሊኖራቸው ይቅር በዛን ወቅት በአጠቃላይ የሴቶች መብት የሚጋፋ ለመብታቸው ጥያቄ ላነሱ ሴት ታጋዮች ፈሚኒስት ናቹሁ እያሉ ሲያጣጡሉዋቸው የነበሩና በሴት ታጋዮች ብዙ ፀረ ዴሞክራሲ

ድርጊት ሲፈፅሙ የነበሩ ናቸው: ይህ ተግባራቸው የሀ.ወ.ሓ.ት ታጋይ የነበሩ ሴት ታጋዮች የሚያረጋግጡት ነበር::

በገጠር የመሬት ሽንሽና የደርግን የከለሱ መለስና ጓዶቻቸው ብቻ አልነበሩም: ኢ.ሀ.አ.ፓም በሰሜን ጎንደር ሰቆጣ በምስራቅ ትግራይ በፀለምት በበለሳ በየዳ ጃንአሞራ ሽንሽነዋል: ስለዚህ አዲስ ራዕዮች ለመለስ ያልሰራው ነገር ብትሸልሙት ምን ዓይነት ሽልማት ታገኛላቹሁ ትርፉ ንቀት ነው::

የመለስ የትግል ታሪክ እኮ ይቅርና የሀ.ወ.ሓ.ት ታጋይ የትግራይ ህዝብ ያውቀዋል: ሰለሆነ መለስ አጠቃልለን ስናየው ለድሃ ሕብረተሰብ መጠለያ ቤት ሊያገኙ የሚያስቡና ፍትሃዊ ሰው አልነበሩም: መለስ ከቀበሌ እስከ ሚኒስተሮች አምባሳደሮች የጦርና የፖሊስ ከፍተኛ መኮንኖች ለደህንነቶች ብቻ መኖርያ ቤት ምርጥ መሬት ሲሰጡ የስልጣናቸው ምሰሶ ለማጠናከር ሲሉ ከመሬት ጋር ተያይዞ የመጣ ሙስና ተሸክመው የተጓዙ ሰው ነበሩ::

መለስ ለኪራይ ሰብሳቢነት ተቃዋሚ አልነበሩም: ምክኒያቱም በሃገራችን የነበሩና ያሉ ባለስልጣኖች የከተማ ምርጥ ቦታዎች በመያዝ ትላልቅ ህንፃዎች ቪላዎች በመስራት ያን ህንፃ በማከራየት ብዙ ሃብት የሰበሰቡ በተጨማሪ የያዙት የመንግስት ቤት በነፃ እየኖሩ እያከራዩ ሀብት የሚሰበስቡ: ከዚህ አልፈው ለዘመድ አዝማዳቸውና መሬት በመስጠት ሃብት እንዲሰበስቡ በማድረግ የሃገራችን ሃብት በእጃቸው እንዲሰበስቡት: በተመሳሳይ ከነሱ ሊስማሙ የሚችሉ ባለሃብቶች በመፍጠር ለሃብታቸው ሽፋን ሊሆኑላቸው በሚችሉ መንገድ በመደራጀት የሃገራችን አንጡራ ሃብት በግለሰቦች እጅ ይገባ እንዳለ መለስ አበጥረው ያውቁ ነበር::

በየ ቀኑ ኪራይ ሰብሳቢነትን በሚመለከት ይነግሩን የነበረው እንደማታለያ እንደነበር ይታወቃል: አዲስ ራዝዮችም ታውቁላቹሁ: መለስ ፀረኪራይ ሰብሳቢነት ቢሆኑ ንሮ ከወይዘሮ አዜብ ጀምሮ የትእምት ድርጅቶች ባጠሩ ነበር: መለስ ለሙስናና ኪራይ

ሰብሳቢነት የሚቃወሙት የነበረ ለስልጣናቸው የምታሰጋ እስከሆነች ድረስ ነበር: መለስ ለስልጣናቸው አደጋ ነው የሚሉት የመነጠል ችሎታቸው ትልቅ ነበር: ስለዚህ መለስ ፀረኪራይ ሰበሳቢነት አልነበሩም::

መለስ ለሰው ልጆች ምቹ ሲሉ ድሆች መኖርያ ቤት እንዲኖራቸው ያሳኩ ፈር ቀያሽ መሪ መሆኑ በመላው ሃገራችን የሚገኙ ከተሞች አካባቢ የሚኖሩ አርሶ አደሮች መኖርያ ቃያቸው በመንጠቅ አብዛኞቹ ያለ ካሳ ክፍያ 140 ኪተር ካሬ መሬት ሰጥተው የቀረው የአርሶ አደር መሬት ነዋሪዎች ከአያትና ቅድመ አያት ጀምረው በመቶ የሚቆጠር ዓመታት ከይዘታቸው ተፈናቅለው ዘር ማንዘራቸው ተበታትነው ቀርተዋል: መለስ ወደ ስልጣን ከመጡ ጀምረው በአዲስ አበባና አካባቢዋ በናዝሬት አዋሳ የተፈናቀሉ አርሶ አደሮች መጠነኛ ካሳ የተሰጣቸው ቢሆንም በሌሎች ክልሎች ግን አብዛኛዎቹ ገበሬዎች ካሳ ማግኘቱስ ይቅር ቅጣት ጨምሮበታል: ለአብነት መቀሌን እንውሰድ በአካባቢዋ የሚገኙ የገጠር መንደሮች ፈለግ ዳዕሮ፣ ዓዲሓ፣ ሮማናት፣ ገንበላ፣ ላጪ፣ መሰቦ፣ አገርሓሪባ፣ ዓዲወለል፣ ዓዲዳዕሮ፣ ኲሓ፣ ሽብጢ፣ ዓይናለም፣ ደብሪ፣ ቀላሚኖ፣ ገፌሕገረብ፣ ሰራዋት የሚባሉ መንደሮች የሚኖሩ አርሶ አደሮች ብዛታቸው 40ሺ አባወራዎች በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ልጆቻቸው ያለ አንዳች ካሳ ተፈናቅለዋል: እነዚህ ሰዎች በሃገር ደረጃ ሲታይ በሚልዮን የሚቆጠር ህዝብ ቤታቸው ፈርሶ መሬታቸው ተነጥቆ መንግስት ለባለስልጣኖች ምርጥ ምርጥ ቦታዎች በመስጠት ሌላው በዉድ ዋጋ በሊዝ በመሸጥ ገንዘቡን ገቢ አድርገዋል: ልብ በሉ የመለስና ጓዶቻቸው መሬት አይሸጥም አይለወጥም መሬት የሚሸጥ የሚለወጥ ከሆነ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግና መለስ መቃብር ነው እያሉ ህዝቡን ከመሬቱ እያፈናቀሉ ወይም በጥቂት ሳንቲሞ ግምት ከአርሶ አደር ከነበረ ባለይዞታ አስገድደው በመውሰድ ራሳቸው ለአንድ ሚተር ካሬ

በሺ የሚቆጠር ገንዘብ በመሸጥ የመለስና ጓዶቻቸው ስልጣን ማራዘምያ ሆኖዋል::

መለስና መዋቅራቸው ይቅርና ቤት ሰርተው ለድሆች ቤት በዝቅተኛ ዋጋ ሰረተው ሊያስረክቡ: በመላው የሃገራችን ከተሞች አካባቢ የሚገኙ የገጠር ቀበሌ መሪዎች በሕጋዊ መንገድ መኖርያ ቤት የሰጡዋቸው ቤት ሰረተው ግብር ከፍለው እየኖሩ: የመለስ መዋቅር ግን ከ20 እስከ 30 ዓመት ተመስረተው የቆዩ ትናንሽ ከተሞች በብዙ ሚልዮን ብር የተሰሩ ቤቶች በዶዘር እንዲሁም አፍራሽ ግብረ ኃይል ኮማንዶ በመመደብ አፍርሶታል: የማፍረስ እርምጃ የተቃወሙ ሰዎች በሰላማዊ መንገድ እንደመፍታት ሰዎቹ ማሰር በመርዛም ጢስ ማፈን ጥይት በመተኮስ መበተን ታይቷል: ይህ ተግባር በአዲስ አበባና አካባቢዋ በጎንደር በመቀሌ በአላማጣ ተፈፅመዋል: በተለይ በመቀሌ በ2003ና 2004 ዓ.ም ገፊሕገረብ በተባለ ቦታ በ2005 ደግሞ ታሕሳስ መጀመርያ ላይ በአላማጣ ዘግናኝ እርምጃ ተወስደዋል: በአዲስ አበባም በመቶሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ቤታቸው ፈርሶባቸው በፀሐይ ብርድና ዝናብ ተሰቃይቶዋል: ታድያ እነኚህ ሰው ለድሃ ሕብረተሰብ ምቾት ለመፍጠር ሲሉ 300ሺ ኮንደሚኒም ሲሰሩ በመቶ የሚቆጠሩ ቤቶች አፍርሰው ሚልዮኖች ህዝብ ቤት አልቦ ማድረጋቸው ለምን ዓላማ ነው::

መለስ የህዝብ ቤት ሕገወጥ ነው ብለው ሲያፈርሱ ኢፍትሃዊ በሆነ መንገድ ነው ያፈረሱት ለዚሁ ለማስረጃ ያህል በአዲስ አበባ አካባቢ ከ14 ዓመት በፊት ጀምረው እስከ አሁን ብዙ ተህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግና አጋሮቻቸው ባለሃብቶች ራሳቸው ቦታ እየመረጡ ብዙ ህንፃዎች ፋብሪካዎች ትምህርት ቤቶች ሰርተዋል: በወቅቱ የነበሩ የአዲስ አበባ ከንቲባዎች ተፈራ ባልዋ አርከበ ዑቅባይ ይልማ ደሬሳ ካሳ ዒላላ ኩማ ደመቅሳ በነበሩበት መለስ ራሳቸው ሕገወጦችን በሕግ እንደመቅጣት ወንበራቸው (ስልጣናቸውን) ልያናጋ ስለሆነ ፕላን እየተሰራ የባለቤትነትን ካርታ እንዲሰጣቸው ተወሰነ: መለስ

ራሳቸው በመድረክ አዲስ አበባ ብዙ ባለሃብቶች ሕገወጥ ህንፃዎች ፋብሪካዎች ሰርተዋል: ይህ ልማት ሕገወጥ ብለህ ማፍረስ የሃገር ሃብት ዉድመት ነው: ስለሆነም ለፈፀሙት ሕገወጥ ድርጅት ቀጥተን ቦታው እንዲወስዱት ምህረት ሰጥተናል ብለው አውጀዋል: ይህ አጭበርባሪ አሰራር የአዲስ አበባ ህዝብ ያወቀዋል: ስለሆነ መለስ ሕገወጥ የከተማ መሬት ወረራ ሲያበራክቱ ነው የኖሩ: ስለዚ መለስ ለሰው ልጅ ምኞት ሲሉ ቤት አልቦ የነበሩ ድሆች የቤት ባለቤት ያደረጉ ሳይሆን 21 ዓመት ሙሉ የስልጣን ዘመናቸው በሚልዮን የሚቆጠሩ ድሃ ህዝቦች ቤት አልቦ ያደረጉ አንባገነንና ዲክቴተር ለሰው ልጆች መልካሙን ነገር የማይመኙ ቀናተኛ መሪነበሩ::

## ክፍል 16

**"አዲስ ራዕይ 8ኛ ዓመት ቅፅ 4 ልዩ እትም 2005 ተራ ቁጥር 110 የደህንነት ተራራ ለመናድ የእውቀት ጥይት ያቀበለ መሪ ከገፅ 46 አዲስ መስመው 2 እስከ ገፅ 47 መጨረሻ መስመር"**

"መለስ በሰው ልጅእ ልዩነት እንዳይኖር ትምህርት ከ 1ኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ዩነቨርሲቲ ምርምር ማእከል ያስፋፋ ምጡቅ መሪ መለስ በኢትዮጵያ አዲሱ የትምህርት ስርዐት ዋነኛ መሃንዲስ ነበረ: መለስ 12 ክፍል ሲጨርስ ከፍተኛ ዉጤት ስለአመጣ ከጃንሆይ ሽልማት አግኝቶ ነበር: መለስ ለዚሂች ሃገርና ህዝቧ ምቶች ሲል በ 6ሺ ብር ደሞዝ ለህዝቡ ሲል በታታሪነት ያገለገለ መለስ ከህዝብ የተነጠለ ሊሂቅነትን አጥብቆ የሚጠላ ሰው ስለነበር ለራሱ በራሱ ጥረት ዕውቀት ሁሉ እንደፈለገና እንደሰበሰበ ነገር ግን መለስ በስልጣን በቆየባቸው በየአንዳንዱ ዐመት ለአንድ ሚልዮን ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት ማምጣት ምክኒያት ሆነዋል: የሃገራችን ሩቡን ያህል 20 ሚልዮን ተማሪዎች ወደ ትምህርት እንዲዘምቱ ያደረገ የሙያና የተክኒክ ትምህርት ተቋማት በከፍተኛ መጠን የተበራከቱት በዚህ የመለስ የአመራር ዘመን ነው: ኢትዮጵያ የሰለጠነ የሰው

ኃይል እንደሚያስፈልጋት በማመን 32 ዩኒቨርሲቲዎች አፍልተዋል: በመለስ አመራር ጥራት ያለው ትምህርት በስፊው እንዲዳረስ ያደረገ ምጡቅ መሪ: መለስ ሴቶች በበለጠ የትምህርት ተጠቃሚዎች ያደረገ: ተማሪዎች ሁሉ በስነምግባር በስነዜጋ አንዲታነፁ የጣረ መሪ ነበር: መለስና ድርጅቱ ሃገራችን ምን ያህል ለህዝቧ የተመቸት እንድትሆን ጥረት አድርገዋል: የተማሩ በመልካም ስነ ምግባርና በስነ ዜጋ እሴቶች የታነፀ ወጣት ትውልድ ያፈራ መሪ: ዴሞክራሲን የሚያውቅ ብቻ ሳይሆን መብቱና ጊዴታው የሚያውቅ ሕብረተሰብ ያነፀ መሪ: ጓድ መለስ ኢትዮጵያ ሃገራችን በትምህርት ፍፁም ለውጥ ለማምጣት የሚጥር የነበረ መሪ: ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ የአዲስ ራዕይ አዘጋጆች ለመለስ የሸለሙዋቸው ታሪክ ነበር: ነገር ግን ሐቁ እንደዚህ አይደለም በማለት የሚከተለው መልስ ተሰጥተዋል::"

በመለስ አገዛዝ ዘመነ በደርግና በጃንሆይ ያልነበሩ ከ 1ኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲዋች የተክኒክና ሙያ ማሰልጠኛዋች ተስፋፍተዋል: ይህ የማይካድ ሐቅ ነው: ነገር ግን በዘመነ መለስ የአካዳሚ ነፃነት አልነበረም: የትምህርት ጥራትም ወደ ዜሮ ወርደዋል: ትምህርት ቤቶች ቢስፋፉም ሥራ ፈጣሪ አልነበሩም: የትምህርት ተቋማት ሁሉ የመለስና ድርጅቶቻቸው የካድሬዎችና የፓርቲ አባላት መመልመያና ማሰልጠኛ ነበሩ: ትምህርት ቤቶች በሙያ እንደ መምራት በመለስ ካድሬዎች በቀበሌ በልማታዊ ሰራዊት የሚመሩ ናቸው: መለስ የመጠቁ መሪ ቢሆኑ ንሮ ትምህርት ቤቶች የሙያና የተክኒክ ማሰልጠኛዎች ዩኒቨርሲቲዎች በየደረጃው የማስተማ መማር ሙያ ያላቸው ሰዎች መምራት ነበራቸው: መለስ ግን የትምህርት ተቋማት ሁሉ በሙያ ሳይሆን በካድሬ መመራት አለባቸ ው የሚል እምነት ነበራቸው: በተጨማሪ ለሁሉም ነገር አማክረው የባለሙያ አስተያየትና ሃሳብ ተቀብለው አልሰሩም: ለሁሉም ነገር

ፈላጭ ቆራጭ አንባገነን ነበሩ: አዲስ ራዕዮችም ለዚሁ ነው የምታረጋግጡ ያላቹሁ::

የመለስ የስልጣን ዘመን ከፍተኛ የትምህርት ዕድል ፍትሃዊ አልነበረም ምክኒያቱም ለህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባላትና ካድሬዎች ቅድሚያ ስለሚሰጥ: የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አመራር ልጆቻቸው ዘመድ አዝማዳቸው የትምህት ዕድል ቅድሚያ ይሰጣቸዋል: ለዚሁ መረጃ የሚሆን የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባል ከሆነ ወደ መንግስትና የግል ኮለጆች ለመግባት የመግቢያ ነጥብ መስፈርት ሳያሟላ ገብቶ ይማራል: የአዲስ አበባ ሲቪል ሰርቪስ ኮለጅ 100% የመለስ አካላት የሚማሩበት ነበር: እነዚህም ወደ ዩኒቨርሲቲ መግቢያ ነጥብ ሳያሟሉ አባላት ፓርቲ በመሆናቸው ሞቅ ሞቅ ብለው ወጥተው ዲፕሎማ ድግሪ ማስተርስ ወ.ዘ.ተ ይዘዋል ተብለው የሙሁር ስም ይዘው በከፍተኛ የስልጣን ደረጃ ደርሰው በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ሌት ተቀን አጥንቶ ለተማረ ባለሙያ እንደፈለጉ ይነዱታል::

መለስ የትምህርት ስርዓት መሃንዲስ ነበር የሚባሉት በየትኛው መስፈርት ነው: መለስኮ ከ7ኛ ክፍል ጀምሮ የነበረ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ካሪኮለም የሰረዙ: ተማሪ ከ 6ኛ እስከ 9ኛ ክፍል እንግሊዘኛ ቋንቋ እንዳይማር ያገዱ ፈላስፋ: 12ኛ ክፍል መልቀቅያ አልፎ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ የእንግሊዘኛ ቋንቋ የማያውቅ ተማሪ ያፈሩ መሪ: የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በምርምር ሥራቸው መስፈርት እንደ ማስቀመጥ ተማሪዎች በህ.ወ.ሓ.ት አባልነታቸው እንዲመዘኑ ያደረጉ መሪ: በዩኒቨረሲቲ መግቢያ ያልተመዘኑ ተማሪዎች በፖለቲካ ታማኝነታቸው በዝቅተኛ ነጥብ ዩኒቨርሲቲ ገብተው በዝቅተኛ ነጥብ ተመርቀው ቅድሚያ ለነዛ የወረዱ ተማሪዎች የሥራ ዕድል የሰጠ:: ለሃገር ዉስጥ ይሁን ለዉጭ ትምህርት ዕድል መስጠት በሚቀመጥላ ቸው መመዘኛ ሳይሆን ታማኝ ፓርቲ አባል መሆን የገገሮዎች ልጆች ዘመድ አዝማድ፣ በጋብቻ፣ በጓደኝነት፣

አካባቢነት፣ ለወደፊት ደላላ ይሆንልኛል በሚል መስፈርት ሃገራችን በብቁ ሙሁራን የመራማሪ ዎች በማነፅ ፈንታ በመሃይሞች የመለስ የልማት ሰራዊት በሚሉዋቸ ው ያባላሹ መሪ ናቸው: በሃገራችን ሃገር አቀፍ ወይም ክልል አቀፍ ለትምህርት ጥራት እንደመስራት ለመለስ መንግስት የስለላ ስራ ለመስራት ተብሎ የአፓርታይድ ዓይነት ትምህርት እንደቀላሚኖ ያሉ ትምህርት ቤቶች በማቋቋም ኢፍትሃዊ የሆነ የመማር ማስተማር አሰራር መከተል: አሁን በትግራይ ብቻ የአባርታይድ ስልታቸው በመቀጠል 50 ቀላሚኖ ምርጥ ትምህርት ቤቶች መቋቋማቸው: ለነዚም በልዩ ተደራጅተው ሊያቋቁሙት መለስ ሰዎች መድበው ያለፉ መሆናቸው: ይህ ዓይነት የትምህርት ስርዓት ለመለስ የትምህርት መሃንድስ ሳይሆን የሚያስብላቸው መለስ ትክክለኛ የትምህርት ሳይንስ ያፈረሱ መሪ ነበሩ መባል አለባቸው::

"መለስ ለዚህ ሃገር የህዝብ ምቾት ሲል ሌላ ጥቅሙ ትቶ በ6ሺ ብር ደሞዝ የሚኖር ይላሉ: መለስ በ6ሺ ብር ደሞዝ ይሰሩ የነበሩ በህዝባዊነት ፍቅር ልባቸው አረው አዝነው የፃፉት የአዲስ ራዕይ አዘጋጆችና አለቆቻቸው: የዋሆች እንዳልላቸው አይደሉም እጅግ ለጥቅማቸው የቆሙ ንፋሱን ተከትለው አድርባይ ምኞታቸው የፃፉት መሆኑ በደንብ ተረድቻቸውለሁ::"

ልብ በሉ መለስ በ1967 ዓ.ም ወደ ህ.ወ.ሓ.ት ከገቡበት ቀን ጀምሮ የአኒማል ፋርም ፍልስፍናቸው በማንበብና በመረዳት ሂወታቸው እንዴት ጠብቀው ቆይተው ወደ ስልጣን ወጥተው ፍላጎታቸው እንደሚያረኩ አበጥረው ያውቁ ነበር: የአኒማል ፋርም-----ፍልስፍና አብዛኛቹ እንደመለስ ያሉ የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች የሚጠቀሙ በት ስልት ነበር: ዋናው ቁምነገር ጉዳይ ለመለስ ስለሆነ ወደዛ ልግባ::

መለስ ከጅምሩ ጀምረው ጦርነት አይወዱም ነበር: በዚያች የነበረችባቸው የመናገር ችሎታና የሰዎችን ሃሳብ መቀማት ሃሳቸዉን

በማድረግ ሆን ብለው በሚያስተሙሩዋቸው ካድሬዎች አድናቆት በመትረፍ ይህ ሰዉየ መሞት የለበትም የሚል ድምፅ በድርጅቱ እንዲያስተጋባ በመድረግ: ለዚያች የነበረች ከጦርነት የመሰወር (መሸሽ) ባህሪያት በመሸፈን የበለጠ የአኒማል ፋርም ፍልስፍናቸው እስከ ሂወተ ህልፈታቸው እየተጠቀሙበት መጡ: ይህ የአኒማል ፋርም ስልታቸው ህ.ወ.ሓ.ት ከተመሰረተ ጀምረው ከ1965 እስከ 1969 ዓ.ም: በ1968 ዓ.ም ከነስብሃት ነጋ ሆነው እነገሰሰው አየለን አስወገዱ: ገሰሰው አየለ ለስብሃትም ለመለስም በአጠቃላይ ለህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ ሃገር ሻያጭ አመለካከት ዋና መቺ ኃይል ስለነበር::

ከ1968 እስከ 1971 ዓ.ም ተነስተው የነበሩ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች በዴሞክራሲ መንገድ እንደመመለስ ፈንታ በድርጅቱ በመነሳሳት የነሱ ሎሌ የሆኑ ካድሬዎች በማሰልጠን ለመለስ ተቃዋሚዎች ለነበሩት በነ ስብሃት ነጋና ሌሎች ማ/ኮሚቴ እንደጋሻ ጦር በመጠቀም ለብዙ ታጋዮች መብት መግፈፍ ማሰር ከባድ ቅጣት መቅጣት ማባረር እንዲሸማቀቁ በመድረጋቸው ማ/ኮሚቴ ህ.ወ.ሓ. ት በጎናቸው በማሰባሰብ ብዙ ገበን የፈፀሙ ናቸው::

ከ1971 እስከ 1975 ዓ.ም የህ.ወ.ሓ.ት ሰራዊት አድጎ ስለነበረ አሰላለፉ ም ከደርግ የተሻለ ዴሞክራሲ አለ ብሎ የተሰለፈ ስለነበረ በወቅቱ ነፃ ሆኖ የሚመስለው ጥያቄ ያነሳ ስለነበረ የነበረ ነፃነት ግን ለህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች የሚመች ስለነበረ በወቅቱ ብዙ የካድሬ ደረጃዎች ማለት 1ኛ 2ኛ ካድሬ የመሰናዶ ካድሬ ትምህርት ቤት በመክፈት የማኦና የኢንቨርሆዣ (አልባንያ) ስነ ሃሳብ በማሰልጠን የበለጠ ግን ጥርናፈ የሚባል (ታዛዥ) እንዲሆን ካለበለዚያ የገበሬ ሰራዊት አጥብቀህ ካልያዝከው ሊቀይረው ስለሚችል: ከጅምሩ አንገቱ አቀርቅሮ (ደፍቶ) እንዲገዛ የሚል ስልጠና ተሰጠ: በተለይ በዛን ጊዜ ኮሚሳርያት (የፖለቲካ ኃላፊዎች) የነበሩ የመለስና የአባይ ፀሃዬ መዋቅር ሆኖው ተመደቡ:

እነዛ ኮሚሳርያት እጅጉን ፀረዴሞክራሲ ሆኖው ታጋዩን የሚያሰቃዩ ነበረ: የመለስ ሁለት ጊዜ ከጦርነት መሸሸን እየተረሳ መጣ: በሺ የሚቆጠር አዲስ ታጋይ እየመጣ በሂደ ቁጥር እነ መለስ በተለያዩ መንገዶች መዋቅራቸው ዘረጉና ተረጋጉ::

ከ1975 እስከ 1977 ዓ.ም ህ.ወ.ሓ.ት በሁለት አንጃ ተከፈለ: አንዱ በነ አባይ ፀሃዬ ስብሃት ነጋ ስዩም መስፍን ሌሎችም የሚመራ: በሌላ በኩል በግደይ ዘርአፅዮንና አረጋዊ በርሀ የሚመራ አንጃ ተፈጠረ: በዛን ጊዜ የነ አባይ ፀሃዬና መለስ ዜናዊ የአኒማል ፋርም ፍልስፍናቸው በተጠናከረ በመቀጠል: የነ አረጋዊ በርሀ አንጃ ለመመታት ከ1800 በላይ ካድሬ አሰለጠኑ: ከአሰለጠኑ በኋላ ለነ ግደይ ለመምታት የማለሊት ጉባኤ ተጠርቶ እነዛ በአንዱ አንጃ የሰለጠኑ ካድሬዎች ፀረዴሞክራሲ በሆነ መንገድ ተወክለው ተሰባሰቡ : በጉባኤው የነግደይና አረጋዊ በርሀ አንጃ በኃይል ተመቱ በመጨረሻም ወደ ዉጭ እንዲሰደዱ ተደረጉ: እንደነ ተኽሉ ሃዋዝ የመሰሉ ጀግኖች የነግደይና አረጋዊ ተከታዮች ናቸው ተብለው ደብዛቸው ጠፋ: ብዙ ጠንካራ ታጋዮችም እየተሸማቀቁ ትግላቸው ቀጠሉና በፀረደርግ ጦርነት ሞቱ አንዳንደቹም በሂወት ይገኛሉ ቢባሉም መጥፎ የሎሌነት ስራ እየሰሩ ተጓዙ: ብዙ ካድሬዎችና ተራ ታጋዮች ወደ ሱዳን ተሰደዱ ሌሎችም ወደ ደርግ ሂወታቸው ለማዳን ብለው ሄዱ:

መለስ በ1985 ዓ.ም ቀደም ብለው ባለፉት ገፆች እንደተቀመጡ ሁሉ ለስልጣናቸው አስጊ ያሉት 32ሺ ታጋይ አሰሩት ቀጡት: ከ1992 እስከ 1993 ዓ.ም የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ ለሁለት ተሰነጠቀ: አንድ ቡድን የበለጠ ቁጥር የነበረው የነ ገብሩ አስራት አንጃ: አነስተኛ ቁጥር የነበረው ቡድን ደግሞ የመለስና የስብሃት አንጃ ነበሩ: መለስ አስቀድመው ታች ወርደው ካድሬውና አባል አደራጅተው በመቆየት የሰራዊትና ደህንነት ይዘው በመቆየት ለአብላጫው ድምፅ አፍነው ስልጣናቸው አረጋገጡ::

መለስ በ1982 ዓ.ም ካለፉት ገፆች እንደተገለፀው የህ.ወ.ሓ.ት ስራ አስፈፃሚ አብዛኛው የኮሚቴ አባል በስብሃት ነጋ ሴራ አማካይነት አባይ ፀሃዬን ፈንግለው ስልጣን ጨበጡ: አሁንም መለስ እንደ ተለመደው አጃቢ የሚሆኑዋቸው አዲስ ካድሬዎች በስየ አብረሃ ዓለምሰገድ ገአምላክ ተወልደ ወማርያም ክንፈ ገመድህን ወ.ዘ.ተ: አሽከርካሪነት ተሰሚነት ጨበጡ::

መለስ በ1982 ዓ.ም በወቅቱ ኃይለኛ አፈና ስለነበረ በሰራዊቱና በደጀን ብዙ ታጋይ የማመፅ መንፈስ አሳይቶ ነበር: መለስ የማጣራት ዘመቻ በሚል በ10ሺ የሚቆጠር ሰራዊት አሰሩ አባረሩ ከሌሎች ማ/ኮሚቴ በመሆን ጭምር::

መለስ ስልጣን ከያዙ በኋላ ለስልጣናቸው የሚያሰጉዋቸው ማግለል ማባረር ስማቸው ማጥፋት: ታጋይ የነበሩ ባለስልጣኖች የተወሰነ አልነበረም: በ21 ዓመት የስልጣን ዘመናቸው በሲቢል ሙሁራኖች ከራሳቸው አማካሪዎች የነበሩ ከጠ/ሚኒስተር ቢሮ ጀምሮ እስከ ክልሎችና ዞኖች አስተዳዳሪዎች በመውረድ ብዙ ብቁ ሙሁራኖች የሃገር መሪዎች የዩኒቨርሲቲ አስተማሪዎች ምክኒያት በመፍጠር ከስልጣናቸው ዝቅ በማድረግ ከስራ ማባረር: በስልጣን የነበሩ ሰዎች በማያውቁት መንገድ ተሰጠዋቸው የነበረ ስራ በሌሎች ታማኞች እንዲሰራ መድረግ እነዛ ባለስልጣኖች ጠረጴዛ አቅፈው ዉለው ቀን ለሲጋራ ለሊት ለመጠጥ ጓደኞች እንዲሆኑ ማድረግ ይጎዱዋቸዋል: ሌላቀርቶ አመሪካ በስደት የነበሩ ሙሁራኖች አማካሪ አድርገው የሸሙዋቸው እንደነ ፕሮፌሶር ተኮላ ሐጎስ ሌሎችም አመሪካ ያሉ ማሎቻቸው ሃገራችን ሊጠቅም የሚችል ሃሳብና ጥናት ሲያቀርቡላቸው ስልጣናቸውን በማስለቀቅ በመበሳጨ ት ራሳቸው ስራ ለቀው እንዲሄዱ አድርገዋል: በአጠቃላይ መለስ ለስልጣናቸው የሚጋፋ ወይም አዕውቀት ከሳቸው የመጠቀ ሰው በድርጅታቸው ወይም በመንግስታቸው ዉስጥ በአቋሙ ፀንቶ የሚሄድ ካዩ እሱን

ለማስወገ ድ ለማራቅ ብሎም ለማባረር እንቅልፍ አይወስዳቸዉም: ጭራሹም መለስ ቀናተኛና ዲክቴተር ነበሩ::

መለስ በወጣትነት ዘመናቸው እያሉ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ይማሩ የነበሩ አንድ ኢርትራዊ ሲናገሩ መለስ ቀናተኛ በትምህርት ለሚወዳደሩዋቸው እንደጠላት የሚያዩዋቸው እንደነበሩ ይናገራሉ: እንዴት አወቅህ ትሉኝ ይሆናል::

መለስ ከኢተዮ ኢርትራ ጦርነት በፊት ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ከፕርተኮል የዘለለ እንደነበር ሁላችን የሚናው ቀው ነው: በመሆኑ መለስ ፕሮተኮል ያልጠበቀ ጉብኝት ለማድረግ ሙሉጌታ ዓለምሰገድ አስከትለው አስመራ ሂደው ነበር: በዛን ጊዜ በአንድ መዝናኛ ቦታ መለስና ኢሳያስ አፈወርቂ ከቅርብ ወዳጃቸው ሆኖው ውስኪ እየተጎነጩ የቤተሰብ ጭውውት ያደርጉ ነበር: በዛን ጊዜ ከመለስ ጋር በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ህክምና ተማሪ የነበረ ብቻ ሳይሆን እጅግ የቅርብ ጓደኛቸው የነበረ ዶ/ር አብሮዋቸው ነበር: መለስ ከዶ/ሩ ጋርም የልጅነታቸው ሒካያ (ታሪክ) አንስተው ያወሩ ነበር: በዛን ጊዜ ኢሳያስ አፈወርቂ የሚያወሩት በጥሞና ያዳምጡ ነበርና ድንገት ቦግ ብለው ትረካቹሁ ሰማሁ እስቲ አብራቹሁ ከነበራቹሁ የመለስ መለያ ባህረ እንዴት ነበር ብለው ለዶ/ሩ ጠየቁዋቸው: ዶ/ሩም ኢሳያስ የመለስን ባህረ ለማወቅ ያዘጋጀው ይመስል::

ዶ/ሩም መለስ በጣም ጎበዝ ተማሪ ነበር አንደኛ ለመውጣት ለማንም ሰው አሳልፎ አይሰጥም ነበር: ይበልጡኛል የሚላቸው ተማሪዎች ካሉም በተለያየ መንገድ ያስፈራራቸዋል: ከማስፈራራት አልፎ ቡድን በመፍጠር ፈርተው የበታችነትን ተሰምታቸው እንዲደነቁሩ ያደርጋል አለ ዶ/ር: መለስ አንድ ቀን ሳያስበው አንድ ተማሪ ያቺ የመለስ አንደኛነት ነጠቀው: መለስ በቀቃ ለሌት ተቀን ለመተኘኛት አልቸቻለም አለቀሰ በአንድ በኩል ከሁሉ ተደብቆ ያጠናል በሌላ በኩል ለዛ የበለጠው ተማሪ ሲገባ ሲወጣ በመስደብ ከተማሪዎች

በመነጠል ድራሹን አሳጣውና መለስ ቀናተኛ የሚበልጠው ሰው በአጠገቡ ሊኖር የማይፈለግ ጎበዝ ተማሪ ነበር ሲለው ኢሳያስና ጓደኞቹ ፀጥ ያለው መዝናኛ በሳቅ ማሚቶ አስተጋቡት: መለስ ግን ተራ ሳቅ ከመሳቅ አልፈው ያሉት አልነበረም: በአንፃሩ ሎሌያቸው ሙሉጌታ ዓለምሰገድ ተናደደና እንሂድ ቀጠሮ አለብን ብሎ ወሰዳቸው::

ይህ የሚያመለክተው መለስ ከጥንት ጀምሮ የነበረ ባህሪያቸው መሆኑ ነው ኢርትራዊው ጓደኛቸው የነገረን: ከላይ የተዘረዘረው የመለስ የ40ና ከዛ በላይ ዕድሜ ታሪክ ነው የተገለፀው ሌላ ምክኒያት አይደለም: በዚህ አርእስት የአዲስ ራዕይ አዘጋጆችና አለቆቻቸው እነ በረከት ሰምኦን አዲሱ ለገሰ ሬድዋን የፃፉት ወየም እንዲፃፍ ያደረጉት መለስን ለማሞገስ (ለመጋለጥ) አልተረዳኝም: መለስ በሙያቸው ሰርተው በአስርሺ የሚቆጠር ደሞዝ እየበሉ ንሮዋቸው በምቾት ሊገፉ እየቻሉ ለሰዎች ምኦት በማስቀደም በ6ሺ ብር ደሞዝ ተሰቃይተው ይኖሩ ነበር ብለውናል::

እነዚህ ሰዎች 80 ሚልዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ደንቆሮ አድርገዉታል መለስ በ6ሺ ብር ደሞዝ ብቻ ይኖራል ሲሉን የቤተ መንግስት ባጀት ስንት ሚልዮን ነው ለመሆኑ ሂሳብ ያወራርዳሉ: የቤተ መንግስት ባጀት እነ ፍሰሃ አፈወርቂ የፕሮተኮል አጃቢ ሙሉጌታ ዓለምሰገድና ሳሙኤል ገ/ማርያም አጃቢዎች: አቶ በዛብህና ወይዘሮ ትዕበ መስፍን የፋይናንስና ሎጂስክስ ኃላፊዎች በነበሩበት በአስር ሚልዮን ብር የሚቆጠር ሙስና ተጠርጥረው ከአካባቢው አልተወገዱም: ከዛ በኋላ ማን ተቆጣጠረው በየ ቀኑ በየ ሰዓቱ ወደ ዉጭ ሲጓዙ የሚወጣ የዉሎ አበል የሥራ ማስከጃ ትርፍ ገንዘብ ቢገኙም በቤተ መንግስት ዉስጥ የሚመገቡት የእንግዳ መቀበያ ባጀት አልነበራቸዉም: ከዚህ የሚገኝ ትርፍ ገንዘብ እጅግ በጣም ብዙ ነው: ይህ እንተወው ሕጋዊ ሽፋን ያለው ነው: ለመሆኑ ወይዘሮ አዜብ መስፍን በሃገራችን ያሉት ሁሉም አቀፍ ሙሰና ንፁህ

ናቸው: ስለዚህ የሚያውቀው ሁሉ እንሸፍንላቸው ብትሉ ይሸፈናል: ለመሆኑ መለስ ለልጆቻቸው መማርያ ወደ ዉጭ ለትምህርት ለሽርሽር ስንት ሚልዮን ዶላር ያወጣሉ ብላቹሁ ሂሳብ ብታወራርዱ ስንት ይሆናል?: ይህ ሂሳብ ማንም መሃይም የሚያወራርደው ሂሳብ ለመሸፈን አትችሉም::

ስለዚህ መለስ የነበራቸው ፍለጎት የስልጣን ጥማታቸው ለዘለቄታ ጠብቀው መኖር: ስልጣናቸው ተጠብቆ ከኖረ ደግሞ የገንዘብ የሃብት ማካበት በሕጋዊና በሕገወጥም ሁሉ በእጃቸው መሆኑ ያውቁ ነበር: ስለሆነ የአዲስ ራዕይ አዘጋጆችና አለቆቻቸው ለራሳቸው ደንቁረው ለኢትዮጵያ ህዝብ እያስደነቀሩት ከህዝብ የሚሰወር ነገር ስሌለ: መለስ ዩኒቨርሲቲዎች እስከ 32 ማድረሳቸው ግልፅና በመሬት ያለ ነው: ሆኖም ግን ከላይ እንደተዘረዘረው የትምህርት ጥራት የለም ስራ ፈጣሪ አይደለም: ከትምህርት መስፋፋት ተያይዞ የተማረ የሰው ሃይል የሚሰራበት በትክክል ኢኮኖሚ ፖሊሲ ተነድፎ የስራ መስክ አልተፈጠረም: የተፈጠረ ስራ ቢኖር ሐኪም የግብርና ሳይንስ ኢኮኖሚስት ወ.ዘ.ተ ተምሮ የድንጋይ ማንጠፍ ስራ ነው መለስ የፈጠሩ የስራ መስክ::

መለስ ተማሪ ሁሉ በስነ ዜጋና ስነ ምግባር የታነፀ ዜጋ ያፈራ መሪ ስትሉን ምን ማለት ነው: በስነ ዜጋና ስነ ምግባር የታነፀ ዜጋ እኮ ሙሰናን የሚቃወም አፍና ፀረዴሞክራሲ የሚቃወም ኢፍትሃዊ አሰራርና ተግባራት የሚያወግዝ ለራሱ ብቻ ከማሰብ የህዝብ ምቾት የሚያስቀድም ለሃገሩ ሂወቱ የሚሰጥ ወ.ዘ.ተ ማለት ነው::

መለስ ያፈሩት ተማሪ ግን የተበላሸ የመለስ አመራር ሁሉ የፀጋ የሚቀበል: በተበላሸ የመለስ ስርዓት ምክኒያት በቁሙ እየሞተ የሚያንጨበጭብ ትውልድ የተበላሸ ስርዓት ከማስወገድ በብስጭት ወደ ሱስ ፋብሪካ ተዘግቶ ራሱን በራሱ የሚገድል ወጣት: በመለስ ስርዓት ነው የተፈጠረው ሃገራችን በመለስ ዘመን በሙስና ኢፍትሃዊ

አሰራር ታውራ እያለች በሩቅ ሆኖ የሚመለከት ወገን ነው የተፈጠረው በመለስ ስርዓት::

መለስ ሃገራችን ለህዝቧ ምቾት የሆነች ያደረገ መሪ ብላቹሃል ራዕዮች: እቺ ሃገር እኮ ባለፉት ገዖች እንደተገለፀም አዲስ ራዕዮች በጎጃም በኦሮሞ በደቡብ ህዝቦች በጎንደር በሰሜን ሸዋ በትግራይ በሰቆጣ በዓፋር በሱማል በጋምቤላና በሌሎች አካባቢዎች በገጠር በከተማ ሂዳቹሁ በቃ ያው የሚገኝ ወጣት ስንት ነው ብላቹሁ ብታጠኑ: በየ ምድረ በዳው የሚሞት የሚታረድ ተዉትና ወደ ዓረብ ሃገር ተሰዶ እዛው በየ ቀኑ ተገድሎ ሬሳው የሚገባው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ይቁጠረው: በየ ከተማውና ገጠር ያለ ስረአጥ ወጣት ስንት ነው ስንት ሴቶች ለመኖር ሲሉ ለዝሙት ገበያ የሚወጡ: የማታውቁት አይመስለኝም ልትዋሹ ስለፈለጋቹሁ ነው::

በየከተማውና ገጠሩ ያለው ስራጥ ወጣት ስንት ነው በየ መጠጥ ቤቱና በየ ጎዳናው የሚታዩ ናቸው ራሳቹሁም ተሳታፊ ናቹሁ: በመለስ ዘመን ወደ ስደት ሃገር ክፍት ነበር አሁንም አለ: ይህ ተግባር ለወገኖች ምቾት ተብሎ የተሰራ አልነበረም ሆን ተብሎ ያ ሁሉ ወጣት በሃገር ቤት ቁጭ ካለ ለመለስ በስልጣን መኖር እንደየተቀበረ ፈንጅ ስለሆነ ዙሮ ዙሮ የኋላ እሳት (Back fire) እንዳ ይፈጥር ከፊቴ ይራቅ ቢፈልግ ይጥፋ: ብለው የፈቀዱበትና ለህዝብ ምቾት ሳይሆን ለራሳቸውና ለጓዶቻቸው ምቾት ተብሎ የተሰራ ነበር: ይህ ደግሞ እናንተም የኢትዮጵያ ህዝብም ያውቀዋል: መለስ ለዜጎች ምቾት የሚያስቡ ቡሆን ንሮ እንሆ የሃገራችን ሃብት በትእምት በጥረት በድንሾና በሌሎች የመንግስትና በፖለቲካ ፓርቲዎች ተይዞ ያለ በመቶ ቢልዮን የሚቆጠር ሃብት በባለስልጣኖ ች በጥቂት ባለሃብቶች እጅ ያለ በሙስና የተሰበሰበ የሃገር ሃብት ወደ ልማት ቢያውሉት የሰዎች የስራ ዕድል ይፈጥር ነበር የዜጎች ምቾትም በኖረ ነበር: መለስ ግን በስልጣን ዘመናቸው ለጥቂት የመንግስት ባለስልጣኖች መለስም ጨምሮ ጥገኛ ባለሃብቶች

ለሙሰኞች ምቾት ጠበቃ የተመቹ ነበሩ እንጂ ለህዝባችን ምቾት የተመቹ አልነበሩም::

## ክፍል 17

## "መለስ ዓለም በአብነትነት የወሰደውን የጤና የቀየሰና ያሳካ መሪ"

የመለስ የሕክምና ፖሊሲ ለዓለም አብነትነት ማለት ምን ማለት ነው: ኢትዮጵያ መጀመርያ ነገር ለዓለም በአብነትነት ስትቀመጥ በየትኛው መስፈርት ነው: በተካኑ የሕክምና ባሙያዎች በማባረር ወይም የሚያሰራቸው የሕክምና ፖሊሲ ብቁ ባለመሆኑ: የሓኪሞች ክብርና ምቾት አጥተው ወደ ዉጭ ሃገር እንዲሄዱ በማድረግ: የመንግስት ሆስፒታሎችና ክልኒኮች በብልሹው አሰራራቸው ምክኒየት የተካኑ ሓኪሞች ስራዉን እየለቀቁ በግል ሆስፒታሎች መቀጠራቸው ወይም የመንግስት ስራ ጥለው የራሳቸውን ክሊኒክ በመክፈታቸው: በኔ እምነት መለስ በሃገራችን ከፍተኛ ሓኪሞች የሚያቀርቡት የጤና አጠባበቅ ሃሳብና ሙያ በመለስ ተቀባይነት አልነበረዉም: በመሆኑ ደግሞ 1ኛ ነባር ሓኪሞች ተቀባይነት በማጣታቸው በሃገራቸው ክሊኒክ በመክፈት ወደ የግል ስራቸው ተሰማርተዋል: 2ኛ አብዛኛቾው ሃገር ለቀው በስደት ይኖራሉ: የስደቱ ዋና መነሻ መለስ የሕክምና ሳይንስ አመራር በመቀበል ፈንታ ለሕክምና ተክኒክ ፖለቲካ ይምራው ስላሉ ነው: የፓርቲ አባል ያልሆነ የሕክምና አመራር ሊሰጥ አይቻለም በማለት የሓኪሞች ሙያ በቀበሌና በሕክምና ሙያ ያልነበራቸው ካድሬዎች የልማት ሰራዊት ይምሩት በማለታቸው

ሓኪሞች ከሙያቸው ዉጭ ሊመሩ ባለመፈለጋቸው ነው: ይህ አመራር አለመቀበላቸው ትክክል ነበር::

"አዲስ ራዕይ ገፅ 48 አዲስ መስመር 2 መስመር 4: መለስ በኢትዮጵያ ለሰው ልጆች መልካም ሁኔታን የፈጠረ የጤና መርሃ ግብር ተዘርገቶ አንፀባራቂ ዉጤት አግኝተዋል: በዚህ ረገድ የመለስ አሰተዋፅኦ የሚጀምረው የበሽታን መከላከል ማእከል ባደረገው የጤና ፖሊሲ ነው::"

የበሽታን የመከላከል ፖሊሲ በህ.ወ.ሓ.ት የተጀመረው በመለስ ዘመነ አገዛዝ ሳይሆን በትጥቅ ትግል ወቅት በ1978 ዓ.ም በህ.ወ.ሓ.ት ለመታገል በተሰለፈው የጀመርያ ዶክተር ተወለ ለገሰ ነበር: በሽታን በማከም ሳይሆን ለመከላከል ቅድሚያ በመስጠት በከተማም በገጠርም የመከላከል ስራ መሰራት አለበት ብሎ ደርግ ከስልጣን ከመወገዱ በፊት መለስ ቁንጮ ከመሆናቸው በፊት 5ዓመት ቀድሞ ነው በነፃ ቦታ የተጀመረው: ከተወልደ በፊትም የህ.ወ.ሓ.ት ሓኪም ሆኖ ከ1968 ዓ.ም ማዝያ ወር ወደ ህ.ወ.ሓ.ት ትጥቅ ትግል የተቀላቀለው አባዲ መስፍን የጤና ሞከነን ባለሙያ የነበረ ከማከም መከላከል ቅድሚያ የሚል በሰራዊት አልፎ አልፎም በህዝብ ያስተምር ነበር: በፖሊሲ ደረጃ ግን የተቀመጠ አልነበረም: የመከላከል ፖሊሲ ያስቀመጠው ዶክተር ተወለ ለገሰ የትውልድ ቦታቸው አክሱም በ1983 ዓ.ም ጉንበት መጨረሻ አዲስ አበባ በህ.ወ.ሓ.ት ቁጥጥር በዋለ ጊዜ ከትግራይ ወደ አዲስ አበባ እየተጓዙ በደሴ ጢጣ አካባቢ በማኪና አደጋ ሂወታቸው አልፈዋል: አዲስ ራዕዮች ግን ፖሊሲው የተወልደ ለገሰ ሃሳብ እያለ መለስ ያመነጨው ሃሳብ ማለታቹሁ ትልቅ ወንጀል ነው ዉሸት ነው::

"ገፅ 48 አዲስ መስመር 2 መሰመር 6: እጅግ ብዙ ያወቁ የነቁ የጤና ሙያተኞች በሃገራችን በሽታን ከመፈወስና ከመከላከል አማራጮች መካከል መፈወስን እንደ መጀመርያ ምርጫቸው ወስደው ሆስፒታል ን ማስፋፋት ቅድሚያ ተግባራዊ መሆን አለበት

ባሉ ጊዜ መለስ የሃገራችን 80% በሽታዎች በመከላከል ይታከማል በሚል ሊፈወሱ የሚችሉናቸው ብለው የመከላከል መርጠዋል ብላቹሃል::"

በ10 ዓመት ዉስጥ በብዙሺ የሚቆጠሩ ህዝቦች የጨረሰ ብዙ አባወራዎች ዘር አልቦ ያስቀረ ተላላፊ በሽታ በጊዜው ተቆርቋሪ በሆኑ ሰዎች በሃገር ዉስጥም በዉጭም ብዙሃን መገናኛ የአምላክ ያለህ ብለው ቢናገሩ ለመንግስት ባለስልጣኖች አመለክተው የሃገር ሚስጢር አሳልፈው የሸጡ ከጂዎች ተብለው የተወቀሱበት ነበሩ:: ከነዚህ ሊጠቀሱየሚገባቸው ከጉዳዩ ስለዜጋቸው የተጣበቁ አስገደ ገ/ስላሰ ጋዜጠኛ ግርማይ ገብሩ የታሕታይ ቆራሮ ወረዳ አስተዳዳሪ ግንባር ቀደም ይጠቀሳሉ::

አዲስ ራዕዮች ለመሆኑ መለስ ዜናዊ ስለበሽታን ከማከምና ሆስፒታል ከማስፋፋት የመከላከል ሕክምናን እናስቀድም ሲሉ እንዴት ብለው ነው: ከሽግግር መንግስት ጀምሮ በኢትዮጵያ ጤና ጥበቃ ሚኒስተር ከፌደራል እስከ ዞንና ወረዳ መዋቅር የተዘረጋ ነበር: ያን መዋቅር በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሓኪሞች በሽታ እንዴት ለመቆጣጠር እንደሚቻል በሙያ የተካኑ ዶክቶሮች ጤና መኮነኖች ከፍተኛና ዝቅተኛ ነርሶች ነበሩ: መለስ በዚህ ሙያ የተካኑ አልነበሩ ም: በየትኝኛው መሙየያቸው ነው የመከላከል ፖሊሲ የነደፉት: እነዛ ባለሙያዎች ሂወት አልነበራቸዉም: የነዶክተር ተወለ ለገሰ ሃሳብ ትርጉም አልነበረዉም: ወይም መለስ ለሙያተኞች የሚሰጡት የነበረ ዕውቅና ዝቅተኛ ስለነበረ ነው: በኔ እምነት መለስ ከትጥቅ ትግል ጀምሮ ህ.ወ.ሓ.ት ለሙሁራኖች በነበረው አለመተማመንና ጥርጣሬ የወለደው አመለካከት ተከትለው የፈለሰፉት ነው: እንጂ መለስ የሃገራችን የሕክምና አቅጣጫ ሊያስቀምጡ አይችሉም: እዚህ ላይ ግን አዲስ ራዕዮች የምትሉን ያላቹሁ መለስ ለሁሉም ነገር እኔ ባልኩት ይፈፀም ካለበለዚያ ግን ወየዉላቹሁ የሚሉ አምባገነን መሪ ነበሩ ብላቹሁ እየነገራቹሁን ነው: እዚህ ላይ እኔም እስማማለሁ:

መለስ ከትጥቅ ትግል ጀምረው ታዋቂነት ለማትረፍ ብለው በሁሉም የስራ መስክ ጣልቃ በመግባት የራሳቸው ምጡቅነት ለማሳየት ሌሎች ታጋዮች የሰሩት አመርቂ ስራ ሳይሰሩ ሳይደክሙ የሰዎችን ስራ የመቀማት ችሎታ እንደነበራቸዉ የህ.ወ.ሓ.ት ሁሉም ታጋይ በተለይ የህ.ወ.ሓ.ት ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ማ/ኮሚቴ አበጥሮ ያውቃል : ስለሆነ በሽታን በሆስፒታል አስተኝቶ ከማከም አስቀድሞ በመከላከል ፖሊሲ ማከም የሚል የመለስ ፍልስፍና አልነበረም: የዶክተር ተወለና የሌሎች ኢትዮጵያውያን ዶክቶሮች ፍልስፍና ነበር::

"በገፅ 48 አዲስ መስመር 3 መስመር 3: በአሁኑ ጊዜ በገጠር ብዙ ተላላፊ በሽታዎች በቁጥጥር ስር ዉለዋል::"

አዲስ ራዕዮች ይህ 80 ገፅ ፅሑፋቹ በገጠርም በከተማም የሚያነበው ሰው የለም: ምክኒያቱም ያቺ 6ሚልዮን መፅሐፍ ከአባላት ዉጭ ስለማትደርስ የሚያውቃት ህዝብ የለም: ስለሆነ ዋሸተን ብንፅፍ በህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግን ተወዳጅነት እናገኛለን ብላቹሁ እንደፃፋቹሁ ተገንዝበናል: ግን ደግሞ ስንቅና ዉሸት እያደረ ይቀላል እንደ ሚባለው አዲስ ራዕዮችም ለራሳቹሁ ክብር ቀነሳቹሁ የመለስ ክብርም አወረዳቹሁ::

ሐቁ አንድ ሁለት ሶስት ሐቆች ልጠቁማቹሁ: መለስ በተወለዱበት ክልል በትግል ጊዜ ይደበቁባት የነበረች ሽሬ አውራጃ በታሕታይ ቆራሮ ወረዳ አስተዳደር በቀላቅል ቀበሌ ፃዕዳ አንባ በተባለ ጎጥ የጀመረ ዘርጨራሽ በሽታ በሰዉነት ኃይለኛ ትኩሳት በመልቀቅ የሚያሳብድ ሰዉነትን የሚያደቅና የሚያቆስል: ሆድ ነፍቶ ጉበትና ኩላሊት አንጀት ጣፍያ ሰንባ እንዚህ አካላት የሚያበሰብስ: በ10 ዓመት ዉስጥ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች እንደፈጀ ነው: ብዙ ቤተሰብ የጨረሰና ተላላፊ በሽታ በቁጥጥር ስር ካልዋለ ለአካባቢው አደገኛ ነው: ይህ በሽታ በሃገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ ኒድያዎች የአምላክ ያለህ ብለው ቢናገሩ ለመንግስት

ባለስልጣኖች አመልክተ ዋል: የሃገር ሚስጢር አሳልፈው የሸጡ ከጂዎች ተብለው የተወቀሱበ ት ነበሩ ከነዚህ ሊጠቀሱ የሚገባቸው ጉዳይ ስለወገኖቻቸው ጠበቆች የሆኑ እንደ አስገደ ገ/ስላሰ፣ ጋዜጠኛው ግርማይ ገብሩ፣ የታሕታይ ቆራሮ ወረዳ አስተዳዳሪ አባገርቹ ግንባር ቀደምት ይጠቀሳሉ: በሽተታው እስከ መለስ ህልፈት ነበረ አሁንም ህዝቦች እየቀጠፈ ይገኛል: መለስ ይህ በሽታ ይፋ እንዳይሆን አፍነዉታል: ይህ በሽታ መለስ በሂወት እያሉ ከሽሬ አውራጃ በምዕራብ እስከ ሑመራ ከሽሬ ወደ አክሱም ዓድዋ ተንቤት ክልተ አውላዕሎ ዉቅሮ ተስፋፍተዋል: ሌላ በሑመራ እንደካላዘር በሽታ በጎንደር በሰሜን ሸዋ በኦሮሞ በአፋር በሌሎች ክልሎች ዘግናኝ በሆኑ ተላላፊ በሽታዎች ብዙ ህዝብ ያልቅ ነበር አሁንም እያለቀ ይገኛል::

የመከላከል ጉዳይ ካነሳን ከሁሉ በፊት ለህዝቡ ንፁህ የመጠጥ ዉሃ ማግኘት አንዱ ነበር: ሆኖም ግን በአብዛኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ዉሃ የላቸዉም: የወረዳ የቀበሌ ከተሞች ዉሃ ሊያገኙ አይታሰብም: ከ70 ሺ በላይ ህዝብ የሚኖርባቸው የነዛ ከተሞች በሙቶ ሺ የሚቆጠር ህዝብ የሚነሩባቸው ከተሞች ዉሃ ባለመኖሩ ሰዎች ለዉሃ ወለድ በሽታዎች ታመው የሚማቅቁና የሚሞቱ ሰዎች ቁጥራቸው ብዙ ነው::

መለስ እንደመፈክር አድርገው የሚጠቀሙበት በኢትዮጵያ ምድረ ሂወት የሰጠችን እናት ሂወት ማጣት የለባትም የሚል ከመፈክር አልፎ በትግራ ትርጉም የለዉም: ለዚህ እንደማስረጃ በትግራይ ክልል አስተዳደር ከ20/5/2005 እስከ 22/5/2005 ዓ.ም በተደረገ ው የምክር ቤት ጉባኤ በ 6 ወር ዉስጥ 72 ሴቶች በወሊድ እንደ ሞቱ አቶ አባይ ወሉ ገልፀዋል: ይህ አሃዝ ግን ከዛ በላይ ሞት እንዳለ ነው የሚታወቀው: በሌላ ክልሎች እጅግ ብዙ ሴቶች በወሊድ እንደ ሚሞቱ ነው የሚታወቀው: ስለዚህ የመለስ የበሽታ መከላከል ሕክምና በሃገራችን አልተተገበረም::

“ገፅ 48 አዲስ መስመር 2 መስመር 6: ከወሊድ ጋር የተያያዘ የእናቶችና የህፃናት ሞት ቀንሰዋል: በሽተኛ በቃሬዛ ለቀናት ተሸክሞ መጓዝም ሆነ በሐኪም እጦት መሰቃየት በእጅጉ ቀንሰዋል: ይህም በጓድ መለስ ትክክልኛ አቅጣጫና ተግባራዊ እቅስቃሴ ነው ይላል አዲስ ራዕይ::”

አዲስ ራዕዮች በአሁኑ ጊዜ በተጨባጭ በተለያዩ ወረርሽኝ በሽታ በሃገር ደረጃ በተለይ በገጠር ነዋሪ ሌላ ቀርቶ እጅግ ኋላ ቀር የሆኑ እንደኩፌኝ ያሉ ከተሞች እንኳን ሳይቀሩ ይከሰታሉ በገጠር ግን ሁሉም ወረርሽኞች አሉ: የህፃናትና የእናቶች ከወሊድ ጋር የተያያዘ ሞት ምንም ለውጥ የለዉም: ከላይ እንደተገለፀው በትግራይ ክልል ብቻ መሪዎች ባመኑበት 72 ሴቶች በ6 ወር ዉስጥ ሞተዋል: ይህ ደፍረው መናገራቸዉም ጥሩ ነገር ነው ሐቁ ግን በገጠሩ ሃገራችን በየ ቀኑ በወሊድ ምክኒያት የሚሞቱ እናቶችና ህፃናት እጅግ ብዙ ናቸው: ስለዚህ የመለስ የህክምና አቅጣጫ መዋቅሩን የማያንቀሳቅስ በአየር የተንሳፈፈ ፖሊሲ ነበር: አሁንም ምንም ለውጥ የለዉም::

መለስ ትክክለኛ ፖሊሲ ቢኖራቸው ንሮ በሃገራችን አንጡራ ሃብት የተማሩ ዶክተሮች በሚገባ በመያዝ ዕውቀታቸዉን በሚገባ ገንብተው ለሃገራቸው እንዲያገለግሉ በማድረግ ፈንታ ለነዚህ ዶክተሮች ክብርና ዕውቅና በመከልከላቸው ሞራላቸው በመነካቱ ምክኒያት ተስፋ ቆርጠው ወደ ዉጭ እንዲሰደዱ አድርገዋል: በአንድ ወቅት ከኦሮሞ ብቻ 70 ዶክተሮች ከትግራይ 40 ሥራ የለቀቁና ወደ ስደት የሄዱ የፌደራል ባለስልጣናት በብዙሃን መገናኛ ተናግረዋል: ይህ ለአብነት ቀረበ እንጂ መለስ ስልጣን ከያዙበት በ21 ዓመት አገዛዛቸው ወደ ዉጭ የሄዱና ሥራቸው የለቀቁ እጅግ ብዙ ናቸው ለማለት ይቻላል::

ሌላ ትልቅ የመለስ ስህተት የሃገራችን ሐኪሞች አቅም ገንብተው ሁሉን አቀፍ ሕክምና በሃገር ዉስጥ እንዲኖርና ሰዎች በእኩልነት በሃገራቸው ባለሙያዎች ታክመው የዉጭ ምንዛሬ ሊያድኑ እንደ

*ማድረግ ፈንታ ሃገራችን በሕክምና ረገድ ለጥቂት የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ባለስልጣኖችና ቤተሰባቸው ዘር ማንዘራቸው ለጥቂት ባለሃብቶች የተመቸት እንዲትሆን ያደረገ የመለስ ፖሊሲ ነበር::*

*በመለስ ዘመነ ስልጣን እኮ ራሴን አመመኝ ወገቤን ቆረጠመኝ ያለ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ባለስልጣንና ዘመድ አዝማድና አጋሮቻቸው ሃብታሞች የሚታከሙት ታይዋን፣ ባንኮክ፣ አመሪካ፣ ጀርመን፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ዱባይ፣ ሰዑዲ ዓረብያ፣ ኮርያ፣ እስራኤል ወ.ዘ.ተ ነው የሚታከመው: የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግና ግብረ አበሮቻቸው ታይዋን ባንኮክ ሄዶ ታሽቶ ስቡን ያላማማና ያላስወገደ የለም: ይህ ሁኔታ የኢ.ትዮጵ.ያ ህዝብ የሚያውቀው ነው: የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ዝቅተኛ አባል ቢያንስ ቢያንስ ባንኮክ ባይሄድም በሃገር ዉስጥ በግል ምርጥ ሕክምና ነው የሚታከም: ወደ የመንግስት ሆስፒታሎች አቅጣጫ ዞር ብለው አያዩም: ወደ መንግስት ሕክምና የመለስን ቅርብ የነበረ ጦር ሃይሎች ነው የሚታከሙ: ስለዚህ በመለስ ጊዜ ሕክምና ለሰው ምቾና በሰዎች መካከል የነበረ ልዩነት የሚያጠብና የተመቸ ሳይሆን የነበረ: አድላዊና መደብ የለየ የሃገራችን ዶላር ለገዢዎች የቅንጦት ሕክምና ያባከነ ነበር: መለስ ለሃዬ ኃይለስላሰና ለደርግ ስርዓቶች እየኮነኑ ንሮው አሁን ራሳቸው መድገማቸው እጅጉን አሳዛኝ ነበር::*

*የመለስ የሕክምና አቅጣጫ በተጨባጭ ለኢ.ትዮጵ.ያ ብዙሃን ህዝብ የቆመ የተመቸ ሳይሆን ከራሳቸውና ቤተሰባቸው ጀምሮ እስከ ታች መዋቅራቸው ያለው ታማኝ አባልና ሽሪካቸው ለሆኑ ጥቂት ባለሃብቶች የተመቸ ነበር: ልብ በሉ በታይዋን ባንኮክና ደቡብ አፍሪካ ሰዑዲ ዓራብያ ዱባይ ወ.ዘ.ተ ምርጥ ሆስፒታሎች ለምርጥ ዜጎችን ለሕክምና የሚወጣ በመቶ ሚልዮን ዶላር ሲከፈል ያዩ የሃገራችን ዜጎችና የዉጭ ሃገር ኢ.ትዮጵ.ያ ምን ያህል የተከማቸ የዉጭ ምንዛሬ ቢኖራት ነው ብለው የሚገርማቸውና የሚያስጨንቃ ቸው ብዙ ናቸው: ስለዚህ የአዲስ ራዕይ አለቆችና አዘጋጆች ሐቁን*

መስክሩ: ዋና ችግር ግን ራሳቹሁን ተጠቃሚዎች ስለሆናቹሁ ሐቀኛ ምስክርነት አይጠበቅም::

የተከበራቹሁ የኢትዮጵያ ህዝቦች በመለስ ዘመነ መንግስት በሺ የሚቆጠሩ ጤና ኬላዎች እንደተሰሩ የሚካድ ሐቅ አይደለም: በትግራይ ክልል ብቻ ከ900 በላይ ጤና ኬላዎች አሉ በሃገር ደረጃ ሲሰላ አጅግ ብዙ ናቸው: በትግራይ ያሉ ጤና ኬላዎች የተሰሩት በህዝብ ጉልበትና ገንዘብ ናቸው የቤቶቹ ስፋት 3x4 =12 ሚተር ካሬ ነው በዛ ቤት የሚሰሩ የሕክምና ባለሙያዎች የወባ ከኒና እንዴት እንደሚሰጥ ማብራርያ የተሰጣቸው አርሶ አደር ናቸው: በጤና ኬላው መድሃኒት የሚባል ነገር የለም: የመመርመርያ ላቦራቶሪ አይታሰብም የለም: ከኒና የሚያከፋፍል ገበሬ ታድያ የወባ ከኒና ሊሰጥ ከሆነ በየትኛው ምርመራ የተረጋገጠ ነው: የወባ በሽታ ያላቸው የሚመስሉ ሙቀትን የሚፈጥሩ በሽታዎች ብዙ ናቸው ታድያ ምን ዓይነት የመከላከል ፖሊሲ ነው የመለስ አቅጣጫ::

ሌላ የጤና ጣብያዎች ክሊኒኮች ለስሙ ይኑሩ እንጂ አብዛኛቸው ላቦራቶሪ መድሃኒቶች ብቁ ሐኪሞች እንኳን የላቸዉም: ታድያ ሂወት የሰጠችን እናት ሂወታችን ማጣት የለበትም የሚል መፈክር በምንድንው የሚገለፀው: ስለዚህ ከበሽታን ለመዳን ሕክምና ቅድሚያ በመከላከል የሚል ፖሊሲ የመለስ ፍልስፍና ባይሆንም የመከላከል ሕክምና ጭራሹን በመሬት የለም: ይህ ሁኔታ የኢትዮጵ ያ ህዝብ ያውቀዋል: ስለሆነ አዲስ ራዕዮች የምትሉን ከሐቅ የራቀ ነው::

## <u>ክፍል 18</u>

## <u>"መለስና የኢትዮጵያ የብርሃን ዘመን"</u>

በአርእስቱ የተቀመጠው መለስና የኢትዮጵያ የብርሃን ዘመን የሚለው ትክክል አይደለም: ብርሃን ማለት ምንድን ነው:

የኢሊክትሪክ አንፖል አድርጌ ብርሃን ባገኝ: ብርሃን ያለ ምግብ ብርሃን ያለ ልብስ ብርሃን ያለ ዉሃ ያለ ፍትህ ያለ ነፃነት ያለ መልካም አስተዳደር ያለ የፕሬስ ነፃነት እንዴት ብሎ ይመጣል::

ብርሃን ነፃ የመደራጀት ሰላማዊ ሰልፍ ለመውጣት ነፃ የኢኮኖሚ ክፍፍል ሰው ሰርቶ የሚኖርበት በሌለበት እንዴት ብሎ መለስ የኢትዮጵያ ብርሃን ይባላል: እስቲ አንድ በአንድ የመለስን ብርሃንነ ት ብለው ያስቀመጡት የአዲስ ራዕይ አዘጋጆችና አለቆቻቸው እንመልከት::

"በገፅ 49 አዲስ መስመር 2 እስከ ገፅ 52: በኩበት በጭራሮ እሳት አሳሯን እየበላች ሌላዋ በከፍተኛ የኢሊክትሪክ ኃይል በመጠቀም ስራና ንሮ ቀሏት የምትኖርበት ይህን ተከትሎ በሰዎች መካከል የሚፈጠሩ የመቀናቀንና የቅናት ባህል በመሰበር ፍቅርን በማጎልበት በሃገራችን ታሪክ ወደር የሌለው ብርሃን የማምረትና የማከፋፈል ስራ የሰራ ታላቅ የህዝብ ልቺ ነው ይላሉ::"

በመለስ ዘመነ ስልጣን በ 21 ዓመት ዉስጥ ብዙ መሰረተ ልማት ተሰርተዋል: ከነሱ ዉስጥ አንዱ የኢልክትሪክ ኃይል በብዛት በማፍራት ህዝብ እንዲጠቀም ተብሎ እንደተወሰደ ነው ሰዎች የሚረዱት: በበኩሌ ግን የምመለከተው የመለስ ስርዓት ለመራመድ መለስን በስልጣን ለመቆየት ከሆነ በዚህ ፅሑፍ መጀመርያ አካባቢ እንደተገለፀው ጣልያን የወራሪ አገዛዙ ለማቆየትና ቅኝ አገዛዙ ለማስፋፋት መሰረተ ልማት መስራት የግድ ይለው ነበር: በመሆኑ ደግሞ በ5 ዓመት ዉስጥ ብዙ መሰረተ ልማት ሰርተዋል: የኢትዮጵ ያ ህዝብ ግን ይገደል ይታሰር በሃገሩ ዉስጥ 3ኛ ዜጋ ሁኖ ነው የነበረው::

መለስም አንባገነናዊ ዲክታቶራዊ ስርዓታቸው ለማራመድና በስልጣን ኮርቻ ሊኖሩ ከሆነ ህዝቡን የሚይዙበት መሰረተ ልማት ማስፋፋት ግድ ይላቸዋል: ሃዬ ኃይለስላሰና መንግስቱ ኃይለማርያም ለስልጣናቸው መኖር ሲሉ የኢሊክትሪክ ኃይል ማመንጫ በመስራት

በናፍጣ የሚሰሩ ሞቶሮች በመዘርጋት ቅድሚያ የራሳቸው ምቾት ለማረጋገጥ ሲሉ ሰረተዋል: ህዝብ ግን ተጠቃሚ አልነበረም::

መለስም የጀመሩት ስራ በተጠናከረ መንገድ በመከተል ብዙ ግድቦች በመስራት በንፋስ ኢሊክትሪክ የሚያመነጭ ኃይል ፈጥረዋል: መለስ የኢሊክትሪክ ኃይል ለራሳችን ችለን ለዉጭም እንሰጣለን ብለው ነግረውናል: ለጁቡቲም ለሱዳን መሸጥ ጀምረው ነበር: ይህ ተግባር ግን አዲስ ራዕዮች እንደምትሉን በሃገራችን ኢሊክትሪክ ትርፍ ሆኖ ሳይሆን የመለስን ጥናት የጎደለው በግብታዊነት መጋለብ ነው የሚያመለክተው::

ሐቁ ግን እንደምትሉት የኢትዮጵያ ህዝብ ኩበትና ጭራሮ ጢስ የተገላገለ አይደለም: የገጠሩ ህዝብ 100% የኢሊክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ አይደለም: የከተማ ህዝብም አብዛኛው አንዲት አምፖል ለመብራት የሚጠቀም እንጂ ለምግብ ማብሰልና ሌሎች የኢሊክትሪ ክ ዉጤቶች የሚጠቀም አልነበረም አለም: የኩበትና የጭራሮ ጭስ የማያገኛቸው ወገኖች በመንግስት ቤት ተቀምጠው በነፃ ኃይል የሚጠቀሙ አብዛኛዎቹ የመለስ አባላትና ወይም አትራፊ የሆኑ ባለሃብቶች አነስተኛና ጥቃጥን ተቋማት ከፍተኛ ደሞዝ ያላቸው የመንግስት ሰራተኛ ናቸው ተጠቃሚ የነበሩ አሁንም አሉ: ሌላው ህዝብ ግን አሁንም የሃገር እፅዋት እያወደሙ የሚገለገሉ ያሉ ናቸው: ምክኒያቱም የኢሊክትሪክ ኃይል እንዳ ይጠቀሙ ዋጋው ከፍተኛ ስለሆነ ተጠቃሚ አልሆነም: ታሪፍ አነስተኛ ቢሆን ኖሮ በከተማ የሚኖር ህዝብ ኢሊክትሪክ በርካሽ ዋጋ ቢጠቀም ደንን አውድመው ለገበያ የሚያቀረቡ ዜጎች የሚገዛ አጥተው ምድረ በዳነት በቀነሰ ነበር: እዚህ ላይ ኢሊክትሪክ የተዘረጋው በብድር ስለሆነ መከፈል ስለአለበት ዋጋው ከረከሰ መቼ ይከፈላል ነው ልትሉን: እኔ የምለው ያለሁ ደግሞ ዕዳው መከፈል የግድ ይላል ግን በተራዘመ ጊዜ ሊከፈል ስለሚችል የመብራት ታሪፍ መቀነስ አለበት: ካለበለዚያ ደንን እንዳይወድም ምድረ በዳነት ለመከላከል

አይቻልም: መለስ የዓለማችን የካርቦን ልቀት በመከላከል የሙቀት መጠንን እንቀንሳለን እያሉ በሃገርም በዓለምም መድረክ እየወጡ ዲስኩራቸዉን የሚያሰሙት በኢትዮጵያ ሊተገበር አይችልም: ከንቱ ዲስኩር ከመሆን አልፎ::

"በገፅ 50 አዲስ መስመር 2: ይህን አቅም የተገነዘቡት መለስ ብርሃን ለሰው ልጆች ለማዳረስ ይህንን አቅም ሃብት ለማልማት ስራዬ ብለው ተያይዘውታል: መጀመርያ ገልገል ግቤ ከዛ ተከዜን ከዛም ጣና ጭስ አባይ: ገልገል ግቤ ሶስትን ተሰራ አሁን ደግሞ ፈለገ ግዮን በመለስ አመራር ተደፈረ አዲሱ የኢትዮጵያ የአፍሪካ ቀንድ የብርሃን ዘመንም 6ሺ ሜጋዋት በሚያመነጨው በታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ተበሰረ ብለውናል::"

አሁንም የምትሉዋቸው ግድቦች ተገድበዋል አባይም ተጀምረዋል እነዚህ መገደባቸው አባይም መጀመሩ ማንም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሚቃወም የለም: ነገር ግን መለስ ለሁሉም ነገር ብቻቸው በግብታዊነት የሃገር ሙያተኞች ሙሁራን ሳያማክሩ የሰሩት ስለነበ ር በተከዜ ከ300 ሜጋዋት በላይ ለማመንጨት ተብሎ የተሰራ የሚያመነ ጭ ወደ 25% ብቻ ነው የሚያመነጨው: ገልገል ግቤ አጥኚው ሳሊኒ ኮንትራክተር ሳሊኒ ተቆጣጣሪ ሳሊኒ ያለ ጨረታ በድርድር ያለዋስትና በሙስና ጓዶቻቸው በመስጠታቸው ስራው ተጨረሰ መለስ ሂደው መርቀዉት ሳምንት ሳይቆጥር ፈርሶ የተጠራቀመው ዉሃ ፈሶ እንደገና በቢልዮን የሚገመት ገንዘብ ወጪ ሆኖ በጠግን ጠግን እየሰራ ይገኛል: የጣና ኃይል ማመንጫም ብዙ ችግር እንዳለው ነው የሚታወቀው: ስለዚህ የመለስ በግብታውነት የተሰሩ የኢሊክትሪክ ማመንጫዎች ይቅርና ለጎረቤት ሃገሮች ሊሸጡ በሃገር ዉስጥም አስተማማኝ አይደሉም: በአሁኑ ጊዜ በመላው ሃገራችን ኃይል እየተቋረጠ ህዝቡ ችግር ላይ ይገኛል: የአባይ ግድብም ኮንትራት የያዘው ሳሊኒ ነው የተለያዩ የስራ ክፍሎች

እንደሳፕኮንትራክት የያዙት የመከላከያ እንጂነሪግና መስፍን ኢንጂነሪግ ናቸው: እግዚአቢሄር መውጫ ይፍጠርላቸው::

መለስ በሰው ልጆች ልዩነትን ያጠበቡ ፍቅርና መቀራረብ የፈጠሩ ሰው ሳይሆን የነበሩ በዜጎች መነጣጠል መራራቅ የዜጎች ምቾት ልዩነቱ የሰማይና የመሬት እንዲኖረው ያደረጉ መሪ እንደነበሩ ነው የሚታወቀው: በተጨማሪ ሃገራችን በጥቂት በሙሰኞች እጅ እንዳ ትወድቅ ያደረጉ ናቸው::

"በገፅ 51 አዲስ መስመር 3: ባለፉት ስርዓቶች በ400 ከተሞች የነበረ መብራት አሁን ግን 6ሺ ከተሞች የገጠር ማእከላት ተደርሳል: እነሆ በኢትዮጵያ ከሌላው ዓለም በተለየ እጅግ ምችው ከተማነት መስፋፋት ጀምረዋል::

አዲስ ረእቶች ለምንድን ነው ወደ ኋላ እየተመለሳቹሁ በ19ኛ ክፍለ ዘመን ከነበረው ታዋዳድሩን ያላቹሁ: ዛሬ እኮ 21ኛ ክፍለ ዘመን ነው: ለመሆኑ በ6ሺ ከተሞችና በገጠር ከተሞች ስንት ህዝብ ይሆናል ይህ ህዝብ እኮ 15% በታች ነው 85% ህዝብ በጨለማ ኖረዋል አሁም አለ::

ሌላ ኢትዮጵያ ሃገራችን ከሌላው ዓለም በተለይ እጅግ ምቹው ከተማነት ታይተዋል ትላላቹሁ: ለመሆኑ መስፈርታቹሁ ምንድን ነው: የሚኒስቴሮች የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ካድሬዎች ከነሱ ዝምድናና በሌላ ጥቅማ ጥቅም የተሳሰሩ ጥቂት ሃብታሞች: እነዚህን እያያቹሁ ያስቀመጣቹሁ መስፈርት ከሆነ ትክክል ናቹሁ እኔም እስማማበታለሁ: ግን እናንተ 80ሚልዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ከዓለም ካሉ ህዝቦች በተለይ ተመችቶታል ስትሉን ግን እዚህ ሰዎች ለመሆኑ የአውሮፓ የአመሪካ የከናዳ የአዉስትራልያ ዕድገት እንተወውና የደቡብ አፍሪካ የኢስራኤል የግብፅ ዕድገት አይታቹሁ ታውቃላቹሁ ትንሽ የኢትዮጵያ ህዝብ ይታዘበናል አትሉም ህዝብን በዉሸት ዕድገት አይገዛም ሃገራችን ከዓለም በተለይ ዕድገት ካስመዘገበች 60 (70%) የሃገራችን ህዝብ የሆነው ወጣት ለምን ወደ ባእድ ሃገር

ተሰደደ በዘመነ መለስ እኮ ሁሉም ዓይነት ሰብአዊ መብቶች የተነጠቁበት ድህነትና የጨለማ ንሮ ስር የሰደደበት ጉቦ ብልሹው አሰራር የተስፋፋበት የሕግ የበላይነት ጭራሹን የጠፋበት ግልፅነትና የጠያቂነት በሌለበት ህዝቦች አንድነታቸው ሆን ተብሎ እንዲቃቃሩ ግንኙነታቸው እንዲላላ የተደረገበት እያለ እንዴት ብሎ ነው ሃገራችን ከሌሎች የተለየችና የለማች የምትሉን ይህን አስፈሪ ነገር ቆም ብላችሁ ብትመለከቱት መልካም ነበር::

"ገፅ 49 አዲስ መስመር 2 መስመር 13: እናቶች የማገዶ እንጨት ለመልቀም የሸሽታቸውን ተፈጥሮ እየረገሙ በየ ዕለቱ ሃገር አቋርጠው ከሚሄዱበትና እንደገናም ዕድላቸዉም እየረገሙ በሸክም ብዛት ጎብጠው ከሚመለሱበት ረጂም ጉዞ አንዲገላገሉ በማድረግ,,,,"

በዘመነ ግዛት መለስ ሴቶች ማገዶ መፈለግ ያቋረጠ አልነበረም ያለ ማቋረጥ ብቻ ሳይሆን ሴቶች ምግብ አብስለው ልጆቻቸው ለመመገብ ስላልቻሉ ማገዶ እንጨት ኩበት ለመልቀም ሲሉ በየ ሜዳውና ጫካው ሲንገላቱ ይታዩ ነበር: ተራ መንገላታት ብቻ ሳይሆን ሕገውጥ ለሆኑ አመፅም ተጋልጠዋል: ይህ የሆነበት ምክኒያት ፍትሃዊ የሆነ የኢሊክትሪክ አከፋፈል ባለመኖሩ በሰዎች መካከል የነበረ ልዩነት አልጠበበም: በተለይ በአሁኑ ጊዜ ሴቶች ብሶታቸው እየከፋ ሂደዋል: መለስና ጓዶቻቸው ግን ሁሉ ጊዜ ስልጣንን ማእከል ያደረገ የሴቶችን ንቃተ ህልና በመጠቀም ሴቶች ምንም ተጠቃሚነ ት የሌላቸው በባዶ ሆዳቸው በመስበክ በተስፋ ምኞት በማንሳፈፍ እየሰበኩዋቸው መጥተዋል: ልብ በሉበአዲስ አበባ የሴቶችን ልዩነት እንመልከት የኢሊክትሪክ ምጣድ ሴቶችን ተራ ምድጃ የሚጠቀሙ ስንት ይሆናሉ የተጠቀሱትን ምግብ ማብሰያ እቃዎች የሌላቸው ሴቶች ስንት ናቸው: በኔ እምነት በአዲስ አበባ ኢሊክትሪክን ተጠቅሞ ምግብን የሚያበስል ህዝብ 20% አይሆንምነበር: አሁንም የተሻሻለ የለም ህዝቡም ያውቃል::

"ሕብረተሰብ ሁሉ ኢሊልትሪክ ተጠቃሚ ስለአደረግነው እፅዋትን መቁረጥ ከስሩ መንቀል ከማስቆረቱ አልፎ የዓለማችን የካርቦን ልቀት በመከልከልም ትልቅ ሚና ነበረው፡ ይላሉ አዲስ ራዕይ አዘጋጆችና አለቆቻቸው፡፡"

ሐቁን እንመልከት መለስ ወደ ስልጣን ከመጡበት 21 ዓመት ዉስጥ በመላው ሃገራችን የነበሩ የተለያዩ እፅዋቶች ሲወድሙ ወደ ምድረ በዳነት ሲቀየሩ ከማየት አልፎ ሲበዙ አልታዩም፡ እርግጥ የአፈርና ዉሃ ስራ መለስ መለስ የፈለሰፉት ሳይሆን በደርግ ጊዜ የተጀመረ ህ.ወ.ሓ.ትም ከትጥቅ ትግል ጀምሮ ሲሰራው የነበረ ነው፡ አዲስ የእፅዋት ችግኝ በማልማት የተራቆቱ ተራራዎች እየተከሉ መሸፈን በደርግም ይሰራ ነበር፡ የመለስ መንግስትም በተጠናከረ መንገድ ቀጥሎበታል፡ ሆኖም ግን በዘመነ መለስ የተተከሉ ደኖች እርግጥ በብዙ ሚልዮን የሚቆጠሩ ተተክለዋል በተለይ በደጋ ቦታዎች፡ በአብዛኛው አካባቢ ግን አልፀደቁም በተለይ ደግሞ በወይና ደጋና በቆላማ ቦታዎች 99% አልፀደቁም፡ መለስ በሬድዮና በተለቪዥን በዓለም መድረክ እየወጡ የሚኮፈሱበት ሐቅነት የለዉም፡ ይቅርና ደን በማፍላት የተራቆቱ ቦታዎች ሊሸፈኑስ ይቅር መለስ ወደ ስልጣን ከመምጣታቸው በፊት የነበሩ ጥቅጥቅ ያሉ ጫካዎች በዉስጣቸው የነበሩ ዝንደነ አንበሳ ነብር ዝሆን ጎሽ ዓጋዘን የሜዳ ፍየሎች ሜዳቋ ሰስ ቆቆች ጅግራዎች ከርከሮ ወ.ዘ.ተ ጠፍቶዋል፡ በተለይ በሰሜን ሃገራችን በፀለምትና ተከዜ ይዞ ወደ ሱዳን፡ በቆላ ወገራ አርማጭሆ መተማ ወልቃይት ፀገዴ በሽሬ አውራጃ በምስራቅ ትግራይ በሰቆጣ በተንቤን የነበሩ ጥቅጥቅ ያሉ ደኖች በአሁኑ ጊዜ መሬቱ ተራቁቶ ወደ ምድረ በዳ ተቀይሮ ከዛ ሁሉ ደን በአሁኑ ጊዜ ለሙዝዮም የሚሆን የሉም፡ በደቡብና ምዕራብ ሃገራችንም መለስ ወደ ስልጣን ከመጡ ጀምሮም ደኖቹ እጅጉን ቀንሰው አደገኛ ሁኔታ እየተፈጠረ ነው፡፡

አንድ አብነት ለመጥቀስ በዘመነ ጃንሆይና የደርግ ስርዓት የዉጭ ምንዛሬ ምንጭ የሆነው እጣን በሰቆጣ ፅለሬሬ ከላሊበላ ተነስቶ ተከዜን በመከተል ግራና ቀኝ ያለው በረሃ እስከ ሱዳን: ከፀሮና መረብ ተከትሎ እስከ ሱዳን: ተንቤን አክሱም ዓድዋ ሽሬ በፀለምት በወልቃይት ፀገዴ መተማ ጭልጋ ቆላማና ወይናደጋ ቦታዎች በጠባብ አንድ ሜትር ካሬ ቦታ ከ3 እስከ 4 የዕጣን ዛፎች አሉበት: ሌሎች እፅዋእት የነበሩበት በአሁኑ ጊዜ በወልቃይትና በአርማጭሆ በተወሰኑ ቦታዎች አሉ እንጂ በሌሎች አውራጃዎች የሉም: በሌላ በኩል በመላው ሃገራችን በይበልጥ ደግሞ በትግራይ ወሎ ሰሜን ሽዋ ዓፋር ህዝቡ ንሮዉን ለመግፋት ሲል ደኖችን ከስራቸው በመንቀል ክሰልና እንጨት ለመሸጥ አብዛኞቹ ቦታዎች ወደ ምድረ በዳ ተቀይረዋል::

የምሊኒም ብልጭ ወ.ዘ.ተ እያሉ በተለቪዥን የሚያሳዩን በዓድዋ በሽሬ በወልቃይት አልፎ አልፎ በወሎ ጎንደር ደጋማ ተራራዎች የሚያሳዩን የነበረ ነባር ደን ጥበቃ ተደርጎላቸው ተሚታዩ አሉ: ሌላ በዘመነ ደርግ የተተከሉ ባህር ዛፎች አሉ: በተረፈ ግን አዲስ ራዕዮች እየተኮፈሳቹሁ መለስ ለካርቦን ልቀት ለመከላከል የጣረ ምጡቅ መሪ የምትሉት ዉሸት ነው: እስቲ በትክክል ለመረዳት ከፈለጋቹሁ ቀደም ብየ ወደ ጠቀስኩዋቸው ሂዳቹሁ እዩት: 4ኪሎ ሁነህ ቡፌ ክትፎ እየተበላ ዊስኪ እየተጎነጨ ዉሸትን መፃፍ ፍትሃዊ አይደለም: ለወደፊት ታሪክ ይጠይቃቹሃል በዉስኪውና በሽታው ቀድማቹሁ ካልተቀጠፋቹሁ::

መለስ በትክክል የካርቦን ልቀት ለመቆጣጠር የዜጎች የሰዎች ልዩነት ለማጥበብና ምቾት እንዲኖራቸው ከተፈለገ የሴቶችን ምቾት ለመፍጠር ቢፈልጉ ንሮ 1ኛ የመብራትን ዋጋ ታሪፍን መቀነስ 2ኛ በገጠር ያለው ህዝብ ትክክለኛ የልማት ፖሊሲ በመቀየስ ጡንቻው አሳርፎ አምርቶ በልቶ ጠግቦ የሚኖርበት ቢፈጥሩ ንሮ 3ኛ የከተማ ነዋሪ ህዝብ ወጣት ሙሁሩ ተማሪ ሴት ወንድ የእሳት አደጋ ፖሊሲ

እያወጁ ሳይሆን የሃገራችን ገንዘብ በትክክል ከሚፈለግ የልማት ቦታ በማፍሰስ ሥራ በመፍጠር ድህነት በማዳከም ብቁ ዜጋ ይፈጥሩ ነበር: መለስ ግን ድህነት ለማጥፋት የወሰዱት እስትራተጂ ስልት ወጣት ዜጎች ያታን በማይለይ ወደ ስደት ሄዶ የስቃይ እንጀራ እንዲበላ የባርያ አገዛዝ ስርዓት በላያቸው እንዲፈፀም ያደረጉ መሪ ነበሩ: ታድያ ባለ ራዕይ ለሰው ልጆች ምቾት የታገለ ምጡቅ መሪ ያስብላል በበኩሌ አልቀበልም: መለስና ጓዶቻቸው ባለፈው 21 ዓመት የሰሩት ሥራ በሙሉ የሕግ በላይነት ንሮ ፈራጅ ዳኛ ቢኖር ይቅርና ከመሬት በላይ ያሉ ግብአተ መሬት የገቡት ባለስልጣናት የነበሩትም ከባድ ቅጣት ይገባቸው ነበር::

በማጠቃለል መለስ በስልጣን በነበሩበት ሃገራችን ከጨለማ ወደ ብርሃን የወጣች ሳይሆን የነበረች መለስና ጓዶቻቸው በአስር የሚቆጠሩ ብዙሃን መገናኛ በእጃቸው ስለነበሩ ስልጣናቸው ለማራዘም በመሬት አንድነት ለሃገር ዉስጥ ህዝቦችና ለዉጭ ዓለምን በማደናገር እነሆ አሁንም እያደናገሩት ይገኛሉ: በመጨረሻ ግን ያ ሁሉ አደናጋሪ ዲስኩራቹሁ ዉሃ ቢወቅጡት እንቡጭ ሊሆን እንደሚችል እርግጠኛ ነኝ::

ይላሉ አዲስ ራዕይ አዘጋጆችና አለቆቻቸው ቀጥሉ ደግሞ በነጠላ እየለያቹሁ ጨመቅ አድርጌ ያስቀመጥኩዋቸውን በዝርዝር አስቀምጫለሁ::

"መለስ ለአካባቢ ችግሮችን የአካባቢ ምላሽ የሰጠ መሪ ነበር:"

አዲስ ራዕይ የአካባቢ ችግሮች ስትሉ የትኞቹ ናቸው: የመለስና ጓዶቻቸው ጉዞ ከትጥቅ ትግል ጀምረው በኢትዮጵያ ከነበሩት ፀረ ደርግ ኃይሎች በነፍጥ እየተጫረሱ እንደመጡ ባለፉት ገፆች በሰፊው ተገልፀዋል: መልሰና ጓዶቻቸው ከደርግ ዉድቀት በኋላም የመለስን ዓፈና አንቀበልም ብለው የሚቃወሙ ፓርቲዎች የትግል ፕሮግራም ነድፈው በምርጫ በመወዳደር በሰላማዊ መንገድ እንታገል ላሉት በብዙሃን መገናኛ እንዳይጠቀሙ በመከልከል

የሚንቀሳቀሱበት ሜዳ በማሳጣት የተለያዩ ሕጎች በማውጣት የመለስ ፓርላማ እጅህን አውጣ ብለው አዋጆችን ሕጎችን በማፅደቅ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ጠንክረው ለመለስ መንግስት ማዛባት ከሞከሩ የለለ ስም በመለጠፍ በመወንጀል እሱር ቤት ማጎር ነበር::

ሜዳው ጠባብ ነው በዘመነ መለስ ሰላማዊ ትግል አያዋጣም ብለው ነፍጥ አንስተው ለሚታገሉ ትናንት ለመንግስቱ ኃይለማርያ ም ይወቅሱ የነበሩ መለስ ስልጣን ከያዙበት እስክ ህልፈተ ሂወታቸው እቺ ሃገር ዉጊያ ሞት መታሰር መቀጣት አልተለያትም:

መለስ ለአካባቢ ሰላማዊ ምላሽ ሲያስቡ በሃገራቸው ሰላም አብሮ ተቻችሎ መኖር ለምን አልመረጡም::

"መለስ በሂወት ዘመናቸው በነበሩበት ጊዜ ትልቅ ንድፈ ሃሳባዊ ጥያቄቆችን የራሱን ምላሽ ለመስጠት የቻለ ምጡቅ ስብእና የነበረው መሪ::"

መለስ እንደማውቃቸው ከትጥቅ ትግል ጀምሮ ለዚች ሃገር አዲስ ንድፈ ሃሳብ አመንጭተው ሲሰሩ አላየሁም: በፖለቲካ ስነ ሃሳብ (በአይዶሎጂ) ህ.ወ.ሓ.ት ይዞት ከነበረ የተለየ አልነበረም: በዚህ ፅሑፍ መጀመርያ አካባቢ እንደመንደርደርያ ሃሳብ አድርጌ አስቀምጨው ነበርኩ እዛው መመልከት ይቻላል: በትጥቅ ትግል ጊዜ መለስ ጨካኝ ኮመኒስት ነበር: እንዲያዉም የጠባብ አልባንያ አክራሪ ነበር የምስራቅ ኮመኒስት ሲፈራርስ ደግሞ ምራባውያን አጭበርብሮትርፍ ለማግኘት ነፃ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ነው የምንከተለው አለ: በዉስጡ ግን ካፒታሊዝም እስኪዳከም ኮመኒስት እስከ ሚያገግም ለነዛ ጨካኝ ካድሬዎች በህቡእ በመቃኘት አድፍጦ ቆይቶ አንባገነኑ ኮመኒስት አቢዮታዊ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ እንዲጨፍር ያደረገ መሪ ነበሩ: ለጋሲውም አሸባሮቹ የነበሩ እየሰሩበት ይገኛሉ: እኔ የሚገረመይ ስብእና የነበረ ምጡቅ መሪ ነበር ሲትሉን መለስ በዚህቹ ሃገር መሪ ከሆነበት ጀምሮ በዚች ሃገር ስንት ተንኮል ተሰረተዋል በጅምላ ታስረዋል በምርጫ 1997 ጊዜ

በጅምላ ተረሽነዋል በኦጋዴን በሱማል በዓፋር በጋንቤላ በኦሮሞ በደቡብ ህዝቦች በትግራይ የተለያዩ ምክኒያቶች በመፍጠር ብዙ ሰዎች ተገድለዋል ንብረታቸው ወደመዋል በገንዘብ ተቀጥተዋል እቺ ሃገር የግለሰቦች መፈንጫ ሁናለች: የመጠቁና ስብእና የተላበሱ ከተባሉ በየትኛው መስፈርት ነው: ከመንግስቱ በምን እንለያቸው::

"መለስ የክራይ ሰብሳቢነት ምንጮች ባህሪያትና ምንጮት ላይ የቀረበ ትንታኔ ታክቲክና እስትራተጂ ቀመሮች የቀመረ መለስ ነበር: በዚህ ረገድ በሃገር ቤት የልማትና የዴሞክራሲ የሰላምና የዕድገት ጥያቄዎች የተመሰረቱ የመለስ በርካታ አስተዋፅኦዎች ተጠቃሽ ናቸው::"

መለስ የክራይ ሰብሳቢነት ምንጮች አውቀው ለመፍትሄው ተቆርቋሪ አልነበሩም ምክኒያቱም መለስ ለስልጣናቸው የማያሰጋ ኪራይ ሰብሳቢ ጨክነው የሚመቱ አይደሉም አልነበሩም: በዘመነ መለስ ኪራይ ሰብሳቢዎች የራሱ ታማኝ ሌሎዎች ነበሩ: በመላው ሃገራችን ከተሞች ምርጥ ቤት መሬት ይዘው ትላልቅ ህንፃዎች ሰርተው ከመቶሺ እስከ ሚልዮኖች ኪራይ የሚያስገቡ: ምንም ሃብት ያልነበራቸው በመቶ የሚቆጠሩ የጭነት ማኪናዎች የገዙ ብዙ ናቸው: የባንክ የእንሹራንስ የትራንስፖርት አክስዮን የያዙት ራሳቸው ካድሬዎች ነበሩ አሉም: አብዛኛቸው የግል ባለሃብቶች ከመለስ አሽከሮች በመመሻጠር ሃብት ያካበቱ ናቸው: በአዲስ አበባ ናዝሬት ባህርዳር መቀሌ አዋሳ ምርጥ ምርጥ የልማት መሬት የወረሩት ቢሄር በማይለይ የመለስ መዋቅር ናቸው: ኪራይ ሰብሳቢነ ትን የሚፃረር (ወደ አለቆቹ) አሸቅቦ ለሃገር ተቆርቁሮ ሂህስ የሚያደርግ በመለስ መንደር ተቀባይነት አልነበረዉም: መለስ በመድረክ ወጥቶ ስለኪራይ ሰብሳቢነት ሲናገር ግን ኪራይ ሰብሳቢነ ትን ጥዋት ጠራርጎ የሚጥላቸው ነው የሚመስል: በተግባር ግን አልሰራዉም: እንዲያዉም ኪራይ ሰብሳቢዎች የመለስ አማካሪዎች ነበሩ::

መለስ የታክቲክና እስትራተጂ የቀመረ መለስ ነበር ትላለቹሁ መለስና ጓዶቹ ሃገራችን የባህር በር ያሳጡ ኢርትራን ሕገወጥ በሆነ ለኢትዮጵያ ህዝብ በማፌን አጭበርባሪ ሪፌረንዶም አካሂዶ ለኢትዮጵያ ህዝብ ዳግም ለጦርነት የዳረገ በግል ከኢሳያስ በነበራቸ ው ግንኙነት የሃገር ሉእላዊነት ከመድፈር አልፎ በአስር ሺ የሚቆጠ ር ኢትዮጵያዊ ሂወት የቀጠፈ ጦርነት፡ በተጨማሪ አካላቸው የጎደለ በቢልዮን የሚቆጠር የሃገር ሃብት ያባከነና ያወደመ፡ በሃገራችን ሰላምና ልማት ኑሮ በሰላም እንዳይኖር ሁሉም ዓይነት ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች የዘጉ መሪ ናቸው ስለዚህ የመለስ ታክቲክና እስትራተጂ መሬት አያስፈልግም ብሎ ሃገር የሸጠ ነበር፡፡

በሃገር ቤት የሰላምና የዴሞክራሲ የዕድገት ጥያቄዎች መልስ ያገኙ የመለስ አስተዋፅኦ ነበራቸው ከተባለ በሃገር ቤት ዴሞክራሲ ዕድገት የለም መለስ ልማት አሳደግን ዕድገታችን 11% ደርሰዋል በእርሻ 25% አድገናል ወ.ዘ.ተ ብሎ የተናገረው ሐቅ ቢሆን ኑሮ ከ80 ሚልዮን የኢትዮጵያ ህዝብ 3ጊዜ በልቶ ጠግቦ ለብዙ ዐመታት የሚቀልበው ተቀማጭ ሃብት በኖሮው ነበር፡ ሰላም ዴሞክራሲ ዕድገት ቢኖር ኑሮ በሚልዮን የሚቆጠር ወጣት ሙሁር በስደት አይኖርም ነበር፡ ታድያ የመለስ ታክቲክና እስትራተጂ ቀመር ምጡቅነቱ የት ነው፡ በበኩሌ መለስ ብቻው ለብቻው በግብታዊነት የሚሮጥ የነበረ፡ ብቁ ሰዎች ወደ ከፍተኛ አመራር ሊመጡ የማይፈለግ ስልጣንን በመኖፖሊ ይዞ የነበረ ሰው ነበር፡ የመለስ ታክቲክና እስትራተጂ መለስ ለራሱ ጥቅም ድዛይን ያደረገ እንቅስቃሴ ነበር፡፡

"መለስ የአካባቢ አስተዋፅኦ ማስረጃዎች ከሱማል እስከ ላይበርያ ከሱዳን እስከ ቡሩንዲ በርዋንዳ በአብየይ ለአፍሪካ ከመልካም አስተዳደር እስከ ንግድ ለአፍሪካዊ የሚል፡፡"

መለስ ሰራዊት ወደ ሩዋንዳና ላይበርያ ሲልኩ ለሁለት ዓላማዎች ነበር፡ 1ኛ ለአመሪካ ለማስደሰት 2ኛ በዘመተው የሰው ኃይልና

ቁሳቁስ ዋጋ የዉጭ ምንዛሬ ዶላር ለማግኘትና ትርፍ ለማግኘት ነበር: በሱማልም 3ዓላማዎች ነበሩት 1ኛ የምዕራባውያን ተልእኮ ለመፈፀም 2ኛ አልሸባብ ወደ ሃገር ገብቶ አደጋ እንዳይጥል 3ኛ ለትርፍ ነው: የሩዋንዳ የነበረው የዘረኝነት ሁኔታ ዘግናኝ ቢሆንም እዛው የተደረገው ዘመቻም ትርፍ ለማግኘት ያለመ ነበር: በጣም የሚገርመው ደግሞ ለትርፍ ማግኘት መሆኑ የሚያረጋግጡ ወደ ሰላም ማስከበሩ የዘመቱ የኢትዮጵያ ሰራዊት ሊከፈላቸው የሚገባ ዶላር ተቀምተዋል: ከዚሁ ለማስረጃ ያህል በአፍሪካ ሰላም ማስከበር የዘመቱ የኢትዮጵያ ፖታልዮን የሚገባቸው ዶላር ይሰጠኝ ብላ አድማ አንስታ ስታበቃ በመለስ በድርድር አታልላቹሁ ያዙዋቸው ተብሎ በተሰጠው ትእዛዝ ፓታልዮና ሐቅ መሰላት ከተደራደረች በኋላ ትጥቅን አራግፈው ወደ ትግራይ ዉቅሮ ክልተ አውላዕሎ ከወሰዱዋት በኋላ የት ደረሰች የሚለው መልሱ ጠፍተዋል: ከዛ በፊት የዘመቱ ወታደሮችም የላባቸውና የሂወታቸው ዋጋ አልተሰጣቸዉም: የተሰጣቸው ቢኖር ከ8ሺ እስከ 10ሺ ብቻ ነበር: የህንድና የሌሎች ሃገሮች ወታደሮች ግን በዶላር ሲታሰብ በአስር በመቶሺ ዶላር የሚገመት ገንዘብ ወስደዋል: ስለዚህ መለስ ወደ አፍሪካ ሰላም ለማስከበር ያሰማሩት ሰራዊት ትርፍ ገቢ ለማግኘት ተብሎ የተሰራ ነበር: አንድ ሰላም አስከባሪ ለቸህጉሮች መላክ በጃንሆይ ወደ ኮንጎ ኮርያም ተልከዋል ይህ የመለስ ፍልስፍና አይደለም::

መለስ የአካባቢ ሰላም እንዲኖር ከፈለጉ ዉጭ ዉጭ እያሉ ከሚንሳፈፉ በሃገራቸው ዉስጥ ያለው የቢሄር የዘር የጎጥ ግርጭትና መበላላት ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የነበራቸው የተበላሸ ግንኙነት ለምን በሰላም ተግባብተው አይኖሩም: ለምን ይመስላቹሃል መልሱ ለስልጣናቸው አስጊ ስለሆኑ ነው: ምክኒያተም በኢትዮጵያ ሰፌ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ካለ የመለስ ስልጣን አይኖርምና::

ሌላ መለስ ለአፍሪካ መልካም አስተዳደርና ነፃ ንግድ ተፋልመዋል ተብሎዋል: ለመሆኑ ለ80 ሚልዮን ህዝባቸው መልካም አስተዳደርና ፍትህ የነሱ ያለመው ያላረጋገጡ እንዴት ብለው ጠረፍ ተሻግረው መልካም አሰተዳደር ፍትህ ያነግሳሉ: ይህ ጉዳይ የመለስን ባዶ ጉራ ልታይ ልታይ ባህረያቸው የሚያረጋግጥ ነበር: ስለሆነ የመለስ የአፍሪካ መሪ መስለው መታየት በራሳቸው ያልሰሩት ስራ ለአፍሪካ አህጉር ሰራሁ ቢሉን ዉሸት ነው: ጃንሆይ እኮ ለአፍሪካውያን ነፃነት አልፈው ለኮርያ ነፃነት ተዋግተዋል ዱባይ ክፉ ዘመን አጋጥሙዋቸው ስንዴ እርዳታ ሰጥተዋል: ለኮንጎ ነፃነት ሰራዊት ልከዋል መንግስቱም እንደተጠቀሰው ለአፍሪካ ሰርተዋል መለስ በነዚህ የተለየ ምን ሰራ::

"የኢትዮጵያ ብዙሃንነትን መገለጫ የሆነው ሕብረቢሄራዊነትን ለዘመናት በአግባቡ ባለመያዙ ምክኒያት ለእርስ በእርስ ግጭትና ደም መፋሰስ እንዳይኖር ያደረገ መንገሰ::"

መለስ መጀመርያ የኢትዮጵያ ብዙሃንነትን ያከበረ አልነበረም: መለስ ብዙሃንነት ያካተተ ስርዓት መሰረትኩ ሲለን እነዛ ራሱ እንደጭቃ ጠፍጥፎ የሰራቸው የቢሄሮች ፓርቲ መሪዎች የህዝብ መሰረት የሌላቸው ሰብስቦ ፓርቲ ናቹሁ ብሎ በቂ ገንዘብ መድቦ የሰራቸው ቡድኖች በፓርላማ ሰብስቦ ነው ሲያደናግር የነበረው: አሁንም የሱ ተከትለው አካሄዱ ቀጥለውበታል ይህን ለማፍረስ ኦሆዴድን አፍራሽ ቡድን በመስራት በሰራዊት አጅቦው ለኦነግ ድምጥማጡቸው አጠፋው: ለደቡብ ሕብረት ለማፍረስ ለነአባተ ኪሾ በመስራት በገንዘብም በወታደር አጂቦ በታተነው: በዓፋር በሱማል ለነበሩም እንደልማዱ የራሴ ኃይል በመፍጠር ፓርላማ የሚያማሙቀው ኃይልሎች ፈጠረ: ራሱ የሰራው በአዴንም ኢ.ህ.አ.ፓ ን ድምጥማጡን በማጥፋት የባአዴን ቂጥ እንደዱሮው እንዲጠብቅ አደረገ: ለቅንጅትም በዉስጣቸው በመግባት በታተናቸው: እነአየለ ጫሚሶ ሬድዋን የያዙዋቸው አባላት በሴራ በገንዘብ

ይዞዋቸዋል: በመጨረሻም ለዓረና ትግራይ ለመከፋፈል ብዙ ገንዘብ በማፍሰስ ብዙ ሞክሮዋል ህ.ወ.ሓ.ት በገንዘብ ሃይል ዓረና ከማፍረስ ሌላ ዓረና ፈጥሮ ነበር ግን ዓረና አልፈረሰም: መለስ ከህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች ጓደቹ ሆኖ በ38 ዓመት ዉስጥ በ10 የሚቆጠሩ ፓርቲዎች ዉጠዋል በታትነዋል ታድያ መለስ ለብዙሃንነትና ለሕብረ ቢሄራዊነት የቆመ ጠበቃ ነበር ይባላል: ሊሆን የማይችል ሐቅ ነው: መለስ ከህ.ወ.ሓ.ት ነፃ ሪፓፐሊክ ትግራይ ለማነፅ ነው የሚለው ማኒፈስቶ ከአረቀቁበት 1968 ዓ.ም ጀምረው እስከ ህልፈተ ሂወታቸው የነራቸው አቋም በጠባብነት የተባላሹ ነበሩ: ስለሆነ በዘመነ መለስ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙሃንነትን የሚያንፀባርቅ ስርዓት አልነበረም::

መለስ የብዙሃንነት እዉነታ ተቀብሎ በህዝቦችን መካከል እኩልነትን በማስፈን ሊፈታ እንደሆነ በተግባር አረጋግጠዋል: የህዝቦችን ማንነት በመቀበልና የእኩልነት መብታቸውን ላይ ተመስርተው የአቢዮታዊ ዴሞክራሲ ስርዓት በጠንካራ መሰረት መገንባት እንደሚቻል ያረጋገጠ ምጡቅ መሪያችን ይሉናል አዲስ ራዕዮች::

መለስ የብዙሃንነትን እዉነታ የሚቀበል አልነበረም: ይህ ሁኔታ ደጋግሜ እንደፃፍኩት ይቅርና በአፍሪካ ብሎም በሃገር ደረጃ የብዙሃንነትን እውነታ ሊቀበል ህ.ወ.ሓ.ት ዉስጥ ከ1967 ዓ.ም እስከ የመለስ ህልፈተ ሂወት ይነሱ የነበሩ የብዙሃንነትን እውነታ መልስ ይሰጠን የሚሉ ታጋዮች አባላት እንኳ ይሰጣቸው የነበረ መልስ ማሰር ማፈን መግረፍ ነው: ለዚሁ ማስረጃ ብዙ ካድሬዎች አባሎች በእሱር ቤት ማቅቀዋል በስደት ተበታትነዋል ቁጥራቸው እጅግ ብዙ ዜጎች ደብዛቸው ጠፍተዋል: እንዲሁም ኋላ ቀር የሆነ ከፋፍለህ ግዛ የሚል ተንኮላቸው በመተግበር ብዙ አፈናዎች የተፈፀሙባቸው ዜጎች በወረዳ በዞን በክልል እንዲከፋፈል ያደረጉ: ዜጎች ለሸቅል እንኳ ከክልል ወደ ክልል ተሰደው እንዳይሰሩ ያበቃን የተበላሸ

ፌደራሊዝማቸው ያገደው: ስለዚህ መለስ ብዙሃንነትን በሚመለከት በዉስጣቸው ያላከበሩ እንዴት ብለው የ80 ሚልዮን ህዝብ ከ80 በላይ ቢሄር ቢሄረሰቦች ብዙሃንነት አክብረው ይባላሉ በበኩሌ መለስ ፀረ ብዙሃንነትን እንጂ ብዙሃንነትን አክባሪ አልነበሩም::

መለስ እኩልነት ያሰፈኑ ሰው አልነበሩም ቢሆን ንሮ በ20 ዓመት ዉስጥ የነበረ ቀውስና አሁን በየአካባቢው ይነሱ ያሉ የመብት ጥያቄዎች እኩልነትን አለመኖሩ ነው የሚያረጋግጠው: እሁልነት ባለመኖሩ በሰላም የሚታገሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሃገራችን ያለ የምርጫ ሕግ ይስተካከል ለሚል በመቃብር ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ካልሆነ አይስተካከልም ብሎ በሚልዮን የሚቆጠር ህዝብ ደጋፊ ያላቸው ፓርቲዎች ታፍነው ንሮዋል: ነፍጥ አንስተው የሚዋጉ አሉ በመለስ የእኩልነት መብታቸ ው ስለአጡ ነው::

መለስ እኮ ከድርጅታቸው ዉስጥ ከመለስ ሃሳብ የመጠቀ ሃሳብ ካፈለቀ በመለስ ቀናተኛነት ምክኒያት ራሱን አጎንብሶ እንዲኖር ተገድደዋል: በራሳቸው ስራ የለቀቁ ሚኒስቴሮች ባለስልጣኖች አሉ: ቤት ዘግተው ታንቀው የሞቱ አሉ: ወደ ዉጭ የተሰደዱ አሉ: ስለዚህ መለስ ለህዝቦች እኩልነት የቆሙ አልነበሩም: እቺ ሃገር እኮ እሳት ለኩሰውባታል ናቸው ያለፉት::

መለስ ህዝባችን እኩልነታቸው መብት ተመስርተው የአቢዮታዊ ዴሞክራሲ ስርዓት በጠንካራ መሰረት መገንባት እንደሚቻል አረጋግጠዋል የሚለው ሃሳብ ለመሆኑ አቢዮታዊ ዴሞክራሲ ማን ነው የመንግስቱ ኃይለማርያም ስነ ሃሳብ (አይዶሎጂ) ነበር እኮ ይህ ስርዓት ደግሞ ፍፁም አንባገነን ፋሺስት ነበር: ይህ ደግሞ መለስና ጓዶቻቸው ያውቁታል: ስለዚህ መለስና መንግስቱ የሚለያቸው መንግስቱ ደንቆሮ የሰው ሂወት ገድሎ በመንገድ ዘርግቶ የሚጨፍር የህዝብ ንብረት ቤት የወረሰ በጅምላ የሚያስር የሚገርፍ ነበር: በዘመነ መለስም ሰው በድብቅና በግልፅ በጅምላ ተገድለዋል: የህዝብ መሬት ተቀምተው ተሸጠዋል: የገጠርም የከተማም መሬት የኔ ነው

ብሎ በመሸጥ 80 ሚልዮን ህዝብ ያለ መሬት ባለቤትነት አስቀረቶዋል: ታድያ አቢዮታዊ ዴሞክራሲ ወራሪ ፋሽስት አልነበረም አሁንስ አለ አይደል: ደርግ የባለስልጣን ልጆችና ዘመድ አዝማድ ዉጭ ሃገር ያስተምር ነበር ሃብታም ዘርፈዋል ይባላል: የመለስና ጓዶቹ ግን በግልፅ ሁሉም የሃገራችን ሃብት ጨምድደው በመያዝ ለተበላሸ ዓላማቸው ለማስፈፀም እያዋለት አይደለም: አሁን ጭራሹን የሃገራችን እንድስትሪዎች በወታደራዊ እጅ እንደገቡ አድርጎ ነው ያለፈው: ለቅን ባለሃትም በግብር አሰባስቦ አንዳያድግ እየደቆሰው ነበር አሁንም እየደቆሱት ነው::

"መለስ ቋንቋ መሰረት ያደረገ ፈደራሊዝም ከሌላው ዓለም በተለየ በኢትዮጵያ ብቻ ተግባራዊ እንዲሆን ያደረገ መሪ::"

መለስ ቋንቋ መሰረት ያደረገ ፈደራሊዝም ማዋቀሩ የሃገራችን ህዝቦች በንጉስና መንግስቱ ስርዓቶች እንኳ ማንም ኢትዮጵያዊ በመንም ክፍለ ሃገር ወረዳ ዞን ወ.ዘ.ተ ሄዶ እንደየትውልድ ቦታው ቆጥሮ ሙሉ መብት አግኝቶ ይሰራና ይኖር ነበር: የመለስ ፈደራሊዝም የፈጠው ችግር ግን ትግራይ አማራ ኦሮሞ ሄዶ አማራ ኦሮሞ ወይም ሱማል ኦሮሞ ደቡብ ጋንቤላ ሄዶ: ዜጋ ነኝ ሃገሬ ነው ብሎ የማይሰራ በት የማይኖርበት ሁኔታ የፈጠረው: ሌላ ቀርቶ ኩታ ገጠም በቅርብ የሚገናኙና በጋብቻ ይተሳሰሩ የነበሩ ህዝቦች አሁን ሁሉም የአስተዳደር ክልል በቋንቋ ስለተከለለ ጋብቻ የገበያ ልውውጥም እየቀረ ሂደዋል: ስለዚህ መለስ ለዚች ሃገር የሚበታትን መርዝ ነው ነዝቶበት ያለፈው::

መለስ በኒዩ ሊበራሊዝምና በአይ ኤም ኤፍ ለደረሰበት ተፅእኖ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካውያን ጭምር ጠበቃ ሆኖ የተማጎተና ያልተንበረከከ ምጡቅ መሪ ነበር ይላሉ::

መለስ በመሰረቱ አንድ አቋም እንዳልነበራቸውና ደንጋጣ መኖሩ አይተን ነበር: አሁንም ከጅሚ ካርተርና የአመሪካና እንግሊዝ ባለስልጣኖች በ1982 ዓ.ም ከተገናኘ በኋላ የኮሚኒስት መንገድ

አያዋጣቹሁም ካሉት በኋላ ለነሱ ለማታለል በ1983 ዓ.ም ታህሳስ ወር ለነሱ ለማጭበርበርና ለማስመሰል ካፒታሊዝምን ስርዓት ነው የምንከተል ብለን ነው ለኢምፐርያሊስቶች የምናታልላቸው ብሎ ነው የተነሳ: እነ አመሪካ የመለስን ሳይኮሎጂ ተደብቆዋቸው ማለቱ ነው: ስለዚህ መለስ ይቅርና ለአፍሪካ መንግስታት ሊጣበቅና ሊከራከር ሃገራችን እንኳ ከሁሉም ነጣጥሎዋት ነው የቀረ: አሁንስ ኢትዮጵያ ሃገራችን ከአይ ኤም ኤፍና ዎርልድ ባንክ ብድርና እርዳታ መቸ ተላቀቀች: መለስ ከ21 ዓመት ሙሉ በተግባር የሌለ በአፍ ነው ሲደልለን የኖረው: ስለሆነ መለስ ለአፍሪካዉያን ያስመዘገበው ድል አልነበረም::

"የመለስ ምጡቅ አመራር በኒዩ ሊበራሊዝምን ባደረሰበት ተፅእኖ ሳይንበርከክ ለኢትዮጵያ ችግሮች ኢትዮጵያዊ መፍትሄ በማቅረብ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ሲቀጥል ከኛ በፊትና ከኛ እኩል የተመሰረረቱ አዳዲስ መንግስታት ለብዙ ቀውስ ሊጋለጡ ተገደዋል ይላሉ አዲስ ራዕይ::"

መለስ ለመሆኑ ካፒታሊስት ሃገሮች መቸ ነው ነፃ የወጡ ብዙ ቢልዮን ዶላር የተጫነው ብድር አሁንም ለኢትዮጵያ ትቶላት ሄዶ ያለ አራጣ መለስ አይደለም: መለስ ጢት ጢት እንግሊዝ አመሪካ ጀርመን ወ.ዘ.ተ እየማለ ብድር የሚጎትት የነበረ መለስ አይደለ: መለስ ተንበረካኪ አልነበረም ስትሉ ይህ መንበረከክ አይደለም: ዋናው ነገር መለስ ከቻይናም ከምዕራብም ድስት እያጣቀሱ መብላት ልምድ ስለአላቸው አዲስ ራዕዮችም ይህን ደግማቹ ልታጭበረብሩን ፍትሃዊ አይደለም: መለስ ግን ድሮውንም ኮመኒስት አልነበሩም ታሪካቸው ደግሞ ይነግረናል ተጋላበጭ እንደነበሩ::

ለመሆኑ ከመለስ ቀድመውና አብረው የተመሰረቱ መንግስታት የቶኞቹ ነበሩ አብሮ ከመለስ ጋር መንግስት የጀመረ ኢሳያስ ነበረ: ከሱ ጋር ካወዳደራቹሁ ከሆነ እጅጉን ወርዳቹዋል: ኢሳያስ ቢሆን

ዘመናዊ ባንዳ ነው መለስም የኢትዮጵያ ህዝብ ጠፍሮ ይዞታል አንድ በአስተሳሰብ በተግባርም ከኢሳያስ አይበልጥም አንድ ናቸው::

## ክፍል 19

## መለስ ምርጥ እስትራተጂስትና የታክቲክ ቀማሪ

"አዲስ ራዕይ 8ኛ ዓመት ቅፅ 4 ልዩ እትም ከገፅ 57 እስከ 62: የአንድ ታላቅ ሰው ምጡቅነት በተለይ ደግሞ የአንድ ታላቅ የፖለቲካ መሪ ምጡቅነት ከሚለካባቸው መስፈርቶች አንዱ የታክቲክና የእስትራተጂ ቀመራ ብቃቱና በዚህም እየተመራና እየመራ ትግሉን ለላቀ ዉጤት ማብቃቱ ነው: ታክቲክና እስትራተጂ ወዳጆቹሁና ጠላታቹሁ (ተፈላሚዎችን) አሰላለፍ የሚጠቁም ነው: መለስ ከእነዚህ ሁለት የአመራር ብቃቶች አኳያ ወደር የማይገኝለት መሪ ነበር::"

መለስ ከጅምሩ ጀምሮ የራሱ ስልጣን እንዴት ትራዘማለች በማለት ለራሱ ታክቲክና እስትራተጂ የአጭርና የረጂም ጊዜ ብሎ መካቢላዊ በሆነ መንገድ ለጊዜዉም ቢሆን እንዴት ዉጤት አገኛለሁ ብሎ በማሰብ ካልሆነ እስከ አሁን በጥናት የተመሰረተ ሙሁራንና ብቁ ባለሙያዎች በመሳተፍ በአንፃር የሃገር ጥቅም አይቶ የሚሰራ አይደለም አልነበረም: ለዚሁ ማስረጃ የሚሆን መለስና ጓዶቹ ታክቲክና እስትራተጂ ሲነድፉ ማን ነው ጠላት ማን ነው ወዳጅ ብለው የኃይል አሰላለፍን አቅጣጫ አስቀምጠው በሃገር ጥቅም አንፃር ሳይሆን ይህ ፓርቲ (ግለሰብ) ለስልጣናቸውን በምን ይጠቅመኛል በሚል ብቻ ነበር የሚያዩት: ስለሃገር ጉዳይ ስለህዝብ ዕድገት የሚባል አስተሳሰብ አልነበራቸዉም: ትንሽ ቢያስቡም ከስልጣናቸው ዕድሜ የሚያያዝ ከሆነ ብቻ::

ለማስረጃ ያህል ህ.ወ.ሓ.ት ደደቢት ወረዶ ያስቀመጠው ታክቲክና እስትራተጂ: ኢርትራን እንደ ሃገር ሲቀበል ስለኢትዮጵያ አንድነት

ና እኩልነት ስለየሃገር ሉእላዊነት ስለፀጥታ ዋና ደህንነት ስለኢኮኖ ሚ እድገትና የፖለቲካ ጂኦግራፊያዊ ጥቅሞች እንደኢትዮጵዊ ማሰብ ፈንታ ምንም ጥናት ሳያደርግ ታሪካዊ መነሻ የሌለው ኢ.ርትራ ነፃ ሃገር ናት ኢ.ርትራ ከኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነፃ ለመውጣት የምታደርገው ትግል እንደግፋለን አለ: ኢ.ርትራ ሲልም ምንም የአቋምና የታክቲክና እስትራተጂ ልዩነት የሌላቸው ጀብሃን እንደጠላት በመቁጠር ከሻዕቢያ መሪዎች ከነበረው የማይታወቅ ርካሽ ግንኙነት ትዉዉቅ ከኢ.ርትራ ፓርቲዎች ያለን ግንኙነት ከጀብሃ ታክቲክ ለስልታዊ ጥቅማችን ስንል ከሻዕቢያ ግን በእስትራተጂ ነው የምንግናኘው ብሎ አወጀ: በዛን ወቅት ጀብሃ ይሻል ነበር::

ቆየት ብሎ በወቅቱ ምንም ታሪካዊ መነሻ የሌላው የሻዕቢያ ለጋሲ በመከተል እኛ ኢትዮጵያውያን አይደለንም እኛ የምንታገለ ው ከአማራ ቅኝ ገዢዎች ነፃ ለመውጣት ነው: ኢትዮጵያ የምትባል ሃገር የ3ሺ ዓመት ታሪክ ያላት ሳትሆን የአንድ መቶ ዓመት ታሪክ ያላት ሃገር ናት: ስለሆነ የአማራ ቅኝ ገዢዎች እንደነምኒሊክ ያሉ ትግራይን በግፍ ለመቶ ዓመት የገዙዋት ብለው በማኒፌስቶ ደረጃ አወጁ: በወቅቱ መለስ የማኒፌስቶው አርቃቂ እንደነበሩ በተደጋጋሚ ተገልፀዋል: ይህ የሚያሳየው መለስና ጓዶቹ አርቀው የሚያስቡ ሳይሆኑ የኖሩ ለዚህች ሃገር አጥፊ እስትራተጂ አንድም ከጥናት የተመረኮዘ ታክቲክና እስትራተጂ አልነበራቸዉም::

መለስና ጓዶቹ ይህ ወንጀል አለበቃቸዉም ብሎ በዛን ጊዜ በ1968 ዓ.ም በምስራቅ ትግራይ በወረዳ ኢ.ሮብ ቢሄረሰብ አካባቢ የሃፀይ ኃይለስላሰ ስርዓት በመቃወም በ1964 ዓ.ም ትጥቅ ትግል የጀመሩ የትግራይ ተወላጆች በጎናቸው ብዙ ሙሁራኖች በማሰለፍ ትግል ጀምረው የቆየ እንደነ ዩሃንስ ተክለሃይማኖት ያሉበት ፓርቲ በኢ.ርትራው ጀብሃ እየተደገፈ ይንቀሳቀስ የነበረው ትግራይ ገድል

ሐርነት የሚባል ለወደፊት እንቅፋት ይሆነኛል በማለት ግፍ በተሞላበት አገዳደል በእንጭጩ ደብዛው አጠፉት::
ለኢ.ህ.አ.ፓም ምንም እንኳ የራሳቸው ድክመት ይኑራቸው መለስና ጓዱቹ ግንኙነት ሲመሰርቱ በአንፃር ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ አንድነት ሉአላውነት እኩልነት ለማረጋገጥ ብለው የአጭርና የረጅም ታክቲክና እስትራተጂ ነድፈው ስለህዝባችን ነፃነት ብለው ሳይሆን የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎችና እስትራተጂ ቀማሪ መለስ ከጥዋቱ ጀምረው አቅም ያለው ፓርቲ በኢትዮጵያ ከኖረ የነሱ ብቻ ዝቅተኛ (እኩል) ስለሚሆን በከፍተኛ ስልጣን ሆነው (ንጉስ) ሆነው የመታየት ህልም ስለነበራቸው ከኢ.ህ.አ.ፓ ያደርጉት የነበረ ለጊዜው ኃላቸው አጠናከረ ው እንደግንባር ገድሊ ሐርነት ትግራይ ለመጨፍለቅ ጊዜ ለመሸመ ት ነበር: ከኢ.ድ.ዩ ጋር ሲደረግ የነበረ ድርድርም እንደዚሁ ለወደፊት ለነበራቸው ህልም ግምት ያስገባ ነበር: በአጠቃላይ የመለስና ጓዶቹ ፀረ ደርግ ከሆኑ ግንባሮች ሲያደርገው የነበረ ግንኙነት ለጊዜያዊ ትርፍ (ፕራግማቲስት) ጥቅሞች ለማሚለት ነው እንጂ አርቆ የሚያስብ ታክቲክና እስትራተጂ አልነበራቸዉም::

ሌላ መለስና ጓዶቹም ትግል ከጀመሩበት ወራት ጀምሮ እስከ 1977 ዓ.ም ታክቲክና እስትራተጂ አልነበራቸዉም: የታክቲክና እስትራተጂ ጥያቄ ያነሱ ግደይ ዘርአፅዮንና አረጋዊ በርሀ ነበሩ: ከዚያ በፊት በህ.ወ.ሓ.ት ዉስጥ ወጥ ታክቲክና እስትራተጂ አልነበረዉም የነበረው አካሄድ በመለስ የሂወት ታሪክ እንደተገለፀው ከማኦ ወደ አልባንያ ከአልባንያ ወደ ስታሊን እንደሱናሚ ንፋስ እየተገላበጡ ናቸው የመጡ: ለዛዉም የህ.ወ.ሓ.ት ፖለቲካዊ ፈላስፋ አቶ አባይ ፀሃዬ ግደይ ዘርአፅዮን ነበሩ: መለስ የነዚህ ፈላስፋዎች ሃሳብና ፅሑፍ በማንበብ እንደመማርያ ሰነድ ተጠቅመው አብረው እየተገላበጡ እንደየዉሃ ትቦ ወደ ካድሬ ተማሪዎች ያስተላልፉ ነበሩ: የአጭርና የረጂም ታክቲክና እስትራተጂ ቀማሪ ግን

አልነበሩም: ይህለመለስ የተሰጠ ከንቱ የዉሸት ሽልማት ነው: ስለዚህ በታክቲክና እስትራተጂ የሚመሩ ምጡቅ መሪ ሁነው ጠላትና ወዳጅ አበጥሮ በማወቅ ሳይሆን የተዓዙ በግብታውነት የሚጋልቡ ብዙ እስትራተጂክ ወዳጆቻቸው ይጎዱ ነበሩ የህ.ወ.ሓ.ት አመራርም ጭምር: የህ.ወ.ሓ.ት ካድሬም በደረጃው በነ መለስ ታክቲክና እስትራተጂ በመጎተቱ ተጠያቂነው::

"አዲስ ራዕይና በአሁኑ በስልጣን ያሉ ጀነራሎችና ሚኒስትሮች መለስ የወታደራዊ፣ የፖለቲካዊና ስነ ሃሳባዊ ፈላስፋ ነበሩ ብለው ተናግረዋ ል አሁንም እየተናገሩ ይገኛሉ::"

መለስ ከወታደራዊ ሳይንስ ፍልስፍና ምንም ግንኙነት አልነበራቸዉም: እስቲ የህ.ወ.ሓ.ት ወታደራዊ አፈጣጠር እንመልከት: ከየካቲት 11/1967 እስከ 8/3/1968 ዓ.ም በቀዋሚነትና በተንቀሳቃሽ ወታደራዊ ስልጠና መጀመርያ ተሰጡ አስገደ ገ/ስላሰ ነበር: ቆየት ብሎ አሕፈም 2ዙር ሰልጣኞች ብቻው አወጣ በመጋቢ ማዝያ ጉንበት 1968 ዓ.ም በወርዓትለ ኡሮፕ አስገደና አሕፈሮም 3ዙር አሰለጠኑ ሁለቱ ወደ ተዋጊ ሻንበሎች (ኃይሎች) ከወጡ በኋላ የህ.ወ.ሓ.ት ማስልጠኛ በሁለት ተከፈሉ በምስራቅ ዓሳጋራ ግርማይ ጃብር ገመስቀል ሃይሉ በሃር ጦር አካዳሚ ከ4 ዓመት በላይ ያሰለጠኑ 5 ቾንቶዎች ማለት ተስፋይ አፅበሃ ሰመረ ታደለቾንቶ ሓለፎምቾንቶ አ4ኛው አላወቀውም ተ/ኸለሃይማኖት ሽሪፎ ነበሩ:: በምዕራብ ቡምበት መረብ አጠገብ ዩሃንስ ገ/መድህን (ዋልታ) ሻምበል ካሕሳይ አባይ በሃረር ጦር አካዳሚ ለ5 ዓመት ወታደራዊ ሳይንስ የተማረ ግርማይ ፖሊስ ግርማይ ጃብር ገ/መስቀል ሃይሉ ያሰለጥኑ ነበር ገመስቀል ሃይሉ ከዓሳግራ የመጣ ነው: ከ1969 ዓ.ም መጨረሻ እስከ ጉንበት 1975 ዓ.ም መጀመርያ አስገደ በወታደራዊ ሰለሞን ተስፋይ ካሕሳይ ስዩም ሓዱሽ መስፍን በፖለቲካ ያሰለጥኑ ነበር ቀጥሎ ሓድጉ ከበደ ባህር ሃይል የነበረ ሓለፎም ቾንቶና ብዙ ተራ አሰልጣኞች ተመደቡ እነዛ ረዳት

ወታደራዊ አሰልጣኞችም የአሰልጣኝ ስልጠና በነአስገደ ሓለፎም ቸንቶ ሓድጉ ከበደ ስልጠና ተሰጣቸው: የኋላ ኋላም እጅግ ከፍተኛ ባለሙያዎች ሆነው ደርግ እስኪወገድ በአንድ ጊዜ 10ሺ 20ሺ 30ሺ 60ሺ 75ሺ ያሰለጥኑ ነበር: ይህ ወታደራዊ ስልጠና በህ.ወ.ሓ.ት ወታደራዊ ባለሙያዎች የተሰጠ ነበር: ሻዕቢያ ህ.ወ.ሓ.ት ደደቢት ከመውጣቱ አስቀድመው ሙሁራንና ተማሪዎች 9ገበሬዎች ከሻዕቢያ የቆዩ 5ኢትዮጵያውያን በድምር 21 ለሁለት ሳምንታት ሰልጥነዋል: ሻዕቢያ ለማዳን ተብሎ ምሽግ ለመጠበቅ ሳሕል ሰልጥነው ምሽግ የገቡም የተወሰነ የሻዕቢያ ድጋፍ ካልሆነ በስተቀር በህ.ወ.ሓ.ት አሰልጣኞች በነ አስገደ ይሰለጠኑ ነበር::

የህ.ወ.ሓ.ት ከፍተኛ ወታደራዊ አመራር ስልጠና ሲሰጡ የነበሩ የተጀመረው 1973 ዓ.ም አሰልጣኞች የነበሩ: አረጋዊ በርሀ የህ.ወ.ሓ.ት ስራ አስፈፃሚ ወታደራዊ አዛዥ ስዬ አብረሃ የህ.ወ.ሓ.ት ማ/ኮሚቴ ምክትል ወታደራዊ አዛዥ ሓለፎም ቸንቶ ሓድጉ ከበደ ጀላኒ ፈረጅ ገ/ማርያም ገብረ ገ/ማርያም ክብሮም ገ/ማርያም ተስፋይ ያይንሸት ጋህረ ፈረስማይ ጌታቸው ተፈሪ አስገደ ገ/ስላሰ መምህር ነጋሽ ለገሰ ሓዱሽ መስፍን ሙሉጌታ ገ/ሂወት (ጫልቱ) ሌሎችም: ይህ ወታደራዊ ሳይንስ የኋላ ኋላ ብዙ ከደርግ ከድተው የመጡ መኮነኖች የተማረኩ መኮነኖች በማሕበር ተደራጅተው እነ ኮረኔል ሰረቀብርሃን የነበሩባቸው ብዙ መኮነኖች ራሻ ሰሜን ኮርያ ቻይና ኩባ ከ5 እስከ 8ዓመት በሁሉም ዓይነቶች ወታደራዊ ሙያ የተማሩ ነበሩ: ወታደራዊ ሳይንስ እንደፈላስፋዎች ሁነው የፈጠሩት::

በከፍተኛ ወታደራዊ አመራር ትምህርት ቤት ሲሰጥ የነበረ ሙያ ከጓድ መሪ እስከ ብርጌድ አመራር በሁሉም የመድፎች ዓይነቶች አየር መቃወምያዎች፣ ቀላል መካከለኛና ከባድ መሳርያዎች የፈንጅ መሃንዲሶች፣ የእጅ ቦምቦች፣ ወታደራዊ ስለላ፣ ስለዉጊያ ታክቲክ፣ ቆረጣ፣ መገናኛ፣ ሬድዮ ጠለፋ ጨምሮ፣ የስንቅና ትጥቅ፣ የትራንስ

ፖርት፣ የማኪና ሽፌርነት ስልጠና፣ ሌሎችም ነበሩ: ወታደራዊ ካርታም ጭምር::

በሌላ በኩል የተዋጊ ሰራዊት አዛገሮች ከደርግ ጋር የሚያጋጥማቸው የዉጊያ ስልት በማዘመድ ከታች ቡድን አመራር እስከ ከፍተኛ አመራር: እነ ሓየሎም ሳሞራ ፃድቃን የሚመሩት ጥልቀት ያለው ግምገማ በመገምገም ለከፍተኛ ወታደራዊ ትምህርት ቤት ለአዲስ ወታደሮች ማሰልጠኛ የልምድ ግብአቶች በማፈስ ለወታደራዊ ሳይንስ ጥልቀት እንዲኖሮው ትልቅ አስተዋፅኦ አድርገዋል: በየ ግንባሩም ሁልጊዜ ወታደራዊ ስልጠና ይሰጥ ነበር::

የህ.ወ.ሓ.ት ወታደራዊ ኮሚቴ በመጀመርያ የትጥቅ ትግል ወታደራ ዊ አዛዥ የነበረ አቶ ገሰሰው አየለ ምክትል ሙሴ ተኽለ ነበሩ: አቶ ገሰሰው ከተሰዉ በኋላ ወታደራዊ አዛዥ ሙሴ ነበር: ሙሴ  ከተሰዋ በኋላ ወታደራዊ አዘዥ አረጋዊ በርሀ ምክትል ስዬ አብረሃ: ከ1978 ዓ.ም እስከ ደርግ የተወገደበት ወታደራዊ አዛዥ ስዬ አብረሃ ምክትል ጀነራል ፃድቃን ለወታደራዊ ኮሚቴ በኮሚቴ ሁነው ይመሩት ነበሩ: ከ1978 ዓ.ም እስከ ደርግ የተወገደበት ድረስ ወታደራዊ ሊቀመንበረ ስዬ አብረሃ ምክትል በወቅቱ ጀነራል ፃድቃን ሓየሎም አርአያ የኮሚቴ አባል ቆየት ብሎ ጀነራል ሳሞራ የኑስ ተጨምሮ ነበር::

እስከዚህ ድረስ ምጡቅ የወታደራዊ ሳይንስ መሃንዲስ እየ ተባለ የተፃፈላቸውና የተነገረላቸው አሁንም ይነገርላቸው ያለው መለስ ወደ ወታደራዊ ፍልስፍና ተጠገተው አያውቁም: በዚያች የፖለቲካ ጉዳይ ግን ከአባይ ፀሃዬ መመርያ እየተሰጣቸው እየተገላበጡ የህ.ወ.ሓ.ት ሰራዊት ሁሉ አስተምረዋል እሳቸው በቀጥታ ባያስተምሩ ትም እሳቸው ያስተማሩዋቸው ካድሬዎች አስተምረዋል ልክ እንደወታደራዊ ሳይንስ የአሰልጣኝ ስልጠና ተሰጥቶዋቸው እንደአሰለጠኑት::

አንድ ሐቅ ግን ላስቀምጥ በህ.ወ.ሓ.ት አመራር ከላይ እስከ ታች የአመራር ኮሚቴዎች ነበሩ: እነሱም ወታደራዊ ኮሚቴ ፖለቲካዊ ኮሚቴ የዉጭ ጉዳይ ኮሚቴ ነበሩ: እነዚህ ኮሚቴዎች በየምድብ ስራቸው ዕቅድ አውጡ ይባሉና ኮሚቴዎች ሁሉ የራሳቸው ዕቅድ ካዘጋጁ ዝምብለው አይደሉም ወደ ተግባር የሚሄዱ የኮሚቴዎች ሁሉ ወደ የህ.ወ.ሓ.ት ስራ አስፈፃሚ ቀርበው ክርክር ይደረግባቸው ነበር: በመድረክ ሁሉም ይከራከራሉ በዛን ጊዜ መለስ በወታደራዊ ኮሚቴ ዕቅድ ተከራክረው ይሆናሉ ስዬም ወታደራዊ ሃላፊ በፖለቲካ በዉጭ ጉዳይ በፋይናንስ ወ.ዘ.ተ ተከራክረው ይሆናሉ: ግን ፈላስፋ ወይም መሃንዲስ አልነበሩም: ስለዚህ መለስም የወታደራዊ ፈላስፋ አልነበሩም በየት አድርገው: ስለሆነ መለስ ሁሉም ወታደራዊ ሙያ መሃንዲስ ነበሩ የሚለው ባዶ ዲስኩር ነው::

መለስ በወታደራዊ ስራ የነበራቸው ኋላ ቀር አስተሳሰብ ምን መሰላቹሁ: በአንድ ወቅት በ1983 ዓ.ም ተታህሳስ ወር አካባቢ ህ.ወ.ሓ.ት ከትግራይ ጀምሮ እስከ ሰሜን ወሎ ሰሜን ጎንደር ሰሜን ሸዋ የዘለቀ በሁሉ ዕድሜ ከ15 ዓመት ጀምሮ ወጣት በግድም በውድም ወደ ወታደራዊ ማሰልጠኛ አግቡት ይላል: በዛን ጊዜ በ10ሺ የሚቆጠር ወጣት በግድ ተሰለፈ እንቢ ያለ ወላጆች ይታሰራሉ የቤት እንሰሳቸው ሃብታቸው ተወርሰዋል: መለስ በአመራሩ ሰልጣኝ በዝተዋል ማሰለፍን ናቁም በማሰልጠኛ ያለዉም ንቀንሰው ተብሎ ሃሳብ ቀረበ: በመለስ የቀረበ ጨካኝ ሃሳብ ይህ ሰራዊት እንደ ዑመር መከተር ሰራዊት ገለባ ነው ገበሬ ነው አያማዛዝንም ወደፊት ግባ ካልከው ግን ክምር ገለባ በተረታ አስቀምጦ እሳት ካቃጣጠልከው አንድ ከተቃጠለ ለሚቀጥለው ያቃጣጥለዋልና ለእግረመንገዱ ሃገርን ያጠፋል: ይህ ሰራዊትም መጀመርያ ወደ ጦርነት የገባ አቃጥሎ ስለሚያቃጥል የሚቀጥለው ተተኪም አቃጥሎ ይቃጠላል: እንደዛ አድርገን በተከታታይ ገለባ በመቃጠል ነው ደርግን የምናቃጥለው አሉ: በዛን ወቅት ብዙ

ተቃውሞ አጋጥማቸዋል: ስለዚህ የመለስ ወታደራዊ መሃንዲስነት ይህ ነበር: ይህ ደግሞ የማካቬሊ ታክቲክና እስትራተጂ ነው: ማካቬሊ ሁሉም ነገር በግብታውነት በመስራት ብዙ ነገር ከስሮና አውድሞ በመጨረሻ ድልና ዉጤት ማግኘት የሚረካ እንደነበረ ሁሉ መለስም እንደዚሁ ናቸው: የሚያስቡ ይህ ደግሞ የመለስ ግብታዊነትን ያመለክታል::

ሌላ በኢትዮ ኢርትራ ጦርነትም መለስ የወታደራዊ ሳይንስ መሃንዲስ ነበሩ ተብለዋል: እዚህ ላይ መለስ ብዙ ስህተት ነው የፈፀሙት: 1ኛ ሁሉ ኢትዮጵያዊ ሻዕቢያ እስትራተጂካዊ ጠላት ነው እያለ በተለይ ደግሞ በቅርብ የሚያውቁት የትግራይ ህዝብ የድሮ ወታደር ወንጀል የሌለው እንደገና እናደራጀው: የህ.ወ.ሓ.ት ሰራዊት አይቀነስ ሻዕቢያ ወታደር ሲገነባ ህ.ወ.ሓ.ት ለምን ሰራዊቱ ያፈርሳል የሚል ጥያቄ ሲየቀርብ እናንተ ጦርነት ናፋቂዎች ከሻዕቢያ ያለን ግንኙነት በአጥንት በስጋ በደም ተለውሶ እንደ ኮንክሪት የተገነባ ነው ብለው የኢትዮጵያ ሰራዊት የበተኑ ናቸው: 2ኛ ሻዕቢያ ሊወረን እየተዘጋጀ በርደርገ ጠረፍ እንደመጠበቅ በመለስ በእንዝላልነት ምክኒያት ሃገራችን በባንዳ ተደፈረች: 3ኛ የኢትዮጵያ ሰራዊት የሻዕቢያ ወራር ድባቅን መትቶ ከሃገራችን አባርሮ አስመራ አካባቢ ተጠግቶ ሲያበቃ ወደ ኋላ ተመለስ ብለው መለስ ትእዛዝ በመስጠት በሰራዊታችን አላስፈላጊ መስዋእት ተከፍለዋል: 4ኛ ሻዕቢያን ለአንድ ጊዜና ለመጨረሻ አስወግደን እስከ ንቆጣጠር ተብሎ ጦርነትን ተጀምሮ ሻዕቢያ ከአስመራ ለቆ ሳሕል ሊገባ እየተዘጋጀ አሁንም መለስ ከወታደራዊ ኮሚቴ መስመር አልፈው ከጥቂት ከፍተኛ መኮነኖች በነበረው ግንኙነት ተጠቅሞ ሰራዊት እንዲያፈገፍግ አደረጎ በሺ የሚቆጠር የኢትዮጵያ ሰራዊት በኢርትራ በረሃ ቀርተዋል: ይህ ተግባር በህ.ወ.ሓ.ት ማኮሚቴ መሰናጠቅ ጠንቅ አንዱ ነበር: 5ኛ መለስ ኢትዮጵያ ሸዕቢያ በሃይል የወረረው በሃይል መልሳው እያለች ጉዳዩ በመተው ነገር ያለ ይግባኝ

በተባበሩት መንግስታት ዘሄግ ፍርድ ቤት እንዲፈረድ ያደረገ የአልጀርስ ስምምነት የፈረመና የሃገራችን ሉአላዊነት አሳልፎ የሰጠ ምጡቅ መሪ አለነበረም: ይህ ሁሉ በመደመር መለስ የአጭርና የረጂም እስትራተጂ ቀማሪ ነበሩ ሊያስብላቹሁ ይቻላል አይሆንም መለስ ለጊዝያዊ ጥቅምና በዓለም ልታይ ልታይ በማለት የማካቬሊ እስትራተጂ አራማጅ ነበሩ: መለስ ከዚህ ፅሑፍ መጀመርያ አካባቢ እንዴት ብለው የሰው ሃሳብ ጠልፈው የራሳቸው ታዋቂነት እንደ ሚያተርፉ አስቀምጨዋለሁ::

"መለስ ከእስትራተጂ አኳያ የነበረው ብቃት ቢያንስ በሁለት ተልልቅ መድረኮች ብቁ እስትራተጂስት እንዳስመሰከረ በማሳየት ማረጋገጥ ይቻላል: 1ኛ እስትራተጂ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ ሲሆን 2ኛ ግን ጀምረናል በአስተማማኝ ሁኔታ በመቀጠል ላይ ያለ እስትራተጂ ነው: የመጀመርያው እስትራተጂ አንባገነን የደርግ መንግስት በመገርሰሰ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይላችን አሸናፊነ ት ለማረጋገጥ የተነደፈው እስትራተጂና ይህንኑ ተግባራዊ በማድረግ የተገኘው የተሟላ ዉጤት ነው: 2ኛ ደግሞ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርዓት መገንባት ከጀመሩ በኋላ ድህነትና ኋላ ቀርነት አሸንፎ የበለፀገ ዴሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ ለመገንባት የተቀየሰውና እስከ አሁን በጥሩ አኳሃን ተግባራዊ ሆኖ ዉጤት እያስመዘገበ ያለው እስትራተጂ ነው: እነዚህን አንድ በአንድ በመመልከት የመለስን የእስትራተጂ አመራር ብቃት ለመመስከር ይቻላል::"

በመለስ ዘመነ መንግስት በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ሳይሆን አሸንፈው ስልጣን የያዙ የመለስን አንባገነን እስትራተጂ ነው ያሸነፈ ምክኒያቱም የመለስና ጓዶቹ ጉዞ ዴሞክራሲያዊ አልነበረም አሁንም የለም: የመለስ የዴሞክራሲ እስትራተጂክና የደርግ ዴሞክራሲ ልዩነት እንዳልነበራቸው ባለፉት ገፆች በሰፊው ተቀምጠዋል: በአሁኑ ጊዜ የመለስ ፀረ ዴሞክራሲ መዋቅር ለዴሞክራሲያዊ ሃይሎች እያሰረ እየገረፈ ደብዛቸው እያጠፋ በጭቁኖች መቃብር

ሲፈነጭ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች መጠግያ አጥተው እየተሰደዱ መሆናቸው ካለፉት ገፆች በዝርዝር ተቀምጠዋ ል::

ድህነትና ኋላ ቀርነት አሸንፎ የበለፀገ ዴሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ ታንፃል የተባለ ዉሸት ነው: አሁንም ደግሜ ልንገራቹሁ አራት ኪሎ እንደምትበሉት እንደምትጠጡት በእናንተው አትገምቱት ደግሞስ ሲያሸኛቹሁ በሶደሬና በሽራቶን እንደምትዝናኑት የኢትዮጵያ ህዝብ እኮ እናንተ ባላቹሁበት አዲስ አበባ እንኳን በአንድ ጠባብ ቤት ከ15 እስከ 20 ሰው ተኝቶ ያድራል በባዶ ሆዱ: ስደቱ መበታተኑ ቀደም ብሎ በሰፊው ተገልፀዋል: መለስ በፀረደርግ ትግል ይሁን በ21 ዓመት ስልጣን ዘመናቸው አርቆ የሚያስብ ወዳጅና ጠላት በትክክል የሚያሳይ እስትራተጂ አልነበራቸዉም ይልቁንስ ሌሎች የሰሩት ታክቲክና እስትራተጂ የራሳቸው አድርገው የማቅረብ ብቃት ነበራቸው: የሰዎችን ሃሳብ ጠልፈው የራሳቸው ማድረግ መለያ ባህሪያቸው ነበር::

"በገፅ 58 አዲስ መስመር 3 መስመር 4: ለደርግ ግዙፍ አደገኛ መንግስት ከ70ሺ የማይበልጥ የታጠቀ ሰራዊትና የህዝብ ትግል ለመንኮታኮት የወሰደው ጊዜ 17 ዓመት ሲሆን መለስ ለዚሁ ትግል አመራር መስጠት ከጀመሩበት በተለይ ደግሞ የእስትራተጂ ጥያቄዎ ች  በአግባቡ መመለስ ከጀመረበት በ1977 ዓ.ም በኋላ ያለው ጊዜ ሲሰላ ደግሞ ከ6 ዓመት ጊዜ የወሰደበት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል::"

አንደኛ ነገር ደርግ በመጨረሻ ጊዜ ሲሸነፍ በግንባር የተሰለፈ የህ.ወ.ሓ.ት ከደጀን ስታፍ ጨምሮ ከ146ሺ በላይ የባአዴን 4ሺ ነበር: በማሰልጠኛ ጣብያ ስልጠና ጨረሶ ቁጭ ያለ በመለስ አነጋገር ለሚቃጠለው ገለባ የሚተካ 75ሺ ሰልጣኝ የህ.ወ.ሓ.ት የባአዴን 2500 በላይ ነበር: ኢሆደድ ገና ምርኮኞች አሰባስቦ ፓርቲ ለመመስረት ይዘጋጅ ነበር: ስለሆነ አዲስ ራዕይ ዋሽታቹሃል መረጃ ያንሳቹዋል: ደርግ ሲወገድ የህ.ወ.ሓ.ት በአዴን ሰራዊት ማሰልጠኛ

የነበረው ጨምሮ 229ሺ. ሰራዊት ነው: በተጨማሪ ህ.ወ.ሓ.ት ከተመሰረተ 1967 ዓ.ም እስከ 1983 ዓ.ም ወደ ህ.ወ.ሓ.ት የተለፈ ወጣት ምልሻና ሲቪል ካድሬ ሳይጨምር 386ሺ. ነበር: ይህ ሰራዊት አብዛኛው ሻዕቢያ ለማዳን ኢ.ርትራን ለመገንጠል በኢ.ርትራ በረሃ ያለቀ እንዲሁም ከትግራይ ጀምሮ በመላው ኢ.ትዮጵያ ተራራዎች ፀረደርግና ፀረሌሎች የመለስ መንግስት ጠላቶች ናቸው ብሎ የፈረጃቸው የሞቱ ታጋዮች በተጨማ ሪ እጅግ ብዙ ታጋዮች በተለያዩ ምክኒያቶች ደብዛቸው የጠፉ ጀግኖች ሞቶዋል: ሻዕቢያ ለማዳን ከ15ሺ. እስክ 20ሺ. ኢ.ትዮጵያዊ በመለስና ጓዶቹ በማያምንበት ሃገራዊ ጥቅም በተፃረረ መንገድ ተዋግቶ ሞተዋል: በዚህ አኳሃን 20ሺ. ወጠት ሞቶ እያለ አንድ አንድ ታሪክ ፀሐፊነን የሚሉ እንደነ ብስራት አማረና ወለገብሪኤል ታደሰ የህ.ወ.ሓ.ት ተላላኪዎች ያሉ ሻዕቢያ ለመርዳት ወደ ኢ.ርትራ ሂዶ የሞተ 400 አራት መቶ ታጋይ ብቻ ነው የሞተው ብለው ፅፈዋል: እንዲሁም አቶ ሕቡር ገብረኪዳን የሚባል አንድ ቀን እኳ ጥይት ተኩሶ የማያውቅ በኢ.ርትራ የሞተ ታጋይ 400 ብቻ ነው ብሎ ተናገረ: እነዚህ ሰዎች ሳሕል ሄዶ በሳሕል ተራራዎች ሬሳው አፈር ሳይለብስ ተጥሎ የቀረው ጀግና የትግራይ ህዝብ አሳምሮ ያውቃል: ይህን ሐቅ መካዳቸው ምን ያህል ሃገራቸው የከዱ ሰዎች ናቸው ያልሆና ታሪክ የሚፅፉና የሚናገሩ: ስለዚህ አዲስ ራዕዮች የዉሸት መረጃ ተሞልታቸሁ ይህን የዉሸት ታሪክ መፃፋቸሁ የጀግኖች እናቶች ሃዘን አሳድሳቹሃል::

በሌላ በኩል በኢ.ርትራ በአስርሺ. የሚቆጠር የትግራይ ወጣት ሞቶ እያለ 400 ሰው ብቻ ሞቶዋል ያሉ ሰዎች እነዚህ ወጣቶች ስለያልወለዱዋቸው ነው: እነዚህ ሰዎች እስቲ በትግራይ ያሉ ቀበሌዎች ሄዳቹ ፈትሹም ጠይቁም ሐቁን ለማረጋገጥ ሞክሩ: እነዚህ ሰዎች የፃፉዋቸው ፅሑፎች ያነበባቹ ሁሉ በተለይ ደግሞ የህ.ወ.ሓ.ት ነባር ታጋቶች ለ4 ዓመትና ወራቶች ይዛቹሁ የሄዳቸሁ

ሰራዊትና በየጊዜው ለሞቱትና ለቆሰሉት መተኪያ ተብለው አዲስ ሰልጣኞች ገብተው በዛ የቀሩና የቆሰሉ: አሁን ኮሮኔል እስከ ጀነራል ደረሳቹ ያላቹ በተለይ ጀነራል ሳሞራ የኑስና ጀነራል አበበ ተ/ሃይማኖት እነ አቶ መድህን በአሁኑ ጊዜ የፌደራል ዳኛ እነ ጀነራል ታደሰ ወረደና ጀነራል ሰዓረ መኮነን ጀነራል ዩሃንስ ገ/መስቀል አቶ አውዓሎም ወሉ አቶ ስብሃት ነጋ አቶ አርከበ ዑቅባይ ጀነራል ተኽላይ አሸብር አቶ ቢንያም ገ/መድህን: ኮሬኔል ሃዋዝ ወልዱ አቶ መድህን በኢርትራ አዲስ ምልምል ታጋይ እያሰለጠናቹ ወደ ሻዕቢያ ምሽግ ስታስገቡ የነበራችሁ የ(02) አሰልጣኞች አቶ አባይ ፀሃዬ አቶ ስዬ አብረሃ አቶ ግደይ ዘርአፅዮን አቶ አረጋዊ በርሀ መላው የህ.ወ.ሓ.ት አመራር ወ.ዘ.ተ: ያ ሁሉ የተቀጠፈ ወጣት እያወቃችሁ ዝምታ የመጣችሁ ምን ያህል ኡነተኛነት እንደሆናችሁ የትግራይ ህዝብ በትዝብት ላይ አስቀምጣችሁ ነው::

2ኛ መለስ በ1977 እስከ 1983 ዓ.ም ለህ.ወ.ሓ.ት ይሁን ለማለሊት የሰጠው እስትራተጂ አመራር አልነበረም በወቅቱ የካድሬ አስተማሪና የፖለቲካ ኮሚቴ ሊቀመንበር ነበሩ: በዛን ጊዜ የህ.ወ.ሓ.ት ሊቀመንበር ስብሃት ነጋ የማለሊት ሊቀመንበር አባይ ፀሃዬ ነበሩ: እስከ 1983 ዓ.ም የህ.ወ.ሓ.ት እስትራጂካዊ አመራር ይሰጡ የነበሩ አባይ ፀሃዬ ናቸው: መለስ በ1983 ዓ.ም ታህሳስ ወር በታሪካቸው እንደገለፅኩት ቡድን በመፍጠር ለአባይ ፀሃዬ ፈንቅለው የህ.ወ.ሓ.ትና የማለሊት ሊቀመንበር ሁነዋል: ለስልጣን የበቁት ደግሞ ስብሃት ነጋ በጀርባ እየነዱ ለነ ስዬ አብረሃ ተወለ ወ/ማርያም ፃድቃን ገ/ትንሳኤ ስዩም መስፍን ክንፈ ገ/መድህን አበበ ተ/ሃይማኖት (ጅብዩ)ና ሌሎች ማኸል ሰፋሪ ከጎናቸው በማሰለፍ ነው: ስለዚህ የነደፈው እስትራተጂ 6 ዓመት ፈጀበት የምትሉ ዉሸት ነው::

መለስ ከ1982 ዓ.ም በኋላ ይሆን ከዛ በፊት የነበረ እስትራተጂ እንጂ ሌላ የፈለሰፋት ታክቲክና እስትራተጂ አልነበረም: በቃ አባይ ፀሃዬ ይሰሩት የነበረ የ5 ኮሚቴዎች የማስተባበር ጉዳይ ነው የነበረ::

"ገፅ 58 አዲስ መስመር 3 በመስመድ 11: በህወሐሓት ትጥቅ ትግል ወቅት በ1976 ዓ.ም አካባቢ ያጋጠመው ወደ ፊት ለመራመድ አልቻለም ወይም በትግርኛ ደውታ በሚል አገላለፅ የሚታወቅ ችግር የተፈታው መለስ የፖለተለካ እስትራተጂና ታክቲክ እንዲሁም የወታደራዊ ንድፈ ሃሳብ ስራዎች ነበር: በነዚህ ስራዎች በታሪካችን ለመጀመርያ ጊዜ የህዝባዊ ጦርነት ባህሪ በትክክል የመለሰ መለስ ነበር::"

በህ.ወ.ሓ.ት ትጥቅ ትግል ደውታ መራመድ አለመቻል ተፈጥሮ የነበረ በ1975 ዓ.ም ነው: መራመድ አለመቻል ዋና ምክኒያት የህዝባዊ ጦርነት ባህሪን ተንትኖ ባለማወቅ አልነበረ ም: በህ.ወ.ሓ.ት ከ1967 እስከ 1972 ዓ.ም የነበረ ታጋይ ከ90% በላይ የተማረ ነበር: ይህ ሙሁር በፀረደርግ ኢ.ድ.ዩ ኢ.ህ.አ.ፓ ጀብሃ ጦርነቶችና ሌላ ምክኒያት ሙተዋል ደብዛው ጠፍተዋል: በ1975 ዓ.ም በአመራር ደረጃ የተማረ ነበር አንጃ ሰራዊቱ 99% አካባቢ ገበሬ ነበር: በመሆኑ የወታደራዊ ፖለቲካዊ አመራር ተዳከመ እንጂ የህዝባዊ ጦርነት ባህረ እንዴት መሆኑ በ1969 ዓ.ም ሃምሌና ነሃሴ በዓድዋ አውራጃ እገላ ወረዳ በሰብአ የሚባለው ቦታ 75 ካድሬዎች ስለህዝባዊ ጦርነት ባህሪና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች አፈታት ለ2 ወር ያህል ሰልጥኖ ያሰለጠነ ካድሬ በታጋይም በህዝብም ተሰራጭቶው አስተምረዋል: ስለዚህ የህዝባዊ ጦርነት ባህሪ ከ1975 ዓ.ም በአባይ ፀሃዬና ሌሎች አማራሮች የተሰራ ነው: በተለይ በግደይ ዘርአፅዮን ወቅት ፖለቲካ አሰልጣኞች የነበሩ አረጋሽ አዳነ የዉብማ ር አስፋው ገ/መስቀል ሃይሉ ዓለምሰገድ ገ/ምላክ አማረ አረጋዊ መለስም ጭምር ነበሩ: ስለዚህ በቅርብ ሃሳብን እያመነጩ አባይ

ፀሃዬና ግደይ ነበሩ: በዛን ጊዜ መለስ ቦታ አልነበራቸዉም ገና በካድሬዎች ተሰሚነት አልፈጠሩም::
አሁንም መለስ የፖለቲካዊና ወታደራዊ ንድፍ ሃሳቦችን አፍላቂ አልነበሩም: ስለፖለቲካ ሃሳብ አፍላቂ እንዳልነበሩ ቀደም ብሎ ተገልፀዋል::

ስለወታደራዊ መራመድ አለመቻል የሚል ግን ቅድም እንደ ገፀው የወታደራዊ ሳይንስ ሃሳብ አፍላቂዎች ተዘርዝረዋል: የህ.ወ.ሓ.ት ወታደራዊ ሳይንስ አጎልብተዋል ለዚህ ደግሞ የህ.ወ.ሓ.ት ከፍተኛ መኮንኖችና ትምህርት ቤቶች በማስፋፋት የነበረው መራመድ አለመቻል ችግር ተፈተዋል: የሚገርም ነገር ግን እነአባይ ፀሃዬ ጀነራል ሳሞራ የኑስ ሌሎች በተለቪዥን መስኮት መለስ ለሁሉም ነገር ፈላስፋ ነበር እያሉ ሲናገሩ የሚያውቅ ታጋይ ምን ይለኛል እንኳ አይሉም: መለስን የሚታወቅ ታጋይ በሺ የሚቆጠር አለ: ለሆዱ ሲል ሰግቶ እንጂ በግልና በቡድን የሚያማ እኮ ንሰማለን: ስለዚህ አዲስ ራዕይ አትዋሹ ለመለስ ግን የራሳቸው ያልሆነ ታሪክ እየደረደራቸሁ ልታስንቁት ነው የሚመስለኝ ለሞተው ሰው ዕረፍት ማሳጣት ደግሞ ትክክል አይደለም::

ሌላ ህ.ወ.ሓ.ት እኮ የራሱ ወታደራዊ ሳይንስ የፈለሰፈው (ያፈለቀው) ሃሳብ አልነበረም: ወታደራዊ ስልጠና ይሰጡት የነበሩ በአመሪካ በእስራኤል በጀርመን በእንግሊዝ በፈረንሳይ በራሻ በሰሜን ኮርያ የሰለጠኑ ናቸው: ለአብነት የሽምቅ ዉጊያና ፀረሽምቅ ዉጊያ ስልጠና ቆረጣ ስልት አካቶ የህ.ወ.ሓ.ት ጠቃሚ ነበር: የሌሎችም ህ.ወ.ሓ.ት በወታደራዊ አደረጃጀት ከፍ እያለ ሲሄድ ተጠቅመንበታል: የደርግ ወታደሮች መኮነኖች ምርኮኞች በእስር ቁጥጥር ሆኖው አሰልጥነዋል: ከህ.ወ.ሓ.ት የበለጠ ሙያ ስለ ነበራቸው ነው: ስለዚህ የሚያስተገብ ር የነበረ መለስ አይደሉም: ስለዚህ የመለስ ታሪክ የራሳቸው ብቻ ይፃፍላቸው ነበር: የመቶሺ

ጀግና ሰዎች ታሪክ ለመለስ መሸለም ፋይዳ የለዉም: ዉሎ አድሮ ታሪክ ሊመሰክረው ነው::

"በገፅ 59 አዲስ መስመር 2 መስመር 7: በሰማንያዎች መጀመርያ ላይ በመለስ ሃሳብ አመንጪነት በተራመደው የሰላም ሃሳብ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ እንዲሰፍንና ለነፃ ፖለቲካዊ ዉድድር የሚያመች ማእቀፍ እንዲፈጠር ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የሰላም ሃሳብ አቀረበ::"

መለስ በ1980 ዓ.ም ያመነጨት ሃሳብ አልነበረም ከዛ በፊትም የሰላም ፕሮፖዛል ቀርቦ ነበር በወርዒ በደጀና ካድሬዎች ሰልጥነውበ ታል: በሌላ በኩል ግን መለስ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ እንዲሰፍንና ለነፃ ፖለቲካዊ ዉድድር የሚያመች ማእቀፍ እንዲፈጠር አድርገዋ ል ትላላቸሁ: አይደለም ይህ የራበው ጂብ በማያውቁት ሃገር ሄዶ አኅዛ አንጥፉልኝ አለ እንደሚባለው አድርጌ ነው የሚወስደው ከመለስ አጭር ታሪክ ከሚለው አርእስት እንደተገለፀው: መለስና ጓዶቹ ህ.ወ.ሓ.ት እኔ በተነፈስኩት ተንፍስ ያልኩህን አድርግ ብሎት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግና ሌሎች ካልተቀበለ በ17 ዓመቱ የትጥቅ ትግል ይሁን ከዛ በኋላ እስከ የመለስ ግብአተ መሬት ስንት ፓርቲዎች ደብዛቸው ጠፋ ስንት ሙሁራኖች ታጋዮች የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት ደብዛቸው ጠፋ በመቶሺዎች የሚቆጠሩ ፖለቲከኖች ታስረዋል: ብዙ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ታጋዮች አመራሮች ተማርከዋል የት እንዳሉ መለስና ጓዶቻቸው የፈፀሙዋቸ ው ተግባራት እኮ በየአንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቤት ያልሻረ ጠባሳ አለ: መለስ በትግሉ ጊዜም ኋላም የሰላም ፈላስፋ የሰላም አባት ነበር ስትሉን ለኢትዮጵያ ህዝብ ማስተዛዘኛ ይሆነዋል ወይ::

መለስና ጓዶቹ እኮ ራሳቸው ጠፍጥፈው ያሳደጉት የድሮ ኢ.ህ.ዴ.ን (የአሁኑ ባአዴን) በኢርትራ የነበረው አቋም ኢርትራ ነፃ ሃገር አይደለችም ጥያቄያቸው የቅኝ ግዛት ሳይሆን ከቢሄር ጥያቄ አይወጣም ብለው ለ8 ዓመት ይዘዉት የቆዩ አቋም መለስና ጓዶቹ

የኢ.ርት ራ መገንጠል መብት የማይቀበል ፓርቲ (ሃይል) አንደኛ የኢ.ርትራ ጥያቄ የማይቀበል የዴሞክራሲያዊነት (ዴሞክራሲያዊ አለመሆኑ) ዋነኛው መስፈርት ነው የነበረው እያሉዋቸው ቆይተው በ1980 ዓ.ም ክረምት ግን በግልፅ ኢ.ህ.ዴ.ን የኢ.ርትራን የነፃነት ጥያቄ ካልተቀበለላቸሁ ግንኙነታችን ያቋርጣል ሲሉዋቸው ሃይለ ጥላሁን ሙሉ ዓለም ሃውጀላ በ1983 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ከተማ የተመታ ሲቃወሙ ታምራት ላይነ አዲሱ ለገሰ ተፈራ ባልዋ ህላዊ ዮሰፍ ታደሰ ካሳ (ቅንጥሸ) ሌሎችም ለነመለስ ፈርተው እሽ ብለው ኢ.ርትራ ለመገንጠልና የኢ.ትዮጵያ ሉአላዊነት ለመፈራረስ ፈረሙ: ስለዚህ መለስና ጓዶቹ በደረዘኖች የሚቆጠሩ ብዙ ሲሂቃን ያቀፈ ፓርቲዎች የዋጡ ሰላም ፈላጊ ለሰላም የቆሙ ስትሉን ተራ ማሾፍ ከመባል ትርጉም የለዉም::

አንድ ሐቅ ልንገራቸሁ ከደርግ ጋር ለመደራደር ጥያቄ የቀረበው በትክክል ደርግ ሰላምን ተቀብሎ ከደርግ ጋር አብሮ የሽግግር መንግስት ለመመስረት አልነበረም ሆን ተብሎ የዉጭ የህዝብ ግንኙነት ትርፍ ለማግኘት ተብሎ እንደተሰራ በወቅቱ መጀመርያ ከላይ እስከ ታች ያለው አመራር በሁለተኛ ደረጃ ለካድሬዎች በሶስተኛ ለህዝብ የተነገረው ለደርግና ለሰላም ንደራደር የምንለው ለዝህጅት ጊዜ ለመሸመትና በዉጭ ያለን ተፅእኖ ለማብረድ ነው: ስለሆነ በኢ.ትዮጵያ ዴሞክራሲ ስርዓት ሊረጋገጥ ከሆነ በደርግ መቃብር ነው የተባለው: ይህ አባባል ከራሴ ጀምሮ ለታጋይ ለህዝብ ቀስቅሰንበታ ል: ስለሆነ መለስና ጓዶቹ ከደርግ ጋር ሲደረግ የነበረ የሰላም ድርድር ማታለል ነበር::

በተጨማሪ አንድ ማስረጃ ልንገራቸሁ: የመጨረሻዋ 11ኛ ከአሻግሬ ይግለጡ ድርድር ሲደረግ: መለስና ስዬም ወደ ድርድሩ ከመሄዳቸው በፊት ለህ.ወ.ሓ.ት ሰራዊይና ለደጀን ታጋይ የተነገረው ደርግ የሰላም ድርድሩ ሊቀበል ስለሚችል ከደርግ ጋር የሽግግር መንግስት መመስረት ማለት ገመድን በኣንገት አግብተህ መታነቅ

ስለሆነ በዚያ የድርድር ቀን መላው ኢትዮጵያ ተቆጣጥረን አዲስ አበባን በአጭር የጥይት ርቀት ተቆጣጥረን መቆየት አለብን ተብሎ ለዘማች ሰራዊት በግልፅ ተነገረው: እኔም በዘማቾች የትራንስፖርት ና ጠቅላላ የስንቅና ትጥቅ አቅራቢ ሁኜ በግንባሩ ስለነበበርኩ ነው የሚመሰክረው: ስለዚህ መለሰና ጓዶቹ ባሳለፍነው 38 ዓመት የትግል ጊዜና የስልጣን ዘመናቸው ሰላም ንደራደር አብረን እንሰራ ሲሉ በዉስጡ ተንኮል ሴራ ነበረው: በተፈጥሮዋቸው ለሰላም የቆሙ አልነበሩም::

"ገፅ 61 አዲስ መሰመር 2 አዲስ ራዕይ: የመለስን ታላቅ እስትራተጂ ስትነት የሚያረጋግጠው ሌላው አብነት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላ በተለይ ደግሞ ከተሃድሶ በኋላ የተነደፈው የለውጥ እስትራተጂ ነው: ይህ እስትራተጂ በዋነኛነት ድህነትና ኋላ ቀርነት በመፋለም ብልፅግናና የህዝብ ተጠቃሚነት ከዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ጋር አዋህዶ ለማምጣት የተነደፈ እስትራተጂ ነው::"

መለስ እስትራተጂስ እንዳልነበሩ መልካም አስተዳደር ዴሞክራሲ እንዲነግስ በሰፊው ተገልያዋል አልደገመዉም::

መለስ ከተሃድሶ በኋላ የነደፈው የልማት እስትራተጂ የሚባልው ግን ከ1983 ዓ.ም በፊት በሰፊው አይተናል ተመልክተናል: መለስ ከሞቱ በኋላ የተነገረላቸው አይተናል መለስ ከተሃድሶ በኋላ የእስትራተጂ ለውጥ በማምጣት ከዚህ ሃገር የልማት ለውጥ አምጥተናል: ከዛ በፊት አግደዉን የቆዩ ከህ.ወ.ሓ.ት የተገነጠሉ አንጃ ናቸው ነው የሚባለው::

እኔ የሚገርመኝ ሀዝብም የሚገርመው ከተሃድሶ በኋላ የመጣ ለውጥ ምንድን ነው ምን ናቸው የወጡ የልማት ፖሊሲና እስትራተጂዎች ሁሉም የእሳት አደጋ ማጥፊያ ናቸው::

ለማስረጃ ያህል በሃገራችን ፈጣን ልማት ለማምጣት ድህነትን ከስሩ ለማጥፋት በገጠር እያንዳንዱ አርሶ አደር የራሱ ዉሃ

የሚያቁርበት (ሁረዮ) በመስራት በዓመት 3 ጊዜ ምርት ያፍሳል: በከተማም ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በማቋቋም ወደ እንዱስትሪ በማሳደግ በቃ ድህነት ደህና ሁኚ እንላታለን ብለዋል: እነዚህ ሁሉ አልተሳኩም: ለአርሶ አደርና ለወጣቱ አክሰሩት እንጂ ትርፍ አላገኘለትም: ይህ ስራ የመለስን የልማት እስትራተጂ መውደቁ አንድ ምስክር ነው::

መለስ ድህነትና ኋላ ቀርነትን ለማጥፋት የጣሩ እያላቸሁ ነው: ድህነት አላጠፉም ብሶታል መለስ ከስሩ ሊያጠፉ የሚችል በጥናት የተመሰረተ እስትራተጂ የላቸዉምና በአንፃሩ ግን በዚህ ፅሑፍ እንደ ገለፅኩት: ድህነት በሃገራችን ቁጥር ስፍር የለዉም በአካባቢያችን ያሉ የአፍሪካ መንግስታትና ዓረቦች መሰከሩ: የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቃል በሂወታቸው የተሰደዱ እንቡጥ ወጣቶች ሬሳቸው በአየር መንገድ ተጭነው የሚገቡ ጅምላ ሬሳ እያዩ ናቸው: ስራአጥነቱ መንገላታቱ ተገልፀዋል::

"በገፅ 62 አዲስ መስመር1 መስመር 8: የመለስን ታላቅ እስትራተጂ ስትነትና ቴክኒሻንነት የሚያመለክቱ አብነቶች ግን እነዚህ ብቻ አይደሉም: በኢሳያስ መንግስት ቀስቃሽነት የተካሄደው የኢትዮ ኢርትራ ጦርነት በድል አድራጊነት የተጠናቀቀው ከዚያም በኋላ ፀረ ሰላሙን የኢሳያስ መንግስት ከጦርነት ግጭት በመለስ በከፍተኛ ፍጥነት ለማዳከም የቻለው የመግታት ስልትም የዚሁ አካል ናቸው::"

በመለስና በሻዕቢያ የተቀሰቀሰ ጦርነት በመለስ እስትራተጂና ተክኒሻንነት ቀመር የተገታ አልነበረም: መለስ ኢሳያስ ዛላንበሳ ወረዳ ኢሮፕ ሲቆጠቀጠር ወረራን ለመከላከል በመንቀሳቀስ ፈንታ ለኢሳያስ ስልክ እየደወሉ እንቅልፍ አጥተው ነበር የሚያድሩ::

ሌላ እስትራተጂስትና ተክኒሻን ከነበሩ መለስ በሃገር ደረጃ ስልጣን ከተቆጣጠሩ ጀምሮ ኢሳያስ አፈወርቂ ኢትዮጵያ የሚያጠቃ መሆኑ ህዝብ ያውቃል መለስም ያወቁ ነበር: የስለላ መዋቅሩም ይናገር

ነበር: እዚህ ላይ መለስ የሁሉም ነገር እስትራተጂስት ተክኒሻን ከነበሩ 80ሚልዮን ህዝብ እየመሩ ለ80 ሚልዮን ህዝብ የሚነካ ጠላት እያለ እያወቁ እንዴት እንከላከለው ስንት ወታደር አለን የተኩስ አቅምና የመከላከል ሃይሉ: ሻዕቢያ በየት አቅጣጫ ሊወር ይችላል ሰራዊታችን የት ቦታ ተቆናጥቶ ይቆይ ተጠባባቂ ሃይል ዝግጅት ህዝቡ ከምን አኳያ ናዘጋጅው ወ.ዘ.ተ የሚሉ ሃሳቦች በማንሳት ከመከላከያ ሚኒስተር ከካቢኔው አልተነጋገረም: ሁሉም ነገር ሳያደርግ ቆይቶ ግን ሻዕቢያ ከወረረን በኋላ እኛ አንገታችን ደፍተን ከድህነት እየተዋጋን ሻዕቢያ ሳናስበው በድንገት ወረረን አለን: አሳፋሪ ነበር የሁሉም ነገር እስትራተጂ ቀማሪ ከኖረ በሻዕቢያ ላይ እርምጃ ለመውሰድ (ለመከላከል) እስትራተጂ አልቀየሰም: ይህ የሚያመለክተን መለስ እስትራተጂስት እንዳልነበረ ነው የሚያረጋግ ጠው::

መለስ በኢርትራ ጦርነት ድል አልተቃዳጀም: 1ኛ ነገር 80 ሚልዮ ን ህዝብ ካላት ኢትዮጵያ ከ2.5 ሚልዮን ህዝብ ኢርትራ ሲዋጉ የመለስን ዝግጁ ሆኖ አለመቆየት የወለደው አላስፈላጊ ሂወት አልፈዋል: አላስፈላጊ ሃብት ወድመዋል እንድያው ከወታደራዊ ዓለም ራቅ ብለው የቆዩ የህ.ወ.ሓ.ትና የቀድሞ የመንግስቱ ኃይለማርያ ም ነባር ወታደሮች እጃቸው ባይጨምሩበት ተዋርደን ነበርን: 2ኛ ከፍ ብየ እንደገለፅኩት መለስ ለሁለተኛ ጊዜ ሃገራችን ቆርጠው ለኢሳያስ ሰጥተዉታል: በኢትዮጵያ ሃገራችን የማይጠፋ ጠባሳ ከመተዋቸው አልፈው ወደ ኋላ የማይጠፋ እሳት (Back fire) ትተዋል: ይህ ለራሱ ትልቅ ወንጀል ነው: 80ሚልዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ከ3ሺ ዓመት በላይ የባህር በር የነበረው ህዝብ መለስና ጓዶቹ ጉረረው ዘግተዉታል በዚህም ወንጀለኞች ናቸው::

## ክፍል 20

## "መለስ ምን ዓይነት ሃገራዊ ዓላማዊ ነባራዊ ሁኔታ ፈጥረው ለሚለው መልስ"

"በገፅ 62 አዲስ መስመር 3 መስመር 3: የቢሂር ጥያቄ እጅግ አብዛኛዎቹን የሃገራችን ህዘቦች በቀጥታ የሚያሳቃያቸው ጥያቄ ነበር: በቋንቋቸው እንዳይናገሩ በባህላቸውና በታሪካቸው እንዳይኮሩ ራሳቸው በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ: አልፎ ተርፎም የመሬታቸው ና የጉልበታቸው ነፃ ተጠቃሚዎች እንዳይሆኑ የተከለከሉ ህዝቦች በማንነታቸው ምክኒያት ለከፍተኛ በደል የተጋለጡ ህዝቦች ነበሩ::"

አዲስ ራዕዮች የምትሉት የ1960 ዎቹ የህዝቦች ቢሂር ቢሂረሰቦች አንገብጋቢ ጥያቄ የነበረው በአጠቃላይ መደባዊና የቢሂር ቢሂረሰቦች የጭቆና ሰቆቃ የፈጠረው ነበር::

ነገር ግን በዘመነ የመለስ አገዛዝ አዲስ ራዕዮች የምትሉት አብዛኞ ቹ አልተተግበሩም ለማስረጃ ያህል የቢሂር የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ዕድል ተረጋግጠዋል: የምትሉን መልሱ አልተረጋገ ጠም ነው: ምክኒያቱም ሕብረተሰቡ በራሱ ተነሳሽነት ያፈራቸው ሳይሆን ሙጡቁ መሪ መለስ ከዚህም ከዚያም አሰባስበው ጠፍጥፈው ያስቀመጡዋቸው (ምረጡዋቸው ተብለው ያቀረቡላቸው) ሰዎች ይመረጡ አይመረጡ የተቀመጡ ናቸው: በተጨማሪ የመለስ የቢሂር ቢሂረሰቦች የራሳቸው ዕድል በራሳቸው የመወሰን ዕድል እስከመገንጠ ል የሚል የሃገራችን አንድነት የሚያናጋ የሚከፋፍል ነው: በተለይ በቋንቋና በባህል ማካለሉ በሚመለከት አስቀድሜ እንደገለፅኩት እጅጉን መጥፎ ነው ሌሎች ነጥቦችም ማካተት አለበት::

የሃገራችን ህዝቦች በታሪካቸው አይኮሩም ነበር ብላቹሃል: ግን እኮ በመለስና ጓዶቻቸው በአሁኑ ጊዜ በህዝብ ተፅኖ ኢትዮጵያ ከ3ሺ ዓመት በላይ ታሪክ ያላት ብለውናል እስከ 1993 ዓ.ም ግን የ100 ዓመት ታሪክ ነው ያላት ብለዋል: በተጨማሪ ባንዴራችን ጨርቅ

ናት ብለው አንቋሺሸውታል: ስለዚህ መለስ የህዝቦችና የሃገር ክብር አይጠብቁም ነበር::

መለስ ጓዶቹ መጀመርያ ወደ ትግል ሲወጡ አንዱ ጥያቄያቸው መሬት ላራሹ የሚል ነበር: በትግል ጊዜም የገጠር መሬት ከፊዩዳሎችና ሰፊ መሬት ከያዙት ሃብታም አርሶ አደሮች በመቀማ ት መሬት የሌላቸው በገመድ በመለካት ሸንሽነው አካፋፍለዋል: መሳፍንቶችና ብዙ መሬት ይዘው የነበሩ ሃብታም አርሶ አደሮች መሬታቸው ብቻ አይደለም የተቀሙ አብዛኞቸው የት እንደገቡ አይታወቅም ደብዛቸው ጠፍተዋል::

ዛሬስ መለስና ጓዶቹ ያለ ማንሳት ባህረያቸውና እስትራተጂያቸው ደብቀው ቆይተው የገጠርና የከተማ መሬት የኔ ነው የመንግስት ነው በማለት 80 ሚልዮን የኢትዮጵያ ህዝብ የመሬት ባቤትነቱን ነጥቀው በገንዘብ እየሸጡ (እየቸበቸቡ) ለከተሜውና ለገጠር ህዝብ በከባድ ችግር ጥለዉታል: ሕገ መንግስታዊ መብቱም ተነጥቀዋል: ስለሆነ በዘመነ መለስ አገዛዝ በ1967 ዓ.ም ሊታገሉለት በረሃ የወጡ የመሬት ጥያቄ በመክዳት መሬት ለንግድ ገበያ ላይ ዘርግተዉታል::

"ገፅ 63 አዲስ መስመር 3 መስመር 4: በንጉሱና በደርግ ዘመን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ለህዝቡ ጥያቄዎች አቢዮታዊ ዴሞክራ ሲያዊ ምላሽ የመስጠት ዕድል እዉን ሊሆን ይችል የነበረው በትጥቅ ትግል ብቻ ነበር: ሃሳብን በሰላማዊ መንገድ ለለመራመድ መሞከር የመንግስታዊ ሽብር ሰለባ በሚያደርግህ በዚህ ዘመን ከትጥቅ ትግል ዉጭ ዴሞክራሲን መገንባትም መጠቀምም አይቻልም ነበር ይላል አዲስ ራዕይ::"

መለስና ጓዶቹ መጀመርያ ወደ ትጥቅ ትግል ሲወጡ ደርግ አዲሱ ፍልስፍና የማኦ ዘዱንግ ፖለቲካዊ ስነ ሃሳባዊ (ዴሞክራሲያዊ አቢዮት) በሚል መፈክር ነበረ መለስና ጓዶቹም በትግርኛ ሓዱሽ ዴሞክራሲያዊ ወያነ የሚል አዲስ ዴሞክራሲያዊ አቢዮት መፈክር ነበራቸው: እዚህ ላይ መለስና መንግስቱ የነበራቸው ልዩነት ደርግ

በግልፅ ከጃንሆይ ሚኒስተሮች ጀምሮ ብዙ ሰዎች በግልፅ በአደባባይ ዘግናኝ በሆነ መንገድ ጅምላ ጭፍጨፋ ፈፅመዋል: መለስና ጓዶቹም ግልፅ ባልሆነ (በህቡእ) ብዙ ስህተት ፈፅመዋል: ስለዚህ በአይዶሎጂ ልዩነት አልነበራቸዉም በተግባርም በመሬት ፖሊሲ ልዩነት አልነበራቸዉም::

ምንም እንኳ በአስተሳሰብ አንድ ወጥ ቢኖሩ ደርግ ግን መፈክሩና ተግባሩ የማይጣጣም ከመሆኑም በላይ ጨካኝና የሆነ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የማይፈቅድ ነበር: በመሆኑ ህ.ወ.ሓ.ትና ሌሎች የደርግ ተቃዋሚዎች ኢ.ህ.አ.ፓ ኦነግ ወ.ዘ.ተ ነበሩ: መለስና ጓዶቹ የንጉስና የደርግ ፋሽሽታዊ ተግባር ብሶት የፈጠራቸው አንባገነን አቢዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የደርግ ዝናር ታጥቀው ዳሩ ግን አስወገደው ስልጣን ከያዘም ነፃ ኢኮኖሚ (የምዕራብ ዓለም) የነፃ ገበያ አቅጣጫ ይዘን እንሄዳለን ብለው የኢትዮጵያ የፓርቲዎች ብዙሃንነትን ፈቅደው ዴሞክራሲያዊ የሚመስል ሕገ መንግስት አፅድቀው ለስሙም የፓርቲዎች ነፃ የፓርላማ ምርጫ ዉድድር ፈቅደው ሲያበቁ የመጀመርያ ትጥቅ ትግል ሲጀምሩ የነበረ ሰው በላ አቢዮታዊ ዴሞክራሲ አገረሸበት: ታግለው የጣሉትን የደርግ ተግባር ተመልሰው የራሳቸውን መመርያ አድርገዉት: በአሁኑ ጊዜ ልክ እንደደርግ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች በግልፅ ባይረሽኑም በደርዘን የሚቆጠሩ ፖለቲካ ፓርቲዎችና ደጋፊዎቻቸው በተለያዩ ሴራዎች ደብዛቸው እንዲጠፋ አድርገዋል: የዘመኑ ስም በመለጠፍ አሸባሪ አልቃዒዳ ወ.ዘ.ተ ስም ተሰጥቶዋቸ ው በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በእሱር ቤት እየማቀቁ ይገኛሉ: ስለዚህ አዲስ ራዕዮች የመለስን አቢዮታዊ ዴሞክራሲ ፍልስፍና ጠቃሚ መሆኑ የመለስ ሙጡቁነት የሚያረጋግጥ ነው ስትሉን እጅጉን አሳፋሪ ነው: ምክኒያቱም ይህ አመራር ፀረዴሞክራሲ ስርዓት በተግባርም በዓላማም ከደርግ ልዩነት የለዉም: በተክኒክ ብቻ ሊለያዩ ይችላሉ: ስለሆነ የመለስና ጓዶቹ ስርዓት እስከ ህልፈተ ሞት መለስ የነበራቸው

ጉዞ የ80 ሚሊዮን ህዝብ ሁሉ ዓይነት መብት የነጠቀ ለጥቂት የመለስ ቡድን የቆመ ስርዓት ነበር::

"አዲስ ራዕይ ገፅ 64 አዲስ መስመር 1 መስመር 8: መለስና ድርጅቱ ህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የፈጠሩት ትጥቅ ትግልን የግድ ይል የነበረው የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ህ.ወ.ሓ.ትና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ብቻ ሳይሆን መለስና ጓዶቹንም የግድ ይፈለግ ነበር::"

አዲስ ራዕዮች የምትሉን ያላቸሁ መለስ አፈጣጠሩም ለፖለቲካ ተብሎ የተሰራ ነበር ነው የምትሉን: በበኩሌ ይህ አባባል የደንቆሮ አስተሳሰብ ነው: በዛን ጊዜ እኮ የነበረው ወደ 60 ሚሊዮን የሚሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ፀረዘውዳዊ አገዛዝና ፀረደርግ ሊታገል ተነስቶበት የነበረ ሁኔታ ነው: ከህ.ወ.ሓ.ት በፊት እኮ ግንባር ገድሊ ሓርነት ትግራይ 4 ዓመት ኢ.ህ.አ.ፓ ከሶስት ዓመት በላይ በበረሃ በከተማ የዓፋር ዓሊሚራሕ በኦሮሞ በፓርቲ ደረጃ ነበሩ: በህዝብ ደረጃ በደብረታቦር በጎጃም ብዙ ተቃዉሞ ነበሩ: ህ.ወ.ሓ.ት ትግል የጀመረ ው ኋላ ነበር: ስለዚህ ወደ እነዛ እንቅስቃሴዎች የዘመቱ ሰዎች ለውጥ ፈላጊዎች ነበሩ በፖለቲካ አስተሳሰብም ፀረ መሬት ከበርቴ ሆኖ አንዳንደቹ ደግሞ የቻይና ሪቮልዩሽን አማኞች ነበሩ: መለስና ጓዶቹም እምነታቸው ልክ እንደሌሎች የቻይና አምላኪ ሆነው ልዩ የሚያደርጋቸው ግን እኛ ኢትዮጵያውያን አይደለንም እኛ ራሳችን የቻልን የትግራይ ገዢዎች ለመሆን ነው ቀንደኛ ጠላታችን: ቅኝ ገዥ አማራ ነው ብለው ነው የተነሱ: እነዛ ግን በተለይ እንደ ኢ.ድ.ዩ ኢ.ህ.አ.ፓ መኢሶን ዓፋር ግን ኢትዮጵያዊነታቸው የካዱ አልነበሩም: ስለዚህ አዲስ ራዕይ በዚህ ደረጃ የሚታዩት ከሆነ እኔም እስማማለሁ: ካለበለዚያ አንስማማም::

ሌላ የመለስና ጓዶቹ መለያ ባህሪያት በ17 ዓመቱ ከእንጭጩ ጀምሮኮ የደርግ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተስማምቶ በመታገል ፈንታ ካለእኔ በዚች ሃገር የሆነ ፓርቲ መኖር የለበትም በማለት አንድ ብሎ ፓርቲዎችን ጨፈለቀ: በዛም እስከ ህልፈተ ሂወት መለስ ከላይ

እንደገለፅኩት ደርዘን ፓርቲዎች አከሰማቸው: በዚህም መለስ አስፈላጊ ነበር አላቸሁ: በኢትዮጵያ ፀረመለስና ጓዶቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መኖር የለባቸዉም እቺ ሃገር የመለስና ጓዶቹ ነበረች አሁንም አለች ስትሉ አሳዛኝ ነው: በተጠማሪ በአሁኑ ጊዜም መለስና ጓዶቹ ይመሩዋት የነበሩ ሃገር መለስ ቢያልፍም ጓዶቹ ለጋሲያቸው ተከትለው በአምላክ ትእዛዝ ይምሩዋት እቺ ሃገር ለነሱ የተሰጠች ናት 80 ሚልዮን ህዝብ ሌላ ዜጋ ነው እያላቸሁ ነው: ስለዚህ ይህ አባባላቸሁ ርካሽና ሊያስገምታቸሁ የሚችል ጉዳይ ነው::

እኛ የምናውቃቸው መለስና ጓዶቹ ግን ለትግራይ ህዝብ በጠባብነት አነሳስተው የ(Animal farm) ፍልስፍናቸው ተጠቅመው ኢትዮጵ ያዊነቱ እንደካደ አድርገው የነበረው ችግር ተጠቅመው ብዙ ንፁህ ሰዎች ደብዛቸው አጥፍተው የሃገር ሉአላዊነትን አፈራርሰው ያ የነበራቸው ጠባብነት አስተሳሰባቸው የማያዋጣቸው መሆኑ አውቀው ሃገራዊ መልክ አስይዘው ወደ ስልጣን ወጥተው 21 ዓመት ፀረ ዴሞክራሲ ስርዓት አንግሰው የዚች ሃገር ልዩ ፍጥረት ሁነው በመታየት ካለፉት ስርዓቶች በአፍ የኢትዮጵያ ህዝብ ወደ ስደት ረሃብ በሽታ የዳረጉት መሆናቸው ነው የምናውቃቸው::

"አዲስ ራዕይ ገፅ 65 አዲስ መስመር 2 መስመር 20: በተፈጥረው ዓለማዊ መድረክም መለስ ንቁ ተዋናይ ብቻ ሳይሆን እንደሶቭየት ሕብረት የመሳሰሉ ከእዝ ኢኮኖሚ ወደ ገበያ ስርዓት የተሸጋገሩ ሃገሮች በከፍተኛ ቀውስ ሲመቱ ኢትዮጵያና ህዝቦቻን ትርጉም ያለው የኢኮኖሚ ቀውጥ ባላጋጠመበት አቅጣጫ መርቶ በገበያ ስርዓት የዕድገት ጉዳና ያራመደ የድህረ ቀዝቃዛው ዘመን ምጡቅ ፖለቲከኛ ነበር ይላሉ አዲስ ራዕዮች::"

አዲስ ራዕዮች አሁን በሃገራችን ያለው ነባራዊ ሁኔታ አብዛኞቹ ሰዎች ሥራ አጥተው ሃገር ለቀው የጠፉ አብዛኛው ህዝብ መጠለያ ምግብ አጥቶ በቀን አንድ ጊዜ በልቶ የማያድርበት: በበሽታ እየ ተሰቃየ ነው የሚኖሮው: የምግብና የዕቃ ፍጆታ ዋጋቸው ሰማይ

ተሰቅሎ ለባለስልጣኖችና ጥቂት ባለሃብቶች ምቾት እንደሆነች ነው የምናውቃት እቺ ሃገር: በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በመለስ ጊዜ ይሁን በአሁኑ ጊዜ በቀውስ ተዘፍቃ ከቀውሱ ለመውጣት ብሩህ ተስፋ የማይታይባት በዉጭ ዕዳ ተወጥራ ባለሃብቶች የአቢዮታዊ ዴሞክራሲ እዝ ኢኮኖሚ በጫንቃቸው ረግጠዋቸው መንቀሳቀሻ ተስኗቸው የዉድቀት ጉዳና የያዙበት ሁኔታ እያለ ሙጡቁ መሪ ከምዕራብና ምስራቅ አውሮፓ ከአመሪካ በበለጠ ቀውሱ ወደ ሃገራችን እንዳይገባ አድርገዋል ስትሉን መለስ ማን ነው: እኔ የምፈራ መለስ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ መሬቱን ሰንጥቆ ከጉድጓድ ወጥቶ ተመልሶ ይመራናል እንዳትሉን ነው: ሌላ ለመሆኑ ኢትዮጵያ ዉስጥ ነው ያላችሁ እስቲ በሃገራችን ያለው ቀውሲ ለማወቅ እንደናሙና የተወሰኑ መንደሮች ወስዳቸሁ አጥኑ: ለነገሩ ግን አሁንም መለስ ቢሞት በመንፈስ ለ50 ዓመት መሪያችን ነው እያላቸሁን ነው::

"ገፅ 68 አዲስ መስመር 3 መስመር 156: መለስ የፈጠረዉን ዓለማዊ ሁኔታ ስናስስ የምንመለከተው የእንቫይሮመንት (Environment) ችግር የአሸባሪነትና አክራሪነት ችግር የስደተኞች ችግር እንዲሁም በካፒታል ፈጣን ተነቃናቂነትና በጉልበት ዝዉውር አዝጋሚነት መከላከል ያለው ያለመጣጣም የፈጠራቸው ችግሮች በምድራችን ሞልተው ተርፈዋል: ክለሳ ይሁን መሰረታዊ ጥያቄ ከማንም በተሻለ ደረጃ ለመገንዘብ በመቻላቸው በሃገር ዉስጥ ሰፊ የአረንጓዴ ሥራ በመስራት መለስ በዓለም ዙርያ የተደረገው ስለአካባቢ ጥበቃ ዋና ተሚጋች ነበር::"

መለስ ወደ መድረክ ወጥተው የሚታወቁበት ነገር ካለች ለማንም አሳልፈው የማይሰጡ እንደነበሩ ታሪካቸው አይተናል: አሁንም መለስ ስለየአየር መዛባት በአፍሪካ ሕብረት መድረኮች በG 20ና G8 ብዙ ተናግረዋል: የመነናገር ችለሎታቸውን የሞተ ይቀሰቅሳል አሳማኝና አደናጋሪም ነበሩ: ስለኢንቫይሮመንታል በሚመለከት ግን አዲስ ራዕይ እየነገራቸሁን ያለው ሃገራችን በአረንጓዴ እንደ

ተሸፈነች ከዓለም መጥቃ እንደሄደች ነው: ሐቁ ግን ባለፉት ገፆች እንደተገለፀው ሁሉ በደርግ ከነበረው የአረንጓዴ ሽፋን በአሁኑ ጊዜ ይቅርና አዲስ ተክል ሊከል ተተክሎ አረንጓዴ ልማት ሊሸፍንስ የነበረ ጠፍተዋል አሁንም እየጠፋ ነው: የገጠር አርሶ አደርና አርብቶ አደር ኑሮው ካልተቀየረ አረንገጓዴን ዝርያ ከስሩ እየነቀለ የማገዶ እንጨትና ከሰል እያመረተ ኑሮው እየገፋ ይገኛል: በሌላ በኩል ከላይ እንደተገለፀው የከተማ ነዋሪ የኢሊክትሪክ ታሪፍ ካለተቀነሰ አርሶ አደርና አርብቶ አደር የማገዶ ገበያ አያጡም: ስለዚህ መለስ የዉስጣቸው ችግር ሳይፈትሹና ሳያስተካከሉ ነው አየር በአየር ሲያንሳፍፉን የቆዩ ናቸው::

ሌላ መለስ ስለአሸባሪነትና አክራሪነት የስደተኞች ችግር በሃገር ዉስጥም በአፍሪካና በዓለም መድረኮች ወጥተው ብዙ ተናግረዋል: አሸባሪነትና አክራሪነት በሚመለከት መለስ ራሳቸው ምንጭ አሸባሪነ ት ነበሩ: ህዝብ በነፃ ሃሳቡ እንዳይገልፅ በነፃ የፈለገው ሰው እንዳ ይመርጥ እንዳይመረጥ ነፃ ሚድያ በመዘጋት በፓርቲ የተደራጀ ውይም ድጋፌ በማሰር ደብዛው ማጥፋት የመለስ ስርዓት ተግባር ነው: ስለዚህ መለስ ስለአሸባሪነት አደጋ በዓለም መድረክ ወጥተው የሚናገሩ ከምዕራባውያን የዶላርና የቁሳቁስ ድጋፍ ለማትረፍ ብለው ነው እንጂ መለስ ፀረሽብርተኝነትና አክራሪነት ሳይሆኑ ራሳቸው አክራሪና አሸባሪ ነበሩ: ለዚሁ የኢትዮጵያ ህዝብ ይመስክር::

ሌላ አዲስ ራዕዮች መለስ ስለስደተኞች ችግር ተጠብቆ በዓለም መድረኮች አስተጋብተዋል ብላቹሃል: የስደተኞች ጉዳይ ምንጩ እኮ ራሳቸው መለስ ነበሩ: ስለስደት ድህነት መናገር ተደጋግመዋል እንዳትሉን እንጂ በ360 ድግሪ የኢትዮጵያ ጠረፎች መለስና ጓዶቹ በፈጠሩት ችግር በየ ቀኑ ስንቱ ነው ጠረፍ አቋርጦ የሚጠፋው: በሱዳን በሱማል በኢርትራ የተሰደዱ ከ200ሺ የማይበልጡ በኢትዮጵያ ጠረፎች አስጠግተው ለዛዉም በሰበብ አስባቡ የፖለቲካ ና የኢኮኖሚ ትርፍ ለማግኘት ብለው ያደረጓት በዓለም መድረክ

ወጥተው ሲኮፈሱበት የዓለም ሕብረተሰብ አበጥሮ ያውቅ ነበር: ስለዚህ መለስ በሃገራችን በህዝቦቻቸው ያለው የስደት ችግር ምንጭ ሳያደርቁ ዓለምን እየዞሩ ቢዘሙሩ ጥሩምባ ቢነፉ ዉጤት አልነበረዉም: የራሳቸው የግል ታዋቂነት ከማትረፍ አልፈው: ስለዚህ መለስ የኢንቫሮመንት ችግር ስለአሸባሪነትና አክራሪነት ስለስደተኞች ችግር ምናቸው አልነበረም ዉሸት ነው ዓላማቸው ልታይ ልታይ ፍላጎታቸው ለማሳካት ነው::

"አዲስ ራዕይ ገፅ 68 አዲስ መስመር 2 መስመር 1: መለስ አሸባሪነት ን ከመታገል አኳያም ዓለማችን ትክክለኛዉን መፍትሄ እንደ ምትፈልግ ሳይታለም የተፈታ ነው: በበለፀገን ዓለም ታላላቅ ሃገሮች አሸባሪነትን እንደ አንድ አደጋ እንመለከተዋለን ቢሉም ይህን የሰው ልጆች አደጋ ከስር መሰረቱ በሚነቅል አኳሃን ለመፍታት አልቻሉም : ይልቁንም የበሽታው መንስኤ ከማከም ይልቅ የበሽታዉን ምልክቶች በመፋለም (መዋጋት) አትኩረዋል: የአሸባሪነትና አክራሪነት ምንጩ ድህነት ተስፋ መቆረጥ እንዲሁም ኋላ ቀርነትና መልካም አስተዳደር እጦት ችግር ናቸው: ከሁሉም በላይ ደግሞ የአሸባሪነትና አክራሪነት መንስኤ ወይም ለም አፈር ድህነትና ይህንኑ ተከትሎ የሚመጣ ተስፋ መቆረጥ ነው: ሐቁ ይህ በመሆኑ ማነኛዉምፅንፈኝነት የማዳከምና የማስወገድ ጉዳይ ሊሳካ የምችለው በመለስ መሪነት ኢትዮጵያ ላይ እንደተደረገው ድህነትና ተስፋ መቁረጥን ከኋላ ቀርነት ጋር አዳብሎ በመፋለም ብቻ ነው::"

አዲስ ራዕዮች አሸባሪነትና አክራሪነት በሚመለከት የዓለማችን መንግስታት (በበለፀጹ ታላላቅ ሃገሮች) አስጊና ሂወት አጥፊ ሃብት አውዳሚ መሆኑ በመረዳት አግራሪና አሸባሪ ሃይሎች አንድ በአንድ በማደን ብዙ ሃብትና ሂወት ቴክኖሎጂ ያጠፋሉ: ይህ መንገድ ግን መሰረታወዊ መፍትሀሄ ሊያመጣ አልቻለው: በተቀራኒን ግን አዳዲ ስ አሸባሪዎች ስም እየቀየሩ በአህጉሮቹ ሁሉ እየተፈለፈሉ ይገኛሉ: ትናንትና የቢንላደን የአልቃዒዳ መርበብ ነበር ቆየት ብሎ

የሚጃሂዲን አልሸባብ የናይጀርያ የኬንያ ወ.ዘ.ተ አክራሪዎች ተፈጥረዋል: በመለስ ዘመነ መንግስት ደግሞ በኢትዮጵያ አልእትሃ ድ ኦነግ አብነግ ጉንበት ሰባት ነውጠኛ አሸባሪ ጋዜኞች አሸባሪዎች የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች አሸባሪ አክራሪ ተብለው ተፈርጀዋል: እነዚህ ቡድኖች ለምን አሸባሪ ተባሉ: ለመሆኑ አሸባሪ ማን ነው::

በኔ እምነት አሸባሪና አክራሪ ሊፈጠሩ የቻሉት የዓለማችን መንግስታ ትና ስርዓቶች ናቸው: እነዚህ ስርዓቶች አዲስ ራዕይም እንዳላቸሁ የአሸባሪነት ምንጭ ድህነት ኋላ ቀርነት ስራአጥነት ተስፋ መቁረጥ ናቸው ብላቹሃል በነዚህ ነጥቦች እንስማማለን ግን አሸባሪ ዓመፅ የሚያስነሱ እነዚህ ጥቃቅን ነጥቦች ናቸው ውይ መልሱ አይደሉም ነው::

ዋና ምክኒያቶች ገዥዎችና ሰርዓቶች ናቸው የአሸባሪነት ምክኒያት የህዝብ ነፃ ኢኮኖሚ መብቱ ስለነጠቁት በሃገሩ ጉዳይ ነፃ የፖለቲካ ተሳትፎ በመከልከል: የህዝቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በመከልከላቸው ፍትሃዊ ያልሆነ የኢኮኖሚ ክፍፍል አለመኖር: የጉልበትና የአእሙሮ ስራዎችና ዉጤታቸው መበዝበዝ: ህዝቦች በሃገራቸው የመናገር የመፃፍ በሰላማዊ መደራጀት ጥያቄዎቻቸው በነፃ የማቅረብና ተገቢ መልስ ማግኘት: በተጨማሪ መሪዎች ሲባልጉ ከስልጣናቸው ማውረድ ብቁና ሃገር ወዳድ ሰዎች ወደ ስልጣን ማውጣት: የነዚህ ሁሉ መብቶች ሲከለከሉ ባለስልጣኖች የሃገር ሃብት ያለአግባብ ሲመዘብሩ: የህዝቡ ፍቃደ ስለማይጠየቅ እንደዚህ ወንጀል የሚፈፅሙ መሪዎች በሃር ያለ ህዝብ ግን በረሃብና በድህነት ስለከፋው: የሃገራችን ሃብት ያለ አግባብ እየተዘረፈ ወደ ዉጭ እየተላከ ሰዎች የመጠለያ የምግብ የልብስ እጦት ሰለባ ሁነው መኖር: ህዝቦች የሕግ የበላይነት ተነፍጎቸው በእስርና በእንግልት ሲሰቃዩ: የሃገርቷ ሃብት በሙስና እየተመዘበረ የሰዎች ንሮ ልዩነት የሰማይና የመሬት ሲሆን: የትምህርት የስራ ዕድል የስልጣን አሰጣጥ አድላዊ ሲሆን: የገዥዎች ልጆች በከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት

በድሆች ሃብት እያማረጡ ሲማሩ ሲዝናኑ ሲንደለቀቁ: ድሃና አቅም ያጡ የሚማሩበት አጥተው ጉዳና ሲንከራተቱ: ገዢዎች ስልጣናቸው ለመራዘም ሰሉ ከፋፍለህ ግዛ በሚል ስልት ህዝቡ በዘረኝነት በመከፋፈል እርስ በእርሳቸው ስልሚያጋጫቸው: ገዢዎች ለጥቅማቸው ሲለ በሃይማኖት ጣልቃ በመግባት በህዝቡ መካከል ልዩነት እንዲኖር ማድረግ: ስርዓቶች የዓለም ገበያ ለመቆጣጠር በቀጥታ ወየም በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አድርገው በሚፈጥሩት ሃብት መውረርና በሚወረር ሃብት ህዝቡ አመፅ ሊነሳ ማድረግ: ሃያላን ሃገሮች የነዳጅ የማዕድን ወረራ ሲፈልጉ በዛ አካባቢ ለሚገኙ ህዝቦች በሚያደርሱ ግፍ ወ.ዘ.ተ ናቸው::

አዲስ ራዕዮች አሸባሪነትና አክራሪነት ሊያስነሱ የሚችሉ እጅግ ብዙ ምክኒያቶች እያሉ የአሸባሪነት ምንጭ ድህነት ተስፋ መቁረጥ ኋላ ቀርነት ብላችሁ ስታቃልሉት ምን ያህል አስመሳዮችና አታለዮች መሆናችሁ ታሪክ ይሰንደው::

ሸለመጥማጥ ድመት አይተዉም ያጎቱ ሸለመጥማጥ እንርሚ: ከላይ የአሸበሪ መንስኤ ብለን ያሰቀመጥነው መለስ በሃገራችን የአሸባሪነትና የዓመፅ ምንጭ መኖራቸው ነው::

ከላይ የተዘረዘሩት የአሸባሪነት ቀስቃሽ ነገሮች አስቀምጫለሁ: በዚህ አኳያ መለስ ፀረአሸባሪነት ነበሩ ወይስ የአሸባሪነትና አክራሪነት ምንጭ ሆነው ነበር::

በኔ እምነትና መለስም እንደማወቃቸው ስልጣን ከያዙነት ጀምረው በኢትዮጵያ ሃገራችን ሁሉም ዓይነት ዴሞክራሲያዊ መብቶች አፍነው በመያዝ ከላይ የተዘረዘሩት የአሸባሪነትና አግራሪነት ምንጭ ብየ ያስቀመጥኩዋቸው በሙሉ የፈፀሙ በመሆናቸው: ፀረአሸባሪነት ና አክራሪነት ፅንፈኝነት መሆናቸው ቀርቶ ራሳቸው አሸባሪ ነበረ::

መለስና ጓዶቹ አሸባሪዎችና ጨካኞች መሆናቸው ማስረጃ ሊሆን ዘንድ ገና ከትጥቅ ትግል ጀምሮ እስከ ህልፈተ ሞታቸው ከላይ እንደ

ተገለፀው ዴሞክራሲያዊ ዓላማ ይዘው ለመብታቸው የታገሉ ወይም የጠየቁ ፓርቲዎች ግለሰቦች የተለያዩ ስሞች በመለጠፍ ከሕብረተሰ ቡ ከማግለላቸው አልፈው ምክኒያት በመፍጠር ብዙ ሰዎች ጎድተዋል ለአብነት ያህል፦

1. በትጥቅ ትግል ጊዜ የነበሩ ሰዎች ፊዩዳል የመሳፍንት መልእክተኛ፣ የኢ.ህ.አ.ፓ ቅጥረኛ፣ ሓንፋሺ (አንጃ)፣ የኢሰፓ ሰላይ፣ ፀረወያነ ወላዋይ፣ ወ.ዘ.ተ የሚሉ ስሞች የመለስና ጓዶቹ ቋንቋ ነበረ: ሌላ በወቅቱ የነበሩ የደርግ ተቃዋሚ ሃይሎች ደጋግሜ እንደገለፅኩት መለስና ጓዶቹ ከአንባገነናዊ እምነታቸው ተነስተው በኢትዮጵያ ያለ ህ.ወ.ሓ.ት ወይም በአዴን በህ.ወ.ሓ.ት ሳንባ የሚያተነፍስ አይኖራትም በሚል በህቡእና በአዋጅ ደበዛቸው እንዲጠፋ አድርገዋል: በታጠቁ ፖለቲካ ፓርቲዎች የተወሰደ አሸባሪ እርምጃ እንተወውና በህ.ወ.ሓ.ት ታጋዮችና በትግራይ ህዝብ ብዙ ስራ ተሰርተዋል:
2. መለስ በሃገር ደረጃ ስልጠን ከያዙነት ጀምሮ በመጀመርያ ለዓለም ሕብረተሰብ ለመምሰል ከደርግ ስርዓት የተለየ ዴሞክራሲያዊ ይዘት እንዳላቸው ለማታለል በኢትዮጵያ ፀረደርግ ስትታገሉ የቆያቸሁ አሁንም ለኛ የምትቃወሙ አሁን አዲስ የተፈጠራቸሁ ፓርቲዎች ኑ ተሰባሰቡ አብረን የሽግግር መንግስት እናቋቁም ማንም ዜጋ የራሱን አማራጭ ይዞ ተወዳድሮ በህዝብ ዳኝነት ስልጣን ለመያዝ ይቻላል አሉ: ይህ መልካም ተግባር ነበር: በሌላ በኩል ማንም ዜጋ የመናገር የመፃፍ የግል ፕሬስ ለማቋቋም ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ መብቱ የተጠበቀ ነው አሉ ይህም አይከፋም ነበር: ከዘዛ በኋላ ከኢ.ህ.አ.ፓ በስተቀር ሁሉም በከተማም በበረሃም የደርግ ተቃዉሞው በህቡእ በግልፅ ሲታገሉ የነበሩ : ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ከተማ ከገባ በኋላ ለመለስና ጓዶቹ ስርዓት

ተቃዋሚ ፓርቲ የመሰረቱም ተሳተፉ ተባሉ: ይህም ለመለስ ከደርግ የተለየ ሰው አስመሰለው::

በአንድ በኩል መለስና ጓዶቹ ኢ.ህ.አ.ፓ ከ1970 ዓ.ም እሰከ ደርግ ዉድቀት ከምስራቅ ትግራይ እስከ መተማ ቋራ ከዛ አልፎም በሽውራ በረሃ እያባረረው የቆየ ኋላም ደርግ ከተወገደ በጎጃም አካባቢ በሽውራ ና በሰዳያ ጠረፎች ጦርነት ተደርጎ በረሃ የነበሩ ኢ.ህ.አ.ፓ ተዳከመ የቀረው በከተሞች በተለይ አዲስ አበባ በጠንካራ ህቡእ ድርጅት ተደራጅተው ይንቀሳቀሱ ነበር: መለስ ከዚህ ሃይል ዴሞክራሲያዊ ጥሪ ከማድረግ ፈንታ ከ1969 ዓ.ም ከነበረው ቂምና ኢ.ህ.አ.ፓ በህዝብ ተቀባይነት አለው ስለተባለ ለስልጣኔ አስጊ ነው ከሚል ጥርጣሬ በአሸባሪነትና ፅንፈኛ የትምክህተኛ ኮር ተብሎ እንዲወገዝ አደረገ: በሌላ በኩል ኢ.ህ.አ.ፓ ወደ ሽግግር መንግስት ከገባ እንደባአዴን መለስ በሚፈልገው ሊታዘዝለት ስለማይችል ለስልጣኑ አደገኛ ስለሆነ ሊያስገባው አልቻለም::

ኦነግም መለስ ሊያስጠጋው የቻለ ኦነግ ከመለስ ጋር እንደማይቀጥል ያውቃል: ግን ደግሞ ለኦነግ እንደኢ.ህ.አ.ፓ እንዳይመታው አንደኛ ኦነግ በኦሮሞ ህዝብ የታወቀ ነው: ስለዚህ ኦነግ ከተመታ ለመለስና ግዶቹ እጅግ አደገኛ በመሆኑ ሊነካው አልቻለም: በዛን ጊዜ መለስ የቀየሰው ስልት (ታክቲክ) ኦህዴድ ከምርኮኞቹ ተሰባስበው እነ አባዱላ ገመዳና ኩማ ደመቅሳ የሚመሩት 300 ሙርከኛና 150 ሲቪሎች ያካተተ ነው የነበረው: ስለዚህ ኦህዴድ በህ.ወ.ሓ.ት ሰራዊትና ካድሬዎች ማኮሚቴ የሚያስተባብሩት በህዝብ በየት አውራጃ ነው የተንቀሳቀሰም: ኦህዴድ እስከ ሚጠናከር ለኦነግ አለሳልሶ መያዝ: ኦህዴድ ከተጠናከረ ለኦነግ ጠራርገን ደብዛው ማጥፋት የሚል ስልት ነበረው መለስ::

በሌላ በኩል መለስ ከሁሉም ቢሄረሰቦች ክልሎች ያ የመለስ መንግስት ባወጀው አዋጅ ሐቅ መሰላቸው የራሳቸው ፓርቲዎች በመፍጠር ወደ ሽግግር መንግስት ገቡ: መለስ ለነዚህም የድመት

ልጅ አይተዉም የአጎቱ ሽለመጥማጥ ተንኮል እንደሚባለው መለስና ጓዶቹ ለነዛ በሽግግር መንግስት የገቡ ፓርቲዎች ልክ ለኦነግ ለማፍረስ ኦህዴድን አጠናከረው: ኦነግ እንዳከሰሙት ሁሉ ለነዛም ለማክሰም በሶማል በሃረር በዓፋር በዒሳ በጋንቤላ በቤንሻንጉል በደቡብ ህዝቦች በየቢሄረሰቡ የመለስ ታማኝ ፓርቲዎች ተፈጠሩ: መለስና ህ.ወ.ሓ.ት ብዙ ገንዘብ በማፍሰስ አጠናከሩዋቸው: የሃገር መከላከያ ሚኒስተር በዚህ ፅሑፍ መጀመርያ አካባቢ እንደተገፀው አባይ ፀሃዬ የሚመሩት የማለሊት ማኮሚቴ ቢተው በላይ አብረሃ ማንጁስ ሰለሞን ተስፋይ ወ.ዘ.ተ የሚያሰተባበሩቸው በመቶ የሚቆጠሩ የህ.ወ.ሓ.ት ካድሬዎች ተሰማሩ::

ከዛ በኋላ ሽግግር መንግስት ተመስርቶ ሕገ መንግስትን መረቀቅ ጀምሮ ከ1983 ክረምት እስከ 1987 ዓ.ም የሕገ መንግስት ምስረታ መለስ በሁሉም አካባቢ የነበሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አንፃራቸው የሆኑ የመለስ መልእክተኞች ፓርቲዎች ተፈለፈሉ: ይህ በመሆኑ የ1987 የፓርላማ ምርጫ የመለስና ጓዶቹ የፓርላማ በከፍተኛ ምልአተ ጉባኤ (ከ75%) የመለስ ስለነበረ የሆነ ሕግ ለፀድቅ አዋጆች ሲወጡ ከ75% በላይ የመለስ ፓርቲ ስለሆነ ሁሉም የአፈና አዋጆች ታወጁ::

መለስ በዛን ጊዜ እነዛ 20% አካባቢ የተቃዋሚ ፓርቲዎች በፓርላማ በመግባታቸው ለፓርላማው ለማሙቅ ይጠቀምባቸው ስለነበር: በምዕራባውያን በኢትዮጵያ ያልተለመደ ስለነበር መድበለ ፓርቲ በኢትዮጵያ ሊሳካ ነው እንዴ የሚል ስሜት በመፈጠር ማታለል ጀመረ: ሁኔታው ግን እንደሱ አልነበረም: መለስ መድበለ ፓርቲ ፍትሃዊ በሆነ በኢትዮጵያ ለመራመድ አጨልመዉታል ነበር: ምክኒያቱም በመላው ሃገራችን የነበሩ የህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ተቃዋሚዎች ለያንዳንዳቸው አንፃራቸው የሆኑ የመለስ ተከታዮች (ባንዳዎች ማለት ይቻላል) በማቋቋም አዳከማቸው: የመለስ ፀጥታ በሙሉ ሃይላቸው እንደጠላቶች አዩዋቸው በቃ በኢትዮጵያ መድበለ

ፓርቲ በሚልዮኖች ኢትዮጵያውያን መስዋእት የተገኘ መብት በመለስና ጓዶቹ ተነጠቀ::

እስከ አሁን የአሸባሪነት ምንጭ ማንነው በሚል አርእስት በመያዝ አጠቃላይ በሆነ ጀምረን ወደ ዝርዝር ነገሮችም አይተናል: አሁን ግን የዓለም አቀፍ አሸባሪ ማንነው ለሚለው በኢትዮጵያ ያለው የመለስ የአሸባሪነት ደረጃ እስቲ እንይ::

መለስ ፀረየአልቃዒዳ መርበብና የአልሸባብ የዓለማችን አሸባሪዎች መቃወም ትክክል ነው::

አሁን ግን በኢትዮጵያ ሃገራችን በሆነው ባልሆነው አሸባሪዎች እየተባሉ ይታሰራሉ: ሌላ ቀርቶ ከሃገራችን ዉጭ ያሉ በተለይ ደግሞ የአልቃዒዳና የአልሸባብ የሌሎችም የአሸባሪዎች መርበብ ሰለባ የሆኑ ሃገሮች እንድነ አመሪካ እንግሊዝ ከሌሎች አውሮፓ ሃገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እነ ጉንበት ሰባት መሪዎች የኢሳት ሬድዮ ጣብያ ጋዜጠኛ ፋሲል እንደነ አበበ በለው የአዲስ ነገር ጋዜጠኞች ወ.ዘ.ተ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች አሸባሪዎች ተብለዋል: በሌሉበት ከ18 ዓመት እስከ እድሜ ልክ ተፈርደዋል: እነዚህ ሰዎች ከዓለም አቀፍ ሽብርተኝነት ግንኝነት ካላቸው ለምን አመሪካና ሌሎች ሃገሮች አይዙዋቸዉም: እነዚህ ሰዎች በአመሪካ መንግስትም በግል ድርጅቶች እየሰሩ ይኖራሉ: እነዚህ መንግስታት ለዓለም አቀፍ ሽብርተኝነት ከኢትዮጵያ አብረው ይሰራሉ ግራ ያጋባል::

አዲስ ራዕዮች የአሸባሪነትና አክራሪነት ምንጭ ድህነትና ተሰፋ መቁረጥ እንዲሁም ኋላ ቀርነት ብላቹሃል: እኔም የአሸባሪነት ምንጭ እነዚህ ብቻ እንዳልሆኑ ተናግራለሁ: አሁን በኢትዮጵያ መለስን በግለሰብ ይሁን በቡድን በፓርቲ የተቃወመ ሁሉ አሸባሪ እየተባለ ታስረዋል ከሃገር ጠፍተዋል: አሁን መለስ ነው አሸባሪ: እነዛ በአሸባሪነት የታሰሩ እስቲ የአቅሜን ልሞክር::

መለስ ከተባለበት ጀምሮ እስከ ህልፈተ ሞቱ ያደረገው እንቅስቃሴ የአሸባሪነትና የአክራሪነት ምንጭ ነበር::

መለስ ከፍ ብየ እንደገለፅኩት የአሸባሪነት ምንጭ ነበር ሲለው በመለስ ዘመነ ስልጣን ዜጎች ሃሳባቸው በነፃ እንዳይገልፁ ከማገድ ነፃ ሁነው ሃሳባቸው ሲገልፁ ስጋት በመፍጠር ማሰር ጋዜጠኞች በማሰር ማስፈራራት ከሃገር ውጥተው እንዲጠፉ ማድረግ ሁሉም ነገር ችለው ጋዜጣ መፅሐፍ ፅፈው ለንባብ ያበቁ ነገሮች እየለቀሙ በመክሰስ በማሰር ራሱ በዜጎች ላይ ስጋትና ሽብር እየፈጠረ ከጋዜጠኞች በሽብርተኝነት ከመፈረጅ እሱር ቤት በመክተት ሰው አጨነቁትና ለሞት በመዳረግ በኢትዮጵያ ለነበሩትና ሌሎችም በፖለቲካ ተቃዋሚ ፐርቲዎች ለይስሙላ ሕጋዊ ፍቃድ በመስጠት በተግባር ግን እንቅስቃሴያቸው በማጥበብ ደህንነት (ሰላዮች) በመክበብ በማስጨነቅ በፖሊሶች በቀበሌ በአስተዳደሮች ማዋከብ ማሰር ምክኒያት መፍጠር መግደል: በአጠቃላይ ለመለስና ፓቲው ለሚቃወሙ ሃይሎች ፍፁም የማይገናኝ የአልቃዒዳ መርበብ የአልሸባብ የጥፋት መልእክተኞች ጀሃዳዊ በማለት ስም በማጥፋት: በሃይማኖት መካከል ጣልቃ መግባት ብጥብጥ መፍጠር: ሰላማዊ ሰልፍ ለሞከሩ ህዝብን በጃምላ ገደሎ 80 ሚልዮን ህዝብ ፍርሃትና ጭንቀት ላይ መጣል ሊንበረከኩ ማድረግ: የመለስ ፓርቲ አባል ያልሆነ በዚህ ዓለም አይኖራትም: ስራ የትምህርት ዕድል አያገኝም: ሰዎች ከቤተሰቦቻቸው ፍቅር መስርተው እንዳይኖሩ በቤትሰብ በትዳር በወላጅና ልጅ እርስ በራሳቸው በማጋጨት ሕብረተሰቡ ሁሉ እርስ በራሱ ተጠራጥሮ እንዲኖር መድረግ: በሺ የሚቆጠሩ ደላዮች በሕብረተሰቡ በመገባት እርስ በራሱ እንዲሰልል ማድረግ: ህዝብ የተረጋጋ ንሮ እንዳይኖር ቀውስ በመፍጠር ለስልጣኑ የሚያሰጉ ሰዎች ሆነ ሆን ብሎ ወደ ወንጀል ማኖ እንዲነኩ ማድረግ ከስራ እንዲፈናቀሉ ወይም ተንበርክከው ታዘው እንዲኖሩ ማድረግ: ዜጎች ለሚደረሳቸው ጭቆናና አፈና የኢኮኖሚ ብዝበዛ የፍትህና የነፃነት

እጦት በተመለከተ ቀና ብለው ጥያቄ ካቀረቡ የተለያዩ ስሞች በመለጠፍ ስጋት ስለሚፈጥርላቸው የሚወዱዋት ሃገራቸው ለቀው በማያውቁት ሃገር ሄደው በበረሃ ይሞታሉ በስደት ሂደው የባርያ አገዛዝ ግፍ ይፈፀምባቸዋል: ዜገጎች በዜግነታቸው የመጠለያ የመሬት ባለቤትነታቸውን በመንጠቅ ጥገኛ ሆነው እንዲኖሩ ማድረግ: የታጠቁ የተለያዩ ሰራዊቶች በማሰልጠን በህዝቡ ላይ ሃይል እንዲያሳዩ ማድረግ ወታደራዊ ሰልፍ በማድረግ ህዝቡና ተቃዋሚ ሃይሎች እንዲሰጉ ማድረግ: ፍርድ ቤቶች አቃቢ ሕግ ሌሎች የፍትህ አካላት በእጅ በማድረግ ህዝብ ትክክለኛ ፍትህ እንዳያገኙ ማድረግ: የመንግስት መስርያ በሙሉ የህ.ወ.ሓ.ት እጅ አለባቸው: የቡዙሃን መገናኛዎች በመንግስት እጅ በመሆናቸው የሚያሰራጩት መልእክት የዉሸት ልማት ህዝቡ ተንበርክኮ እንዲኖር ከሕግ ዉጭ ሰዎች ማሰር ያልሰሩ ት ወንጀል በመለጠፍ አልቃዒዳ አልሸባብ የሻዕቢያ የጥፋት መልእክተኞች ናቸው በማለት ድራማዊ ፊልም በማሳየት ህዝብን ማደናገርና ስጋት መፍጠር: ደጋግመው በሬድዮ በተለቪዥን በጋዜጣ በመፅሄት በመናገር ህዝቡን ማደንቆር አረ ስንት ተብሎ ይነገራል::

መለስ ብዙ አፈናዎች ህዝቡ ላይ በማድረሱ ራሱ አሸባሪነት ምንጭና የዓለም ስጋት ነበር: በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተጣባቂዎች የዓለም ብዙሃን መገናኛዎች የተባበሩ መንግስታት የዴሞክራሲ መመዘኛዎች ኢትዮጵያ ከሻዕቢያና አልሸባብ ቀጥላ በሰብአዊ መብት ጥሰትና ረገጣ ተሰልፋ ያደረች ናት: ለዚሁ ደግሞ መለስ ነው ተጠያቂውና አሸባሪው::

አንድ ነገር ግን መለስ ቢሞትም ያሉት ጓዶቹ ሊመልስልኝ: መለስና ጓዶቹ ወደ ትግል ሜዳ የወጡበት ዓላማ በዚህ ፅሑፍ መጀመርያ አካባቢ ነካ አድርጌ እንዳለፍኩት አሁንም ላነሳው የፈለግኩ መለስና ጓዶቹ 17 ዓመት ሲታገሉ በዘ ድልድዮች ብዙ የህዝብ ተሽከርካሪዎች ብዙ የመንግስት ተቋሞች ፋብሪካዎች ጦር

ካንቦች በሺ የሚቆጠሩ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ታንኮች አውድመ ዋል በሚልዮን ዶላድ የሚቆጠር ገንዘብ ንብረት ወረዋል በሙቶሺ የሚቆጠር ወታደሮች ለደርግ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች የነበሩ ፓርቲዎች እንደኢ.ህ.አ.ፓ ወ.ዘ.ተ የተለየየ ስም ተሰጥቶዋቸው ነበር: በኔ እምነት ግን በአሁኑ ጊዜ መለስ አሸባሪዎች ያሉዋቸው የመለስና ጓዶቹ ተቃዋሚዎች ያደረሱት ጉዳት መለስና ጓዶቹ ካደረሱት ጥፋት ሲነፃፀር በፍፁም አይመጣጠንም: ስለዚህ መለስና ጓዶቹ ድሮም የወጣላቸው አሸባሪዎች ነበሩ: አሁንም የአሸባሪነት ምንጭና አሸባሪዎች ናቸው: ወይ ደግሞ አሁን አሸባሪዎች የሚባሉ ያሉ ቡድኖች መለስ ቢሞትም የተሰራ ወንጀል አይሞትም ጓዶቹ በሂወት ስለአሉ ተጠየቂ ናቸው: የነዚህ ወንጀለኞች ስራቸው ወደ ህዝብ ይቅረብና ህዝቡ ይፍረደው::

"አዲስ ራዕይ ገፅ 70 አዲስ መስመር 2 መስመር 9: መለስ ትጉህ ተማሪና ፅኑ ታጋይ ነበር ይላሉ::"

መለስ ፅኑ ታጋይ ነበር የሚለው የመለስ አጭር ታሪክ በሚለው ክፍል ተቀምጠዋል: መለስ ራሱ የሚወድና ለክፉ ነገር ራሱ የማያጋልጥ የአኒማል ፋርም ፍልስፍና ስልት ተከትሎ የተጓዘ ብልጥ ታጋይ ነበር::

"አዲስ ራዕይ ገፅ 70 አዲስ መስመር 2 መስመር 8: የመለስ ምጡቅ ስብእና ጎልቶ ሊወጣ የቻለበት ምክኒያት ከሌላ ሳይሆን ከራሱ ጥረት ጋር የተያያዘ ጭምር ነው: ምንም እንኳ ታጋዮች ሁሉ በየራሳቸው አቅም ለሃገራችንና ለዓለማችን መልካምነት የየበኩላቸው አኩሪ አስተዋፅኦ እንደአበረከቱ ባይዘነጋም መለስ ታላቅ ዓለማዊ ስብእና ያደረገው ምክኒያት ከሌሎች ጓዶቹ በተለየ ሁኔታ ካደረገው የግል ጥረት ጋር የተያያዘም ነው::"

መለስ ምጡቅ ነበር: መለስ በራሱ ጥረት ምጡቅ የሆነ ትላላቾሁ አዲስ ራዕዮች: መለስ እኮ እስከ 1983 ዓ.ም የሰዎችን ፅሑፍና ሃሳብ ተቀብሎ ሲያስተምር ነበር: አንድ ነገር ግን አምንበታለሁ መለስ

መፅሐፎችን ያነብ ነበር: ሲያነብ ግን መፅሐፎቹ ለሰዎች ሊያንሳፍፉ የሚችሉ መርጠው ነው የሚያነቡት: መለስ የሰዎችን ሃሳብ በመቅዳት የዓለም መርሆች ጥቅሶች በመውሰድ መድረከ ሲወጡ እነዚህ በማጎላት ታዋቂነት ለማትረፍ የሚንቀሳቀስ ነበር: ከመለስ የሚበል ጡ ታጋዮች ነበሩ አሁንም አሉ: የመለስ ገበና እየደበቁና ያለ አቅሙ ሰማይ ይሰቅሉታል: እነሱም እነ ስብሃት ነጋና ሌሎች የህ.ወ.ሓ.ት አመራር ናቸው: መለስ ራሳቸው የፈጠሩዋቸው እነ አዲስ ራዕይ ጭምር ናቸው: እነዚህ ሁሉ መለስ ያልሰራው ስራ ያልፈለሰፈው ፍልስፍና ያልሰራው ታሪክ የመለስ ነው እያሉ እያጋነኑ በጎዳና እየዘመሩ የኖሩ ሰዎች ናቸው: ህ.ወ.ሓ.ት ወደ ከፍተኛ ደረጃ ያደረሱ ሙሁራኖችን ፈላስፋ በፀረኢ.ድ.ዩ ኢ.ህ.አ.ፓ ደርግ ሰው በላ ጦርነቶች አልቀዋል በተለያዩ ምክኒያቶች ደብዛቸው ጠፍተዋል: ንቁ ሙሁራን መለስና በወሩ መሪዎች ያውቁዋቸዋል: መለስ መድረክ ሲያጋጥመው ምርጥ ቃላቶች በመጠቀም ድጋፍ እያገኘ መጥተዋል: በተረፈ መለስ ይቅርና የህ.ወ.ሓ.ት ምጡቅ ሰው ሊሆን እስከ 1977 ዓ.ም በፍፁም አልነበረም: ከዛ በኋላም መለስ ኋላ አንጃ ብሎ የመታቸው የህ.ወ.ሓ.ት አመራር ነበር: ስብሃት ነጋ ምንም ያልሰራው ሰማይ ሰቅሎት ምንም አቅምም ቦታም አልነበረዉም::

ወደ መንግስታዊ ስልጣን ከመጣም በኢትዮጵያ የነበሩ ብቁ ሙሁራን ሃሳብ በመቅዳት ስልጣኑ ብዙ የዉጭ መሪዎች ሙሁራን የሚናገሩት ሁሉ ለማግኘት ይፈቅዱለት ስለነበር በመቅዳት የራሱ ሃሳብና ፍልስፍና አድርጎ ያቀርብ ነበር: ህዝቡ እንደሚያውቀው መለስ የሙሁራን የአስተማሪዎች የመንግስት ሰራተኞች የሃይማኖት መሪዎች የተማሪዎች የባለሃብቶች ለዲያስፖራ ስብሰባ በሚያደርግበ ት ጊዜ እዛው የለቀማቸው ቃላቶች (ሃሳቦች) በነጋታው በሚያደርገ ው ስብሰባ በሚገባ ይጠቀምበታል: መለስ የሚታወቅባቸው በፖርላማ በሌሎች መድረኮች የስድብ ናዳ ናቸው የሚቀድሙት

በተለይ ደግሞ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች በሁሉም ነገር ይበልጡኛል የሚላቸው ሙሁራን ለስራ ባልደረቦች እጅጉን የስድብ ናዳ ይለቅባቸዋል: ሰዎች በመስደብና የሰዎችን ሃሳብ በመቅዳት ቅናተኛ በመሆን መለስ በጣም የመጠቀ ነበር: በዚህ ላይ ምጡቅ ነበር የሚል ሰው ካለ እንስማማለን::

"አዲስ ራዕይ ገፅ 70 አዲስ መስመር 3 መስመር 1: ይህ መነሻ በማድረግ ብዙ ነገሮች ማንሳት ይቻላል: የመጀመሪያዉን ለየት ያለ ጉዳይ: መለስ ለህዝብ ያለው ተቆርቋሪነት መነሳትን የህዝብን ሂወት ለመቀየርና ለማሻሻል ከምንም ነገር በላይ በከፍተኛ የኃላፊነት መንፈስ ከእርሱ የሚጠበቀዉን ሁሉ ለሚሟላት የተንቀሳቀሰ ታጋይ መሆኑ ነው::"

መጀመርያ ነገር ለህዝብ ተቆርቋሪ ከሆኑ ህዝብን እንዲሻሻል የሚጥሩ ከነበሩ: የኢትዮጵያ ህዝብ ከበሰበሰ የእርዳታ ስንዴ አላላቀቁትም: ሰብአዊ መብቶች በማስጠበው ፈንታ ኢትዮጵያ ሃገራችን ብዙ ፀረዴሞክራሲ ተግባራት እየተሰሩ ይታያሉ: ለህዝብ ከሆኑ ግርጭቶች በሰላም መፍታት ትተው መፍትሂው አፈሙዝ በመምረጣቸው ብዙ ሂወት ብዙ ሊሂቃናት መለስ በሚመራው መንግስት ደብዛቸው ጠፍተዋል: ለህዝቡ ተቆርቋሪ ከሆኑ በ1997 ዓ.ም ብዙ ወጣት በጎዳና ተዘርግተዋል: ለህዝብ ምቾት ተቆርቋሪ ቢሆኑ ሙስና ጉቦኛነት ወገናዊነት ስርቆት አመፅ በተቆጣጠሩ ነበር: ለህዝብ ተቆርቋሪ ቢሆኑ ንሮ ድሃ ሕብረተሰብ የመኖርያ መጠለያ አያጡም ነበር: መለስ ፀረደርግ ለመዋጋት ብለው የወጡ ጀግኖች በፈለጉበት ቦታ እያሰማሩት የተጓዘ ታጋይ ጓዳቸው አካል ጉዳተኛም እንኳ በአግባቡ ልይዙት አልቻሉም: እነዚህ አካል ጉዳተኞች ወድቀዋል በየ ክልሉ በልመና ተሰማርተዋል: ስለሆነ መለስ ለህዝብ የተመቹና ተቆርቋሪ አልነበሩም::

መለስ ይቅርና ከሁሉ በተለይ ተንቀሳቅሰው ህዝብን ሊያገለግሉ በአፍ በየ መድረኩ ከመናገር አልፈው በሕብረተሰቡ ያመጡት

ፋይዳ የለም: ከመለስ በላይ ስንትና ስንት ሰርተው ያለፉ ጀግኖች ነበሩ: እንደመለስ ግን ለግል ታዋቂነትና ክብር ብለው በየ ሽንጥረው ፎቶግራፍ እየተነሱ ብቻቸው ለብቻቸው እየታገለ አልመጡም: መለስኮ በዋሻ ተደብቀው ለመጪው ጊዜ ታሪክ የሚሆን ታሪክ ሰሪ መስለው እንዲገኙ ፎቶግራፍና ቪድዮ እየተነሱ ሰብስበው በአርካይፍ (መዝገብ ቤት) አስቀምጠው ነው ያቆዩት: ሐቀኛ ቢሆኑ ንሮ ለብዙሺ የሚቆጠር የተሰዋ ታጋይ ታሪኩ መዝግበው በያዙ ነበር::

"አዲስ ራዕይ ገፅ 71 አዲስ መስመር 2 መስመር 1: ይህ መለስን ከሌሎች ታጋይ ጓዶቹ ጋር የሚያመሳስለው ነው ይህም ሆኖ መለስ ከትግል ጓዶቹና አጋሮቹ በተለየ ደረጃ የህዝቦችን ታሪክ በተለይ ደግሞ ሲፈፅምባቸው የነበረዉን በደል የሚመለከተዉን ታሪክ ሁሉ ጠንቅቆ አጥንተዋል: ከራሱ ሃገር የጥንትና የቅርብ ዘመናት ታሪክ አልፎ እንደአየርላንድ በመሳሰሉና ከ 600 ዓመታት በላይ ለክፉ ቢሄራዊ ጭቆና የተጋለጡ አውሮፓዊ ሃገሮች ታሪክ ጠንቅቆ አጥንተዋል::"

አዲስ ራዕይ የምትሉን ያላቸሁ የመለስ ማንነት ያጋለጠው አንዱ ከ3ሺ በላይ ታሪክ ያላት ኢትዮጵያ ዋነኛዉን በር የቀይ ባህር አድርጋ የይሓና አክሱም ጎንደር ፋሲል ላሊበላ ወ.ዘ.ተ ታሪክ ያላት ሃገራችን መለስ ለጌቶቻቸው ሻዕቢያ ለማስደሰት ሲሉ ኢትዮጵያ የ3ሺ ዓመት ታሪክ ከየት አመጣችውና እኛ የምናውቀው ኢትዮጵያ የአንድ መቶ ዓመት ታሪክ ብቻ ነው ያላት ብለው በኢትዮጵያ የተለያዩ መንገዶች እያወጡ ሳያፍሩ ተናግረዋል: አዲስ ራዕዮችና አለቆቻቸሁ ይህ ሐቅ ወዴት ልትደብቁት ነው: መለስ የሃገራቸው ቢሄር ቢሄረሰቦች ሳያጠኑ ከየት አድርገው ነው የአየርላንድ ቢሄራዊ ጭቆና በአውሮፓ ያጠኑ: በዚች ጠባብነት ሃገር የ80 ሚልዮን ህዝብ ያላት ሃገር ቢሄር ከቢሄር ሃይማኖት ከሃይማኖት ክልል ከክልል አውራጃ ከአውራጃ ጎጥ ከጎጥ እያጋጬ ሃገራችን የብጥብጥ ማእከል

እንድትሆን እያደረጉ ነበሩ ሰውየ አሁን ያየነው የምናውቀው የመለስ ታሪክ ልታጭበረብሩን አትችሉም::

ከላይ እንደተጠቀሰ ስለባንዴራ ስለ 3ሺ ዓመት የኢትዮጵያ ታሪክ እሬት እየጣማቸው ደፍረው ሊናገሩ የቻሉ በ1990 ዓ.ም በሻዕቢያ ወረራ ሰግተው ተጨንቀው ለኢትዮጵያ ህዝብ በሃገራዊ ስሜት አነሳስተው ወደ ጦርነት ለማስገባት ነበር: ሳይወዱ በግድ ያመኑት: መለስና ሃገራዊ ፍቅር ቢኖራቸው ንሮ የሰይድ ባረ መንግስት ሃገራችን ሲወር ከደርግ ጎን ተሰልፈው ባይዋጉም አቋማቸው ለደርግ ደግፈው ለምን አልተናገሩም: በአንፃሩ መለስና ጓዶቻቸው በሱማል የህ.ወ.ሓ.ት ፅፈት ቤት ከፍተው ነበር: ህ.ወ.ሓ.ት ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም መሪዎች ሁሉ በሱማል ፓስፖርት ይንቀሳቀሱ ነበር: መለስ ለሃገር የቆሙ ቢኖሩ ለ3ሺ ዓመት የባህር በር የነበራት ሃገራችን ያለ ምንም ክርክርና ማቅማማት ለሻዕቢያ የሰጡት ናቸው: ከህዝብና ከባለሙያዎች ሳያማክሩ መለስ የሃገር ፍቅርና ለህዝብ ታማኝ ቢኖሩ ንሮ የአልጀርስ ስምምነት ፈርሶ እያለ ሃገራችን ነፃ አውጥተን እያለን ለምን ከጓዳቸው ኢሳያስ አፈወርቂ ተፈራረሙ: በኔ እምነት መለስ የኢትዮጵያ ታሪክ ጠባቂ ለህዝብ ተቆርቋሪ አልነበሩም: መለስ ዝም ብለው ባልተገራ በቅሎ ነው ሲጋልቡት የነበሩ::

"ገፅ 72 አዲስ መስመር መስመር 4: የዓለማችን ሃገሮች የተካሄዱ ታላላቅ የህዝብ እንቀሳቃሾች ሰዎችን ታሪክ በዝርዝር አጥንቶ ከመገነዘብም በላይ በህዝብ ላይ በተለያዩ መልኮች ይፈፀሙ የነበሩ የጭቆና መልኮችን ሁሉ በማስወገድ የተሻለ ስርዓት ለመገንባት የሚያስችሉ ዘመን ተሻጋሪ ሃሳቦችን ያመጣ ታጋይ ነበር::"

መለስኮ ሃገር ተሻጋሪ ሃሳብ እያመለኩ የመጡ ናቸው ተደጋግሞ እንደተገለፀው መለስ እየለቃቀሙ አንድ ጊዜ ከማኦ ፍልስፍና ሌላ ጊዜ የአልባንያ ቆየት ብለው የመካቪሊ ፍልስፍናና እስትራተጂ በመከተል በመለቃቀም ዋና ስልታቸው ደግሞ የጆርጅ አርዌል

አኒማል ፋርም ተከትለው ሂወታቸዉን በመጠበቅ እስከ ህልፈተ ሞታቸው ነው ሲጓዙት የኖሩት::

መለስ የሃገራችን ታሪክ በጥልቀት አጥንተው ራሳቸው ባያውቁም የታሪክ ባለሙያዎች ሙሁራን ሳያማክሩ የኢትዮጵያ ታሪክ አያቶቻችን ወዳሞት አያቶቻችን ያቆዩንን ታሪክ በመናድ ኢትዮጵ ያ የ100 ዓመት ታሪክ ያላት ሃገር ናት ብለው ሳያፍሩ የተናገሩ መለስ እንዴት ብለው ነው: የአህጉራችን ታሪክ አጥንተውና ተገንዝበው የዘመኑ ተሻጋሪ ሃሳብ ያመጣ ታጋይ ነበር ይባላሉ: በበኩሌ ይህ አባባል ለመለስ ለማይገባቸው ሽልማት ነው: መለስና ጓዶቹ የሃገራችን ታሪክ ጥናት የጎደለው የያዙት ገና ሀ ብለው ደደቢት ከወረዱበት ዕለት ነበር ይህም በዚህ ፅሑፍ መጀመርያና ማኸል ላይ ተቀምጠዋል: ስለዚህ መለስ ሃገር ተሻግረው ያጠኑ የተመራመሩ ታላቅ መሪ ነበሩ የሚለው የአዲስ ራዕይ አቀራረብ ስህተት ነው: ለዚሁ ምስክር 21 ዓመት ሙሉ ለመለስ ይታዘብ የነበረ 80 ሚልዮን ህዝብ ነው::

"ገፅ 73 አዲስ መስመር 1 መስመር 2: ያነባል ይፅፋል ያስተምራል ያስተማረዉን በተግባር ይፈፅማል እንደገና ይማራል: በዚህ የትግልና የመማር ተመጋጋቢ ጉዞ ከአንድ የዕውቀት ጠርዝ ወደ ሌላው የዕውቀት ጠርዝ እየተሸጋገረ የማታ ማታ ምርጥ የሚባሉ ዘመን ተሻጋሪ ንድፈ ሃሳባዊ ስራዎች እስከ ማምረት ደረሰ::"

መለስ እስከ 1982 ዓ.ም ተማሪም አስተማሪም ነበሩ: ይህ ደግሞ መለስ በሌሎች ተዘጋጅቶ የተሰጣቸው መማርያ ፅሑፍ የማሳለፍና የማስተማር ችሎታ እንደነበራቸው በግልፅ ተቀምጠዋል: ግን ደግሞ ከመለስ የሚበልጡ ፖለቲካዊ ወታደራዊ አስተዳደራዊ አስተማሪዎ ች ነበሩ: በተግባርም የበለጡና በቆራጥነት ጫፍ ድረስ ሂደው የሚመሩ ነበሩ: መለስ ግን በዚያች የኋላ ደጀን ሁነው በዋሻ ዉስጥ ሆነው ያስተምሩ ያነቡ ነበሩ: ጫፍ ሆነው ተግባር መሳተፋቸው ግን አላየነም: መለስ የሆነ ነገር አደጋ ሊያደርስ የሚችል የተኩስ የአየር

ድምፅ ሊሰሙ ፍቃደኛ አልነበሩም: ከህልፈተ ሞታቸው በኋላ የምናየው ያለን ግን በ 17 ዓመት ትግል ዋና ተዋናኝ እንደነበሩ የሚያሳይ ፎቶግራፎች እናያለን: መለስ ብልጥና ያልሰሩትን ታሪክ እንደሰሩ የሚያመለክት ማስረጃ እየሰበሰቡ እንደቆዩ ያመለክታል::

መለስ የማታ ማታ ምርጥ የሚባሉ ዘመን ተሻጋሪ ንድፍ ሃሳብ አፍላቂ አልነበሩም አሁንም ህ.ወ.ሓ.ት ይሁን መለስ የዓለማች ፈላስፋዎች ከፈለሰፉት ንድፈ ሃሳብ ዉጭ የነደፉት ፍልስፍና አልነበረም: አዲስ ራዕዮች ግን አሁንም ደግማቸሁ ደጋግማቸሁ የምትሉን ያላቸሁ መለስ ከዓለም ሊሂቃን አልፎ የመጠቀ ሰው የምትሉን ያላቸሁ በኔ እምነት ግን ወደ ሩቅ የሚገኝ አበይት ፈላስፋዎች እንሂድና ለመለስ ከማንዴላ አጠገብም አላስጠጋቸዉም: አሁንኮ በ17 ዓመት የትግል ጊዜና ከዚያ በኋላ ብዙ ታሪክ ሰርተው በመቶሺ የሚቆጠሩ የተሰዉ ጀግኖች ተረስተዋል: ስዉአን እናስታዉስ ፀሎት ቀርቶ ለባለራዕይ መለስ ብቻ የህልና ፀሎት እናድርግ ትላላቸሁ: የኢትዮጵያ ጀግኖች መስዋእት ፋዉብዳሽን እንመስርት ማለት ቀርቶ የመለስ ፋዉንደሽን እንመስርት ትላላቸሁ ፋና ፅሑፎች ፎቶግራፎች የንግግር ቪዮዎች ሙዝየም እናሰራለን እያላቸሁ ነው: በመለስ የተሳሳተ የአመራር ስልት ምክኒያት በኢትዮ ኢርትራ ጦርነት የተቀጠፈ በ10ሺዎች የሚቆጠሩ ጀግኖች ማስታወሻ ሙዚየም ያልተሰራላቸው ታሪክ ያበላሸና ሃገር ገንጥሎ አሳልፎ የሰጠ የባህር በር የሸጠ መሪ ይህን ያህል ማሽሞንሞን ምን ያህል የሃገር መካድ መሆኑ ሰው ሁሉ ግምት ዉስጥ ማስገባት አለበት::

"ገፅ73 አዲስ መስመር 2 መስመር 1: መለስ አንባቢ ፀሐፊ አስተማሪ አደራጅ ብቻ አልነበሩም: ዕውቀት ካለበት ቦታ የሚማር በጣም ትሁት ሰውም ነበር: በቅርብ የሚያውቁት ጓዶቹ እንደ ሚያረጋግጡት ብቻ ሳይሆን የዉጭ ሰዎችም ሳይቀር እንደ ሚመሰክሩለት ማንም ሰው ሲናገር በፅሞና በማስተዋል የሚያዳምጥ:

ሰዎች ከሚናገሩት መካከልም ጎጂና ጠቃሚዉን ለይቶ ጠቃሚዉን የሚቀበል: ጎጂዉን ደግሞ በምክኒያታዊነት ተደግፎ በሚያካሂደው ክርክር: በዚህም የተሳካለት ሰው ነበር::"

መለስ ቢያነብ ለአንድ መድረክ መከራከርያ ይጠቅሙኛል በሚል አልፎ አልፎ አርእስት በመያዝ ያነባል በተለይ ደግሞ ለሰዎች ሊያንሳፍፉ የሚችሉ (ሃይላይት) ለይቶ በመያዝ ብዙ ጊዜ ሲያጭበረብር ይታይ ነበር: በተለይ ለሙሁራኖች ለተማሪዎች ለባለሃብቶች ሲያዋያይ: አንድ ጊዜ የተካነ ኢኮኖሚስት ሌላ ጊዜ የጤና ዶክተር ስቪል መሃንድስ: መካኒካል ኢሊክትሪካል ኢንጂነር: ቆየት ብሎ የእርሻ ሳይንስ የሳይንስ ተመራማሪ ወ.ዘ.ተ መስሎ ለመቅረብ አዲስ ቃላቶች በመምረጥ ሲናገር አጀቤ ሊቀ ሊቃዉት ያሰኝ ነበር::

መለስ ራሱም የሚጠቀምበት በራሱን አለመተማመን የመነጨ ሁልጊዜ የሚናገረው የኛ ፖሊሲ የኛ ሕግ የኛ ኢሞኖሚ ዕድገት የበለፀጉ ሃገሮችም ይመሰክሩልናል በማለት ይናገራል: ይህ ጉዳይ ባለቤቱ የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቃል የሚራበው የሚጠግበው የሚሰደደው ፍትህ ነፃነት ወ.ዘ.ተ ያጣው የኛ ህዝብ ነው ለማጭበርበር ካልሆነ: ለአብነት ያህል ባለፉት ዓመታት በዓለም ላይ ተፈጥሮ በነበረው የንሮ ዉድነት መለስ ያለው ቢኖር: ዓለም በመላው አመሪካ አውሮፓ ሳይቀሩ በትልቅ የኢኮኖሚ ቀውስ ገብተው እያሉ ኢትዮጵ ያ ግን ባለን የጠራ ፖሊሲ ትክክለኛ ፖሊሲ ህዝባችን ያለ አንዳች ችግር እየኖረ ነው ብሎ ተናግረዋል: ይህ ትልቅ ማጭበርብርና ለራሱ ማንነት የዉሸት በላይነት ለማስተጋባት ተብሎ የተነገረ ነበር::

መለስ የሰዎችን ሃሳብ በፅሞና የሚያዳምጥ አይደለም: ባለፉት 21 ዓመት የመራቸው መድረኮች የራሱን ግብአት የነበረው ብዙ ሰዓታት ቀናቶች በስብሰባ በቪድዩ ኮንፍረንስ ማፍሰሰ ካልሆነ የተለያዩ ሰዎች በተለይ ደግሞ የሙሁራኖች ባለሙያዎች ሃሳብ አዳምጦ አያውቅም: ሌላ ቀርቶ መለስ ከፈደራል እስከ ቀበሌ

የመዋቅር ሰንሰለት በሙያቸው የተሰማሩ ሰዎች እያሉት በነዛ ሰንሰለቶች አስፈላጊ የመረጃ ግብአት በማግኘት ፈንታ ለነዛ አልፎ የራሱ ሰንሰለት በመፍጠር በየክልሉ ዞኖች ወረዳዎች ቀበሌዎች ሳይቀሩ ቡድኖች ከማደራጀት ልዩ የዉሎ አበልና የመጓጓዝያ ወጪ በመመደብ ማንም የክልል ባለስልጣን ሳያውቀው የስለላ መረጃ ይሰበሰብ ነበር: ይህ አሰራር የአንድ የሰዎችን ሃሳብ አዳምጦ ትክክለኛ ስራ የሚሰራ ሰው ሳይሆን የአንድ ደንቆሮ አፈኛ አሰራር ነው የምለው: በየ ወሩ ጠሚኒስተር ቢሮ እየሄደ መረጃ የሚያቀብሉ ሰዎች ነበሩት::

መለስ ሰዎችን በሚያናገሩት ጎጂና ጠቃሚ ሃሳብ ለይቶ ጠቃሚ ሃሳብ የሚቀበል አልነበረም: እንዲያዉም የሆነ ጠቃሚ ሃሳብ በሰዎች ከቀረበለት በተለይ ደግሞ አዋቂ ከሚባሉ ሰዎች ከመጣ ለጊዜው ባለመቀበል ቆየት ብሎ ግን የራሱ ሃሳብ አድርጎ ይናገራታል: ስለዚህ መለስ የሰዎች ጠቃሚ ሃሳብ የሚቀበል ሳይሆን የነበረ የሰዎችን ሃሳብ በመስረቅ የሚኮፈስ መሪ ነበር::

"አዲስ ራዕይ ገፅ 73 አዲስ መስመር 2 መስመር 7: መለስ ገጠር በመውረድ ፋብሪካዎች በመጎብኘት የተለያዩ የሕብረተሰቡ ክፍሎች ሲያነጋግር በፅሞና ከማዳመጥ አልፎ በሰራው ላይ ከተሰማሩት ሰዎች የሚቻለዉን ያክል በተግባር ላይ የተመሰረተ ዕውቀት ለማግኘት ያደርጋል::

መለስ አሁንም ወደ ገጠር ወርዶ ፋብሪካዎች ሌሎችም መጎብኘት አልቃወመዉም: የመለስ ጉብኝት ግን ከትግል ሜዳ ጀምሮ ይዞት የመጣ ባህሪ ሰዎችን የሰሩትን ስራ በማኸል ጣልቃ በመግባት ለሰዓታት ለደቂቃዎች በምርጥ ቃላቶች ታጅቦ በመናገር ፎቶግራፍ እየተነሳ ተሰሚነት ለመፍጠር ያደርገው እንደነበረ ሁሉ ባለፉት 21 ዓመታትም ብዙ የመንግስት ባለሙያዎች የሰሩትን ስራ ዋጋዉን ለራሱ ለማድረግ ሆን ብሎ በየገጠሩ እየሄደ ሲናገር ሲሸልም ወጣቶቹ በሚሊንዮምና በክልል አዳራሾች ሲናገር በቪድዮ ኮንፍረንስ ሲደሰኩ

ር ሁሉም እንቅስቃሴው ለራሱ ለብቻው ተሰሚነት አካብቶ ህዝቡ በየ አካባቢው ያሉ ባለስልጣኖችና ባለሙያዎች እምነት እንዳያሳድሩ የሚያደርግ አሰራር ይከተል ነበር: ይህ ደግሞ እጅግ ኋላ ቀርና የመለስ ራስን ወዳድነት የሚያመለክት ነበር::

## ማጠቃለያ

የአዲስ ራዕይ 8ኛ እትም ቅፅ 4 ልዩ እትም መፅሄት (መፅሐፍ) አስመልክቶ ስለመለስ ዜናዊ የ17 ዓመት የትጥቅ ትግል ጊዜና የ 21 ዓመት የመንግስት ስልጣን ጊዜው አስመልክተው የአዲስ ራዕይ የዉሸት ፈላስፋዎችና የመለስ ኳዶች የፃፉት ታሪክ መልስ ልሰጥ የተገደድኩት የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች ባለፉት 21 ዓመታት ስለህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የትግል ጉዞ ሲተርኩ ብዙ ያልሆኑ ታሪክ እየደረደሩ እየፃፉ የየግላቸው የዉሸት ጀብድኛነት እንደድራማ እየሰሩ እንደመጡ የሚታወቅ ነው::

ይባስ ብሎ የአሁኑ አዲስ ራዕይ ደግሞ የታጋይ ጀግኖች ሰዎችና የሙሁራኖች አዋቂዎች ሥራ በመቀማት ጠቅለል አድርጎ ለመለስ በመሰጠቱ እኔም ይህ መፅሐፍ በ100 ብር ገዝቼ ደጋግሜ ሳነበው ለካስ ታሪክ ሰሪ ታሪኩን አይፃፍም: ታሪክ የሚፃፍለት ታሪክ በተሰራበት ላልነበረ ተጠግቶ ቆይቶ ወደ ስልጠን ለመጣ ነው የሚፃፍለትና የሚሰጥ ሲባል ሲሰማ ብዙዉን ጊዜ የሚያስተውለው አልነበረም: ይህ መፅሐፍ ካነበብኩ በኋላ ግን እኔ ራሴ ያየሁት የማውቀው በተግባር የነበርኩበት በሺዎች የህ.ወ.ሓ.ት ጀግኖች የሰሩት የተመራመሩበት የፈለሰፉት የተሰዉለት ሥራ በዋሻ ተወሽቆ ለነበረ መለስ ሲለጥፉለት በሺዎች የሚቆጠሩ የሃገራችንን ሙሁራኖች ባለሙያዎችና ፈላስፋዎች የአእሙሮ መስዋእትነት የከፈሉበት ተመራማሪዎች መለስ ባልሰራው ሲሸልሙት ስለአየሁ የመጣ ይምጣ ረሞት ትመፅእ እንደሰራቁ እንደሚባለው 100 ዓመት

አልኖርም: ለዚህ ትውልድ ሐቅ ምስክርነቴን ላስቀምጥ በማለት መልስ መስጠት አለብኝ ብዬ ወሰንኩ::

ይህ መፅሐፍ 80 ገፅ 140 ሉክ ወረቀት ነው: ትንሽ ነው በዉስጡ ያለ ይዘት ግን በትግሉ ወቅት ለነበሩ ኋላም በመንግስት ስልጣን የነበሩ ሰዎች ለዚህ መፅሐፍ አንብበው ትክክለኛዉን መልስ ለመስጠት ከፈለጉ ብዙ መፃሕፍቶችን በመፃፍ ብዙ ሐቅና ዉሸት ለይተው ለማጋለጥ ይችላሉ: እኔ ከዛ በላይ ለማስፋት ጊዜውን አቅምን ላገኝለት ባለመቻሌ እች አጭር ፅሑፍ እንሆ ለበረከት::

የኮምፕዩተር ፅሕፈትና የአማርኛ ቋንቋ እርማትና ማስተካከል በኢንጂነር ዓብደልወሃብ ቡሽራ ተሰርተዋል::